# የድህነት ቅነሳ ጥረቶች በኢትዮጵያ

**አርታዒ**

**ዘሪሁን መሐመድ**

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

**Forum for Social Studies (FSS)**

© 2008 ዓ.ም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው
አዲስ አበባ

ISBN: 978-99944-50-58-9

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል፡ fss@ethionet.et
ድሕረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

ይህ መጽሐፍ የታተመው በናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (National Endowment for Democracy) የገንዘብ ድጋፍ ነው።

በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣ የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል።

## ማውጫ


መቅድም ........................................................................................v

መግቢያ ....................................................................................... vii

የአነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦትና የድሆች ተጠቃሚነት በኢትዮጵያ...............1

አራጋው ይመር

የከተማ ድህነትና ሥርዓተ ጾታ በኢትዮጵያ ..........................................45

ትዝታ ሙሉጌታ

የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እና የድህነት ማስወገጃ እርምጃዎች በኢትዮጵያ........................................................85

ፈለቀ ታደለ

የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው የልማት ሚና ...107

ገብሬ ይንቲሶ፣ ደበበ ኃይለገብርኤል እና ከልክላቸው አሊ

በድህነት ቅነሳ ላይ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሚና .....................................129

ተሾመ በየነ

Rural Household Poverty and Its Determining Factors in Ethiopia...... 141

Abraham Seyoum

## ስለፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (Forum for Social Studies) ለትርፍ ያልተቋቋመ በአገራዊ የልማት ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ሕዝባዊ ውይይቶችን የሚያካሂድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በተወሠኑ የዩኒቨርሲቲ ምሁራንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በሚሠሩ አገር ወዳድ ግለሠቦች በ1990 ዓ.ም የተመሠረተ ነው፡፡ የድርጅቱ እንቅስቃሴም በመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈፃሚዎች፣ የሲቪል ማኅበረሠቡና በአጠቃላይ በሕብረተሠቡ መካከል በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ጤናማ የውይይት ባህል መዳበር ግልጽና አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረትን ለማጎልበት ያስችላል በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

ድርጅቱ ከምስረታው ጀምሮ በተለያዩ የልማት መስኮች አያሌ የፖሊሲ ጥናቶችንና ምርምሮችን ያካሄደ ሲሆን ውጤቶቹንም ለመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈፃሚዎች፣ የሲቪል ማኅበራት፣ የጥናትና ምርምር ተቋማትና እንዲሁም ለሠፊው ሕብረተሠብ አድርሷል፡፡ የተለያዩ የፖሊሲ ውይይት መድረኮችን (ወርክሾፕ፣ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች፣ የፓናል ውይይቶች፣ ሴሚናሮች) በማዘጋጀት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተለያዩ ወቅታዊ በሆኑ አገራዊ የልማት አጀንዳዎች ላይ ግልጽና ቀና ውይይትና ክርክር (debates) እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡ በተለይ በተመረጡ መሪ ርዕሶች ላይ የሚደረጉት ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች ድርጅቱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርበው እንዲነጋገሩና ሁኔታዎች ከተለያዩ ጎኖች (perspectives) እንዲጤኑ የሚያደርግበት አንዱ ዋናው የሥራ መስኩ ነው፡፡ ለዚህም *የጾታ ዕኩልነትና ልማት፣ ዕውቀትን ለትውልድ ማሸጋገር፣ ባሕልና ልማት፤ የአየር ለውጥና የዘላቂ ልማት ትስስር በኢትዮጵያ፣* ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ በሚሉት ርዕሶች የተካሄዱት ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ድርጅቱ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የሕዝባዊ ውይይት ውጤቶቹን በማሳተም ለሕብረተሠቡ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ይህ ‹‹የድህነት ቅነሳ ጥረቶች በኢትዮጵያ›› የተሠኘው መጽሐፍ የድርጅቱ የሥራ ባህል ውጤት ሲሆን በርዕሱ ለአንድ ዓመት የዘለቁ ስድስት የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ በእነዚህ መድረኮች ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በውይይቶቹ ዳብረው፣ ተስተካክለውና አርትዖት ተደርጎባቸው እነሆ ለአንባቢያን ቀርበዋል፡፡

## መቅድም

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ለትርፍ ያልተቋቋመ አገር በቀል የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ድርጅቱ በ1983 የተካሄደውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ በተፈጠረው መልካም ሁኔታ በአገሪቱ ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የተቋቋመ ነው። ድርጅቱ ከመነሻው ሲመሰረት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ግልጽና ቀና ውይይት ማድረግ በልማት ያደገች፤ በዲሞክራሲ የበለጸገች አገር ለመገንባት ያስችላል በሚል ዕምነት ላይ ተመስርቶ ነው።

በዚህ መሠረት በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የፖሊሲ ግምገማና አማራጮችን ከመስጠት ባሻገር የመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ይታወቃል። ድርጅቱ በእነዚህ መድረኮች አማካይነት በፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈፃሚዎችና ማኅበረሠቡ መካከል ጤናማ የውይይት ባህል እንዲዳብር ከማድረግ በተጨማሪ፤ አሳታፊ የፖሊሲ ቀረፃና ትግበራ ሥርዓት እንዲዳብር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን ድርሻ ሲያበረክት ቆይቷል።

በዚህ ረገድ ድርጅቱ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት በተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች አዘጋጅቷል። ሥርዓተ-ጾታና ልማት፣ የከፍተኛ ትምሕርት ፖሊሲና አፈጻጸም፣ የመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ በአፍሪካ፣ የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ፣ ወጣትና ልማት እንዲሁም የሕዝባዊ አግልግሎቶች አሠጣጥ ከነዚህ መካከል ይጠቀሳሉ። የእነዚህን ውይይቶች ውጤቶችን በማሳተም ለተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ለሕዝብ እንዲደርሱ አድርጓል።

አሁንም ይህንን ባህል በመከተል **የድህነት ቅነሳ ጥረቶች በኢትዮጵያ** በሚል መሪ ርዕስ ስር ከጥቅምት 2007 ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል የዘለቀ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች ሲያካሂድ ቆይቷል። በእነዚህ መድረኮችም በየመስኮቹ ያሉ ከፍተኛ ባለሙያዎች የመወያያ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዲያቀርቡ በማድረግ በአገራችን ከድህነት ቅነሳ አንፃር እየተደረጉ ባሉት ሥራዎች፣ በተገኙ ውጤቶችና በሚታዩ ተግዳሮቶች ላይ ውይይቶችና ክርክሮች ተካሂደዋል።

በእነዚህ መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ በማቅረብ፣ በአወያይነት፣ በተቺነት እና በተሳታፊነት የተሳተፉትን የልዩ ልዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ ምሁራንና መላውን ተሳታፊዎችን ላመሰግን እወዳለሁ። እንዲሁም ይህ የውይይት መድረክ እንዲዘጋጅና በመድረኩ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች አርትዖት ተደርጎባቸው በሕትመት ለሕዝብ እንዲቀርቡ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልንን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (National Endowment for Democracy) የተባለውን ድርጅት ከልብ አመሠግናለሁ።

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ወደፊት አቅም በፈቀደ መጠን በመስኩ ሌሎች ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በማንሳት የተለመደውን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ ውይይቶች ማካሄዱን እንደሚቀጥል መግለጽ እወዳለሁ።

ምሕረት አየነው

አስፈፃሚ ዳይሬክተር

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

***መግቢያ***

*ድህነት የዓለም አንዱ ዋና ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር መንስኤ መሆኑ ከታመነበት ውሉ አድሯል። ድህነት ብዙ መገለጫዎች ቢኖሩትም የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶች ሳይሟሉ ሲቀሩ የሚፈጠር ሁኔታ ነው። ድህነት የሌለበት አገር ባይኖርም፤ በልማት ባልገፉት አገራት በአስከፊ መልኩ ጎልቶ የወጣ ነው። የድህነት ምንነትና ትርጓሜ እንደየጊዜው ተጨባጭ ሁኔታው ሲለዋወጥ ይስተዋላል። ቀደም ሲል የነበረውና በምግብ፣ ልብስና መጠለያ ተደራሽነት ላይ ያተኩር የነበረው የድህነት ትርጓሜ በአሁኑ ጊዜ አዳዲስ ጽንሠ-ኃሳቦች በማካተት የፖለቲካ ተሳትፎና ማኅበራዊ ደህንነት ዋስትናን ያካተተ ትርጓሜ ሲሰጠው ይታያል።*

*የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) ድህነትን ለጤናማ አኗኗር በቂ ያልሆነ ገቢ ዕጦት፣ ዝቅተኛ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ዕድል፣ ለአደጋና ተጋላጭነት፤ ተደማጭነት ማጣትና አቅመቢስነት ሲል ይተረጉመዋል። በተመሣሣይ ሁኔታ የአውሮፓ ኮሚሽን ገቢያቸው በሚኖሩበት ማኅበረሠብ ውስጥ በቂ ነው ተብሎ ከሚገመተው በታች የሆኑ ሰዎችን ድሆች ሲል ይፈርጃቸዋል። በተጨማሪም በድህነታቸው የተነሳ ላልተመቻቸ የመኖሪያ ቤት፣ ለህክምናና የትምህርት አገልግሎቶች ዕጦት የተጋለጡ ከመሆናቸው በላይ የባህል፣ ስፖርት እና መዝናኛ አገልግሎቶች ከማግኘት ያግዳቸዋል ሲል ይተነትናል።*

*የማኅበራዊ ሣይንስ ባለሙያዎች ሁለት የድህነት ዓይነቶችን እንዳሉ ያሠምራሉ— ፍፁም ድህነት እና አንፃራዊ ድህነት። ፍፁም ድህነት የሚለካው ሰዎች በቀን በሚመገቡት ምግብ ውስጥ በሚያገኙት የካሎሪ መጠን ሲሆን፤ በመልካም ጤንነት ለመኖር የሚያስችል በቂ ምግብ የማያገኙ ሰዎች በፍፁም ድህነት ውስጥ እንዳሉ ይቆጠራሉ። በሌላ በኩል አንፃራዊ ድህነት የሚባለው ሰዎች በመንግሥታት በሚወሰነውንና አብዛኛው የኅብረተሠብ ክፍል የሚኖረውን ዝቅተኛውን የኑሮ ሁኔታ መኖር ሲሳናቸው የሚከሠት ሁኔታ ነው። አንፃራዊ ድህነት በማንኛውም አገር (በኢኮኖሚ የበለጸጉትን ጨምሮ) የሚገኝ፣ በሰዎች የኑሮ ሁኔታ መበላለጥ የሚፈጠርና ለማስወገድ የሚያስቸግር የድህነት አይነት ነው።*

*ድህነት በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰት፣ ኦኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዕንድምታዎች ያዘለ ዘርፈ ብዙና ተለዋዋጭ ጽንሠ-ኃሳብ በመሆኑ የድህነት ቅነሳ ጥረቶችም ዘርፈ-ብዙ አቀራረብና ስትራቴጂዎች ያስፈልጋቸዋል። ድህነት*

ቅነሳ ለማኅበራዊ ሠላምና ለፖለቲካ መረጋጋት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የማኅበረሠብ ጥናት ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው በድህነት የተተበተበ የኅብረተሠብ ክፍል የያዘ እና በዜጎች መካከል ሠፊ የኃብት መበላለጥ በስፋት የሚስተዋልበት ማኅበረሠብ ለማኅበራዊ ውጥረትና ወንጀልን ጨምሮ ለተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች የመጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ውጤታማ የድህነት ቅነሳ እርምጃዎች ከኢኮኖሚ መሻሻል ባሻገር ማኅበራዊ ሠላምንና ፖለቲካዊ መረጋጋትን የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡

ኢትዮጵያም እንደሌሎች በኢኮኖሚ ያልበለጸጉ አገራት ሁሉ ድህነት አንዱ መገለጫዋ ሆኖ ቆይቷል፤ አሁንም በስፋት ይስተዋላል፡፡ ለድህነታችን በመሠረታዊነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል ኋላ ቀር የሆነው የግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ፤ የአካባቢ መራቆትና የአፈር መሸርሸር፣ ተከታታይ የአየር መዛባትና የሚያስከትለው መዘዝ፣ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ዕድገት መጠን፣ የመሠረታዊ ግልጋሎቶችና መሠረተ-ልማቶች አለመስፋፋት፣ አመቺ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና መዋቅራዊ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በደርግ ዘመን የነበረው ርዕዮተ-ዓለምና ተዛማጅ የኢኮኖሚ መርሆዎች የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ በእጅጉ በማቆርቆዝ፣ የውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን በማገድ እና አሉታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ በማዋል የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዳያድግ ዕንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ዜጎች የድህነት ዋና መገለጫ ለሆነው በምግብ ራስን አለመቻል ተጋላጭ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ከ1970ዎቹ ወዲህ ያለውን ብንመለከት በየጊዜው የደረሱት አቢይ ድርቆችንና ያስከተሉት ረሀብ የብዙ ወገኖችችንን ህይወት የቀጠፉ፣ አገሪቱን በተረጂነት ያስመዘገቡና ስምና ዝናዋን ያጎደፉ የድህነታችን ዋና መገለጫዎች ሆነው ኖረዋል፡፡ ዝናብ ላይ የሙጥኝ ያለው የአገራችን ግብርና በአነስተኛ ደረጃ እንኳን ለሚከሠት የአየር ለውጥና የዝናብ ወቅት መዛባት ተጠቂ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተወሠነ ደረጃ መሻሻሎች ይታዩ እንጂ ይህ ሁኔታ አሁንም አልተለወጠም፡፡

በኢትዮጵያ የ1983 የፖለቲካ ለውጥን ተከትሎ መንግሥት ድህነትን በመቀነስ ላይ ያተኮረ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ውጤት ለማስመስገብ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በአንዳንድ ዘርፎችም አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ መንግሥት ከመነሻው ዓይነተኛ የልማት ግቡ ድህነትን መዋጋትና ማስወገድ መሆኑን በማወጅ ተከታታይ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ነድፎ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

በተለይ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታ የሆነውን የግብርናውን ክፍለ-ኢኮኖሚ በማሳደግ ለሌሎች ክፍለ-ኢኮኖሚዎች መንደርደሪያ እንዲሆን የሚያስችል የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ቀርጾ ተግባራዊ አድርጓል። በዚህ መሠረታዊ ግብ ላይ የሚያጠነጥኑ ተከታታይ የልማት ፕላኖችና ፕሮግራሞች ተነድፈው ተግባራዊ ተደርገዋል። የዘላቂ ልማትና ድህነት ማስወገጃ ፕላን (1995-1997)፣ የፈጣንና ዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገጃ ዕቅድ (1998-2002)፣ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድ (2003-2007) እና በቅርቡ ጸድቆ የወጣው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሁለት (2008-2012) ይጠቀሳሉ።

በዚህም ድህነትን በመቀነስና ልማትን በማምጣት ረገድ መልካም ውጤት መገኘቱን የመንግሥትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መረጃዎች ያመለክታሉ። እንደ የዓለም ባንክ ዘገባ ኢትዮጵያ ከእ.ኤ.አ. ከ2000 ጀምሮ ባሉት ዓመታት ከፍተኛ የድህነት ቅነሳ እመርታ አሳይታለች። በቤተሰብ ደረጃ በድህነት ይኖሩ ከነበሩት መካከል 33 ከመቶ መቀነስ ችላለች። የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ለዚህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም ባሻገር መንግሥት ትኩረታቸውን በድሀው የሕብረተሠብ ክፍል ላይ ያደረጉ የመሠረታዊ ግልጋሎቶች አቅርቦትና የገጠር ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ማስፋፋቱ በድህነት ላይ ለታየው ለውጥ በምክንያትነት ተቀምጠዋል። ይህ ሁኔታ በአማካይ በዓመት 10.9 በመቶ ባደገው ኢኮኖሚ ታግዞ ውጤታማ መሆኑ ይዘገባል። የመሠረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦትን በተመለከተ የጤና ኬላዎች ብዛት በእ.ኤ.አ በ2002 ከነበረበት 6,191 በ2013 ወደ 16,048 አድጓል። ይህም የ159 ከመቶ ዕድገት ማለት ነው። በተመሳሳይ የጤና ጣቢያዎች ቁጥር በ386 በመቶ አድጓል።

ነገር ግን አሁንም ድህነት ቅነሳ ላይ አያሌ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ድህነት በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ እንደሆነ ቢነገርም፣ ዛሬም አያሌ ዜጎች በድህነት ውስጥ እየማቀቁ ይገኛሉ። ይህ ሁኔታ በተለይ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ተከትሎ በተከሠተው የኑሮ ውድነት ሳቢያ ተባብሷል። እንዲሁም ተመዘገቡ የተባሉት ውጤቶች በተለይ እንደትምህርትና ጤና የመሣሠሉት መሠረታዊ አገልግሎቶች የአቅርቦት ዕድገት ምን ያህል ከጥራት ጋር ተጣጥሟል የሚለው መሠረታዊ ጥያቄም አብሮ ይነሳል።

በሌላ በኩል ከፍተኛ ዕድገት ተመዝግቦባቸዋል በተባሉት እ.ኤ.አ በ2009 6.2 ሚሊዮን በ2010 ደግሞ 5.2 ሚሊዮን ዜጎች ለዕለት ጉርሳቸው እርዳታ ለመጠበቅ ተገድደው ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ዓመት (2007/8) በደረሰው የአየር መዛባት ሳቢያ በ 2008 ዓ.ም. በገጠር ሴፍቲ ኔት ከታቀፈው 7.9 ሚሊዮን ሕዝብ በተጨማሪ 10.2 ሚሊዮን ሕዝብ የአስቸኳይ ምግብ

እርዳታ የሚያፈልግ መሆኑን መንግሥት መግለጹ ሲታይ በአገርም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ ተጋላጭነታችን አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን ያመለክታል።

**ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** ከተቋቋመበት ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ሕዝባዊ ውይይት ከሚያካሂድባቸው መስኮች መካከል ልማትና የድህነት ቅነሳ እርምጃ አንዱ እንደመሆኑ መጠን ከግንቦት 1993 ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል የዘለቀ **ድህነት ቅነሳ በኢትዮጵያ** በሚል መሪ ርዕስ ስር ሕዝባዊ ውይይቶችን ማካሄዱ ይታወሳል። በዚህም በጊዜው የነበረውን የልማት በተለይ የድህነት ቅነሳ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ በየሴክተሩ የተመዘገቡ ውጤቶችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና ሊወሠዱ የሚገባቸውን ተጓዳኝ እና ማስተካካያ እርምጃዎችንና የፖሊሲ ኃሳቦችን ዳስሷል። በሕዝባዊ ውይይቶቹ ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎችንም ታትመው ለሕዝብ መድረሳቸው ይታወሳል።

ልማትና ድህነት ቅነሳ የማያቋርጥ ሂደት በመሆኑ **ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** ከእነዚህ ሕዝባዊ ውይይቶች ወዲህ የተመዘገቡ ውጤቶችን፣ የሚታዩ ተግዳሮቶችንና ሊወሠዱ የሚገባቸውን ዕርምጃዎች የሚመለከት **‹‹የድህነት ቅነሳ ጥረቶች በኢትዮጵያ››** በሚል መሪ ርዕስ ስር ከጥቅምት 2007 እስከ መስከረም 2008 ድረስ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ አካሂዷል። በዚህ የውይይት መድረክ ላይ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩች ላይ ስድስት የውይይት መነሻ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ውይይቶች ተካሂደዋል። በውይይቶቹ ላይ ጉዳዮቹ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራማሪዎች፣ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ተወካዮች፣ ምሁራን ተካፍለውባቸዋል። በመድረኮቹ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በውይይቶቹ ወቅት በአወያዮችና በተሳታፊዎች በተሰጡ ኃሳቦችና አስተያየቶች ዳብረውና አርትዖት ተደርጎባቸው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካትተዋል።

የመጀመሪያው ጽሑፍ የቀረበው በአቶ አራጋው ይመር ሲሆን ጽሑፉ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦትና የድሆች ተጠቃሚነትን በኢትዮጵያ የሚዳስስ ነው። ጽሑፉ የተለያዩ የመረጃ ምጮችን በመጠቀም በኢትዮጵያ የአነስተኛ ፋይናስ ሁኔታን፣ ተግባራዊ ለማድረግ የወጡ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን፣ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦት፣ ዕድገትና ተግዳሮቶችን በአኃዛዊ መረጃ በማስደገፍ ከመተንተኑ ባሻገር፤ አነስተኛ ፋይናንስን ይበልጥ ለድሀው የሕብረተሠብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግና በድህነት ቅነሳ ውስጥ የበለጠ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወት ለማስቻል አሁን ያለው የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ

በመስኩ እየታዩ ካሉ አዳዲስ ለውጦች አንፃር ዳግም መዳሰስ አስፈላጊ መሆኑን ያሳስባል።

ሁለተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ በዶ/ር ትዝታ ሙሉጌታ የተዘጋጀ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ድህነት እጅግ ጎልቶ ከሚታይባቸው አካባቢዎች አንዱን (በተለምዶ ዶሮ ማነቂያ ሠፈር የሚባለውን) በመውሰድ የከተማ ድህነትን ከሥነ-ጾታ አንፃር የገመገመ ነው። ጽሑፉ ደሀ ሴቶች (በተለይ እማወራዎች) በጾታቸው ምክንያት እንዴት ለተደራራቢ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንደሚጋለጡ የተለያዩ መረጃዎች በማስደገፍ ያብራራል። ምንም እንኳን በቅርብ ዓመታት የተደረጉ የድህነት ቅነሳ ጥረቶች የተወሠኑ ለውጦችን ያመጡ ቢሆንም፣ አሁንም ደሀ ሴቶች በከተሞች ውስጥ ለተለያዩ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮች ተጋላጭነታቸው እንደቀጠለ መሆኑን ያሳያል።

በኢትዮጵያ የአረጋውያንንና አካል ጉዳተኞችን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚዳስሰው ሶስተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ በዶ/ር ፈለቀ ታደለ የቀረበ ነው። ጽሑፉ የአረጋዊነትና አካል ጉዳተኞተኙነትን ትርጓሜ፣ በኢትዮጵያ የአረጋውያንንና አካል ጉዳተኞችን ብዛት፣ ያሉባቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ እነዚህን የሕብረተሠብ ክፍሎች ለመርዳት የወጡ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን ይቃኛል። በመደምደሚያውም ምንም እንኳን በፖሊሲና የማስፈጸሚያ ሕጎችን በሚመለከት በጎ ተግባራት ቢከናወኑም፤ የወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና ደንቦች በማስፈጸምና አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች የተሻለ ሕይወት እንዲመሩ በማስቻል ረገድ ገና ብዙ መሠራት እንዳለበት ያሠምራል።

አራተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ በዶ/ር ገብሬ ኢንቲሶና ባልደረቦቹ የተዘጋጀ ሲሆን በኢትዮጵያ በድህነት ቅነሳና ልማት ጥረት ውስጥ የሲቪል ማኅበራትን ሚና የሚዳስስ ነው። እነዚህ ማኅበራት ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ቁጥራቸው እየጨመረ በመምጣት ከነፍስ አድን እርዳታ ባሻገር በልማት ሥራ በመሣተፍ ዓይነተኛ አጋዥ ኃይል መሆናቸውን ያሳያል። በተጨማሪም ጽሑፉ የሲቪል ማኅበራት በልማትና በድህነት ቅነሳ ጥረት ውስጥ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ፣ ያሉባቸውን ተግዳሮቶችና ሊሻሻሉ ይገባቸዋል የሚላቸውን የፖሊሲና አፈፃፀም ጉዳዮች ያሳያል።

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በድህነት ቅነሳ ላይ ሊጫወት የሚችለውን ሚና የሚቃኘው አምስተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ በአቶ ተሾመ በየነ የቀረበ ሲሆን ክፍለ-ኢኮኖሚው ድህነትን በመቀነስና ልማትን በማሳካት በኩል ከመንግሥት ጋር በመሆን ከፍተኛ ውጤት ሊያስመዘግብ እንደሚችል ያትታል። ጽሑፉ የድህነትን ጽንሠ-ኃሳብ፣ መገለጫዎቹንና የድህነት ቅነሳ ኃሳብን በአጭሩ ከቃኘ

በኋላ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፣ የሥራ ዕድል በመፍጠርና ምርት በማምረት ያስመዘገበውን ውጤት ይተነትናል።

ስድስተኛውና የመጨረሻው ጥናታዊ ጽሑፍ የገጠር የቤተሠብ ድህነትና ምክንያቶቹን የሚመለከት ሲሆን የቀረበውም በዶ/ር አብርሐም ስዩም ነው። ጥናቱ እ.ኤ.አ. በ1994፣ 1999፣ 2004 እና 2009 የተካሄዱትን የኢትዮጵያ የገጠር የቤተሠብ ዳሠሣን (Ethiopia Rural Household Survey - ERHS) ውጤት በመጠቀም በኢኮኖሜትሪክስ ሞዴል በመተንተን በየጊዜው የነበሩትን የገንዘብና የንብረት ድህነት ሁኔታዎችን ያወዳድራል፣ ለውጦችንም ያሳያል። በውጤቱም በአራቱ ጊዜያት የተደረጉትን ዳሠሣዎች በማነፃፀር የገጠር ድህነት እ.ኤ.አ በ1999 እና በ2004 መቀነሱን የሚያሳይ ሲሆን፤ በ2009 መጨመሩን ያመለክታል። ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተጠቀመው የጥናት ዘዴ (ኢኮኖሜትሪክስ ሞዴሎች)፣ የትንተናው አይነትና በውስጡ የያዛቸው ፅንሠ-ኃሳቦች ጥናቱን በአማርኛ ለመተርጎም ያደረግነውን ጥረት በሚገባ ለማሳካት አላስቻሉንም። በመሆኑም ጥናቱን በተጻፈበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት አድርገናል።

በመጨረሻም እነዚህ ጥናታዊ ጽሑፎች በኢትዮጵያ የሚደረገውን ፈርጀ-ብዙ ድህነትን የመቀነስ ጥረቶች በሙሉ ያልሸፈኑ ቢሆንም፤ ይህ መጽሐፍ በዘርፉ ለሚደረጉ የፖሊሲ ውይይቶችና ጥናቶች ግብዓቶችን ይሰጣል የሚል ዕምነት አለን።

አርታዒው

# የአነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦትና  የድሆች ተጠቃሚነት በኢትዮጵያ

አራጋው ይመር

## 1 መግቢያ

ይህ የፖሊሲ መወያያ ጥናታዊ ጽሑፍ በከፊል ቀደም ሲል በመስኩ "*የአብቁተዎች ተቋማዊ አቅም ሁኔታ* (2006)"[1]፣ "*አነስተኛ ፋይናንስ (ማይክሮፋይናንስ)*[2] *አገልግሎት ለሴቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ኢምፓወርመንት ያለው አስተዋፅኦ* (2012)" እና "*የሴቶችና የደሀ ሰዎች አነስተኛ ፋይናንስ ፍላጎት በኢትዮጵያ* (2015)" በሚሉ ርዕሶች በተለያዩ ጊዜያት በተሠሩ ተከታታይ ጥናቶች ላይ ተመርኩዞ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናታዊ ጽሑፉ የተለያዩ ጥናቶች ግኝት ውጤት በመሆኑ አንድ ወጥ የሆነ የምርምር ሥነ-ዘዴ ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም፡፡

የጥናታዊ ጽሑፉ የመጀመሪያ ክፍል መግቢያን፣ የጥናቱ ዓላማዎችንና የምርምር ዘዴዎችን ሲይዝ፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ አጭር ዕይታና የአነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት ፅንሠ-ኃሳባዊ ማብራሪያ ይዟል፡፡ ክፍል ሦስት የአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፍን ይዳስሳል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ለድሆች አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነትንና አቅርቦትን ዕድገት ይመረምራል፡፡ ክፍል አራትና አምስት አነስተኛ ፋይናንስ ለድህነት ቅነሳ ያለውን አስተዋፅኦ ሲዳስስ፤ ክፍል አምስት በዘርፉ ያሉትን ችግሮችና ተግዳሮቶችን በመዘርዘር የፖሊሲ ምክረ-ኃሳቦችን ያመላክታል፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ለድሆች የሚሰጠውን አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት ሁኔታን፣  ያጋጠሙ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን በመፈተሽ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆን በመረጃ የተደገፈ ኃሳብ ማቅረብ ሲሆን፤ በዝርዝር ሲታይ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ዓላማዎች አሉት፡-

- በኢትዮጵያ የድህነት ሁኔታን በአጭሩ መዘገብ፣
- ለድሆች አነስተኛ የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮችን መፈተሽና ተደራሽነትን መገምገም፣

[1] በልዩነት ካልተገለፀ በስተቀር ሁሉም ዓመተ ምህረቶች እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ናቸው፡፡

[2] አነስተኛ ፋይናንስ እና ማይክሮፋይናንስ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው አንዳንድ ጊዜ በማቀያየር ተጠቅመንባቸዋል፡፡

- ድህነት ተኮር የፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት ተደራሽነትን መዳሰስ፣
- የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አነስተኛ የፋይናንስ አቅርቦት ፕሮግራሞችን በመፈተሽና ያጋጠሙ ችግሮችን በመንቀስ የፖሊሲ ግብዓት ምክረ-ኃሳብ ማመንጨት ናቸው።

## 1.2 የምርምር ዘዴዎች

ከላይ በመግቢያው ለመጥቀስ እንደተሞከረው ጥናቱ በከፊል የተከታታይ ዓመታት ጥናት ውጤት ስለሆነ ወጥ የሆነ የምርምር ሥነ-ዘዴ ይኖረዋል ተብሎ ባይገመትም የወቅቱን ሁኔታ  ለመረዳት ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች እንዲካተቱበት ተደርጓል። በዚህ መሠረት ተጨማሪ መረጃዎች በሚያዝያና ግንቦት ወሮች 2015 ዓ.ም በቃለ-መጠይቅ፣ ከኦፊሴላዊ ሪፖርትና ከሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ተሠብስበዋል። በዚህም መሠረት ሀተታዊ እና አሃዛዊ መረጃዎችን ከፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ፣ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ዳይሬክቶሬት፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ተሰብስቧል። በተጨማሪም ከ8 ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት፣ 2 ኅብረቶች እና ከ4 አብቁተዎች ከተመረጡ ቁልፍ መረጃ ሠጪዎች (Key Informants) ጋር ቃለ-መጠይቅ ተካሂዷል።

# 2 የድህነት እና የአነስተኛ ፋይናንስ (ማይክሮፋይናንስ) ሁኔታ በአጭሩ

## 2.1 የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ አጭር ምልከታ

ፍፁም ድህነት (Absolute poverty) በኢትዮጵያ የሚለካው የአንድ ቤተሠብ ፍጆታ በአንድ ጎልማሳ ፍጆታ መጠን ተሠልቶ በ2011 ዓ.ም ከተቀመጠው የብሔራዊ ድህነት ወለል መጠን ብር 3,781 ጋር በማወዳደር ነው። ይህ የድህነት ወለል መጠን ለምግብና ከምግብ ውጭ የሆኑ ፍጆታዎችን በዓመት ለማሟላት የሚያስችል ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ነው። በተጨማሪ 3 በስፋት የሚጠቀሱ የድህነት መለኪያ ዘዴዎች አሉ። "የድህነት ክስተት ብዛት" (Incidence of poverty/Head count index) የሚባለው የመጀመሪያው ሲሆን፤ መለኪያው ከጠቅላላው የሕዝብ ቁጥር ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ሰዎችን አንፃራዊ ብዛት (Proportion) ያመለክታል። "የድህነት ጥልቀት" (Depth of poverty/Poverty gap) የሚባለው ሁለተኛው መለኪያ ደሀ ሰዎች ከድህነት ወለል በታች ምን ያህል ርቀት ላይ እንዳሉ የሚያሳይ ነው። ይህ ማለት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ሰዎች ፍጆታ በአማካይ ከድህነት ወለል (3,781 ብር በዓመት) በታች በምን ያህል እጥረት መኖሩን የሚያሳይ ነው። መለኪያው ሁሉንም ሕዝብ ከድህነት ለማውጣት የሚያስችል አስፈላጊ የኃብት መጠንን በእያንዳንዱ ግለሠብ ደረጃ አስልቶ ለማወቅ ያገለግላል። "የድህነት

መንሰራፋት" (Poverty severity/Squared poverty gap) የሚባለው ሶስተኛው መለኪያ ከድህነት ወለል በታች የድሆችን ርቀት መጠን እና በድሆች መካከል ያለውን የኃብት ልዩነት (inequality) መጠንን በማጣመር የሚለካ ነው (World Bank, 2013:3)።

ከ1990ዎቹ ጀምሮ ኢትዮጵያ የምትከተለው የ"ልማታዊ መንግሥት" ሞዴል ዓላማ ድህነት ቅነሳ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ይህ ሞዴል በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች መንግሥት ጠንካራ ሚና እንዲኖረው እና በመሠረታዊ ግልጋሎቶች ላይ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ከፍተኛ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። የግብርና መር ኢንዱስትሪ ስትራቴጂ "የግብርናው ዕድገት አጠቃላይ የኢኮኖሚውን ዕመርታ ይፈጥራል" በሚል ዕሳቤ ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት በድህነት ቅነሳ ላይ ያተኮረ ዘርፈ ብዙ የፖሊሲ ስትራቴጂዎችንና አቅጣጫዎችን በመተግበር ብሔራዊ የኢኮኖሚ ልማት ግቦችን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል። ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የኢትጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ 8.3% ዓመታዊ ዕድገት በማሳየት ላለፉት 10 ዓመታት አመርቂ ዕድገት አስመዝግቧል (World Bank, 2013)። ምንም እንኳን ዕሴት በመፍጠር ረገድ የግብርናው ዘርፍ አሁንም ከፍተኛ ቢሆንም፤ የዘርፉ ድርሻ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረደ መጥቷል (በ2004 ዓ.ም ካለው የ52% ድርሻ በ2014 ወደ 40% ዝቅ ብሏል)። በአንፃሩ የአገልግሎት ዘርፉ ድርሻ እየጨመረ በመሄድ በ2004 ዓ.ም ከነበረው የ37% ድርሻ በ2014 ወደ 46% ከፍ ብሏል።

እንደ የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ የድህነት ዳሰሳ ሪፖርት (2015) ኢትዮጵያ ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ አመርቂ የድህነት ቅነሳና የጋራ ብልፅግና አሳይታለች። ለምሳሌ በ2000 ዓ.ም ኢትዮጵያ ከዓለም በከፍተኛ የድህነት መጠን ላይ እንደነበረችና 56% ያህሉ የአገሪቱ ሕዝብ በቀን ከአሜሪካን ዶላር 1.25 (የመግዛት አቅም ምጣኔ) በታች እና 44% ከብሔራዊ የድህነት ወለል በታች ይኖር እንደነበር በጊዜው የነበረው መረጃ ያሳያል። በ2011 ዓ.ም ግን ከ30% በታች የሆነው የአገሪቱ ሕዝብ ብቻ ከብሔራዊ የድህነት ወለል በታች እና 31% ያህሉ ደግሞ በቀን ከ1.25 የአሜሪካን ዶላር (የመግዛት አቅም ምጣኔ) በታች ይኖራል።

### 2.1.1 የድህነት ቅነሳ ገፅታዎች በኢትዮጵያ

1. *ከ10 እስከ 15 ዓመታት በፊት ድህነት አስከፊ በነበረባቸው ክልሎች የታየው የድህነት ቅነሳ ፈጣን መሆን*- በ1996 ዓ.ም የድህነት ሁኔታ በተለያዩ ክልሎች የተለያየ ሥፋትና ጥልቀት ነበረው። ለምሳሌ በትግራይ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ክልሎች 56% ድሆች የነበሩ ሲሆን፤ በኦሮሚያ ግን 34% ነበር። ነገር ግን በተገኘው የግብርና ዕድገትና የመሠረታዊ ግልጋሎቶች መሻሻል

በ2011 ዓ.ም የድህነት ሁኔታ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ተቀራራቢ መጠን በማሳየት ወደ 30% ቀንሷል። በከተማና በገጠር ያለው የድህነት ሁኔታም ክፍተቱ እየጠበበ መጥቷል።

2. *የተለያዩ መሠረታዊ ግልጋሎቶች ጥቅል እጦትን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ መሻሻል መታየት*፡- በተለይም በገጠር የአገሪቱ ክፍሎች የጤና፣ የትምህርት እና ንፁህ የመጠጥ ውኃ ሦስቱንም በአንድ ወቅት እጥረት የነበረባቸው ከ10 ቤተሠቦች አራቱ የነበሩ ሲሆን፤ አሁን ግን ከአስሩ አንድ ቤተሠብ ብቻ ሆኗል። የትምህርት፣ ጤናና የንፅህና (Sanitation) ተደራሽነት በፈጣን ሁኔታ በመሻሻሉ ተጠቂና ተጎጂ የነበሩ የሕብረተሠብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል። አጠቃላይ የወሊድ ምጣኔ በ1995 ዓ.ም 7 ልጆች በ1 እናት የነበረ ሲሆን፤ በ2011 ግን ወደ 4 ልጆች በ1 እናት ደረጃ ወርዷል። በተመሳሳይ መልክ የሕጻናት መቀጨጭ ከ58% ወደ 44% ዝቅ ብሏል። ትምህርት አልባ የሕዝብ ቁጥር ከ70% ወደ 50% ዝቅ ብሏል። የመብራትና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት በእጥፍ ዕድገት አሳይቷል።

3. *የኑሮ ሁኔታ ልዩነት (inequality) በተለይ በገጠር ዝቅተኛ መሆን*፡- በገጠሩ ክፍል የኑሮ ሁኔታ በአብዛኛው ዝቅተኛ በመሆኑ የተነሳ በአጠቃላይ በአገሪቱ የኑሮ ሁኔታ (ኃብት) ልዩነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህ ሁኔታ ከ2005 እስከ 2011 ባሉት ዓመታት በከተሞች ሲታይ መጠነኛ ለውጥ ያሳያል።

### 2.1.2 ወሳኝ የድህነት ቅነሳ መዘውሮች (Key drivers of poverty reduction)

በድህነት ቅነሳው ጥረት ሒደት ውስጥ ዋና ዋና መዘውር የነበሩት የሚከተሉት ናቸው።

- የግብርና ዕድገት፡- የ1% የግብርናው ኢኮኖሚ ዕድገት ለ0.9% የድህነት ቅነሳ አስተዋፅኦ አድርጓል፣
- ድህነት ተኮር የመሠረታዊ ግልጋሎቶች አቅርቦት፣
- ውጤታማ የገጠር ሴፍትኔት ፕሮግራም፣
- የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገት ለከተማ ድህነት ቅነሳ መጠነኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፣
- የአገልግሎት ዘርፍ ለድህነት ቅነሳ ያደረገው አስተዋፅኦ ዘርፉ ካሳየው ዕድገት አንፃር በጣም ውስን ነው። ለዚህ ዋናው ምክንያት በዘርፉ የተሰማሩ የድሆች ቁጥር በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ነው።

### 2.1.3 **ተግዳሮቶች**

ሀ. በአገሪቱ አሁንም የድህነት ምጣኔ ከፍተኛ መሆንና እንዲሁም ከ2005 ዓ.ም ወዲህ የደሀ ደሀ በሆነው የሕብረተሠብ ክፍል የፍጆታ መጠን የተሻለ ለውጥ አለመታየቱ፣

ለ. የትምህርት፣ የጤና፣ የንፁህ ውኃ እና የንፅህና ግልጋሎቶች በበቂ ሁኔታ አለመዳረስ፤

ሐ. ለድህነት ተጋላጭነት መጠን (Vulnerablity) ከፍተኛ መሆን፡- ለምሳሌ በ2002 እንደደረሠው ዓይነት ድርቅ ቢያጋጥም የድህነት ምጣኔው ከ30% ወደ 51% ከፍ እንደሚል የትንበያ መስፈርቶች ያሳያሉ:: በተጨማሪ 14% ያህል ከድህነት ወለል በላይ የሚገኘው የሕብረተሠብ ክፍል በአንድ ወቅት ላይ በሚከሰት የዋጋ ንረት ወይም የአየር ንብረት መዛባት ተመልሶ ከድህነት ወለል በታች የመግባት ዕድሉ ከፍተኛ እንደሚሆን ተጠቁሟል፤

መ. የመዋቅራዊ[3] ለውጥ ያለመኖር፡- እስከአሁን በታየው አስገራሚ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የመዋቅራዊ ለውጥ ያለመኖር ትልቅ ተግዳሮት መሆኑ ተጠቁሟል፤

ሠ. የመልክዐ-ምድር ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆን፡- ለከተማ ቅርበት ባላቸው ቦታዎች የሚታየው ዕድገት በርቀት ከሚገኙ የሕብረተሠብ ክፍሎች በጣም የተሻለ መሆኑ ናቸው::

### 2.1.4 **ቀጣይ ምክረ ኃሳቦች፡**

- እየታየ ያለውን የግብርና ዕድገትና ድህነት ተኮር የመሠረተ-ልማት ግንባታ ማስቀጠል፣
- ከግብርና ውጭ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን (Non-Farm Enterprises) ሚናን ማሳደግ፣
- ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሠት ላይ ትኩረት መስጠት (ለምሳሌ የመሬት ይዞታ አስገዳጅነትን በማሻሻል)፣
- የከተማ ሴፍቲኔት ፕሮግራምን በመተግበር ለከተማ ድህነት ቅነሳ ትኩረት መስጠት፣
- የሴት አርሶና አርብቶ አደሮችን ምርታማነት ማሻሻል::

[3] በዚህ ጽሑፍ አገባብ መሠረት መዋቅራዊ ለውጥ ማለት ከግብርና ወደ ሌሎች የኢኮኖሚ ተግባራት የሚደረግ ሽግግርን እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የሰዎች እንቅስቃሴን ያካትታል፡፡

## 2.2 የአነስተኛ ፋይናንስ ፅንሠ-ኃሳብ እና አስፈላጊነት በአጭሩ

አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ማለት አነስተኛ ብድር፣ ቁጠባ፣ መድን፣ ሐዋላ፣ ገንዘብ አስተዳደር፣ የፋይናንስ ሊዝ እና ሌሎችንም ተመሳሳይ አገልግሎቶችን በተለያዩ የሥራ መስኮች (በግብርና፣ በአሳ ማስገር፣ በንብ ማነብ፣ በከብት ማድለብ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን በማንቀሳቀስ፣ በማምረት፣ በአገልግሎትና በንግድ፣ ወዘተ.) ለተሠማሩ ግለሠቦች፣ ቡድኖችና የሕብረተሠብ ክፍሎች በገጠርና በከተማ ማቅረብና ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚደረገው እነዚህ የሕብረተሠብ ክፍሎች፣ ቡድኖችና ግለሠቦች ብዙውን ጊዜ ለመደበኛ የባንክና ኢንሹራንስ አገልግሎቶች ተደራሽ ባለመሆናቸው ነው፡፡

ከባንግላዲሽ መልካም ተሞክሮ በመነሳት በዓለም ላይ በሚገኙ ታዳጊ አገራት በሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ አነስተኛ ፋይናንስ (ማይክሮፋይናንስ) ለልማት ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ዋነኛ መሣሪያ እንደሆነ በመገንዘብ ላለፉት 15 ዓመታት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ማይክሮፋይናንስ ከሁሉም አፍ የማይለይ ቃል ሆኗል፡፡ በዚህም የተነሳ በዓለም ላይ በአሁኑ ሰዓት የማይክሮፋይናንስ ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር ከ130 ሚሊዮን በላይ ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት በ1990ዎቹ በወሰዳቸው ብዙ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ለውጦች ውስጥ ማይክሮፋይናንስ እና ሕብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነተኛ የድህነት ቅነሳ መሣሪያዎች መሆናቸውን በመገንዘብ በሁሉም የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ውስጥ ትኩረት ሰጥቷቸዋል፡፡ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2010) የብሔራዊ ወጣቶች ፖሊሲ (2004)፣ የሥርዓተ-ጾታ ልማት ፕሮግራም (2001)፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስትራቴጂ (2012)፣ የግብርና እና ገጠር ልማት ስትራቴጂ፣ የብሔራዊ ማኅበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ (2015) ሁሉ ለማይክሮፋይናንስ እና ሕብረት ሥራ ማኅበራት ልዩ ትኩረት በመስጠት ወሳኝ የማስፈፀሚያ መሣሪያ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

# 3 የአነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎትና አቅርቦት ዕድገት በኢትዮጵያ

ይህ ክፍል ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት የአነስተኛ ፋይናንስ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም በአጭሩ በመቃኘት አነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦት ለድሆች ያስገኘውን ውጤት፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን እና ክፍተቶችን በመንቀስ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ምክረ-ኃሳቦችን ያመላክታል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በኢትዮጵያ አነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት በመደበኛ እና ኢ-መደበኛ በሆኑ ተቋማት ይሰጣል፡፡ የኢ-መደበኛ ተቋማት (ዕቁብ፣ ዕድር፣ ማኅበር እና ሌሎች የራስ አገዝ ቡድኖች) አገልግሎት አስተዋፅኦ ለተመራማሪዎች፣ ለፖሊሲ አውጪዎች እና ለልማት ዕቅድ ነዳፊዎች በአብዛኛው ግልፅ አይደለም፡፡ በመስኩም የተደረጉ ጥናቶች በጣም ውስን ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሠንጠረዥ 1 የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን ቁጥር፣ ባህሪና ስብጥር በአጭሩ ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡-** መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የሆኑ የማይክሮፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢ ተቋማት ሁኔታ፡፡

| ተቁ | የተቋማት ሥም | ብዛት | ባሕሪያት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | አደረጃጀት | መስራችና አመሠራረት | ዓይነት |
| 1 | አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት (አብቁተዎች) | 40 | አክሲዮን/ኩባንያ | መንግሥት፤ ሲቪል ሶሳይቲ፤ግለሠቦች | መደበኛ |
| 2 | ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት | 14,453 | አባላት ተኮር | ሲቪል ሶሳይቲ፤ መንግሥት | መደበኛ |
| 3 | ራስ አገዝ ቡድኖች | 10,521 | አባላት ተኮር | ሲቪል ሶሳይቲ | ኢ-መደበኛ |
| 4 | ባሕላዊ ማኅበራት (ዕድር፣ ዕቁብና ማኅበር የመሣሠሉት) | --- | አባላት ተኮር | የማኅበረሠብ አባላት | ከፊል መደበኛ |

ምንጭ፡- Own Survey from FCA, (2014); CoSAP, (2014); NBE, (2014)

ሆኖም የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማ በመደበኛ ሁኔታ የማክሮፋይናንስ አቅርቦት ሥራ ላይ የተሠማሩ ተቋማት አገልግሎታቸው ለደሀው የሕብረተሠብ ክፍል ያለውን ተደራሽነት መዳሰስ በመሆኑ በአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት (አብቁተዎች) እና በቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

በኢትዮጵያ በሕግ የታቀፈ የማይክሮፋይናንስ አገልግሎት መስጠት የተጀመረው ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የማይክሮፋይናንስ ሴክተር በቁጥር፣ በተደራሽነትና በዓይነት ከፍተኛ የሆነ ዕድገት አሳይቷል፡፡

## 3.1 የኢትዮጵያ የማይክሮፋይናንስ ፖሊሲ አጭር ዕይታ

እንደ ሌሎች የልማት ሴክተሮች ሁሉ የፋይናንስ ሴክተር ሊበራላይዜሽን የፋይናንስ ሴክተር ስትራቴጂ ለውጥን በማስከተል ከንግድ ባንኮች በተጨማሪ የማይክሮፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቶችን ማቋቋምና ማሳደግ አስፈላጊነትን አመላክቷል፡፡ በዚህ

ረገድ የሴክተሩ ስትራቴጂ በዋናነት የማክሮፋይናንስ ተቋማት በሂደት ወደ ገጠር ባንክነት እንዲሸጋገሩ እና ከንግድ ባንኮች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የገንዘብ ፍሠቱን ማጠናከር እንደሚገባ ይጠቁማል። በተጨማሪም የአገር ውስጥ ቁጠባን ለማሳደግ፣ በገጠር የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋፋት እና ሁለገብ የፋይናንስ አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችል አዋጅ እና የሕግ ማዕቀፍ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ አድርጓል።

በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 40/96 እና አዋጅ ቁጥር 626/2009 የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት (አብቁተዎች) ግልጋሎትን በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 147/98 እና አዋጅ ቁጥር 402/2004 ደግሞ ለቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የወጡ የሕግ ማዕቀፍ አዋጆች ናቸው። ከእነዚህ አዋጆች በተጨማሪ በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ውስጥ ማይክሮፋይናንስ እና ሕብረት ሥራ ማኅበራት ዋና የማስፈፀሚያ መሣሪያዎች መሆናቸው በትኩረትና በብዛት ተጠቅሷል። ለምሳሌ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2010)፡ የአገር አቀፍ የወጣቶች ፖሊሲና (2004) የከተማና ገጠር ወጣቶች ልማት ፓኬጅ፤ የሥርዓተ-ጾታና ልማት ፕሮግራም (2001)፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስትራቴጂ (2012)፣ የግብርና እና ገጠር ልማት ስትራቴጂ፣ የብሔራዊ ማኅበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ (2015) ወዘተ. የማክሮፋይናንስ አቅርቦትና የሕብረት ሥራ ማኅበራት ግንባታ አስፈላጊ የማስፈጸሚያ መሣሪያዎች እንደሆኑ በአትኩሮት ይገልፃሉ።

### 3.1.1 የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት (አብቁተዎች)ፖሊሲ ማዕቀፍ

የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ሥራን፣ ፈቃድና ሱፐርቪዥን ሁኔታን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ (40/96) እና በተከታይ በብሔራዊ ባንክ የተደነገጉ 17 መመሪያዎች በመስኩ የመጀመሪያና መነሻ የሕግ ማዕቀፎች ሲሆኑ፤ በዚሁ ሴክተር በታየው ዕድገት መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥትና ብሔራዊ ባንክ ቀጣይ ማሻሻያ በማድረግ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2009ን እና ተከታይ 19 መመሪያዎችን አውጥተዋል።

አዋጅ ቁጥር 40/96 አነስተኛ የፋይናንስ ሥራን "ማንኛውም አነስተኛ ብድርን በገንዘብም ሆነ በዓይነት ለአርሶ አደሮች ወይም ለከተማ አነስተኛና ጥቃቅን አንቀሳቃሾች የሚያቀርብ ተግባር" በማለት ይተረጉመዋል። ይህ ትርጉም በተሻሻለው አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2009 የበለጠ ተብራርቶ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ተግባር "በከተማና በገጠር ለሚገኙ ገበሬዎች፣ ሌሎች በተመሣሣይ ተግባር ለተሠማሩ ሰዎች፣ እንዲሁም በከተማና በገጠር ለሚገኙ

ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት አንቀሳቃሾች ብድርን የማቅረብ፣ ቁጠባን የመሠብሠብ እና ሌሎች ፋይናንስና ተዛማጅ ሥራዎችን የማከናወን ሲሆን፤ የብድር ጣሪያውም በብሔራዊ ባንክ እነደሚወሰን" ይደነግጋል።

እንደአዋጆቹ አገላለፅ የእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች ዋና ዓላማ "በገጠር በግብርናና መሠል ሥራዎች እንዲሁም በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሠማሩ ሰዎች የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት አነስተኛ ፋይናንስ ዕድገትና ጤናማነት ይበልጥ እንዲጎለብት ተስማሚ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ መኖር አስፈላጊ በመሆኑ" ነው።

በዚህም መሠረት አዋጁ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ፈቃድ የመስጠት የመከታተል እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል። አነስተኛ ብድር እና ቁጠባ ተቋማትም በራሳቸው በመሰባሰብ የኢትዮጵያ አነስተኛ ብድር እና ቁጠባ አቅራቢ ተቋማት ማኅበርን (Association of Ethiopian Microfinance Institutions) መስርተዋል።

በአዋጅ ቁጥር 626/2009 አንቀጽ 3(2) ስር እንደተገለፀው የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት (አብቁተዎች) ተግባራት፡-

- የፈቃደኝነትና የግዴታ ቁጠባን እንዲሁም የፍላጎትና የጊዜ ገደብ ተቀማጮችን መቀበል፣
- የብድር አገልግሎትን በገጠር በግብርና እና በሌሎች መሠል ሥራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሠማሩ ሰዎች ማቅረብ፣
- የአገር ውስጥ የሐዋላ አገልግሎት መሥጠት፣
- በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የአነስተኛ መድን ሽፋን መስጠት፣
- እንደ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሠነድ  እና መሠል የአጭር ጊዜ ገቢ አመንጪ የፋይናንስ መሣሪያዎችን መግዛት፣
- ተንቀሳቃሽና ተንቀሳቃሽ ያልሆኑ ንብረቶችን መያዝና ማስተላለፍ፣
- ለደንበኞች የሥራ አመራር፣ የገበያ፣ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- በካፒታል ዕቃዎች ሊዝ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1998 መሠረት የፋይናንስ ሊዝ ግልጋሎትን መስጠት፣ እና
- በሌሎች በብሔራዊ ባንክ በተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች መሠማራት ናቸው።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ አቅራቢ ተቋማትን ለማቋቋም ከታች በሠንጠረዥ 2 የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላት እንደሚኖርባቸው አዋጁ ይደነግጋል።

## ሠንጠረዥ 2፡- አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ወደ ሥራ ለመግባት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡፡

| መስፈርት | አስፈላጊ ሁኔታዎች |
|---|---|
| ዝቅተኛ የካፒታል መጠን | አዲስ አብቁተ ለማቋቋም 200,000 ብር ወይም 10,000 የአሜሪካን ዶላር፡፡ |
| ተቋማዊ ምስረታና ባለቤትነት | አብቁተዎች ለኢትዮጵያዊያን ብቻ የተፈቀዱ ሲሆን በአክሲዮን ማኅበር ቅርፅ ይመሠረታሉ፡፡ |
| ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ | ዋና ሥራ አስኪያጁ በማኅበራዊ ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪስራ አስኪያጁ በማኅበራዊ ሳይንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው ሆኖ 3 እና ከዚያ በላይ ዓመት በፋይናንስና ተዛማጅ ተቋማት አገልግሎት እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡ የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አባላት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ |
| ብድርና የብድር ጣሪያ | ብድር በቡድን፤ በግለሠብ ደረጃ፡ በመያዣ/ዋስትና ከመያዣ/ዋስትና ውጭ ማበደር እንደሚቻል ሆኖ ሙሉ ለሙሉ ውሳኔው የተቋሙ ይሆናል፡፡ የግለሠብ እና የቡድን ብድር ጣሪያ ከተቋሙ አጠቃላይ ካፒታል ከ1% እና 4% እንደ ቅደም ተከተሉ መብለጥ አይኖርበትም፡፡ |
| የወለድ ምጣኔ | ለቁጠባ እና ተቀማጭ ገንዘብ ዝቅተኛ የወለድ መጠን 4% ሲሆን የብድር የወለድ መጠን በሥራ አመራር ቦርድ ይወሰናል፡፡ |

ምንጭ: FDRE, (2009)

### *በአነስተኛ ብድርና ቁጠባ አቅራቢ ተቋማት የሕግ ማዕቀፍ የታዩ ዕድገቶች*

ከዚህ በታች የቀረቡት ጠቃሚ ነጥቦች በተሻሻለው አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ የተካተቱ ናቸው፡፡

- የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ ትርጓሜ ሰፊ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትት መሆኑ፤ (ማለትም ብድር፣ ቁጠባ፣ ሐዋላ፣ አነስተኛ መድን፣ እና ሌሎች ተዛማጅ ግን ከፋይናንስ ሥራ ውጭ የሆኑ ተግባራትን እንዲጠቃለል መደረጉ)፣
- የንግድ ባንኮች ተጨማሪ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ መሣተፍ እንዲችሉ መፈቀዱ፣
- አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ እስካሟሉ ድረስ አነስተኛ ብድርና ቁጠባ አቅራቢ ተቋማት ወደ ንግድ ባንክነት ማደግ የሚችሉ መሆናቸው፣
- የብድር አሠጣጥ ዘዴው እንደተጨባጭ ሁኔታው ለማድረግ የተፈቀደ መሆኑ፣
- የብድር ጣሪያው መነሳት፣
- የብሔራዊ ባንክ የሥራ ድርሻ በግልፅ የተደነገገ መሆኑ ናቸው፡፡

### 3.1.2 የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የሕግ ማዕቀፍ

ለቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የተለየ የሕግ ማዕቀፍ ባይኖርም አዋጅ ቁጥር 147/1998 እና የሕብረት ሥራ ማኅበራት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/2004 ጠቅላላ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን አሠራር ይወስናሉ። የሕብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1998 ሠፊ ጉዳዮችን የሚያካትት ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ትርጓሜ፣ ዓላማ፣ መርሆዎች፣ አመሠራረትና ምዝገባ፣ መብትና ግዴታ፣ የሥራ አመራር ኃላፊነትና ግዴታ፣ ልዩ ጥቅም፣ ዕሴትና ንዋይ አስተዳደር፣ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ውህደትና መከፋፈል እና የመንግሥት ድጋፍ ያጠቃለሉ ጉዳዮችን ይደነግጋል።

እንደ አዋጁ መንፈስ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን የማቋቋም ዋናው ምክንያት ተመሳሳይ ፍላጐት ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሕብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ ዕውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር በቁጠባና እርስ በርስ በመደጋገፍ በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማስቻል መሆኑ ተመልክቷል። በተጨማሪም አዋጁ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ሉዓላዊ ራስን የማስተዳደር (autonomy) መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 2 እንደሚያሳየው የሕብረት ሥራ ማኅበራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማኅበራት ያካትታል።

ሀ. የገበሬዎች የሕብረት ሥራ ማኅበራት፤
ለ. የመኖሪያ ቤት የሕብረት ሥራ ማኅበራት፤
ሐ. የኢንዱስትሪና የዕደ ጥበብ የሕብረት ሥራ ማኅበራት፤
መ. የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት፤
ሠ. የገንዘብ ቁጠባና ብድር የሕብረት ሥራ ማኅበራት፤
ረ. የዓሳ አስጋሪዎች የሕብረት ሥራ ማኅበራት፤
ሰ. የማዕድን የሕብረት ሥራ ማኅበራት።

አንቀፅ 4 በተጨማሪ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ዓላማዎችን እንደሚከተለው ይዘረዝራል፡-

1. አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን ችግሮች በጋራ መፍታት፣
2. አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ኃብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ማግኘት፣
3. በራስ መተማመንን ማጎልበት፣
4. የኢኮኖሚ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መከላከል፣ መቋቋምና ማስወገድ፣

5. ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን በመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብዓት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ፣ ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ፣
6. የቴክኒክ ዕውቀትን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ዘዴዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፣
7. የቁጠባና ብድር አገልግሎት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ማድረግ፣
8. አባላቱ በግላቸው ቢሠሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሳራ በጋራ በመካፈል የእያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሳራ መካፈል፣
9. አባላትን በማስተማርና በማሠልጠን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅማቸውንና ባሕላቸውን ማጎልበት ናቸው::

### 3.1.3 የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የሕግ ማዕቀፍ ዕድገት

የፋይናንስ ጉዳይን በተመለከተ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ማሻሻያ አዋጅ ቀጥር 402/2004 አንቀፅ 16 (1-7) እንደሚያሳየው በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ማንኛውም የሕብረት ሥራ ማኅበር፡-

1. ሥራውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን ካፒታል ማግኘት እንዲችል ዕኩል ዋጋና ብዛት ያላቸውን ዕጣዎች በጠቅላላ ጉባዔው አስወስኖ እንዲሸጡ ያደርጋል፣
2. ሲመሰረት በጠቅላላ ጉባዔ እንዲሸጥ ከተወሰነው ዕጣ መጠን ውስጥ ቢያንስ 1/5ኛው ከአባላት ይሠበስባል፣
3. ቀሪውን ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ ባሉት 4 ዓመታት ውስጥ መሸጥ ይኖርበታል፣
4. በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሠረት ተጨማሪ ካፒታል ካስፈለገ ተጨማሪ ዕጣዎች ይሸጣል፣
5. የካፒታል እጥረት ያጋጠመው ማኅበር የማኅበሩን መርሕ በማይቃረን ሁኔታ የተወሰነ ዕጣ የማኅበሩ አባል ላልሆነ ሰው መሸጥ ይችላል፣
6. በማኅበሩ ደንብ መሠረት ከአባት ወይም ከሌላ ድርጅት መበደር ወይም ቁጠባ መቀበል ይችላል፣
7. ከአባላት ውጭ ብድር ማበደር አይፈቀድም፣
8. ከአባላት ወይም ከሌላ ድርጅት ለሚሠበሠብ ቁጠባ ወለድ ከባንክ ወለድ መብለጥ የለበትም::

በዚህ መሠረት የሕብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴን ለመምራት ራሱን የቻለ ተቋም በማስፈለጉ የፌዴራል የሕብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ተቋቁሞ በአገሪቱ

በሚገኙ ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች በተዋረድ ጽ/ቤቱን አቋቁሟል፡፡ የዚህ መንግሥታዊ ተቋም ዋና ዓላማ የሕብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴን ለማገዝና ለማስፋፋት፣ ለማጐልበትና የቴክኒክ ዕገዛ ለመስጠት፣ የአቅም ግንባታና ሌሎች ግብዓቶችንም ለመስጠት ነው፡፡ በተጨማሪም የሕብረት ሥራ ማኅበራት ሦስት ተዋረዳዊ አደረጃጀቶች እንዳሏቸው ይታወቃል፡፡ እነሱም የመጀመሪያ የሕብረት ሥራ ማኅበር፣ የሕብረት ሥራ ሕብረት እና የሕብረት ሥራ ፌዴሬሽን እና ሌጉ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ እንደታየው በኢትዮጵያ ያለው የፖሊሲ ማዕቀፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እና እያደገ የመጣ ቢሆንም በአገሪቱ አነስተኛ የፋይናንስ አልግሎት በሁለት የተለያዩ ተቋማት ማለትም በብሔራዊ ባንክና በፌዴራል የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ አስተባባሪነት ይመራል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በአነስተኛ የፋይናንስ አልግሎት አቅርቦት መሳለጥና ቅንጅት ላይ አሉታዊ ውጤት እንዳያመጣ ጥንቃቄ መወሠድ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም አሁን ባለው ሁኔታ ለቁጠባና ብድር የሕብረት ሥራ ማኅበራት የተለየ ፖሊሲ ባለመኖሩ ሁሉም ዓይነት የሕብረት ሥራ ማኅበራት በአንድ የሕግ ማዕቀፍ ሥር እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ግን ከሚሠሩት የፋይናንስ ሥራ አኳያ የተለየ የፖሊሲ አቅጣጫ እንደሚያስፈልጋቸው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የሕብረት ሥራ ባንክ፣ የሕብረት ሥራ መድን እና የመሣሠሉትን ተቋማት ለመፍጠር የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ ያለመኖር በተጨማሪ የሚታይ የፖሊሲ ክፍተት ከመሆኑም ባሻገር፤ ለወደፊት ሁሉን ያካተተ አነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት ለመፍጠር ከወዲሁ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

## 3.2 በኢትዮጵያ የአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዕድገትና ውጤት

መደበኛ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት በኢትዮጵያ የተጀመረው በ1996 ዓ.ም ቢሆንም ኢንዱስትሪው ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ ዕድገትና መስፋፋት አስመዝግቧል፡፡ ሆኖም እስከ አሁን ድረስ በጣም ትልቁን ድርሻ የያዙት የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት (አብቁተዎች) ናቸው፡፡ የአብቁተዎች ብዝኃነት፣ ፈጠራና ዕድገት አነስተኛ የፋይናንስ ቢዝነስ በፈጣን ለውጥ ውስጥ እንዲገኝ አድርጐታል፡፡ አሁን ባለው ወቅታዊ መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ 40 የሚደርሱ አብቁተዎች ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ ቢሆንም 35 ያህሉ ብቻ በተከታታይ ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት እንደሚያደርጉ ታውቋል፡፡

ከዚህ በታች በምስል 1 እንደቀረበው አነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶች ካፒታል/ንዋይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደገ መሔዱ ይታያል፡፡ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የአብቁተዎች ካፒታል ከመንግሥት ወይም ከሲቪል ሶሳይቲ የተገኘ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ሁሉም አብቁተዎች ተመሳሳይ መጠን የሌላቸው ሲሆን፤ አራቱ

አብቁተዎች ማለትም የአማራ፣ የአዲስ አበባ፣ የኦሮሚያ እና ደደቢት አብቁተዎች በኢትዮጵያ አነስተኛ የፋይናንስ አቅርቦት መጠነ ሰፊ ድርሻ የያዙ ናቸው:: ምንጮች እንደሚያሳዩት ከላይ የተጠቀሱት 4ቱ እና ዊዝደም/ቪዥን የተሠኘሌላ አብቁተ ከጥቅል የአገሪቱ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ከ75% እስከ 85% ይሸፍናሉ ተብሎ ይገመታል::

**ምስል 1፡-** <u>የአነስትኛ ፋይናንስ አቅራቢዎች ካፒታል/ንዋይ ዕድገት</u>::




ምንጭ: Own Survey April-May, 2015

በአንፃሩ የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራት በጥቅሉ 5.1 ቢሊዮን ብር ካፒታል በማስመዝገብ 21% ያህሉን የአገሪቱን አነስተኛ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ድርሻ ይዘው ይገኛሉ:: ክልልዊ ስርጭቱ እንደሚያሳየው 11 አብቁተዎች በዘጠኙ ክልላዊ መንግሥቶችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች የተቋቋሙ ሲሆኑ ቀሪዎቹ መንግታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ ባለኃብቶች የተመሠረቱ ናቸው::

### 3.2.1 አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች ዕድገት

ብዙ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከአነስተኛ የፋይናንስ አቅርቦት ባልተናነሰ መልኩ የተለያዩ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች መኖር እና የተጠቃሚዎችን ፍላጐት መሠረት ያደረገ አቅርቦት መኖር ለድህነት ቅነሳ ዕኩል አስተዋፅኦ አለው:: ምክንያቱም የተቀናጀ እና ተደራሽ የሆነ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት የደሀ ሰዎችን እና የሴቶችን ዘላቂ ተጠቃሚነት ከማረጋገጡም በላይ ሰዎች ከድህነት ለመውጣት በሚያደርጉት ትግል ዘርፈ ብዙ እገዛ ስላለው ነው::

## የአብቁተዎች የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች

ሁሉም አብቁተዎች ለማለት በሚቻል ሁኔታ ተመሳሳይ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶችን ይሰጣሉ። ብድር እና ቁጠባ ዋናዎቹ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች ሲሆኑ፤ በተጨማሪም የሐዋላ፣ የጡረታ ፈንድ ማኔጅመንት፣ የንብረት፣ የማሽነሪ እና የቁሳቁስ ሊዝ አገልግሎቶች በተወሠኑት አብቁተዎች ይሰጣል። ለምሳሌ አዲስ አብቁተ የፋይናንስ ሊዝ ወይም የማሽነሪ ሊዝ አገልግሎት ሲሰጥ፤ አማራ እና ደደቢት አብቁተዎች (እንደቅደመ ተከተላቸው አማራ እና ትግራይ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ናቸው) ከተለመዱት የብድር ዓይነቶች በተጨማሪ የምግብ ዋስትና ብድር (Food security loan or package loan) የሚባል የብድር ዓይነት አላቸው። ይህ የብድር ዓይነት ዋና ዓላማ ገበሬዎች ወይንም በገጠር የሚኖሩ ሰዎች በቤተሠብ ደረጃ የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ እንዲችሉ ለመርዳት የታለመ ነው። ብድሩ በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጥ ሲሆን፤ የሚሰጠውም በፖኬጁ ውስጥ ለተካተቱ 9 የግብርና መስኮች ነው። እነዚህም ዶሮ፣ የወተት ላም፣ በግ ወይም ፍየል እርባታ፣ ቀንድ ከብት እና ሌሎችንም ማድለብ፣ ዘመናዊ እና ባሕላዊ ንብ ማነብ፣ መስኖ እና ዘመናዊ የግብርና ግብዓት ሥራዎች ናቸው።

ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ በአንዳንዶች ከሚታየው ፈጠራ የታከለበት የፋይናንስ አቅርቦት በስተቀር የአብዛኞቹ አብቁተዎች የብድር አገልግሎት ዓይነቶች የግብርና ብድር፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ቢዝነሶች ብድር፣ የሠራተኞች ብድር፣ የቤት ብድር ተብለው ይጠቀሳሉ። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ሁሉም አብቁተዎች በግለሠብ ደረጃ ብድር እየሰጡ ይገኛሉ። ምንም እንኳን ዋስትና የሚያስፈልግ መሆኑ ቢገለፅም ይህ የቅርብ ጊዜ ለውጥ ሰዎች ብድር ለማግኘት የግድ ቡድን መመስረት ይኖርባቸው የነበረውን ሁኔታ በአማራጭነት አስፍቶታል። ሠንጠረዥ 3 የአንድ ለምሳሌ የቀረበ አብቁተ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶችን ሁኔታ ያሳያል።

## ሠንጠረዥ 3፡- የመክሊት አብቁተ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ዓይነቶች፡፡

| የብድር ዓይነት | ዝቅተኛና ከፍተኛ ጣራ | የመ መለሻ ጊዜ | የወለድ ምጣኔ (% በዓመት) | የሰርቪስ ክፍያ (በ%) | የመድን ክፍያ (በ%) | የዕፎይታ ጊዜ | አመላለስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የእርሻ | 500-18,000 | 12 | 20 | 3 | 2 | የለም | ዓመታዊ |
| አግሪቢዝነስ | 500-20,000 | 24 | 19 | 2 | 2 | የለም | ዓመታዊ |
| የከተማ የቡድን ቢዝነስ | 500-18,000 | 12 | 19 | 2 | 2 | የለም | ወርኃዊ |
| የግል ብድር | 500-150,000 | 24 | 18 | 2 | 2 | የለም | ወርኃዊ |
| የአደጋ ጊዜ ብድር | 500-5000 | 3 | 24 | 5 | 2 | የለም | ሳምንታዊ |
| የኃይል ብድር | 500-7000 | 24 | 16 | 2 | 2 | የለም | ዓመታዊ |
| ግራንድ | ≤4000 | 12 | 16 | 1.5 | 2 | የለም | ዓመታዊ |
| የፍጆታ | ≤5000 | 24 | 18 | 2 | 2 | የለም | ዓመታዊ |
| የሕብረት ሥራ | 500-18,000 | 12 | 20 | 3 | 2 | የለም | ዓመታዊ |
| | | | የቁጠባ ዓይነት | | | | |
| የግዴታ ቁጠባ | የብድሩን 5% | -- | 4 | -- | -- | -- | ሳምንታዊ |
| መደበኛ ቁጠባ | | -- | 6 | -- | -- | -- | -- |
| የጊዜ ገደብ ተቀማጭ | | -- | 7.5 | -- | -- | -- | -- |
| ከወለድ ነፃ ቁጠባ | | -- | 4 | -- | -- | -- | -- |
| የድርጅቶች ቁጠባ | | -- | 6 | -- | -- | -- | -- |

ምንጭ: Own survey, April-May, 2015

ሁሉም አብቁተዎች የግዴታና የፈቃደኝነት የቁጠባ ዓይነቶችን ይሠጣሉ፡፡ ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 3 እንደቀረበው መክሊት አብቁተ ግን ዘረፈ ብዙ የሆነ የቁጠባ አገልግሎት አቅርቦት እንዳለው መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህም መደበኛ ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ የድርጅቶች ቁጠባ፣ ከወለድ ነፃ ቁጠባ ናቸው፡፡ ይህም ሁኔታ አብቁተዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቁጠባ ግልጋሎት የሰጡትን ከፍተኛ ትኩረት ያመለክታል፡፡

## የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች

በአዋጁ ላይ እንደተመለከተው የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የፋይናንስ ምንጮች ሶስት ሲሆኑ እነርሱም ሀ) ከአባላት መዋጮ፣ ለ) ከተጣራ ትርፍ እና ሐ) የውጭ ብድር ወይም የአክሲዮን/ድርሻ ሽያጭ ናቸው፡፡

ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የግዴታ ቁጠባና የፈቃደኝነት ቁጠባ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። እዚህ ላይ የፈቃደኝነት ቁጠባን ልዩ የሚያደርገው የቁጠባው መጠን እንደየአባላቱ ችሎታ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ሴቶችንና ደሀውን የሕብረተሠብ ክፍል ለመሳብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በመጀመሪያዎቹ ወቅቶች አባላት ቁጠባ እንዲያስቀምጡ ይገደዳሉ። ይህ ሁኔታ የቁጠባ ልምድን ከማዳበሩም በላይ ለብድር የሚሆን ገንዘብ ወይም ካፒታል መጠንን ይጨምራል። የቁጠባ የወለድ መጠን ዝቅተኛው 4% ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ እንደ ሕብረት ሥራ ማኅበራቱ ሁኔታና እንደ ቁጠባው ዓይነት ይለያያል። ሆኖም እስከ 10% እንደሚደርስ በቃለ መጠይቅ ጊዜ ተጠቁሟል።

የብድር አገልግሎት በቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚቀረበው ማኅበሩ ከተቋቋመ ከተወሠኑ ወራት በኋላ ነው። አንድ አባል የብድር ተጠቃሚ ለመሆን ቢያንስ ከ3 እስከ 4 ወር ድረስ መቆጠብ ይኖርበታል። በብዙዎቹ ማኅበራት የመጀመሪያው ዙር የብድር መጠን የግለሠቡን የቁጠባ መጠን እስከ ሶስት እጅ ብቻ እንደሆነ ተጠቁሟል። ለዚህም ዋና ምክንያቱ ብዙ ብድር ፈላጊ አባላትን ለማዳረስ እንዲቻል መሆኑም ተጠቅሷል። የብድር መመለሻ ጊዜውም ለመጀመሪያ ዙር ብድር አንድ ዓመት ነው። ከአብቁተዎች ጋር ሲነፃፀር የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የብድር ወለድ መጠን በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ብዙ ሴቶችና ድሆች ይመርጡታል። ለማጠቃለል ሠንጠረዥ 4 በአንድ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት የተቋቋመ ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበር እና ሕብረት በጋራ የሚያቀርቡትን የብድር ዓይነቶች ያመለክታል።

**ሠንጠረዥ 4፡-** <u>በራሴድ (WISE) የተቋቋመ የሕብረት ሥራ ማኅበር እና ሕብረት የሚያቀርቡት የብድር ዓይነቶችና ሁኔታዎች</u>፡፡

| የብድር ዓይነት | ዝቅተኛና ከፍተኛ ጣራ (ብር) | የመመለሻ ጊዜ (በዓመት) | የወለድ ምጣኔ (% በዓመት) | አስፈላጊ ሁኔታዎች 4 |
|---|---|---|---|---|
| የንግድ ብድር | 1,000 - 100,000 | 1-4 | 16 | ከስድስት ሳምንት በላይ በተከታታይ የቆጠበች፣የመሠረታዊ ንግድ ክህሎት ሥልጠና ያጠናቀቀች፣የቀድሞ ብድሯን ¾ የከፈለች፡፡ |
| የልጆች የትምሕርት ቤት ወጪ ብድር | በልጅ 300 ብር | 1-4 | 16 | በማኅበሯ ከዓመት በላይ የቆየች፣ በአከፋፈልና በማኅበር አባልነት ጥሩ ታሪክ ያላት፣ ልጆች ወይም ጥገኞች ያላትና ማስረጃቸውን ማቅረብ የምትችል፡፡ |
| የከፍተኛ ንግድ ብድር | 1,000-100,000 | 1-4 | 15 | የማኅበሯን የመጨርሻ የብድር ጣሪያ የወሰደች፣ ንግዷን ያሳደገች፣የቢዝነስ ፕላን ማቅረብ የምትችል፣የሰው ወይም የንብረት ዋስ ማቅረብ የምትችል፡፡ |
| የቡድን ንግድ ብድር | 1,000-60,000 | 1-4 | 14 | በጋራ የሚሠሩ 5 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አባላት ስምምነታቸውን፤ አዋጭነት ያለው ዕቅዳቸውን፣የንግድ ፈቃድ እና ዋስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |
| የቤት ግንባታና ዕድሳት ብድር | 1,000-100,000 | 1-4 | 15 | የቤት ባለቤትነት ማስረጃ፣ሕጋዊ የሆነ የቤት ካርታ፣የግንባታና የዕድሳት ፈቃድና ከማኅበሩ መሪ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ |
| የኮንደሚኒየም ቤት ቅድመ ክፍያ ብድር | 1,000-40,000 | 1-4 | 14 | በማኅበሯ ከዓመት በላይ የቆየች፣ በአከፋፈልና በማኅበር አባልነት ጥሩ ታሪክ ያላት፣ የኮንደሚኒየም ቤት ዕጣ እንደደረሳት ማስረጃ የምታቀርብ፣ ከማኅበሩ መሪ የድጋፍ ደብዳቤና፣ የሰው ወይም የንብረት ዋስ ማቅረብ የምትችል፡፡ |

ምንጭ: Own Survey April-May, 2015

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው የቁጠባና ብድር የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚያቀርቡት ወቅታዊ እና የተጠቃሚዎችን ፍላጐት መሠረት ያደረገ የአነስተኛ ብድር አቅርቦት የተሻለ ተመራጭ መሆኑን ያነጋገርናቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ይህን የመሠለ ዘርፈ ብዙ የብድር አቅርቦት በሁሉም ሕብረት ሥራ ማኅበራት በአሁኑ ጊዜ ይገኛል ማለት አይቻልም፡፡ የሚሠጡትን አገልግሎት በስፋትና በጥራት ለማሳደግ የሕብረት ሥራ ማኅበራቱን አቅም በተከታታይ ማጐልበት፣ የሰው ኃይል አቅማቸውን በባለሙያ ማጠናከርና የልምድ ልውውጥን ማመቻቸት በጣም አስፈላጊ ጉዳዮች መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡

### 3.2.2 አነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢዎች መልከዓ-ምድራዊ ስርጭት

በመረጃ እጥረት የተነሳ የተሟላ ባይሆንም አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢዎች (አብቁተዎችና የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት) በከተማና በገጠር ያላቸውን ስርጭት ለማየት ተሞክሯል፡፡

**ምስል 2፡-** <u>የአብቁተዎች ቅርንጫፎች፣ ንዑስ ቅርንጫፎች እና የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት</u>፡፡




ምንጭ: Own Survey April-May, 2015

ከላይ በሥዕሉ ላይ ለመመልከት እንደሚቻለው የአብቁተዎች ቅርንጫፎች እና ንዑስ ቅርንጫፎች ብዛት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ ሄዷል፡፡ ለምሳሌ በ2014 ዓ.ም ተጨማሪ 255 ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች በአዲስ መልክ ተከፍተዋል፡፡ ይህም የቅርንጫፎችን ቁጥር በ20.7% አሳድጕታል፡፡ በዚሁ ዓመት ተጨማሪ 4 አብቁተዎች ማለትም ንስርና ራይስ የሚባሉ አብቁተዎች በአዲስ አበባ፣ አደዳይ አብቁተ በትግራይ እና አፋር አብቁተ በአፋር ክልል እንደተቋቋሙ ከብሔራዊ ባንክ የተገኘ መረጃ ይጠቁማል፡፡ በአጠቃላይ የአብቁተዎች የቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ቁጥር መጨመር የሕብረተሠቡ የአነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት ፍላጐት እየጨመረ መምጣቱን ይጠቁማል፡፡

የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራትም እንዲሁ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሪቱ በብዛት እየተፈጠሩ መጥተዋል፡፡ የእነዚህ ፋይናንስ ማኅበራት ዕድገት በገጠርም ሆነ በከተማ በጣም ከፍተኛና ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተጫወቱት ሚና በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡-** <u>የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት እና በገጠርና በከተማ ስርጭት (ሠኔ 2014)</u>፡፡

| | ከተማ | | ገጠር | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| **የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት** | 1,922 | 13.3 | 12,531 | 86.7 | 14,453 | 100 |
| **የሕብረት ብዛት** | 3 | 3.4 | 86 | 96.6 | 89 | 100 |
| **የፋይናንስ ሕብረት ሥራ አባላት ብዛት** | 327 | 11.9 | 2,418 | 88.1 | 2,745 | 100 |

ምንጭ: Own compilation from FCA reports, 2015

በዚህ ጊዜ 14,453 የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ይገኛሉ፡፡ 86.7% ያህሉ በገጠር ሲሆኑ ቀሪዎቹ በከተማ ውስጥ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ባለፉት ዓመታት በገጠርና በከተማ የሚገኙ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት ከመቼውም በላይ የተፋጠነ ነው፡፡ ከ2003 ዓ.ም በፊት የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት በከተማ ብቻ የተወሰኑ ነበሩ፡፡ የአይፋድ (IFAD) የገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ኘሮግራም አንድ እና ሁለት የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራት በገጠር እንዲስፋፉ አይነተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ የገጠር የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት በ2003 ዓ.ም 132 የነበረ ሲሆን (Gessesse, 2010) በ2014 ይህ ቁጥር ወደ 14,453 አድጓል፡፡

ከክልላዊ ስርጭት አኳያ ሲታይ የኦሮሚያ ክልል ትልቁን የገጠር ፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ቁጥር ሲይዝ፤ አማራ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ሕዝቦች እና ትግራይ በተከታታይ ይገኛሉ (Gessesse, 2010)፡፡ በተለይ የገጠር ሕብረት ሥራ ማኅበራት ልዩ ዕድገትና መሥፋፋት ሁሉን ያካተተ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦትን በማረጋገጥ፤ እንዲሁም ለድሆችና እስከ አሁን ተጠቃሚ ያልሆኑ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ሆኖም የመጀመሪያ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ሕብረት (Union) የመመስረት ሒደት የተጓተተ ሆኖ ይታያል፡፡ ለምሳሌ ከ1,922ቱ የከተማ ሕብረት ሥራ ማኅበራት መካከል እስከ አሁን

327ቱ (17%) ብቻ ሦስት ሕብረቶችን የመሠረቱ ሲሆን፤ ከ12,531 የገጠር ማኅበራት መካከልም 2,418ቱ (19.3%) ብቻ 86 ሕብረቶችን መመስረት ችለዋል።

የጥምረት (ፌዴሬሽን) እና የሕብረት (ዩኒየን) መመስረት የመጀመሪያ ደረጃ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን የቴክኒክና የሥራ አመራር አቅም ከማጐልበት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ከማስገኘቱ በላይ ለብድር የሚውል ገንዘብ በማፈላለግ እና ተጨማሪ የብድር ዓይነቶችን በማቅረብ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች በአንክሮ ይገልፃሉ።

የአብቁተዎች እና የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ሥርጭት እንደሚያሳየው ሕብረት ሥራ ማኅበራት ከአብቁተዎች በተሻለ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ተደራሽ መሆናቸው ግልፅ ቢሆንም ባላቸው ውስን አቅም የተነሳ ብዙ ሰው የአነስተኛ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ገና ብዙ ሥራ እንደሚያስፈልግ መረጃዎች በግልፅ ያመለክታሉ። በአንፃሩ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የአብቁተዎች ሥርጭት በከተሞች አካባቢ በተለይም በአዲስ አበባ የተወሰነ እንደነበር ይታወቃል። ይህን ሁኔታ ለማስረዳት አንድ ቁልፍ መረጃ ሠጪ "አንዳንድ አብቁተዎች ወደ ገጠር ገብቶ ለመሥራት ምቾት አይሰማቸውም" በማለት በአጭሩ ገልጸውታል። በመሆኑም በገጠርና በከተማ ከታየው አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢዎች አመርቂ ዕድገትና ስርጭት በተቃራኒ የአነስተኛ ፋይናንስ ተደራሽነት በአጠቃላይ ሲታይ አሁንም በጣም ውስን ነው። በጥናቱ የተሳተፉ ብዙ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት መንግሥት እና የልማት አጋሮች አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢዎች ወደ ገጠር እና ፍላጐቱ አንገብጋቢ ወደ ሆነባቸው ቦታዎች ሄደው መሥራት እንዲችሉ አንዳንድ ማበረታቻዎችን መፍጠር ይኖርባቸዋል። በዚህ ረገድ ዋናው ችግር የሥራ ማስኬጃ ወጪ ከፍተኛ መሆን እንደሆነም ተጠቁሟል። ወጪን ለመቀነስ ከማኅበረሠብ ወለድ ድርጅቶች (community-based organizations) ጋር መሥራት ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

### 3.2.3 በደንበኛ ተደራሽነትና በአባላት መጠን የታየ ዕድገት

ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ የአነስተኛ ፋይናንስ ደንበኞች ቁጥር እና የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራት አባላት ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ በመሔዱ በየጊዜው እያደገ የሚገኘውን ፍላጐት ተደራሽ ለማድረግ ተሞክሯል።

**ሠንጠረዥ 6፡-** የአብቁተ ተበዳሪ ደንበኞችና የሕብረት ሥራ ማኅበራት አባላት ብዛት ዕድገት በጾታ፡፡

| | ሠኔ 2012 | ሠኔ 2013 | ሠኔ 2014 |
|---|---|---|---|
| የአብቁተዎች ተበዳሪ ደንበኞች ብዛት | 2,887,043 | 3,245,080 | 3,757,093 |
| የአብቁተዎች የሴት ተበዳሪዎች ብዛት | - | 1,669,784 | 1,610,642 |
| የፋ/ሕ/ሥራ ማኅበራት አባላት ብዛት | 840,887 | 1,377,880 | 1,736,122 |
| የፋ/ሕ/ሥራ ማኅበራት የሴት አባላት ብዛት | - | - | 676,620 |

ምንጭ: Own Survey April-May, 2015

እስከ ሠኔ 2014 ዓ.ም ድረስ የአብቁተዎች ተበዳሪዎች ቁጥር 3.76 ሚሊዮን ሲሆን ከዚሁ ቁጥር 43% ያህሉ ሴቶች ናቸው፡፡ 14,453 የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ደግሞ 1.74 ሚሊዮን አባላት ሲኖራቸው ከነዚህ ውስጥ 39% ሴቶች ናቸው፡፡ በሠኔ ወር 2013 በተገኘ መረጃ መሠረት 358,037 (12.4%) ተጨማሪ ደንበኞች በአብቁተዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም በሠኔ ወር 2014 ዓ.ም ተጨማሪ 512,013 (15.8%) ደንበኞች ግልጋሎት አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በ2013 እና በ2014 ዓ.ም የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት አባላት ቁጥር በ63.9% እና በ26% ዕድገት አሳይቷል፡፡

ሆኖም ምንም እንኳ የጾታ ስብጥርን የሚያሳይ የተሟላ መረጃ ባይኖርም ከቀረበው መረጃ እንደሚታየው የሴት ደንበኞች ቁጥር በ3.6% (59,142) ቀንሶ ይታያል፡፡ ለዚህም ዋና ተጠቃሽ ምክንያት በሴት ደንበኞች ፍላጐት ላይ የተመሠረተ የብድር አቅርቦት ሥርዓት ዝቅተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ ነው፡፡ በአራዳ ክ/ከተማ በቅርብ ጊዜ የተጠና ጥናት እንደሚያሳየው የወለድ መጠን፣ የመያዣ ሁኔታ፣ የብድር መመለሻ ጊዜ እና የሠለጠነ የሰው ኃይል አለመመጣጠን ለደንበኞች ቆይታ ማጠር ዓይነተኛ ተጠቃሾች ናቸው (Getnet and Edilegnaw, 2013)፡፡

በሕብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ የሴቶች የአባልነት ተሳትፎ በከተማ አመርቂ ቢሆንም በገጠር ግን ዝቅተኛ ነው፡፡ አባላትን የመሳብ ሁኔታ በአጠቃላይ በገጠር አካባቢ ዘገምተኛ መሆኑም ይታያል፡፡

### 3.2.4 በአጠቃላይ የተሰጠ ብድርና የተሰበሰበ ቁጠባ መጠን ዕድገት

እስከ ሠኔ ወር 2014 ዓ.ም ያለው መረጃ እንደሚያሳየው በአብቁተዎች ብቻ የተሰጠው የብድር መጠን 16.8 ቢሊዮን ብር ሲሆን፤ ይህም ለ3.76 ሚሊዮን ተበዳሪዎች ነው፡፡ በአንፃሩ 11.8 ቢሊዮን ብር በቁጠባ የተሠበሠበ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም የብድሩ 60.9% ያህል ከቁጠባ በተገኘ ገንዘብ ፋይናንስ ማድረግ መቻሉን ያመለክታል፡፡

**ምስል 3፡-** ባለፉት ሦስት ዓመታት የተሠጠ የብድርና የተሠበሠበ የቁጠባ መጠን፡፡




ምንጭ: Own Survey (April-May, 2015)

ከላይ በምስሉ ላይ እንደሚታየው አጠቃላይ የቁጠባ መጠን በሠኔ ወር 2013 ዓ.ም 40% እና በሠኔ ወር 2014 ዓ.ም 54% ዕድገት ሲያሳይ፤ የተሰጠው የብድር መጠን ደግሞ በእነዚሁ ዓመታት በ37.6% እና 31.8% ዕድገት አሳይቷል፡፡ የዚህ ዕመርታ ዋና ምክንያት አዳዲስ አብቁተዎች በክልሎች (ለምሳሌ በአፋር ክልል) መቋቋም እና አንዳንድ አብቁተዎች ከንግድ ባንኮች ጋር የፈጠሩት መልካም የሥራ ግንኙነት መሆኑን ቁልፍ ቃል አቀባዮች ይገልፃሉ፡፡

ሌላው ጠቃሚ ምልከታ ከሠኔ ወር 2012 እስከ ሠኔ ወር 2014 ዓ.ም ባሉት ዓመታት አብቁተዎች ከሰጡት አጠቃላይ ብድር መጠን 58.7%፣ 59.8% እና 60.9% ያህሉን ከቁጠባ በተሠበሠበ ገንዘብ መሸፈኑ ነው፡፡ ይህ አመርቂ ሁኔታ ዝቅተኛ ገቢ

ያለውን ማሕበረሠብ የቁጠባ ልምድ ማዳበሩን ከማሳየቱ በላይ ለአብቁተዎች ዘለቂታዊ እና ራስ አገዝ የፋይናንስ አቅርቦት ዕድገት አስተዋፅኦ አለው፡፡

በሌላ መልኩ በፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ደግሞ በ2014 ዓ.ም ብር 5,126,912.681 (90% ከከተማ ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት ነው) በቁጠባ ተሠብስቧል፡፡ ይህም መጠን በ2010 ዓ.ም ከተሠበሠበው ብር 108 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል፡፡ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት በ2010 ዓ.ም ብቻ 118 ሚሊዮን ብር ለ327,085 አባላት ብድር ሠጥተዋል፡፡ ከእነዚህ ተበዳሪ አባላት መካከል 48% ሴቶች ናቸው፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የተበዳሪ ሴቶች ተሳትፎ ከአብቁተዎች ይልቅ በፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ልቆ ይታያል፡፡

የአብቁተዎች አማካይ የብድር እና ቁጠባ መጠን በሠኔ ወር 2014 ዓ.ም 4,500 እና 1,800 ብር የነበረ ሲሆን፤ ይኸው መጠን በፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ደግሞ 462 እና 400 ብር ነበር፡፡ አማካይ የብድር እና የቁጠባ መጠን በተዘዋዋሪ መንገድ አገልግሎቱ ምን ያህል ዝቅተኛ ገቢ ላለው የሕብረተሠብ ክፍል ተደራሽ እንደሆነ የሚያመለክት በመሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫ ጠቋሚም ነው፡፡ በዚህም መሠረት የተቀናጀ እና ሁሉን አቀፍ አነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት ለዝቅተኛው የሕብረተሠብ ክፍልና ለደሀ ሰዎች በማቅረብ ረገድ የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ከአብቁተዎች የተሻሉ መሆናቸው በዚህ ጥናት በተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ የደሀ ደሀ የሆነውን የሕብረተሠብ ክፍል እና ሴቶችን ወደፊት የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን በበለጠ ማጠናከር፣ ማስፋፋትና ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትልቅ ርብርቦሽ እና የኃብት ኢንቨስትመት ይጠይቃል፡፡

የአብቁተዎች የብድር አቅርቦት ስርጭት ከመንግሥት የፖሊሲ ትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ በ2002 የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ ልማት ኤጀንሲ ስትራቴጂ መሠረት የመንግሥት ልዩ ድጋፍና ትኩረት የተሠጣቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች በሠንጠረዥ 7 ተመልክተዋል፡፡ ለእነዚህ የኢኮኖሚ ንዑስ ዘርፎች ትኩረት የተሰጠበት ዋና ምክንያት የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለመቀነስ፣ የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት እና ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ለማምረት በማስቻላቸው እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡

**ሠንጠረዥ 7፡-** በመንግሥት ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው አነስተኛና ጥቃቅን ዘርፎች፡፡

| ማኑፋክቸሪንግ | ኮንስትራክሽን | ንግድ | አገልግሎት | የከተማ ግብርና |
|---|---|---|---|---|
| • ጨርቃጨርቅ<br>• ቆዳና የቆዳ ውጤቶች<br>• የምግብና መጠጥ ዝግጅት<br>• የብረትናኢንጅነሪንግ ሥራዎች<br>• የእንጨትና ቁሳቁስ ሥራዎች<br>• የባህላዊ ዕደ-ጥበብ<br>• አግሮ-ፕሮሰሲንግ | • ኮንትራክተር<br>• የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ<br>• የባህላዊ ማዕድን አንጣሪዎች<br>• የከበረ ድንጋይ ልማት<br>• ኮብልስቶን<br>• የመሠረተ ልማት ግንባታ ኩባንያዎች | • የአገር ውስጥ ምርት ጅምላ አከፋፋይ<br>• የአገር ውስጥ ምርት ችርቻሮ ንግድ<br>• ለአገር ውስጥ ምርት ግብዓት አቅራቢ | • የገጠር ትራንስፖርት<br>• ካፌና ሬስቶራንት<br>• የመለዋወጫ አገልግሎት<br>• የቱሪዝም አገልግሎት<br>• የማማከር አገልግሎት<br>• የማሽኒያ አገልግሎት<br>• የፕሮጀክት ኢንጅነሪንግ<br>• የዲዛይን ልማት<br>• የውበት ዕዳትና ጥበቃ አገልግሎት<br>• የጥገና አገልግሎት<br>• የውበት ሳሎን<br>• የሶፍትዌርና የኤሌክትሮኒክስ ልማት<br>• ዲኮሬሽን<br>• ኢንተርኔት ካፌ | • ዘመናዊ እንስሳት ማድለብ<br>• ንብ ማነብ<br>• ዶሮ ርባታ<br>• ዘመናዊ የደን ልማት<br>• አትክልትና ፍራፍሬ<br>• ዘመናዊ መስኖ<br>• የዕንስሳት መኖ ማምረት |

ምንጭ: own survey, April-May, 2015 + Complied from FeMSEDA, (2011)

**የአብቁተዎችን የብድር ስርጭት ስንመለከት በዚሁ የመንግሥትን ትኩረት መሠረት ባደረገ መንገድ የተቃኘ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በሠኔ ወር 2014 በአጠቃላይ ከተሰጠው የብድር መጠን ውስጥ 60% ያህሉ የዋለው ለግብርና ሥራዎች (የከተማ ግብርናን ጨምሮ) ነው፡፡ በቀጣይ 18.9% ያህሉ ብድር ለንግድ ሥራዎች የተሠጠ መሆኑ ይታያል፡፡ ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን እና አገልግሎት ዘርፎች ዝቅተኛ ድረሻ ያላቸው ሲሆን እንደቅደም ተከተላቸው 4.7%፣ 4.5% እና 4.5% ይዘዋል፡፡**

**ሠንጠረዥ 8፡-** <u>የብድር ሥርጭት በኢኮኖሚ ዘርፎች ሠኔ 2014</u>፡፡

| ተቁ | ዘርፍ | መጠን ('000ብር) | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና | 10,121,967.5 | 60.1 |
| 2 | ንግድ | 3,175,705.0 | 18.9 |
| 3 | ማኑፋክቸሪንግ | 796,275.3 | 4.7 |
| 4 | ኮንስትራክሽን | 760,032.4 | 4.5 |
| 5 | አገልግሎት | 760,099.2 | 4.5 |
| 6 | ሌሎች | 1,237,291.1 | 7.3 |
| 4. | **ጥቅል** | **16,851,369.7** | **100** |

ምንጭ: Own survey April-May, 2015

ጠቅለል ባለ መልኩ በኢትዮጵያ አነስተኛ የፋይናንስ አቅርቦት ሁኔታን ስንመለከት ለብድር የሚውል ካፒታል ዕጥረት፣ አስፈላጊው ዕውቀትና ክህሎት ያለው በቂ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማለትም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ሥራ አመራር ኢንፎርሜሽን ሴስተም መጠቀም አናሳነት ቁልፍ እጥረቶች መሆናቸው ለጥናቱ መረጃ የሰጡት ቁልፍ መረጃ ሠጪዎች ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር የኢትዮጵያ አነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት ከአቅርቦት እና ከፍላጐት አንፃር ብዙ ተግዳሮቶች ይታዩበታል፡፡

አነስተኛ የፋይናንስ ፍላጐት ከአቅርቦቱ በላይ በፍጥነት እያደገ ይገኛል፡፡ አብቁተዎችና የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት በጋራ በአገሪቱ ካለው ፍላጐት እስካሁን ከ25% እስከ 30% ብቻ ተደራሽ አድርገዋል፡፡ ለዚህም በተደጋጋሚ የሚጠቀሱት ተግዳሮቶች ለብድር የሚውል ካፒታል (ፋይናንስ) ዕጥረት፣ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ማስኬጃ ወጪ፣ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ሥራ መልቀቅና ዕጥረት፣ ውስን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ዘመናዊ የአሠራር ፈጠራ የአቅራቢ ተቋማትን አቅም ተፈታትኗል፡፡ በተጨማሪም ውስን ቁጠባን የመሠብሠብ አቅም፣ አባላትን የመሳብ ውስንነት፣ ዝቅተኛ የፋይናንስ ዕውቀት፣ ተመሳሳይ የፋይናንስ ዓይነቶች፣ የሥራ አመራርና የቴክኒክ ብቃት ውስንነት፣ ደካማ የፋይናንስ ሪፖርት ሲስተም እና ውስን የቴክኖሎጂ ግብዓትን የመጠቀም አቅም የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ልዩ ተግዳሮቶች እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡

## 3.2 የአነስተኛ መድን (Micro-insurance) አገልግሎት ዕድገት

በኢትዮጵያ የአነስተኛ መድን ሁኔታን ከመመልከታችን በፊት የደሀውን ሕብረተሠብ ክፍል የኑሮ ሁኔታ የሚያናጉ ስጋቶችንና አደጋዎችን በአጭሩ መቃኘት ጉዳዩን የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል። ቁልፍ መረጃ ሠጪዎች እና ሁለተኛ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ የደሀው ሕብረተሠብ የኑሮ ሁኔታና የኑሮ መሠረት ለተለያዩ ስጋቶች ወይም አደጋዎች ተጋላጭ ነው። የእነዚህ ስጋቶች ወይም አደጋዎች መከሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ በስፋትም ሆነ በጥልቀት እየጨመረ መጥቷል። ከነዚህ ስጋቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት ድርቅ፣ የዕንስሳትና የዐዝዕርት ውድመት፤ የገበያ መዋዠቅ፤ የዋጋ ንረት፤ የጤና ችግር ፤ግጭትና ቅዕበታዊ አደጋዎች (የእሳት፤ ጉዳት፤ የመኪና አደጋ፤ ስርቆትና የመደፈር) እና የኑሮ ውድነት ስጋቶች ናቸው (Zelalem et. al, 2014; Wolday et. al, 2013; Oxfam America & MDTCS, 2009)።

እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ስጋቶች በአግባቡ ካልተያዙ ለዝቅተኛው ሕብረተሠብ ክፍል የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆል ምክንያት ብቻ ሳይሆኑ የወደፊት የገቢ ዕድገት ዕድል ሥጋትን በማጤን የሚወሰደውን የፈጠራና አዳዲስ ሙከራዎች የማድረግ ተነሳሽነትን በመቦርቦር ከድህነት አዙሪት እንዳይወጣ ያደርጉታል። ከዚህም በላይ ሲታይ የአጭር ጊዜ አደጋዎች የረጅም ጊዜ አሉታዊ ውጤቶች ይኖራቸዋል።

ዘመናዊ የመድን ሽፋን በሌለበት ሁኔታ ዝቅተኛው የሕብረተሠብ ክፍል እነዚህን ስጋቶች ለመቋቋም እስካሁን የተለያዩ ዘዴዎችን እየተጠቀመ ይገኛል። ከነዚህም ውስጥ ሀ) ጥሪት ማጠራቀም፤ ቁጠባና ብድር፤ ለ) የገቢ ምንጭን ማስፋፋት፤ ሐ) ጥሪት መሸጥ፤ መ) የፍጆታ ወጪን መቀነስ፤ ሠ) ተቀጥሮ መሥራት እና ረ) በባሕላዊ መድን ተቋማት (ዕድር፤ ማኅበር፤ ወ.ዘ.ተ.) መሳተፍ ተጠቃሽ ናቸው። ሆኖም እነዚህ የስጋት መቋቋሚያ ዘዴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሸርሸራቸውና የሚደርሰውን አደጋ ሁሉ ሙሉ ለሙሉ መሸፈን ባለመቻላቸው የተነሳ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች በእርግጠኝነት "በአገሪቱ የአነስተኛ መድን ሽፋን አገልግሎት ጠንካራ ፍላጎት አለ" (Oxfam America & MDTCS, 2009:11) የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል። ከአደጋ በኋላ ከሚደርስ የመድን አገልግሎት ይልቅ የቅድሚያ መድን ሽፋን ተመራጭነትም በአንክሮ ይጠቀሳል።

በመሆኑም አነስተኛ መድን አገልግሎት ለድሆች የቀጣይ ዘመናት አብዮት በመሆን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የሕብረተሠብ ክፍሎች የአደጋ ተጋላጭነት ሥጋት ይቀርፋል። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የአነስተኛ መድን አገልግሎት በብዛት የለም። ሆኖም አንዳንድ የመድን ኩባንያዎች፤ አብቁተዎችና የሕብረት ሥራ ማኅበራት

አገልግሎቱን ወጥነት በጎደለው መልኩ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ግን በኢትዮጵያ አነስተኛ መድን ሽፋን ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ በስፋት አይታወቅም፡፡ የአንዳንድ አብቁተዎችና የሕብረት ሥራ ማኅበራትን አቅርቦት ሁኔታ ከዚህ በታች በአጭሩ እንቃኛለን፡፡

### *አነስተኛ መድን በአብቁተዎች*

አነስተኛ መድንን ጨምሮ አብቁተዎች 3 ተዛማጅነት ያላቸው የአደጋ ጊዜ የፋይናንስ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ እነዚህም ሀ) የግዴታና የፈቃደኛነት ቁጠባ፤ ለ) የአደጋ ጊዜ ብድር እና ሐ) የብድር ጊዜ መድን ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 9፡-** በአብቁተዎች የሚሠጡ አነስተኛ መድን ዓይነቶች (መጋቢት 2012)፡፡

| ስም | አነስተኛ መድን ዓይነቶች | የደንበኞች ብዛት |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ አብቁተ | • የብድር ጊዜ የሕይወት መድን<br>• የንብረት መድን (ለቤት ብድር) | 146,482<br>**3.3** |
| ኦሮሚያ አብቁተ | • የዕንስሳት መድን<br>• የብድር ጊዜ ሕይወት መድን ለቡድን ተበዳሪዎች<br>• የሙከራ የጤና መድን | 469,713 |
| ሲዳማ አብቁተ | • የብድር ጊዜ የሕይወት መድን | 47,810 |
| ቪዥን አብቁተ | • የብድር ጊዜ የሕይወት መድን | 46,118 |
| አጋር አብቁተ | • የብድር ጊዜ የሕይወት መድን ለቡድንና ለግል ተበዳሪዎች | -- |
| አማራ አብቁተ | • የብድር ጊዜ ሕይወት መድን ለቡድን ተበዳሪዎች | 633,659 |
| ደደቢት አብቁተ | • የሙከራ የአየር ንብረት መድን የጤና መድን | 402,661 |
| መክሊት አብቁተ | • የብድር ጊዜ የሕይወት መድን ለቡድን ተበዳሪዎች | 6,991 |
| ጋሻ አብቁተ | • የገንዘብ ዝውውር መድን (Cash in transit insurance) | -- |

ምንጭ: Wolday et. al, (2013)

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚታየው ሁሉም አብቁተዎች የብድር ጊዜ የሕይወት መድን (Credit-life micro-insurance) አቅርቦት አላቸው፡፡ የብድር ጊዜ የሕይወት መድን በቡድንና በግለሠብ ብድር ለሚወስዱ ሁሉ ተፈፃሚነት አለው፡፡ አንዳንድ አብቁተዎች የእንስሳት፤ የንብረት፤ የገንዘብ ዝውውር መድን ዓይነቶችን መስጠት ጀምረዋል፡፡ የኦሮሚያ አብቁተና ደደቢት አብቁተ የአየር ፀባይና የጤና

መድን አቅርቦት በሙከራ ደረጃ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ የኦሮሚያ አብቁተ ሁለት ዓይነት የብድር ጊዜ የሕይወት መድን ያሉት ሲሆን እነርሱም ሀ) ደንበኛው የብድሩን 1% ለመድን ከፍሎ እንዳጋጣሚ ብድሩን ሳይጨርስ በሞት ቢለይ ቀሪው የብድር መጠን በመድኑ ይሸፈናል፤ ለ) ደንበኛው የብድሩን 1.5% ለመድን ከከፈለ ቀሪ የብድር መጠኑን ከመሸፈን በተጨማሪ ያንኑ ያህል ገንዘብ ለሟች ቤተሠብ ይሰጣል፡፡ የአዲስ አብቁተ የንብረትና የቢዝነስ መድን እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከቤት ብድር (የዚህ ተመን 2% ሲሆን) በስተቀር ለሌሎች ብድሮች የመድን ተመኑ የብድሩን 1% ብቻ ነው፡፡

ሆኖም አብቁተዎች በመጀመሪያውኑ ብድር የሚሰጡት በዋስትና በመሆኑ የብድር ጊዜ የሕይወት መድን መስጠቱ ብዙ ፋይዳ የለውም የሚል አስተያየት ይሰነዘራል፡፡ በተጨማሪ ትላልቆቹ አብቁተዎች ራሳቸውን ችለው የመድን ሽፋን እየሰጡ ሲሆን፣ ሌሎች ልምዱ የሌላቸው ግን ከመድን ኩባንያዎች ጋር በመጣመር አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አብቁተዎች በአገሪቱ 3.7 ሚሊዮን ደንበኞችን ተደራሽ በማድረጋቸውና በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች (በገጠርም ሆነ በከተማ) በመገኘታቸው አነስተኛ መድን አገልግሎትን ለመሰጠት የተለየ ቦታ አላቸው (Smith and Chamberlain, 2009)፡፡

ምንም እንኳ አብቁተዎች ለሰጡት ብድር ስጋት ለመቀነስ የብድር ጊዜ የሕይወት መድንን በስፋት ቢሰጡም ባለው ተጨባጭ ሁኔታ እንደሌሎች አገሮች የገበያ፣ የምርት፣ የጤናና ሌሎች የመድን ዓይነቶችን እየሰጡ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል ባሲክስ (BASIX) የሚባለውን የሕንድ ማይክሮፋይናንስ ተቋም ተሞክሮ ብንመለከት ተቋሙ የግብርና እና የእንስሳት ብድርን በግዴታ ከሚሰጥ የአየር ፀባይ (Weather index) እና የእንስሳት አነስተኛ መድን አገልግሎቶች ጋር በማቀናጀት ለድሆች ያቀርባል፡፡

በኢትዮጵያ አብቁተዎች አነስተኛ መድን አገልግሎትን ለመስጠት የተለየ ዕድል (comparative advantage) አላቸው ቢባልም ከዚህ በታች የተቀመጡት ቁልፍ ማነቆዎች ተጋርጠውባቸዋል፡፡

- ✓ የጤና፣ የዕድሜ፣ የአየር ንብረት እና ሌሎች ተመሳሳይ ኩነቶች ላይ በቂ መረጃ ያለመኖር ደንበኛ ተኮር አነስተኛ መድን ዓይነቶችን ለመፍጠር እንቅፋት መሆን፣
- ✓ ጅምር የአየር ፀባይና የሕይወት አነስተኛ መድን አቅርቦቶች አበረታች ቢሆኑም ይህን መልካም ተሞክሮ ቀምሮ ለማሳደግ ያለው ተነሳሽነት አዝጋሚ መሆን፣
- ✓ የደንበኛ ፍላጐት ተኮር አነስተኛ መድን ዓይነቶችን ለመፍጠርና ለማቅረብ የአብቁተዎች አቅምና ብቃት ውስን መሆን፣

- ✓ የብድር ጊዜ የሕይወት መድን አገልግሎትን መስጠት ከመድን አገልግሎቶች ሁሉ በጣም ቀላል ሲሆን እንደ የጤና፣ የአየር ፀባይ፣ የገበያ እና የዋጋ መድንን ማቅረብ ከፍተኛ ብቃት ያለው የሰው ኃይል እና ሠፊ ይዘት ያለውን ይገባኛል ሒደት (Claims processing) የመምራትና የማስተናገድ ችሎታን መጠየቁ፣
- ✓ የአርብቶ እና የአርሶ አደሮችን የአነስተኛ መድን ግንዛቤ ለማዳበር ከፍተኛ ታማኝነትን ከመጠየቁ በላይ ከፍተኛ ኃብትን የሚጠይቅ መሆኑና በአገሪቱ በቂ የፋይናንስ ዕውቀት ያለመኖር፣
- ✓ በመስኩ የጥናት፣ምርምርና ማሠልጠኛ ተቋም ያለመኖር እንዲሁም የዳግም መድን (re-insurance) አገልግሎትን የሚያቅፍ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፍ በግልፅ አለመኖር ናቸው (Wolday et.al, 2013)፡፡

## *አነስተኛ መድን በፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት*

የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት የብድር ጊዜ የሕይወት መድን እየሰጡ ሲሆን የአገልግሎቱ ዋጋ የብድሩን መጠን 2% ያህል ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቹ ሙሉ ለሙሉ በራሳቸው አገልግሎቱን ሲሰጡ አብዛኞዎቹ ግን እንደ ኤጀንት በመሆን ሥራውን ያከናውናሉ፡፡ ለምሳሌ አዲስ ቁጠባና ብድር ሕብረት ከኢትዮ ላይፍ እና አጠቃላይ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር በመሆን የብድር ጊዜ የሕይወት መድን ለሁሉም ተበዳሪ አባሎቹ ይሰጣል፡፡

በኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ የተደረገ የናሙና ጥናት የገበሬዎች የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ሕብረቶች ውጤታማ የሆነ አነስተኛ መድን መስጠት እንደሚችሉ ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪ ከሕብረቶች ጋር በሽርክና የሚሰጥ አነስተኛ የመድን አገልግሎት ወጪ ቀናሽ፣ ተፈላጊና ውጤታማ መሆኑ በተመሳሳይ ተጠቁሟል፡፡ የሎሜ አዳማ ገበሬዎች ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ሕብረት፣ የረር የገበሬዎች ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ሕብረት እና ደደቢት አብቁተ ለኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ ተመራጭ አነስተኛ መድን አስተላላፊ ኤጀንት በመሆን የግብርና ግብዓቶች ብድርን ከአየር ፀባይ ስጋት መድን ጋር በማስተሳሰር ይሰጣሉ (Meherette, 2009)፡፡

**ሠንጠረዥ 10፡-** የራስ አገዝ ሴቶች ድርጅት (ራሴድ) እና የፋሲሊቴተር ፎር ቼንጅ (FC) የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራትና ሕብረት አነስተኛ መድን ዓይነቶች፡፡

| የአነስተኛ መድን ዓይነቶች፤ | ድርጅት | መግለጫና አስፈላጊ ሁኔታዎች (Product Description) |
|---|---|---|
| የብድር ጊዜ የሕይወት መድን | ራሴድ WISE | ✓ በመጋቢት 2012 ከኢትዮ ላይፍና ጄኔራል ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር በትብብር የተጀመረ ሲሆን አባላት ወይም የአባላት የትዳር አጋር በሞት ቢለይ፣ በወቅቱ ሊቀር የሚገባው ያልተከፈለ ብድር መጠን ተከፋይ ይሆናል፤ በተጨማሪም 1,000 ብር ለቀብር ማስፈፀሚያ ይሰጣል፡፡<br>✓ በአባላት ወይም በአባላት የትዳር አጋር ላይ ለሚደርስ ቋሚ የአካል ጉዳት፣ በወቅቱ ሊቀር የሚገባው ያልተከፈለ ብድር መጠን ተከፋይ ይሆናል፡፡<br>✓ የዓባላት ወይም የዓባላት የትዳር አጋር ሁለት ዐይን፤ሁለት ዕጆች ወይም ሁለት እግሮች መቆረጥ ወይም አንድ ዐይን፤እጅ ወይም ዕግር በአደጋ ምክንያት በጠፋ፣ በወቅቱ ሊቀር የሚገባው ያልተከፈለ ብድር መጠን ተከፋይ ይሆናል፡፡<br>✓ አባላት በብድር መክፈያ ዘመናቸው ዕርግዝና/ወሊድ ቢገጥማቸው፣ የዘጠነኛ ወርና ከወሊድ በ"ላ ያለውን የአንድ ወር ወረኃዊ የብድር መጠን ኢንሹራንስ ይከፍላል፡፡<br>✓ አባላት በረጅም ጊዜ ህመም (አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ) ሙሉ በሙሉ አልጋ ላይ መሆናቸው በማኅበሩ ቦርድ ሲረጋገጥ፣ የቀሪው ዘመን ዕዳ በኢንሹራንስ ይከፍላል፡፡ |
| የዕርጅና ጊዜ መድን | ራሴድ WISE 3.3.1 | ✓ ትንሹ ወረኃዊ ክፍያ 30 ብር ሲሆን አባላት ይህን ቁጠባቸውን የሚወስዱት በዕድሜ መግፋትና ህመም ምክንያት ከሥራ ሲወገዱ ብቻ ነው፡፡<br>✓ አንዲት አባል በመሀል ከዚህ ዓለም በሞት ብትለይ ያስቀመጠችው የዛሬ ለነገ የዕርጅና ዘመን ተቀማጭ በአገሪቱ የፍ/ር ሕግ መሠረት ለወራሾች ይሰጣል፡፡<br>✓ ፕሮግራሙ በግል ሥራ ለሚተዳደሩ የአባላት የትዳር አጋሮችም የሚሰራ ይሆናል፡፡<br>✓ አባላት 50% የወለድ ምጣኔ የሚያገኙ ሲሆን በከባድ ህመም የተያዙና የህክምና ገንዘብ ችግር የገጠማቸው አባላት ከተቀማጫቸው እስከ 50% ለማውጣት ይችላሉ፡፡; |
| አነስተኛ የጤና መድን | ፋሲሊቴተር ፎር ቼንጅ | ✓ በሴቶችና በቤተሠባቸው የተቋቋመ ሲሆን ዓላማው የጤና እክልን ለመቅረፍ ነው፤ አባላት መጠነኛ ገንዘብ ይከፍላሉ፡፡.<br>✓ ፕሮግራሙ የህመም ዓይነቶችን በመለየት የሚሰጠውን ከፍተኛ የክፍያ መጠን ያስቀምጣል፡፡<br>✓ ለሁሉም ማኅበራት ወጥ የሆነ ደንብ የለውም፣ ለእያንዳንዱ ማኅበር እንደአመችነቱ የራሱን ደንብ በማወጣት ይመራዋል፡፡ |

**ምንጭ**: Own Survey, April-May, 2015

በዚህ ጥናት የተካተቱ ቁልፍ ቃል አቀባዮች እንደሚገልጹት አነስተኛ መድን አገልግሎትን ለመስጠት የፋይናንስ[4] ሕብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች ኩባንያዎች እና አብቁተዎች የተለየ አመቺነት አላቸው፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ የአባላቶቻቸውን ሁኔታ ለመከታተል የሚያወጡት ወጪ አነስተኛ መሆኑ፣ በመቀጠል ደሀ አባላቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ከእነርሱ በላይ ሌላ የተሻለ አማራጭ ባለመኖሩ እና ሲጀመር

[4] የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት እና የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማኅበራት ዕኩል ትርጉም ሲኖራቸው አንዳንድ ጊዜ በማቀያየር ተጠቅመንባቸዋል፡፡

የጋራ መረዳዳትና መተማመን በሕብረት ሥራ ማኅበራቸው የተወጠነ በመሆኑና ይህንኑ ጅምር በትንሽ እገዛ ወደተሻለ የመድን አገልግሎት መቀየር ቀላል በመሆኑ፣ በመጨረሻም የሕብረት ሥራ ቡድን በተጠቃሚዎች እና መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የአነስተኛ መድን አቅራቢ ድርጅቶች መካከል ለሚፈጠረው የመረጃ እና የመተማመን ክፍተት አገናኝ ድልድይ ሆኖ ለማገልገል መቻሉ ናቸው።

የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች እንደሚጠቀሙት ለምሳሌ ከሠሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ብዙ ባሕላዊ የሆኑ የጤና መረዳጃ ጅምሮች የተፈጠሩት በመልካም ፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ መረዳዳት ነው። በአውሮፓም እንዲሁ ብዙ ማሕበራዊ ዋስትና አገልግሎቶች ማለትም እንደ ጤና መድንና የሥራ አጥነት መድን (Unemployment insurance) በመጀመሪያ የተጠነሰሱት በሕብረት ሥራ ማኅበራትና በሠራተኛ ማኅበራት አማካኝነት መሆኑ ይጠቀሳል (Dercon, 2009)።

ሆኖም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የአነስተኛ መድን ሥራን እንዲሠሩ የሚፈቅድ የሕግ ማዕቀፍ የለም። በተጨማሪ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን ልዩ ጥቅም ለማጉልበት የኢትዮጵያ የሕብረት ሥራ እንቅስቃሴ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግዳሮቶችን መፍታት ይኖርበታል።

- የክህሎት፣ የልምድ፣ የፈጠራና የመድን ዓይነቶች ውስንነት፣
- የፋይናንስ ዕውቀት ውስንነት እና የአነስተኛ መድን ጥቅሞች በስፋት አለመታወቅ፣
- በፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት የአነስተኛ መድን አቅርቦትን ለማስፋፋት የሚደግፍ ግልፅ የፖሊሲ ማዕቀፍ አለመኖር፣
- የአነስተኛ መድን ተጠቃሚዎችን ከምዝበራ ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓትን የሚደነግግ መመሪያ አለመኖር፣
- የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን ተግባራት የሚያስፋፉ፣ የሚያግዙና የሚቆጣጠሩ መንግሥታዊ ተቋማት ብዛት በአሠራር ስልጠት ላይ የሚያስከትሉት ችግሮች፣
- በተለይ አነስተኛ መድንን በመምራት ረገድ የፌዴራል ሕብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ አቅም ውስን መሆን፣
- የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን በተመለከተ ልዩ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር።

ስለዚህ አነስተኛ መድን አልግሎትን በሕብረት ሥራ ማኅበራት በኩል ለመስጠት ይቻል ዘንድ በተዋረድ የሚገኙ ባለድርሻ አካላትንና ተጠቃሚዎችን ያካተተ ትልቅ የአቅም ግንባታ ሥራ መሥራት ከወዲሁ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው።

## 4 አነስተኛ ፋይናንስ ለድህነት ቅነሳ ያለው አስተዋፅኦ

ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ በጥናት በግልፅ የተረጋገጠ ባይሆንም ማይክሮፋይናንስ ለድህነት ቅነሳ ዓይነተኛ መሣሪያ እንደሆነ በዓለም ላይ ያለው ግንዛቤ በርግጠኝነት ያስረዳል፡፡ ሆኖም ይህ ጉዳይ ብዙ ክርክሮችን የሚያስነሳ ከመሆኑም ባሻገር እንደሁኔታው የተለያየ ውጤት እንዳለው በተደጋጋሚ ይጠቀሳል፡፡ ክርክር ከሚነሳባቸው ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ✓ የማይክሮፋይናንስን ተጨባጭ ውጤት ለማጥናት የሥነ-ምርምር ዘዴ አስቸጋሪ መሆን፣
- ✓ በኘሮግራሙ ከመታቀፋቸው በፊት የደንበኞችን (ተጠቃሚዎችን) የኑሮ ሁኔታ የሚያሳይ የተጠናቀረ መረጃ አለመኖር፣
- ✓ ትናንሽ ብድሮች ከብድር መመለሻ ጊዜ አጭርነት ጋር ተደምሮ ለኢንቨስትመንት ከመዋላቸው በፊት በከፊል ለሌላ ጉዳዮች መዋላቸው እና ቢዝነስ ለመፍጠር በቂ አለመሆናቸው፣
- ✓ ብዙ ተጠቃሚዎች ወይም ደንበኞች ብዙ ጊዜ በደንበኝነት አለመቆየታቸው እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ደንበኝነት ማቋረጣቸው፣
- ✓ ከፍተኛ የብድር ወለድ መጠን፣ ደንበኛን ያማከለ ግልጋሎት ማነስ፣ የተቀናጀና ሁሉን ያካተተ የፋይናንስ አገልግሎት አለመኖር፣
- ✓ የቢዝነስ ልማት አገልግሎትና የፋይናንስ ዕውቀትን የማጐልበት ሥራዎች አለመቀናጀት ናቸው፡፡

ሆኖም እነዚህ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው በአንዳንድ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተጠኑ ጥናቶች ማይክሮፋይናንስ ለድህነት ቅነሳ አዎንታዊ እና አሉታዊ አስተዋፅኦ እንዳሉት ያመለክታሉ (Guruswamy, 2012; Aragaw, 2012; Getnet and Edilegnaw, 2013)፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የተደረሰበት የመደምደሚያ ምክረ-ኃሳብ ማይክሮፋይናንስ ለድህነት ቅነሳ የአፋጣኝነት ሚና (catelizing role) እንደሚጫወት በብዙ አኃዛዊና ሀተታዊ መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ጥናቶች በሚባል ሁኔታ ማይክሮፋይናንስ ብቻ ሰዎችን ከድህነት አዘቅት መንጥቆ የማውጣት አቅሙ ውስን መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ "ማይክሮፋይናንስ ብቻ ድህነትን እና ረሀብን ያጠፋል ብሎ መገመት በራሱ አላዋቂነት ከመሆኑም ባሻገር የሌሎች ኘሮግራሞችን አስፈላጊነት መፈታተን ነው" በማለት አንድ በመስኩ የብዙ ጊዜ ልምድ ያላቸው ቃል አቀባይ ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ይላሉ እኚሁ የመረጃ ምንጭ "ማይክሮፋይናንስ በጣም አስፈላጊ ኘሮግራም ነው፡፡ ነገር ግን የሁሉም ችግሮች 'መፍቻ ቁልፍ' እና 'ብቸኛ መፍትሔ' ተደርጎ መወሰድ የለበትም" በማለት ኃሳባቸውን ይደመድማሉ፡፡

## 5 ችግሮችና ተግዳሮቶች

ባለፉት 15 ዓመታት በኢትዮጵያ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዕድገትና ልማት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ አበረታች የሕግ ማዕቀፍ መኖር፣ የአነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢ ተቋማትንና ማኅበራትን የሚመሩ ተቋማት ማለትም እንደ ብሔራዊ ባንክ እና ፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ መጠናከር፣ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በብዙ ክልሎች የተቋቋሙ አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት መመስረት፣ ወደ ኢንዱስትሪው ለመቀላቀል የሚጠየቀው የካፒታል መጠን ዝቅተኛ መሆን፣ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶችን ጥራት ከተጠቃሚዎች ፍላጐት ጋር ለማጣጣም የሚደረግ ጥረት በመስኩ የሚታዩ አዎንታዊ ዕመርታዎች ሲሆኑ፤ በአንፃሩ በኢትዮጵያ የአነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎት ከፖሊሲ፣ ፍላጐት እና አቅርቦት ጐን የሚታዩ ተግዳሮቶች ይስተዋሉበታል፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና የማይክሮፋይናንስ ተቋማት ብቻ የአነስተኛ መድን አገልግሎትን መስጠት እንደሚችሉ ሕጉ ሲፈቅድ የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን ግን አያካትትም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት እነዚህ ማኅበራት በአክሲዮን ማኅበርነት ባለመቋቋማቸው ነው፡፡ በተጨማሪም የውጭ ባንኮችና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ዜጐች በአነስተኛ የፋይናንስ አንዱስትሪ እንዲሠማሩ ባለመፈቀዱ በመስኩ ሊገኝ የሚችለውን ዓለም አቀፍ ልምድ፣ የካፒታል ፍሠትና የቢዝነስ ሞዴል እየገታ ይገኛል፡፡
- የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢዎችን የሚቆጣጠሩና የሚመሩ መንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች የተለያዩ መሆናቸው (ብሔራዊ ባንክ፣ ፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ወዘተ) በአሠራር ወጥነትና ስልጠት ላይ የበኩሉን አሉታዊ አስተዋፅኦ አስከትሏል፡፡
- የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን በተመለከተ የተለየ የፖሊሲ ማዕቀፍ አለመኖርና የፋይናንስ እና ሌሎች የሕብረት ሥራ ማኅበራትን ለመምራት የወጣው አዋጅ ሁሉንም ማኅበራት በአንድነት በማየቱ ግልፅ የዕድገት አቅጣጫን ለመጠቀም ውስንነት ፈጥሯል፡፡
- አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ወደ መደበኛ ባንክ ማደግ እንደሚችሉ እና ባንኮች የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ሥራዎችን መሥራት እንደሚችሉ ቢፈቀድም እንዴትና በምን ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት በግልፅ የሚያሳይ መመሪያ እስካሁን የለም፡፡

- ❖ የሕብረት ሥራ ባንክ፣ የሕብረት ሥራ መድን እና የሕብረት ሥራ ፌዴሬሽን ወይም ጥምረት ለማቋቋም የሚያስችል መመሪያ እስካሁን አልወጣም።
- ❖ እስከአሁን ባለው ሁኔታ አመርቂ መስፋፋት ቢታይም በአገሪቱ ያለው የአነስተኛ ፋይናንስ አግልግሎት ፍላጐትና አቅርቦት በስፋት አይጣጣምም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት እስካሁን ያለው አቅርቦት ፍላጐቱን ከ25% እስከ 30% ብቻ የሚያረካ ሆኖ ተገኝቷል (Getaneh, 2006; Wolday & David, 2010)። በተጨማሪ ሁሉንም ያካተተ ፋይናንስ አገልግሎት በአጠቃላይ በአገሪቱ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነው (Genet, 2014)። የሚከተለው ሠንጠረዥ የአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ተቋማት ያጋጠሟቸውን ችግሮች በዝርዝር ያሳያል።

**ሠንጠረዥ 11፡-** አነስተኛና ጥቃቅን አንቀሳቃሾች ሥራቸውን ለማስፋፋት ያጋጠሟቸው ችግሮች በተለያዩ ከተሞች (በቁጥር)።

| ከተማ | የፋይናንስ እጥረት | የመሬትና የሥራ ቦታ ዕጥረት | የግብዓት ዕጥረት | የሥራ አመራር ዕጥረት | የቴክኒክ ብቃት ማነስ | የገበያ ችግር | ሌሎች | ያልተገለፀ | ጥቅል ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 193 (25.3)* | 199 | 108 | 8 | 10 | 190 | 44 | 11 | 763 |
| ሀዋሳ | 47 (41.2) | 26 | 6 | 1 | 1 | 29 | 4 | 0 | 114 |
| መቀሌ | 46 (28.2) | 47 | 10 | 2 | 2 | 48 | 8 | 0 | 163 |
| ጎንደር | 26 (24.8) | 43 | 9 | 2 | 0 | 22 | 3 | 0 | 105 |
| ባህርዳር | 122 (48.8) | 98 | 6 | 2 | 0 | 17 | 5 | 0 | 250 |
| ደሴ | 71 (41.5) | 42 | 16 | 3 | 2 | 32 | 5 | 0 | 171 |
| ጂማ | 92 (39.8) | 54 | 18 | 4 | 4 | 51 | 7 | 1 | 231 |
| ሻሸመኔ | 75 (48.1) | 43 | 9 | 2 | 2 | 22 | 3 | 0 | 156 |
| ድሬዳዋ | 85 (45) | 51 | 16 | 2 | 1 | 22 | 5 | 7 | 189 |
| ቢሾፍቱ | 108 (44.8) | 67 | 22 | 0 | 4 | 32 | 8 | 0 | 241 |
| አዳማ | 114 (44.4) | 65 | 10 | 7 | 6 | 52 | 3 | 0 | 257 |
| ጅግጅጋ | 108 (46.8) | 78 | 3 | 0 | 0 | 40 | 2 | 0 | 231 |
| ሐረር | 55 (34.8) | 26 | 17 | 5 | 0 | 43 | 6 | 6 | 158 |
| **ጥቅል** | 1142 (37.7) | **839** | **250** | **38** | **32** | **600** | **103** | **25** | **3029** |

ምንጭ: Compiled from MSE Sample Survey, MoUDC, 2013

* መቶኛ

- ለብድር የሚውል የፋይናንስ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ የተቋማቱን ተደራሽነት ውስን አድርጎታል፡፡
- ከፍተኛ የሥራ ማስኪያጃ ወጪ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረትና ዝውውር፣ ውስን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተቋማቱንና የማኅበራቱን አቅም በጣም ወስኖታል፡፡ በተጨማሪ ለቁጠባ እና አባላትን ለመሣብ የሚሰጥ ትኩረት አናሳነት፣ ዝቅተኛ የፋይናንስ ዕውቀት፣ ውስን የአገልግሎት ዓይነቶች፣ የሥራ አመራር ዕውቀት ዝቅተኛነት፣ ውስን ድጋፍ እና በአጠቃላይ የተቋማዊና አስተዳደራዊ አቅም ውስንነት በተለይ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን ተብትበው የያዙ ችግሮች ናቸው፡፡
- አነስተኛ ፋይናንስ አቅርቦት መኖር እና አቅርቦቱን መጠቀም ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው በግልፅ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በተለይ ፍጹም ደሀ የሆነው የሕብረተሠብ ክፍል፣ መደበኛ ባልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ የተሠማሩ ሰዎች፣ ሴቶችና ሌሎች የሕብረተሠብ ክፍሎች ተጠቃሚነት በጣም ውስን መሆኑ ተደርሶበታል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አገልግሎቱን (ብድሩን) ለማግኘት የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎች እንደ የወለድ ምጣኔ ከፍተኛ መሆን፣ የዋስትና (Collateral) አስፈላጊነት፣ የቅንጅት እጥረት፣ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ፍላጐት የሚያረካ የፋይናንስ አገልግሎት አለመኖር፣ ብድር ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ መርዘም፣ የብድር መመለሻ ጊዜ ከሥራው ባህሪ ጋር አለመጣጣም፣ ከላይ የተጠቀሱትን የሕብረተሠብ ክፍሎች አግልሏቸው ይገኛል፡፡

**ምስል 4፡-** <u>ከአብቁተዎች ብድር ለማግኘት ያጋጠሙ ችግሮች በመቶኛ</u>፡፡




ምንጭ; PIN, (2012)

# 6 የፖሊሲ ግብዓት ምክረ-ኃሳቦች

አነስተኛ ፋይናንስ አገልግሎትን ለድሆች የበለጠ ተደራሽ፣ እንዲሁም የተቀናጀና ውጤታማ ለማድረግ በኢትዮጵያ መንግሥት፣ የልማት አጋሮች፣ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መታየት የሚገባቸው የፖሊሲ እንድምታ ምክረ-ኃሳቦች ከዚህ በታች ሠፍረዋል።

*በመንግሥት መታየት የሚገባቸው ምክረ-ኃሳቦች*

- የአነስተኛ ፋይናንስ እና የአነስተኛ መድንን የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፍ እንደገና በመዳሰስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢንዱስትሪው ዘርፍ እያደጉ የመጡትን ለውጦች ማቀፍ አስፈላጊ ነው። ለምሣሌ የአነስተኛ መድን አቅርቦት፣ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን የፖሊሲ አቅጣጫ፣ የአነስተኛ ፋይናንስ ማስተባበሪያ እና መምሪያ ተቋማትን አቅም በተመለከተ ትኩረት ሊሠጥ ይገባል። የአነስተኛ ፋይናንስ የሕግና ፖሊሲ ማዕቀፍ ተዋረዳዊ ዕይታ (tired approach) እንዲኖረው ይመከራል።

- የአነስተኛ ፋይናንስ እና መድን አቅራቢ ተቋማትና ማኅበራት ከመደበኛ ባንኮች እና መድን ኩባንያዎች ጋር የሚያደርጉትን የሥራ ግንኙነቶች የበለጠ ማጠናከር ያስፈልጋል። ለዚህም መንግሥት ትልቅ ሚና መጫወት ይኖርበታል።

- የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ማኅበራትን እና ተቋማትን በማጠናከር ሌሎች ተጨማሪ ተቋማትና ማኅበራት እንዲፈጠሩ ማመቻቸትና ማበረታታት ከመንግሥት የሚጠበቅ ወሣኝ ተግባር ነው።

- መንግሥት በአነስተኛ መድን ረገድ ደንበኞችን ከምዝበራና ከችግር የመጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት የደንበኞች ጥበቃን የሚያረጋግጡ መመሪያዎች ማውጣት ይኖርበታል። ከብዙ በጥቂቱ እነዚህ መመሪዎች በሚከተሉት መርሆዎች ላይ መመስረት ይኖርባቸዋል።

    ሀ) ደንበኞች ከአቅም በላይ ብድር እንዳይጫናቸው ማድረግ ፣

    ለ) ግልፅና በኃላፊነት ላይ የተመሠረተ የዋጋ ተመን እንዲኖር ማድረግ፣

    ሐ) አግባብ ያለው የመድን አሠባሠብ ዘዴ እንዲኖር ማድረግ ፣

    መ) ሠራተኞች ሥነ-ምግባር የተከተሉ መሆናቸው በማረጋገጥ፣

    ሠ) አግባብ ያላቸው የቅሬታ መፍቻ ዘዴዎችን እንዲኖሩ ማድረግ፣

ረ) የደንበኞችን የግል መረጃ ሚስጥርነት መጠበቁን ማረጋገጥ (IAIS and CGAP, 2007)።

***በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትና ማኅበራት መታየት ያለባቸው ምክረ-ኃሳቦች***

- ✓ አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ማኅበራትና ተቋማት ተቀባይነት ያለው የቢዝነስ ዕቅድ በመንደፍ ከባንኮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር ያስፈልጋል።
- ✓ የፋይናንስ የሕብረት ሥራ ማኅበራት አባላትን ለመሳብና ቁጠባን የመሠብሠብ አቅማቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።
- ✓ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራት የጐንዮሽና የወደላይ ግንኙነታቸውን በማጠናከር የልምድ፣ የዕውቀትና የትምህርት ልውውጥ መድረኮችን መፍጠር ይጠቅማል።
- ✓ አብቁተዎች የሠራተኞቻቸውን ውጤታማነት የሚያረጋግጡ ስልቶችን በመዘርጋት እና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን በመቀነስ የተቋማቸውን ቀጣይነት ማረጋገጥ እና የወለድ ምጣኔ ተመጣጣኝ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ✓ ደንበኛ ተኮር የፋይናንስ ዓይነቶችን በብዛት ማጥናትና አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ ብዙ ደንበኞችን ለመሣብ እንደሚያስችል መረዳት ተገቢ ነው።
- ✓ የሴቶችን ተጠቃሚነት የበለጠ ለማሣደግ ሴት አንቀሳቃሾችን የሚያሣትፍ ልዩ የፋይናንስ ዓይነት ወይም መስኮት መፍጠር ጠቀሜታው የጐላ ነው።
- ✓ የተቀናጀ፣ ዘርፈ ብዙና አካታች የፋይናንስ አገልግሎት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ ሲሆን በተጨማሪ የቢዝነስ ልማት ግልጋሎትን ማካተት የሚቻልበትን ስልት መንደፍ የበለጠ ተጠቃሚዎችን ከድህነት ሊታደግና ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል።
- ✓ ልምድና ብቃት ያላቸውን ሠራተኞች በተቋማቱ ውስጥ ለማቆየት የሥራ ዕድገት መሠላል ከተዛማጅ ጥቅሞች ጋር ማዘጋጀትና መተግበር አስፈላጊ ይሆናል።

***በለጋሽ ድርጅቶችና ሲቪል ማኅበራት መታየት ያለባቸው ምክረ-ኃሳቦች***

- ❖ የሕብረት ሥራ ፌዴሬሽንና ጥምረትን ለመመስረት የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ የፋይናንስ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን የካፒታል፣ የሥልጠና፣ የልምድና የማስተዋወቅ ውስንነቶችን መፍታት።
- ❖ አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ማኅበራትን አቅም በማጐልበት ረገድ ከፍተኛ ኢንቨስትመት ስለሚጠይቅ የተለያዩ አካላት ዕገዛ ወሣኝ መሆኑን መረዳት።

- በተለይ አነስተኛ መድን አገልግሎትን ለማጐልበትና ለማስፋፋት ከከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ማኅበራትና ተጠቃሚዎች ድረስ በፅንሠ-ኃሳቡ ግልፅነትና ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤ መፍጠር፡፡
- የሴቶችንና በጣም ደሀ የሆኑትን የሕብረተሠብ ክፍሎች የበለጠ ለማሳተፍ መደበኛ ያልሆኑ ትናንሽ ቡድኖችን በመፍጠር፣ ማጠናከር እና ወደ ሕብረት ሥራ ማኅበራት እንዲያድጉ ድጋፍ ማድረግ፡፡ ያልተደራጁ የሕብረተሠብ ክፍሎችን መደበኛ ባልሆኑና አመቺነት ባላቸው ትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት አቅማቸውን ማጠናከርና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፡፡ በዚህ ረገድ የራሴድን (WISE) ልምድ መጋራት ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡
- የመማማሪያና የመወያያ አወደ ጥናቶችን በስፋት ማገዝ፡፡ በተጨማሪም በአነስተኛ መድን ረገድ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መደገፍ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡

## ዋቢ መፃሕፍት

Aragaw Yimer, (2012) Women's Participation in and Empowerment through Microfinancing: A Study of ACSI Clients of Dessie Zuria Wereda, Ethiopia. *OSSREA's Gender Issues Research Report Series No.25. PP 73-160.* Ethiopia: Addis Ababa.

___________ (2010) Rural Microfinancing and Women's Empowerment: A Study from Rural Districts of Ethiopia. *The Asian Man. An International Journal of Rural Development and Management Studies.*Vol.4 (2), PP 114-136. Lucknow: India.

Berhane Kidanu (2012) "Current status and future prospects of financial cooperatives: A proposal to support the RUSACCOs in Ethiopia." A paper submitted to the design of RUFIP II. Addis Ababa.

CoSAP (Consortium of Self-help Approach Promoters) (2014) Annual Report for Year 2014. Addis Ababa.

Dereje Kifle, Yenenesh Tadesse and Jemal Yousuf (2013) Constraints of Rural Women to Utilize Microfinance Institutions: the case of Members of Microfinance Institutions in Rural Districts of Dire Dawa Administration, Ethiopia.

Dercon, S (2009) *Risk, poverty and insurance*. Innovations in insuring the poor, 2020 vision for food, agriculture and the environment, Focus 17, Brief 3. Washington, DC: International Food Policy Research Institute (IFPRI).

Dercon S., J. Hoddinott, P. Krishnan, and T. Woldehanna, (2008) "Collective Actions and Vulnerability: Burial Societies in Rural Ethiopia." In *Collective Action and Property Rights for Poverty Reduction: Lessons from a Global Research Project*, edited by Mwangi, E., H. Markelova, and R. Meinzen-Dick. Washington, DC: International Food Policy Research Institute (IFPRI).

FCA (Federal Cooperative Agency) (2014) Ethiopian Cooperatives Movement: Successes and Challenges (Amharic version). A document Presented for Discussion. Addis Ababa.

___________ (2011) Cooperatives. Volume 8. Annual publication of the FCA public relations directorate. Addis Ababa.

FDRE (Federal Democratic Republic of Ethiopia) (2009) The Micro-financing Business Proclamation No 626/2009, NEGARIT GAZETA, 12th May, 2009. Addis Ababa.

___________ (2004) Proclamation No 402 /2004. Cooperative Societies (Amendment) Proclamation. NEGARIT GAZETA, 11th May, 2004. Addis Ababa.

___________ (1998) Proclamation No 147/1998. A Proclamation to Provide for the Establishment of Cooperative Societies. NEGARIT GAZETA, 29 December, 1998. Addis Ababa.

___________ (1996) Proclamation No 40/1996. A Proclamation for the Licensing and Supervision of MFIs in Ethiopia, NEGARIT GAZETA, Addis Ababa.

FeMSEDA (Federal Micro and Small Enterprise Development Agency) (2011) Micro and Small Enterprise Development Strategy, Provision Framework and Methods of Implementation. Addis Ababa.

Gessesse, D. (2010) "Current status and future prospects of financial cooperatives: A proposal to support the RUSACCOs in Ethiopia." In *Proceedings of the Seventh International Conference on the Ethiopian Economy*, edited by Getnet Alemun. Addis Ababa: Ethiopian Economic Association (EEA).

Getaneh Gobezie (2006) Gender, Poverty and Micro-enterprise Services in Ethiopia: Why only Few Women are Joining? A Paper Presented at National Fair – Women's Empowerment in the New Millennium 2006. *Organized by the Women Development Initiative Programme (WDIP) inEthiopia, April 6, 2006.*

___________ (2005) Regulating Microfinance in Ethiopia: Making it more Effective. Addis Ababa.

Getnet Alemu and Edilegnaw Wale (2013) Evaluating the effects of microfinance service on urban poverty reduction: the case of Arada Sub-city. Ethiopian Economic Association/Ethiopian.

Getnet Alemu (2014) Financial Inclusion, Regulation and Inclusive Growth in Ethiopia. *ODI Working paper 408, Shaping policy for development*.

GIZ and MoUDC (2012) Urban governance and decentralization program (UGDP): state of urban poverty and livelihoods analysis in eight cities final report for Debre-markos city.

Guruswamy, D. (2012) The Role of Microfinance Institutions on Poverty Alleviation in Ethiopia. Addis Ababa.

IAIS and CGAP (International Association of Insurance Supervisors and Consultative Group to Assist the Poor) (2007) *Issues in regulation and supervision of micro-insurance.* IAIS Issues Paper. Basel, Switzerland: IAIS and CGAP.

IFAD (International Fund for Agricultural Development) (2011) Federal Democratic Republic of Ethiopia: Rural Financial Intermediation Program Interim Evaluation. Addis Ababa.

Kidist G/Sillase, Bamlaku Alamirew and Aragaw Yimer (2012) *Civil Society Organizations (CSOs) supporting women's economic empowerment in Ethiopia: mapping and case studies.* Forum for Social Studies (FSS) and Atos Consulting Research Series Report.

Meherette, E. (2009) *Providing weather index and indemnity insurance in Ethiopia*. Innovations in insuring the poor, 2020 vision for food, agriculture and the environment, Focus 17, Brief 8. Washington, DC: International Food Policy Research Institute (IFPRI).

MoFED (Ministry of Finance and Economic Development) (2010) Growth and Transformation Plan (GTP). Addis Ababa.

MoUDC (Ministry of Urban Development and Construction) (2013) Survey on Micro and Small Enterprises (MSEs) in Selected Major Cities of Ethiopia. Addis Ababa.

NBE (National Bank of Ethiopia) (2013) Annual Report, Addis Ababa

Oxfam America and MDTCS (2009) Micro-insurance demand study for Ethiopia. Addis Ababa.

Oxfam America (2009): Estimating the demand for micro-insurance in Ethiopia. A report commissioned by the International Labour Organization (ILO) and

United Nations Capital Development Fund (UNCDF). Boston, MA, US: Oxfam America.

___________ (2011) “HARITA quarterly report: January 2011 – March 2011.” Boston, MA, US: Oxfam America.

Population In Need (PIN), (2012): A Draft Report on Market assessment towards women entrepreneurs working under the Informal sector in selected areas of Addis Ababa

Ruchismita, R., and S. Varma. (2009) *Providing insurance through microfinance institutions: The Indian experience.* Innovations in insuring the poor, 2020 vision for food, agriculture and the environment, Focus 17, Brief 13. Washington, DC: International Food Policy Research Institute (IFPRI).

Smith, A., and D. Chamberlain (2009) Opportunities and challenges for micro-insurance in Ethiopia: An analysis of the supply-side and regulatory environment. The Center for Financial Regulation and Inclusion (cenfri), International Labour Organisation (ILO), United Nations Capital Development Fund (UNCDF).

Wolday Amha (2015) Ten year after: What is special about the development of financial cooperatives (SACCOs) in Ethiopia? Paper presented at Two Days National Conference on Cooperatives Development in Ethiopia, jointly organized by Hawassa University & Federal Cooperative Agency, May 7-8, 2015. Addis Ababa.

Wolday Amha and David Peck (2010) Agricultural finance potential in Ethiopia: Constraints and opportunities for enhancing the system. AEMFI, Addis Ababa.

Wolday Amha, David Peck, Guush Berhane, Yoseph Aseffa and Berhane Kidanu (2013) Diagnostic Study of Providing Micro-Insurance Services to Low-Income Households in Ethiopia: An Input to a National Micro-Insurance Strategy. Ethiopia Strategy Support Program II (ESSPII). IFPRI/EDRI. Addis Ababa

World Bank (2015) Ethiopia: Poverty Assessment. Washington DC.

___________ (2013) Ethiopia Economic Update II: Laying the foundation for achieving middle-income status. Washington DC.

___________ (2009) Unleashing the Potential of Ethiopian Women – Trends and Options for Economic Empowerment. Washington DC.

Yigrem Kassa (2010) Regulation & Supervision of Microfinance Business in Ethiopia: Achievements, Challenges & Prospects. A Paper presented at International Conference on Microfinance Regulation, March 15-17, 2010, Bangladesh, Dhaka.

Zelalem Yilma, Anagaw Mebratie, Robert Sparrow, Degnet Abebaw, Marleen Dekker, Getnet Alemu, Arjun S. Bedi (2014) "Shocks and Coping Strategies in Rural Ethiopia A Policy Brief**".** *OSSREA Bulletin* Vol. XI No. 1 (February 2014)

Zeleke, H. (2007). *Insurance in Ethiopia: historical development, present status and future challenges.* Addis Ababa: Master Printing Press.

# የከተማ ድህነትና ሥርዓተ ፆታ

## ትዝታ ሙሉጌታ

## 1 መግቢያ

ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው አስከፊ ገጽታዎች አንዱ ለዘመናት ስር ሠዶ የቆየው የድህነት ሁኔታ ነው። ይህ ድህነት አብዛኛውን ዜጎቿን ለተመጣጠነ ምግብ እጥረት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለምግብ እጦት ጭምር አጋልጦት ቆይቷል። በኢትዮጵያ ለሚታየው የድህነት ሁኔታ በርካታ ምክንያቶች ተጠቃሽ ቢሆኑም፤ በተለያየ ጊዜ የሚከሠት ድርቅ፣ አስከፊ የሆነ የአካባቢ መራቆት፣ አነስተኛና የተበጣጠሰ የመሬት ይዞታ፣ በግብርና የሥራ መስክ ያለው ልማት አነስተኛ መሆን፣ ከግብርና ውጭ ያለው የሥራ ዕድል እጥረት መኖር፣ የራስን የገቢ ምንጭ ለመፍጠር የሚያስችል የክህሎትና የመነሻ ገንዘብ እጥረት እና ደካማ የሆነ የገጠርና የከተማ ቁርኝት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

በኢትዮጵያ ግብርና የዜጎች የሕይወት መንገድ ብቻ ሳይሆን ዋነኛ የገቢ ምንጭ በመሆንም ያገለግላል። ሆኖም ግን ከግብርና የሚገኘው ምርት በአብዛኛው ከእጅ ወደ አፍ ሲሆን፤ አንዳንዴም የሚገኘው ምርት የቤተሠብን የምግብ ፍላጎት ለሟሟላት እንኳን የማይችልባቸው ሁኔታዎችም ይታያሉ። በተጨማሪም ከግብርና የሚገኘው ገቢ እጥረት መኖር ዜጎች የምግብ ማብሰያ የኃይል ምንጭና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ። ይህን ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ለመለወጥ በአገሪቱ ብሔራዊና ክልላዊ መንግስታት የተለያዩ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው (Abegas; 1995)።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያለው ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ በከተማ ባለው ነዋሪ ላይም የራሱን ተፅዕኖ እያሳደረ እንደሆነ ይታያል። እንደሚታወቀው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሠት ለበርካታ ዓመታት ያልተቋረጠ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ እየጨመረ መሄዱን መረጃዎች ያሳያሉ (CSA, 2011)። ሆኖም ግን ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሱ ሰዎች በከተሞች አካባቢ ሲደርሱ የሚያጋጥማቸው በአመዛኙ ያሠቡት የተሻለ ሕይወት ሳይሆን መልኩን የቀየረ ድህነት (የከተማ ድህነት) ነው። ምንም እንኳ የከተማ ድህነት በአባወራዎችም ሆነ በእማዎራዎች ላይ ያለ ቢሆንም እናቶችና ልጃገረዶች በድህነት ከሚኖሩት መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ። በማሕበረሠቡ ውስጥ ባላቸው ዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባሕላዊ ደረጃ ምክንያት በከተማ ድህነት ውስጥ የሚገኙ ሴቶችና ልጃገረዶች በአብዛኛው የሚኖሩት ለኑሮ ተስማሚ ባልሆኑ ደሳሳ ቤቶች በሚበዙባቸው የከተማ ክፍሎች ነው። በቂ የመተዳደሪያ ሥራ አለመኖርና የኢኮኖሚ ችግሮች የከተማ ሴቶችን የኑሮ

ጫና ከማባባሱም ባሻገር ተመጣጣኝ ክፍያ ለሌላቸው ሥራዎች ያጋልጧቸዋል። በዚህም ሳቢያ በተለይ በከተማው ማሕበረሠብ ውስጥ ሴቶች የኢኮኖሚ ጫናዎችንና የመተዳደሪያ እጦት ለመታገል ይገደዳሉ። ሴቶች መደበኛ ባልሆኑ የሥራ መስኮች ላይ በብዛት በተሠማሩ ቁጥር በምግብ ራሳቸውን የመቻል ዕድላቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖው እየጨመረ ስለሚሄድ ድህነቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገርበት ሁኔታ ይፈጠራል።

## 2 የጥናቱ ዓላማ፣ አሠራርና አካባቢ

ይህ ጥናት የተካሄደው አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 10 ቀበሌ 10 ውስጥ ልዩ ስሙ ዶሮ ማነቂያ በሚባለው አካባቢ ነው። የጥናት ቦታው የከተማ ድህነት በብዛት የሚታይበት በመሆኑ ሌሎች ድህነት በብዛት የተንሰራፋባቸውን ተመሳሳይ የከተማ ክፍሎችን ይወክላል ተብሎ በመታመኑ ሆን ተብሎ የተመረጠ ነው። ጥናቱ የከተማ ድህነት ከፆታ አንፃር ምን እንደሚመስል ይመረምራል። ለከተማ ድህነት ከፍተኛ ሚና ያላቸውን ዋና ዋና ነገሮች ከፆታ አንፃር በመለየት ድህነትን ለመቋቋም ከሚደረገውን ጥረት አንጻር የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች ያነሳል።

- ወደ ከተማ በመከተም ሒደት ላይ ያሉ ሕዝባዊ ሁኔታዎች ከሥርዓተ ፆታ አንፃር ምን ይመስላሉ?
- የከተማ መጠለያና የከተማ አገልግሎት ሠጭዎች የሚባሉት የትኞቹ ናቸው? ከፆታ ጋር ያላቸው ተዛምዶስ ምን ይመስላል?
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሠት በፆታና በድህነት ላይ በምን መልኩ ተፅዕኖ ይኖረዋል?
- የቤተሠብ አደረጃጀትና መዋቅር በፆታና በድህነት እንዴት ሊገለጹ ይችላሉ?

ጥናቱ የዓይነታዊ የጥናት ሥነ-ዘዴን (Qualitative research method) ተከትሎ የተካሄደ ሲሆን፤ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችም በጥልቅ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ውይይት፣ በጥልቅ-ምልከታ (critical observation) እና ከሁለተኛ ደረጃ ምንጮች (secondary sources) ተሠባስበዋል። በዚህም 20 ከሚሆኑ ሴት የመረጃ ምንጮች ጋር ጥልቅ የሆነ ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል። አባወራ፤ እማወራ እና ላጤ ወንዶችን ያካተተ 3 የቡድን ውይይቶችም ተደርገዋል። በተጨማሪም ከቀበሌ ባለሥልጣናትና ከጤና ባለሙያዎች ጋር በተደረጉት ቃለ-መጠይቆች ጠቃሚ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል። ከቀበሌና ወረዳ መስተዳደሮችም ሁለተኛ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማካተት ተሞክሯል።

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከተለያዩ የአገራችን የገጠር ክፍሎች ወደ አዲስ አበባ ፈልሠው በመጡ ሰዎች ላይ ሲሆን ጥናቱ በተካሄደበት ዶሮ ማነቂያ ሠፈር ያሉ አብዛኞቹ ቤተሠቦች ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው። ሠፈሩ ያረጁና ከፍተኛ ጥግግት ያላቸው ቤቶች የበዙበት፤ እንዲሁም ንጽህና የጎደለው በመሆኑ ነዋሪዎቹ ለከፋ የጤና፣ የኢኮኖሚና የአካል ጉዳት ጠንቆች የተጋለጡ ናቸው። ጥናቱ የሠፈሩ ሴቶች (እማወራዎችም ሆኑ የአባወራ ሚስቶች) የድህነቱን ከፍተኛውን ድርሻ እንደተሸከሙና የቤተሠባቸውን ኑሮ ለማሻሻል ትልቁ ኃላፊነትና ሸክም እነርሱ ላይ እንደወደቀ ያሳያል። እነዚህ የሕብረተሠብ ክፍሎች ንፅህና በጎደላቸው የመጸዳጃ ቤቶች አካባቢ እንዲኖሩ ከመገዳደቸውበላይ፣ በቂ የውኃ አቅርቦት በሌለበት ሁኔታ ሳይቀር የቤት ውስጥ ንፅህናን ለመጠበቅ ጥረት ያደርጋሉ። የመጸዳጃ ቤትና የማድቤት እጥረትና እጦትም አለባቸው። በአንድ ማድቤት በርካታ ሰዎች ይገለገላሉ፣ በጠባብ ግቢና ብዙ ሰዎች በሚኖሩበት መጠለያ የቤተሠባቸውን ጤና የመጠበቅ ኃላፊነትም አለባቸው። በዚህ ጥናት ተሳታፊ የነበሩ ወንድና ሴት መረጃ ሠጪዎች የሚኖሩበት አካባቢ ብዙ ሕዝብ የተጠራቀመበትና ለኑሮ ምቹ ያልሆነ ነው። አብዛኞቹ የሚኖሩት አሮጌና በአንድ ክፍል የቀበሌ ቤቶች ውስጥ ሲሆን፤ የንፅህና ጉድለት፣ የተበላሹ የቆሻሻ መተላለፊያ ቱቦዎችና ቦዮች፣ የኤሌክትሪክና የንፁህ ውኃ ችግር ዋና ዋና የአካባቢው መገለጫዎች ናቸው። የጥናቱ ተሳታፊዎች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆኑ የተሻለ ሥራ ሠርተው ራሳቸውንና ቤተሠባቸውን ለመደገፍ የሚያስችል በቂ የሆነ የሙያ ክህሎት እንዳይኖራቸው አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የሥራ እጦት ያለበት ሲሆን አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎችም ሥራ የሌላቸው ወይም አስተማማኝ ባልሆኑ ኢ-መደበኛ የገቢ ማመንጫ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ለመገመት የሚያስቸግር በጣም አነስተኛ የገቢ መጠን አላቸው።

የእናቶችና የልጆች የጤና ሁኔታ ደግሞ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ ነው። በንጽህና ጉድለት ሳቢያ አብዛኞቹ ሕጻናት ለቆዳና አይን ችግሮች የተጋለጡ እንደሆነ በምልከታ ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል። እናቶች ደግሞ ባብዛኛው የመተንፈሻ አካላት ችግር ተጠቂዎች ናቸው። ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በቤተሠብ ውስጥ ለከፋ የምግብ እጥረት ተጋላጭ እንደሆኑና ይኸው ሁኔታ ሴቶች በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ እንዲኖሩ እንዳደረጋቸው ለመረዳት ተችሏል።

## 3 የከተማ ድህነት ምንነት

የከተማ ድህነትና የገጠር ድህነት የሚለያዩበት ብዙ ገጽታዎች አሉ:: ለምሳሌ ያህል የከተማ ነዋሪዎች ከገጠር ሰዎች በበለጠ ሁኔታ የገንዘብ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ ጥገኛ ናቸው (Beal and Fox, 2007):: በከተሞች አካባቢ ውድ የሆነው የዕለት ከዕለት የሕይወት እንቅስቃሴዎች፤ ድሆች ለአገልግሎትና የመሠረት ልማት ግልጋሎቶች ያላቸው ቀረቤታ አነስተኛ መሆን፣ ለአየር ሁኔታ ለውጥ አደጋዎች ያላቸው ተጋላጭነት እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የወንጀል ክስተት እና ነውጦች የድህነት ደረጃን በከተሞች ይበልጥ የሚያባብሱና የከተማ ድህነትን የተለየ ፆታዊ ገጽታ የሚሠጡ ምክንያቶች እንደሆኑ ይታመናል:: ከላይ የተዘረዘሩት በከተሞች የሚከሠቱ ነገሮች ከፍተኛውን ጫና የሚያሳድሩት በዚሁ አካባቢ ነዋሪ በሆኑ የሕብረተሠብ ክፍሎች ሲሆን በተለይም ደግሞ ሴቶችን ዝቅተኛ ገቢ ወደሚያስገኙ የቤት ውስጥ ሥራዎች ማለትም ጽዳት፣ ምግብ ማብሰል፣ እንዲሁም ሕጻናትን፣ በሽተኞችንና አዛውንትን ወደመንከባከብ እንዲገቡ ይገፋቸዋል:: በተመሳሳይ መንገድ በከተሞች አካባቢ ያለው በጥሬ ገንዘብ የሚገኝ ገቢ ደሀ ሴቶችን ከወጣትነት ዕድሜ ጀምሮ ጥሬ ገንዘብ ለሚያስገኙ ሥራዎች ተጋላጭ ሲያደርጋቸው ቆይቷል:: ይህ ሁኔታ ደሀ ሴቶችን ለተለያዩ እጅግ ዝቅተኛ ገቢ ለሚስገኙ መደበኛና ኢ-መደበኛ ለሆኑ ሥራዎች የዳረገ ሲሆን፤ አስከፊው ሁኔታ ደግሞ እነዚህ አይነት የሥራ ዓይነቶች ለእርጅና ጊዜ ዋስትናና ለአደጋ ጊዜ ካሳ የሚያስገኙ አለመሆናቸው ነው::

ሌላው ከፆታ ሥርዓት አንፃር በሴቶች ላይ ተፅዕኖ ያለውና ለድህነት መባባስ አስተዋፅኦ የሚያደርገው የጊዜ ድህነት ነው:: ይህ ጉዳይ የዕኩልነትና የማኅበራዊ ፍትህ ጥያቄዎችንም የሚመለከት ነው:: በከተሞች የጉልበት ገበያ ውስጥ ሴቶች ያላቸው ደረጃ ከወንዶች ያነሰ መሆኑ፣ ራሳቸውን ችለው ዕሴት የመፍጠር ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑና እንዲሁም ለሁከትና ብጥብጥ ያላቸው ተጋላጭነት ከፍተኛ መሆኑ የዕኩልነትና የማኅህበራዊ ፍትህ ጥያቄዎችን ማስነሳቱ የሚጠበቅ ነው::

የከተማ ድህነት ለየት ያለ ሥነ ፆታዊ ገጽታም አለው:: ለምሳሌ ያህል በበርካታ ከተሞች ያሉ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነጻጸሩ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው እንዲሁም ጤናና ትምህርት ከማግኘት አንጻርም ተጠቃሚነታቸው አነስተኛ ሲሆን፤ በመደበኛ ተቋማትና በከተማ አስተዳደር ያላቸው ውክልናም በጣም ዝቅተኛ ነው (Chant, 2011)::

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ጫና ቢኖርባቸውም ሴቶች ጉልበታቸውን ክፍያ ላለውም ሆነ ለሌለው ሥራ በማዋል ለከተሞች ዕድገትና ብልጽግና ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: ነገር

ግን እነዚህን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከሚያበረክቱባቸው የከተሞች ዕድገት ውስጥ የተሻለ የሥራ ዕድል፣ የኑሮ ሁኔታና፣ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘት ዕድላቸው ውስን ሆኖ ይታያል፡፡ እንዲሁም ዕሴት በመፍጠር፣ በመደበኛ ተቋማትና በከተማ አስተዳደር ውስጥ ያላቸው ውክልናም በጣም ዝቅተኛ ነው (Chant, 2011)፡፡ በእርግጥ ይህ ጉዳይ የሴቶች ችግር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የማኅበረሠብ ችግር ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ ክፍያ የማያስገኙ ሥራዎች ማለትም ሕጻናትን፣ አዛውንትን፣ ህሙማንንና የአካል ጉዳተኞችን መንከባከብ በአብዛኛው የሴቶች ድርሻ ብቻ ሆነው ይታያሉ፡፡

በከተማ የሚኖሩ ድሆች ለተለያዩ ከፍተኛ አካባቢያዊ አደጋዎች፣ ለመጠለያ ችግር፣ ለንፁህ ውኃ እጥረት የተጋለጡ ሲሆን ለእነዚህ አገልግሎቶችም ያላቸው ተደራሽነት ዝቅተኛነት በመሆኑ የራሳቸውንና በስራቸው የሚገኙ የቤተሠብ አባላትን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት እጅግ ከፍተኛ የሆነ ጊዜ እንዲያባክኑ ያደርጋቸዋል (UNFPA, 2007)፡፡

## 4 የከተማ ድህነት ከገቢና ገቢ-አልባነት አንፃር

የተሻለ የሥራ ዕድልና መሠረተ-ልማት ከመኖሩ አንፃር የዓለም ሕዝብ ስርጭት በከተሞች አካባቢ እየበዛ መጥቷል፡፡ ከተሞችና ከተሜነት በሦስተኛው ዓለም አገሮች በፍጥነት እያደጉ በመምጣታቸው በተመሳሳይ ሁኔታ የከተማ ድህነትም በበርካታ የእስያና የአፍሪካ አገሮች በፍጥነት እየሠፋና ስር እየሠደደ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ (UNFPA, 2007)፡፡ ምንም እንኳ የኑሮ ውድነት የከተማውንም ሆነ የገጠሩን ደሀ እያንገላታው ቢሆንም የከተማ ነዋሪዎች ከገጠር ነዋሪዎች በበለጠ ሁኔታ መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለሚሟላት በጥሬ ገንዘብ ገቢ ላይ ጥገኞች ናቸው (Banerjee and Duflo, 2007)፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው የገቢ እጥረት መኖር የድህነት ዋናው ምክንያትና መገለጫም ነው፡፡ ነገር ግን የድህነት መስመርን ከመወሠን አንፃር የዘርፉ ባለሙያዎች የገቢ መጠንን የድህነት የመወሠኛ (የማወቂያ) መሠረት አድርገው መረዳታቸው የድህነትን ውስብስብ ባህሪና ገጽታ በእጅጉ ያሳንሠዋል፡፡ (Bapat, 2009, Sabry, 2009; Satterth, 2004)፡፡

በርካታ ተዛማጅ ፅሁፎች እንደሚያሳዩት የገቢ ድህነት የሚባባሠው ከዘወትር ከባድ የኑሮ ሁኔታ ጋር በተያያዙ ችግሮች ነው (Rakodi, 2002; Written, 1995)፡፡ በመሆኑም የገቢ መጠንን እንደዋና የድህነት ማሳያ መውሰድ የከተማ ድህነትን ዝቅ አድርጎ እንደማየት ከመቆጠሩም ባሻገር የድህነት ዘርፈ-ብዙ ገጽታዎች በትክክል እንዳይታዩ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሳቢያ ለድህነት ቅነሳ የሚያግዙ ፖሊሲዎችን ለሚቀርጹ ብዙ ጠቀሜታ አይኖረውም፡፡

የመሠረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት የከተማ ድሆችን በቂ ላልሆነ መጠለያና በብዙ ሰዎች በተጨናነቀ አካባቢ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የመኖሪያ ቤታቸውና አካባቢያቸው ጥራቱ ዝቅተኛ ቢሆንም ገቢ ከማስገኘት አንጻር ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል፡፡ እንደሚታወቀው የከተማ ነዋሪዎች የራሳቸውን ምግብ የሚያመርቱበት ዕድል በጣም ውስን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ያልተጠበቀ የዋጋ ንረትን ከማስከተሉ ባሻገር የከተማ ድሆች ለፍጆታ የሚያውሉትን ነገር ሁሉ መጠኑንና ጥራቱን እንዲቀንሱ ያስገድዳቸዋል፡፡ እነዚህ ዜጎች በቤታቸው የሚጠራቀሙት የፍጆታ ሽቀጥ ባለመኖሩ የሚስፈልጋቸውንና መግዛት የሚችሉትን ነገር በአካባቢያቸው ከሚገኙ የችርቻሮ ሱቆች በየቀኑ መግዛት ይኖርባቸዋል (Tolossa, 2010)፡፡

ለንጹህ ውኃና ኤሌክትሪክ ያለው ተደራሽነት አንዱ የከተማ ድህነት ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በተለያዩ አገራት በከተማ የሚኖሩ ድሆች ለውኃ የሚከፈሉት ዋጋ በአጠቃላይ ሲታይ ከፍተኛ ሲሆን ዋጋው በአብዛኛው በውኃ መኖር አለመኖር ላይ ይወሠናል፡፡ ህገ ወጥ በሆኑ ቤቶች የሚኖሩ የከተማ ድሆች ለቧንቧ ውኃ ያላቸው ተደራሽነት በእጅጉ ዝቅተኛ በመሆኑ ከግለሠብ ውኃ ሻጮች መግዛት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ አብዛኞዎቹ ድሆች ለሚጠቀሙበት መጸዳጃ ቤትም ክፍያ ይጠየቃሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በየስፍራው ስለሚፀዳዱ በነዚህ ደሳሳ ሠፈሮች የሚኖሩ ሰዎች ለተለያዩ የጤና ጠንቆች ተጋላጭ ናቸው፡፡

ድሆች በሚኖሩበት ጎስቋላ የሆኑ የከተማ ክፍሎች የፍሳሽ መተላለፊያ ፈጽሞ የሌላቸው ወይም ቢኖራቸውም ለብልሽት የተጋለጠ በመሆኑ ነዋሪዎች ለጎርፍ አደጋ የተጋለጡ ናቸው፡፡ መተላለፊያ (መፍሰሻ) በማጣቱ በአካባቢው የሚጠራቀመው ፍሳሽ ለተለያዩ በሽታ አስተላላፊ ተዋኅሲያንና ትንኞች መራቢያ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ እነዚህ ያለዕቅድና ያለ ሕጋዊ ፈቃድ የተመሠረቱ የመኖሪያ አካባቢዎች ለደረቅ ቆሻሻ አወጋገድም ከፍተኛ ችግር ይፈጥራሉ፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ንጽህና ያልተሟላና ለኑሮ ምቹ ባለመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችን የጤና ሁኔታ አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ በተለይም ደግሞ ሕጻናትና በዕድሜ የገፉ አዛውንት ብዙ ጊዜያቸውን በቤትና በአካባቢው የሚያሳልፉ በመሆናቸው በይበልጥ የችግሩ ተጠቂዎች ይሆናሉ፡፡

ክፍያ በሌላቸው ማለትም ድጋፍ የሚስፈልጋችውን መንከባከብና የስነ-ተዋልዶ ሥራዎች የሚሠሩ ዜጎች የድህነት ገቢ-አልባ ገጽታዎች ተጠቂ ናቸው፡፡ በቂ የውኃ አቅርቦት በሌለበትና የአካባቢ ንፅህና፣ ኤልክትሪክና የመሳሰሉት አገልግሎቶች ባልተማሉበት ሁኔታ በምግብ ዝግጅት፣ በቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ጽዳት ላይ የተሠማሩ ሴቶች ለተጨማሪ ጫናዎች ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ እንደ ቻንት አገላለጽ (Chant, 2007b) ይህ ሁኔታ በሴቶች ላይ *የጊዜ ድህነትና የስሜት ጫና* የሚባለውን

ይፈጥራል፡፡ በተመሳሳይ ይህንን ሁኔታ ጋሜጅ የተባለ ተመራማሪ ‹‹የድህነት ዘርፈ ብዙ ገጽታዎች›› በማለት ያስቀምጠዋል (Gammage, 2010)፡፡ ከዚህ በላይ የከተማ ድህነትን ከሥርዓተ-ፆታ አንፃር ከሚያባብሱ ነገሮች መካከል ለመብቶች በቂ ከለላና እውቅና አለመስጠት፣ በቢሮክራሲውና በፖለቲካው ውስጥ ያለው ውክልናና ስልጣን ውስን መሆን ተጠቃሽ ናቸው (Satterhwaite, 2004)፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይ በሴቶች ላይ የሚንፀባረቅ ሲሆን በዚህ ጽሁፍ ሌሎች ክፍሎች ላይ ወደፊት እንደሚጠቀሰው የሴቶች መብት ከወንዶች መብት ጋር ሲነጻጸር ደህንነቱ አስተማማኝ አለመሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡

# 5 የከተማ ሥነ-ሕዝባዊ አካላት ሁኔታ እና ሥርዓተ-ፆታ

ይህ የጥናቱ ክፍል ሁለቱን የከተማ አካላት ማለትም የሕዝብ ዕድገትን እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሠት በሠፊው ያብራራል፡፡ በተለይም ደግሞ በከተሞች ያለውን የሥርዓተ-ፆታ ንጽጽር ልዩነት ከአጠቃላይ ሕዝብና ከገጠሩ ሕዝብ ጋር በማነፃፀር ለማሳየት ይሞክራል፡፡ በመቀጠልም ለእማወራ ቤተሠቦች ልዩ ትኩረት በመስጠት በከተሞች በሚገኙ በእማወራ ቤተሠቦች መዋቅራዊ አደረጃጀት ላይ ያለውን እንድምታ ለማሳየት ጥረት ያደርጋል፡፡

## 5.1 መዋለድ (fertility)

ለከተሞች የሕዝብ ቁጥር መጨመር ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሠት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው በሠፊው ይታመናል፡፡ እንደ 1999 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት 48% የሚሆነው የአዲስ አበባ ነዋሪ ከገጠር የፈለሠ ነው፡፡ በተጨማሪም ቆጠራው በተከናወነበት ወቅት 14% የሚሆኑት ፈላሾች በአዲስ አበባ መኖር ከጀመሩ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ ያነሰ ቆይታ እንዳላቸው ታውቋል (CSA, 2009)፡፡ ይህ ሁኔታ በአብዛኛው በዝቅተኛና በመካከለኛ ገቢ አገሮች ካለው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ፍልሠት ለከተማው ሕዝብ ዕድገት ዋና ምንጭ በሆነባት አዲስ አበባ እንኳ የተፈጥሮ የሕዝብ ዕድገት 50% ያህሉን ይይዛል፡፡ ሆኖም ግን በከተሞች ያለው የሕዝብ ማደግ ወይም ውልደት ፍጥነት ከገጠሩ ጋር ሲነፃፀር በጥቅሉ ዝቅተኛ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ለዚህም በርካታ ጉዳዮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡ ሕጻናትን ለማሳደግ የሚጠይቀው የገንዘብና የጊዜ ወጪ ከፍተኛ መሆኑ፣ የከተማ ነዋሪዎች የትምህርት ደረጃቸው የተሻለ መሆንና ለተለያዩ የኑሮ ዘይቤ ሞዴሎች ያላቸው ቀረቤታ ከፍተኛ መሆን (ለምሳሌ ዘግይቶ ማግባት- በተለይ ለሴቶች)፣ ለወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ተደራሽ መሆን እና ሴቶች በተለያየ የሥራ መስክ የተወጠሩ መሆናቸው እንደማሳያ ይጠቀሳሉ (National Research Council, 2003)፡፡

የመዋለድ ደረጃ በፍጥነት ሊለወጥ ይችላል። ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሡ ሰዎች ከተማ ከደረሱ በኋላ ራሳቸውን ከአዲሱ የመኖሪያ አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማለማመድ የመውለድ መጠናቸውን ይቀንሳሉ። ሆኖም ግን የገቢ መጠንንና የመኖሪያ ቦታን ከግምት ውስጥ በማስገባት የከተማንና የገጠርን የመውለድ መጠንን ስንመለከት ልዩነቱ በጣም ጉልህ ሆኖ አይታይም (Schovmarker, 2004)። ይህ የሚሳየው ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮችና ትናንሽ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ለሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎትና ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ያላቸው ተደራሽነት አነስተኛ መሆኑን ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ አበባም የመውለድ መጠን በጣም ዝቅተኛ (TFR =1.9) እና የወሊድ መቆጣጠሪያ የስርጭት መጠን መጠነኛ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ። በመውለድ ዕድሜ ክልል (15-49 አመት) በሚገኙ 2,976 የአዲስ አበባ ነዋሪ ሴቶች ስነ-ተዋዷዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ እሸቱና ሩት (2008) የተባሉ ተመራማሪዎች ያደረጉት ጥናት እንደሚያሳየው ድሆች (በቀን ከአንድ ዶላር በታች ወይም በወር 250 ብር አካባቢ የሚያገኙ) የመጀመሪያና ሁለተኛ ልጃቸውን የሚወልዱበትን ጊዜ የሚያራዝሙ ሲሆን፤ በንጽጽር የተሻለ ኑሮ የሚኖሩ ሴቶች ግን በቶሎ እንደሚወልዱ ያሳያል።

በዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ ግለሠቦች እንደገለፁት ደግሞ በአማካይ እያንዳንዷ ሴት 2.9 ልጅ አላት ። ይህ አማካይ የውልደት መጠን ከአገር አቀፍ አማካይ የውልደት መጠን ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ሊባል የሚችል ነው። ሆኖም ግን ከመረጃ ሠጪ ግለሠቦች መካከል የተወሰኑት እስከ 5 የሚደርሱ ልጆች ያላቸው ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ ምንም ልጅ ያልወለዱ ይገኙባቸዋል። የሕጻናትን ቁጥርና ድህነትን የመቋቋሚያ ዘዴዎችን አስመልክቶ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት ምንም እንኳን ሕጻናትን ከማሳደግ ጋር ተያይዞ በርካታ ፈተናዎች የሚገጥሙ ቢሆንም ሕጻናት የእርጅና ጊዜ አለኝታዎች በመሆናቸው በቂ የገቢ መጠን አለመኖር ልጆች ከመውለድ እንደማያግዳቸው ይናገራሉ። በውይይቱ ወቅት በግልፅ እንደተንፀባረቀው አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች በቂ መረጃና ግንዛቤ አላቸው። ለምሳሌ ያህል የመረጃ ምንጭ 21 እንደምትለው ሦስቱንም ልጆቿን የወለደቻቸው አይነ-ስውር ከሆነች በኋላ ነው። ግለሰቧ እንደምትለው የኑሮ ዘይቤዋና የገቢ ምንጯ የአይን ብርሃን ማጣቷን ተከትሎ ሙሉ በሙሉ እንደተለወጠ ትናገራለች። ይሁንና ይህ ክስተት ልጅ ከመወለድ እንዳላገዳት ታሠምርበታለች። ይህች ግለሠብ ሁኔታውን ስታብራራ "የአካል ጉዳት ከደረሰብኝና የገቢ ምንጬ ከቆመ በኋላ ልጅ ወልጄ ማሳደግ እንደሚከብደኝ በደንብ እረዳ ነበር።፡ ሆኖም ግን ይህን እያወቅኩ ነው ልጆቼን ለመውለድ የወሰንኩት" ብላለች። ምክንያቷን ስትገልጽ

"ብታመም ወይም ሌላ ችግር ቢገጥመኝ ማንም ለችግሬ ደርሶ ሊንከባከበኝ አይችልም" ብላለች። እንዲሁም "አሁን ምንም ያህል ሕጻናት ቢሆኑ ልጆቼ የኔን የኑሮ ሁኔታ የመረዳት ጥሩ ልብ ያላቸው ሲሆን እኔን ለመርዳትም የተቻላቸውን ያህል ያደርጋሉ" ብላለች። ሌሎች የመረጃ ምንጮችም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳዩን ሲገልፁ በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ለሚኖር ሰው ልጅ ወልዶ ማሳደግ ከባድ እንደሆነ እንደሚረዱ ይናገራሉ። ሆኖም ግን ስለ ልጆቻቸው ሲያስቡ የደስታ ስሜት እንደሚሰማቸው ይናገራሉ። በእርግጥ ከጎረቤቶቻቸው የሚሰነዘረውን አስተያየትና አሽሙር ለመቆጣጠር አስቸጋሪ የነበረበት ጊዜ እንደነበር ያስታውሳሉ። ይሁንና ሁሉን ነገር የሚያደርገው ፈጣሪ መሆኑን በማመን የሆነውን ሁሉ በፀጋ እንደተቀበሉ ይመሠክራሉ።

## 5.2 ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሠት እና ፆታዊ ምርጫ

በአንድ አገር ውስጥ የሚደረግ የዜጎች የፍልሠት አቅጣጫ በአካባቢዎች የከተማነት ደረጃ ይወሠናል። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የከተማነት ደረጃ አነስተኛ በመሆኑ ግብርና የአብዛኛው ሕዝብ ዋነኛ የሥራ መስክ ነው። ስለዚህ የገጠር ነዋሪዎች ለተሻለ የኑሮ ሁኔታ ፍለጋ በአካባቢያቸው ወደሚገኙ ከተሞች ይፈልሣሉ። በ2005ቱ አገር አቀፍ መረጃ መሠረት ወደ 18% የሚገመተው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው ከትውልድ ቦታው ውጪ ነው። በኢትዮጵያ የከተሞች መስፋፋት እና መመስረት በፍጥነት እየተከሠተ ያለ ሁኔታ ቢሆንም (4.4% በዓመት ይገመታል)፤ የከተሞች የዕድገት ደረጃ ግን አሁንም ዝቅተኛ ነው። ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ 16% ያህሉ ብቻ በከተሞች እንደሚኖር በ2006 የተገኘው መረጃ የሚያሳይ ሲሆን፤ በ1999 ደግሞ ይኸ አሀዝ 13% እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ (CSA, 2006)። በ2020 ደግሞ በከተሞች የሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 22 ሚሊዮን እንደሚደርስ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህ ስሌት 4.4% ዓመታዊ የሕዝብ ዕድገት ፍጥነትን መሠረት ያደረገ ነው (PASDEP, 2006)።

ፍልሠት ለማድረግ ከመወሰን ጀርባ የሰዎች ፆታ ራሱን የቻለ ሚና እንዳለው ማወቅ ይቻላል። ለሴቶች ፍልሠት ብዙውን ጊዜ የሚሰጠው ምክንያት የጋብቻ ሁኔታና የትዳር መፍረስ ሲሆን፤ ለወንዶች ፍልሠት ደግሞ እንደምክንያት የሚጠቀሰው ሥራ ፍለጋ እንደሆነ ነው። ምቹ ሁኔታ በማጣት የሚከናወን ፍልሠት፤ ማለትም በመፈናቀል፣ በጦርነት፣ በድርቅ ለሁለቱም ፆታዎች እንደምክንያት እንደሚጠቀስ ጥናቶች ያሳያሉ (World Bank, 2006)።

በኢትዮጵያ ፍልሠት ለሴቶች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን በዚህም የቤት ውስጥ የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል እንደሚቻል በዘርፉ የተደረገ ጥናት ያሳያል (ILO, 2004)

በቋሚነት የሚደረግ ፍልሠት ከወንዶች ይልቅ በሴቶች በብዛት እንደሚፈፀም የሚገመት ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ከሥራ ፍለጋ ጋር በተያያዘ ለአጭር ጊዜ የሚያደርጉት ፍልሠትም እየጨመረ እንደመጣ ጥናቱ ያሳያል (Gold Stein et al; 2000)። አንድ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ የሴቶች ፍልሠት ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው በላጤዎች፣ በፈቱና ለአጭርም ይሁን ለረጅም ጊዜ ከባሎቻቸው በኑሮ በተለያዩ ሴቶች እንደሆነ ይጠቁማል (CSA, 2009)።

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮችን የሕይወት ታሪክ (profile) ስንመለከት ከ20 ሴቶች መካከል 16 ያህሉ ከገጠር አካባቢዎች (በይበልጥ ከወሎና ጉራጌ አካባቢዎች) በፍልሠት የመጡ ናቸው። ከሞላ ጎደል ሁሉም ወደ ከተማ የመጡት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ እንደሆነ ይናገራሉ። ከ16 ፈላሾች መካከል ደግሞ 4ቱ በቀድሞ የመኖሪያ አካባቢያቸው ትዳር የመሠረቱ ሲሆን ትዳራቸውን ትተው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ ችለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ 14 ያህሉ ሴቶች ወደ ከተማ በፈለሡበት ወቅት ላጤዎች የነበሩ ሲሆን ከነሱ መካከል አንዷ ብቻ ባሏ የሞተባት ነበረች። ከነዚህ ፈላሾች መካከል አንዷም ብትሆን የተሻለ ትምህርት ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ እንደመጣች በምክንያትነት አላቀረበችም። ሁሉም ለፍልሠታቸው በምክንያትነት የሚያቀርቡት በከተሞች ጥሩ የሥራ ዕድል እንዳለ የሰሙት መረጃ እንዳነሳሳቸው ሲሆን፤ ወደ ከተማ እንደመጡ ያረፉት በየዘመዶቻቸው ቤት መሆኑንም ይናገራሉ። አብዛኞቹ የመረጃ ምንጮች እንደሚናገሩት አንዳንድ በቤት ሠራተኛነት ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ ሴቶች ትምህርት የመማር ዕድል ያገኙ ሲሆን፤ በሌሎች የቀን ሠራተኝነትን በመሳሰሉ ሌሎች የሥራ መስኮች የቆዩ ሴቶች ግን ትምህርት የመጀመሩ ዕድል እንዳልገጠማቸው ገልፀዋል። መረጃዎች በግልጽ እንደሚያሳዩት የአብዛኞቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ዕጣ ፈንታ በግለሰብ ቤቶች ውስጥ በአገልጋይነት መቀጠር ሲሆን የተወሰኑ ሴቶች የወር ደመወዝም 7 ብር ብቻ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በሌላ በኩል አብዛኞቹ ወንድ የመረጃ ምንጮች ወደ ከተማ የመጡት በቅርብ ጊዜ እንደሆነ ቢገልጽም አዲስ አበባ ውስጥ መጀመሪያ ላይ የነበረው የሥራ እጦት ተቀይሮ አሁን የተሻለ የሥራ ዕድል እንዳለ ይናገራሉ።

በከተሞች ውስጥ ያሉ የሥራ ዕድሎች እየጨመሩ በመጡ ቁጥር ለፆታ ተኮር ፍልሠት መጨመር እንደመንስኤ የሚወሰድ ነው። እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ነገር የሴቶች ፍልሠት መንስኤ ከሆኑት መካከል ከገጠር መሬት ተደራሽነት እና ከውርስ ጋር በተያያዘ የሚደርስባቸው በደል አንዱ ነው። ይህ ሁኔታ በተለይ በእማወራ በሚመሩ ቤተሠቦች ላይ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ነው (Mabala and Cooksey, 2008)። ይህ ጥናት እንደሚያሳየው በቤተሠብ አባላት መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ሳቢያ መኖሪያ አካባቢያቸውን ትተው ወደ ከተማ የመጡ የተወሰኑ

ሰዎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ ያህል መረጃ ሰጪ 17 እንደምትለው አባታቸው ከሞቱ በኋላ የቤተሠብ አባላት ተስማምተው የእርሻ መሬታቸውን መጠቀም እንዳልቻሉና ቤተሠቡ አስከፊ ችግር ውስጥ እንደገባ ከገለፀች በኋላ በዚሁ ምክንያት እናታቸው ሁሉን ነገር ትታ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣች ትናገራለች።

በተጨማሪም በገበያና የአየር ንብረት ችግሮች ምክንያት ከግብርና የሚገኘው ገቢ መቀነስ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የገጠር ነዋሪ በገጠር ያለውን ተጋላጭነት ለመቀነስና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት በማሠብ ወደ ከተሞች እንዲፈልስ ያደርጋሉ። አብዛኞቹ ወንድ የመረጃ ምንጮችም ይህንን ኃሳብ ይጋራሉ። እነዚህ ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት አስተማማኝ የሆነ የዝናብ እጦት እና የእርሻ መሬት መጠን መቀነስ ለግብርና ምርታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀነስ ዋነኛ ምክንያቶች ሲሆኑ፣ በዚህ ሳቢያም የተለያዩ የገቢ ምንጮች ፍለጋ ወደ ከተሞች ለመፍለስ እንደተገደዱ ይናገራሉ። ከሴት የቡድን ውይይት አባላት በተቃራኒ አንዳንድ ወንድ የቡድን ውይይቶች አባላት እንደገለፁት በትውልድ አካባቢያቸው የራሳቸው ይዞታ የሆነ የእርሻ መሬት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ረገድ 20 ከሚሆኑ ሴት የመረጃ ምንጮች መካከል አንዷ ብቻ በትውልድ አካባቢዋ የራሷ ይዞታ የሆነ መሬት እንዳላት ስትናገር ሌሎቹ ግን እንደሌላቸው ገልፀዋል።

ስለ ፍልሠት ሲወራ የዕድሜ ሁኔታ ልክ እንደ ፆታ ሁሉ የማይቀር ተጠቃሽ ነገር ነው። በዓለም ላይ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ራሳቸውን ችለው (ከቤተሠብ ተነጥለው ለብቻቸው) ፍልሠት የሚፈጽሙ ሕጻናት ዕድሜ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚያስገርም ሁኔታ ዝቅ እያለ እንደመጣ ለመረዳት ተችሏል። በጥናቶቹ መሠረት ወንድም ሆነ ሴት የመረጃ ምንጮች በህፃንነት ዕድሜያቸው ወደ አዲስ አበባ እንደመጡ የገለፁበት ሁኔታ አለ። አንዳንዶቹም በ7 ዓመት ዕድሜያቸው ሳይቀር በፍልሠት ወደ ከተማ እንደመጡ ይናገራሉ። ይህን ጉዳይ መረጃ ሰጪ 16 ስትገልጽ "እኔ ወደ አዲስ አበባ የመጣሁት በ14 ዓመት ዕድሜዬ ሲሆን እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ከ40 ዓመት በላይ ኖሬያለሁ፣ የተለያዩ ሥራዎችንም ለመስራት ሞክሬያለሁ፣ ሆኖም ግን ምንም ዓይነት ዕሴት ሳይኖረኝ ይህ ሁሉ ጊዜ አለፈ" ብላለች።

በብዙ ምክንያቶች ሳቢያ ሕጻናት ተቀጣሪዎች ከቀጣሪያቸው ጋር በሚኖሩበት ሁኔታ (በቤት ውስጥ ሠራተኛነት) ወይም በቅርብ የዘመድ ድጋፍ በማያገኙበት ወቅት ለተለያዩ አደጋዎች የሚጋለጡበት አጋጣሚ ይፈጠራል (Mabala and Cooksey, 2008)። ከዚህ አንጻር የተወሰኑ የመረጃ ምንጮች ያጋጠማቸውን ተሞክሮ ሲገልጹ ከአሠሪዎቻቸው ጋር አብረው እንዲኖሩ የተደረጉበት ሁኔታ እንደነበረና በዚህም ምክንያት የተለያዩ ችግሮች እንደደረሱባቸው አስረድተዋል። ለምሳሌ ያህል መረጃ

ሠጪ 2 የደረሰባትን ችግር እንደሚከተለው ተናግራለች፡፡ ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ የ15 ዓመት ልጅ ነበረች፡፡ አዲስ አበባ እንደገባች ለጥቂት ወራት ያህል አክስቷ ቤት ከቆየች በኋላ በቤት ሠራተኛነት ሌላ ሰው ቤት ተቀጠረች፡፡ እንደ ግለሠቧ አገላለጽ ከሌላ ሰው በቤት ሠራተኛነት ስትቀጠር የ19 ዓመቷ ነበር፡፡ እዚያም በቤቱ አባወራ በመደፈሯ ለእርግዝና እንደተጋለጠች ትናገራለች፡፡ ከተቀጠረችበት ቤት ለጥቂት ወራት ከሠራች በኋላ የተጓዘችው ወደ አክስቷ ቤት ነበር፡፡ አክስቷ ቤት ሆናም የተለያዩ የቀን ሥራዎችን በመሥራት ልጇን ማሳደግ እንደጀመረች በመግለጽ የችግሩን አስከፊነት አብራርታለች፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የችግሩ ደረጃ አብዛኞቹን ሴቶች እንዴት ዝቅተኛ ገቢ ወደሚያስገኙ ሥራዎች እንደሚገፋቸው ሲሆን፤ የቤት ውስጥ በደሎችና አስገድዶ መድፈር የሚያመጡትን ችግሮች መሸከምም ዕጣ ፈንታቸው እንደሆነ ነው፡፡

## 5.3 የቤተሠብ ዓይነቶች እና አወቃቀር

በአብዛኛው ዓለም የተለመደው ቤተሠብ አባወራ፣ ሚስትና ልጆችን የሚያቅፍ ነው፡፡ በኢትዮጵያም ቢሆን ተመሳሳይነት አለው፡፡ ቤተሠብ የሚባሉት በአንድ ቤት የሚኖሩና በጋራ የሚመገቡ ሰዎች ስብስብ ሲሆን፤ በከተሞች ያለው ነባራዊ ሁኔታ ግን ይህን የተለመደውን የቤተሠብ አባላት ስብስብ የመነጣጠልና የመበተን ሚና አለው፡፡ ለዚህ ለቤተሠብ አባላት መነጣጠል እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ነገሮች አንዱ በከተሞች ውስጥ ያለው የመጠለያ ችግር ነው፡፡ አንዳንድ የመረጃ ምንጮች እንደተናገሩት ብዙ የቤተሠብ አባላትን ይዘው በተጨናነቀ ሁኔታ በጠባብ መጠለያ መኖር በከተሞች አካባቢ የተለመደ የአኗኗር ዘይቤ እየሆነ መጥቷል፡፡ ነገር ግን ለሥራ የደረሱና መሥራት የሚችሉ የቤተሠብ አባላት ቢያንስ እንኳ ሥራ ሠርተው ቤተሠቡን መደጎም እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

መረጃ ሰጪ 5 የአኗኗር ሁኔታዎን በሚከተለው መልክ ገልፃዋለች፡፡ በአጠቃላይ 6 ሆነው በአንድ ጠባብ መጠለያ የሚኖሩ ሲሆን የቤተሠቡ አባላትም አንድ ወንድ ልጇ፣ አንድ የተፋታች ሴት ልጇ፣ ሁለት የወንድሟ ወንድ ልጆች እና አንድ የልጅ ልጇ ናቸው፡፡ ግለሠቧ በምን መልኩ እየኖረች እንደሆነ ስትገልጽ፤ “ይህን ያህል የቤተሠብ አባላት ይዞ በአንድ ጠባብ ክፍል ቤት መኖር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ግን ምንም አማራጭ የለንም፡፡ የትም መሄድና መኖር አንችልም፡፡ የእኔ አንዱ ልጅና የወንድሜ ልጅ ትምህርታቸውን ጨርሰዋል፡፡ ነገር ግን የትም የሚሄዱበት የላቸውም፡፡ ሴት ልጄ ደግሞ ከባሏ ተፋታለች፡፡ እናም ራሷንና ሴት ልጇን የምታስተዳድርበት ምንም ዓይነት ገቢ የላትም፡፡ በመሆኑም ከእኛ ጋር አብራ ለመኖር ተገዳለች” በማለት አብራርታለች፡፡

በዚህ ጥናት ለማወቅ እንደተቻለውና ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደተናገሩት በከተማ ውስጥ ያለውን የመኖሪያ ቤትና የኑሮ ችግር ለመቋቋም ብዙ ወንዶች በጋራ በመሆን በአንድ ጠባብ ቤት ውስጥ መኖር እየተለመደ መጥቷል፡፡ አንድ የወንድ የቡድን ውይይት አባል ይህን ሁኔታ ሲገልፅ "እኔ የምኖረው በተከራየናት አንዲት ጠባብ ቤት ውስጥ ሲሆን ከእኔ ጋር ሦስት ሌሎች ጓደኞቼ አብረው ይኖራሉ፡፡ ሁላችንም የምንሠራው የተለያየ ሥራ ነው፡፡ በዚች ቤት ውስጥ ሁላችንም የራሳችን የሆነ የተለያየ የመኝታ ስፍራ (ቦታ) አለን፡፡ ይኸ ነው የሚባል ጠቃሚ ዕቃ ወይም ንብረት ግን የለንም፡፡ ሌላው ቀርቶ እዚች ቤት ውስጥ የምንበላው ነገር እንኳ የለም፡፡ ቤቷን በጋራ የተከራየናት ለመኝታ ብቻ ነው፡፡ በጋራ ሆኖ በአንድ ቤት መኖር ገንዘብ ይቆጥብልናል" ብሏል፡፡

በጥናቱ መሠረት ወንዶች አንድ ክፍል ቤት ካለው ግለሠብ የክፍሏን አንድ አራተኛ(1/4) ወይም የተወሰነ መጠን ያለው ቦታ በመከራየት አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ ነጥብ ዙሪያ አንድ ወንድ የጥናቱ ተሳታፊ ሲገልፅ "የማገኘው ገቢ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ራሴን ችዬ አንድ ክፍል ቤት መከራየት አልችልም፡፡ በዚህ ላይ ምንም ዓይነት የቤት ቁሳቁስ የለኝም፤ የምመገበውም ውጪ ነው፡፡ አለኝ የምለው ንብረት ጥቂት ለቅያሬ የሚሆኑ የቀን ልብሶችና ለመኝታ የምጠቀምባቸው አንሶላና ብርድ ልብስ ብቻ ናቸው፡፡ የምተኛው ከቤቱ ላይኛው ክፍል ማለትም በቤቱ ጣሪያና በኮርኒሱ መካከል በተሰራ ፎቅ መሰል ክፍል ውስጥ ነው፡፡ ይኸ ነው እንግዲህ የእኔ የአኗኗር ሁኔታ" በማለት ችግሩን አስረድቷል፡፡

የዚህ ጥናት ግኝቶች በግልፅ እንደሚያሳዩት ሰዎች የሚያገኙት የገቢ መጠን ዝቅተኛ በሆነ ቁጥር ራሳቸውን ችለው ለመኖር የሚቸገሩበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ጊዜ እነዚህ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ዝምድና ወይም ትውውቅ ባይኖራቸው እንኳ አብረው በደባልነት ለመኖር ሁኔታው ያስገድዳቸዋል፡፡ ከዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽሁፎች እንደሚገልጹት ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም በጋራ ሆነው በአንድ ቤት በደባልነት የሚኖሩበት ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ጥናት በጋራ የሚኖሩ ሴቶች አላጋጠሙም፡፡

የተፋቱ ወይም ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች ከድሮ ባሎቻቸው ምንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ አያገኙም፡፡ እንደዚሁም የባሎቻቸው ዘመዶች ምንም የሚሠጧቸው እርዳታ የለም፡፡ ይህ ሁኔታ ነው እንግዲህ በከተሞች አካባቢ ያለው ነባራዊ ሁኔታ የተለመደውን ጋብቻና የጋብቻ ዝምድና እያዛባው ነው የሚያሠኘው፡፡ እዚህ ላይ መረጃ ሰጪ 5 የተናገረችውን ለምሳሌ ያህል ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ ግለሠቧ ጋብቻ መመስረት ራሷንና የምትወልዳቸውን ልጆቿን እንደሚጠቅማት ታስብ ነበር፡፡ ጋብቻ ከፈፀመች

በኂላ የገጠማት ግን ተቃራኒው ነው፡፡ በጋብቻ ሕይወቷ ውስጥ የገጠማትን ሁኔታ በሚከተለው መልክ ገልፃዋለች፤ "ሕጋዊ የጋብቻ ውል ባይኖረንም ከተጋባንና የመጀመሪያ ልጃችንን ከወለድን በኃላ ባለቤቴ ትቶኝ ሄደ፡፡ ብቻዬን መኖር ሲከብደኝ ሌላ የወንድ ጓደኛ ያዝኩና ከዚህ ጓደኛዬም ሌላ ልጅ ወለድኩ፡፡ ሁለተኛውን ልጄን ከወለድኩ በኂላ ከልጄ አባት ጋር ለተወሰኑ ወራት ያህል አብረን ኖርን፡፡ ሆኖም ግን ከጥቂት ጊዜ በኂላ የከተማን የኑሮ ውጣ ውረድ መቋቋም እንዳልቻለ በመግለጽ እኔንም ወደ ትውልድ አገሬ እንድሄድ ይገፋፋኝ ጀመረ፡፡ እኔ ወደ ትውልድ አገሬ መሄድ እንደማልፈልግ ስነግረው እርሱ ትቶኝ በመጥፋቱ በብቸኝነት መኖሩን ተያያዝኩት" ብላለች፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ መረጃ ሰጪ 6 ያለፈችበትን የሕይወት ገጠመኝ ተናግራለች፡፡ ይህች ግለሠብ ከአንድ ሰው ጋር ጋብቻ የመሠረተችው አዲስ አበባ በመጣች በጥቂት ጊዜ ውስጥ ነበር፤ ነገር ግን አንድ ልጅ ከወለዱ በኂላ ወዲያው ተፋቱ፡፡ እናም ለተወሰነ ጊዜ ያህል በእማወራነት ከቆየች በኂላ ከሌላ ወንድ ጋር ጋብቻ መሠረተችና ሁለተኛ ልጅዋን ወለደች፡፡ በአሁኑ ሠዓትም ልጆቿን ይዛ ከባለቤቷ ጋር እየኖረች እንደሆነ ትገልፃለች፡፡ ሆኖም ግን እንደዚች ግለሠብ አስተያየት ትዳር መመሠረቷና ከባሏ ጋር አብራ መኖሯ በሕይወቷ ውስጥ ምንም ዓይነት ለውጥ አላመጣላትም፡፡ ሌላው ቀርቶ ከመጀመሪያ ባለቤቷ የወለደቻት ሴት ልጇ እሷ ጋር ትውልና የምታድረው ግን ከዘመዶቿ ቤት ነው፡፡ ባል ያገባችው አስፈላጊ የሆኑ የምግብ ሸቀጦችንና የቤት ውስጥ ወጪዎችን እንዲሸፍንላት አስባ ቢሆንም በአሁኑ ሠዓት የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ሕይወትን ለማሸነፍ በመፍጨርጨር ላይ ያላቸው እርሷ ራሷ እንደሆነችና የባለቤቷ ዕርዳታና ድጋፍ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ በምሬት ትናገራለች፡፡ ነገር ግን እንደግለሠቧ አገላለጽ የባለቤቷ አብሮ መኖር ቢያንስ ልጆቿ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያዳብሩ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ምናልባት ከቤተሠብ አወቃቀር አንፃር ጉልህ ሆኖ የሚታየው ልዩነት በከተሞች አካባቢ ከገጠር በበለጠ ሁኔታ በእማወራዎች የሚመራ ቤተሠብ እየተፈጠረ መምጣቱ ነው፡፡ እነዚህ የከተማ እማወራዎች ረዘም ላለ ጊዜ ያለትዳር አጋር ቤተሠባቸውን የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ለልጆቻቸው የሚሆኑ ጥቃቅን ነገሮችን ከድሮ ባሎቻቸው ከማግኘታቸው በስተቀር ጉልህ የሆነ የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ የለም (Chant, 2007)፡፡ አንድ ሌላ ተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፍ እንደሚገልፀው ከዓለም አቀፍ ደረጃ ጋር ሲነፃፀር በኢትዮጵያ ውስጥ የእማዎራዎች ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል (Kodama, 2006)፡፡ ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ የሚገኙ እማወራዎች ቁጥር ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነጻጸር አምስተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይኸው ጥናት ያሳያል (Kodama, 2006)፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ

የእማወራዎች ቁጥር ከገጠር ይበልጥ በከተሞች በእጅጉ ተስፋፍተው ይገኛሉ፡፡ ከከተማ ከተማ ጉልህ ልዩነት በሌለበት ሁኔታ ከአጠቃላይ በከተሞች ከሚኖሩ ቤተሠቦች መካከል 33% የሚሆኑት በእማወራ የሚመሩ ሲሆን፤ በገጠር የሚኖሩ የእማወራዎች ቁጥር ግን ከ17% የማይበልጥ ነው (Kodama, 2006)፡፡ ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ እማወራዎች ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ድጋፍ ከድሮ የትዳር አጋሮቻቸው አያገኙም፡፡ ጥቂት እማወራዎች ግን አነስተኛና ቋሚ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ከልጆቻቸው አባቶች የሚያገኙበት ሁኔታ አለ፡፡ ሆኖም ግን ይህ ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ኑሮን ለማሸነፍና ቤተሠብን ለማስተዳደር ደፋ ቀና ብሎ የመሥራት ኃላፊነቱ በእማወራዎች ላይ የተጣለ ነው፡፡ ይህንን ርዕሰ-ጉዳይ በተመለከተ መረጃ ሰጪ 12 ስትገልፅ፤ “ሦስት ልጆች አሉኝ፤ የልጆቼን መሠረታዊ ፍላጎቶች የማሟላት ኃላፊነቱ ደግሞ በእኔ ላይ ያረፈ ነው፡፡ አባታቸው በደላላነት ሥራ የሚተዳደርና ቋሚ የሆነ ገቢ የሌለው በመሆኑ ከእርሱ የሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ አስተማማኝ አይደለም፡፡ የልጆቼን ፍላጎት ለማሟላትና የቤት ኪራይ ለመክፈል ሁሌም የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ” በማለት ተናግራለች፡፡

ለእማወራነት የዳረጋቸውን ምክንያት በምንመለከትበት ጊዜ አብዛኛዎቹ መረጃ ሰጪዎች ባሎቻቸው ስለሞቱባቸው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ መረጃ ሰጪ 16 እማወራነትን ስትገልፀው፤ “ባለቤትሽ ሲሞትብሽና ደሀ ስትሆኚ ማንም ዘወር ብሎ አያይሽም፡፡ እንኳን ጓደኞቹ የባለቤትሽ ቤተሠቦች እንኳ መጥተው አይጠይቁሽም” በማለት ትናገራለች፡፡ መረጃ ሠጪ 8 በበኩሏ “ባለቤቴን በኤች.አይ.ቪ ምክንያት ካጣሁ በኋላ የሕይወት አቅጣጫዬ በሙሉ ተቀየረ፡፡ ደስታዬ ሁሉ ከባለቤቴ ጋር አብሮ ተቀበረ፡፡ ምንም ዓይነት ገቢ በሌለበት ሁኔታ ቤተሠብ ማስተዳደር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ እናም የቤተሠብ መሪ ነኝ ለማለት አልደፍርም፡፡ በዚህ ላይ እኔም የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ተሸካሚ ነኝ” በማለት ታሪኳን አካፍላለች፡፡

የትዳር አጋርን በሞት ማጣት ተፈጥሯዊ ክስተት ቢሆንም ተከትሎ በሚከሠተው የኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ቤተሠብን በኃላፊነት የመምራት ልምድ ያልነበራቸው ሴቶች ይህንን ኃላፊነት እንዲሸከሙ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡ በኑሮ ውድነቱ ሳቢያ ትዳር የፈቱ ደሀ ሴቶችን ቁጥር በእጅጉ እየጨመረ እንደሆነም በግልጽ ይታያል፡፡ መረጃ ሰጪ 3 እና 4 እንደሚሉት ወደ ትዳር የገቡት ለሕይወታቸው የሚሆን የኢኮኖሚ ድጋፍ ከባሎቻቸው ለማግኘት ቢሆንም ኑሮን መቋቋም ሲከብዳቸው ባሎቻቸው ትተዋቸው እንደሄዱና ኑሮን በብቸኝነት መምራት እንደጀመሩ ገልጸዋል፡፡

ተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፎች እንደሚያስረዱት በእማወራነት መኖር ሴቶች በኑሯቸው ላይ የወሳኝነት ሚና እንዲጫወቱ ያስችላቸዋል (Doss, 2011)፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ይህን ኃሳብ በመደገፍ አስተያየት ሲሠጡ ምንም እንኳ ከኢኮኖሚ አንፃር ሕይወትን

በብቸኝነት መምራት አስቸጋሪ ቢሆንም፤ በራሳቸው ኑሮ ላይ የመወሠንና ማድረግ የሚፈልጉት ሁሉ በነፃነት የማድረግ ዕድሉ በትዳር ውስጥ ከነበሩበት ወቅት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ ከፍተኛ ነው:: መረጃ ሰጪ 4 ከዚህ ኃሳብ ጋር የሚመሳሰል ተሞክሮዋን እንዲህ ትገልፃለች፤ "ባሌ በሕይወት በነበረ ጊዜ ስለቤተሠቡ ግድ አልነበረውም:: ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት የመውሰዱና የቤተሠቡን ቀለብ የማዘጋጀቱ ኃላፊነት በእኔ ላይ የወደቀ ነበር:: ድጋፍ እንዲያደርግ ስጠይቀው ስለማይቀበለኝ ብዙ ጊዜ እንጋጭ ነበር:: እሱ ከሞተ በኂላ ግን በቤተሠብ ውስጥ ምንም ዓይነት ግጭት የለም፤ ልጆቼም አድገውልኛል:: እኔ ደግሞ ያለኝን ገንዘብ ለፈለግኩት ነገር የማዋል ሙሉ ነፃነት አለኝ" በማለት ኃሳቧን ሠጥታለች::

በተመሳሳይ ሁኔታ መረጃ ሰጪ 6 የራሷን የሕይወት ተሞክሮ አጋርታናለች:: ይህች ግለሠብ ከአንድ በቀን ሥራ ከሚተዳደር ሰው ጋር ትዳር ስትመሰርት ቤተሠቡን የሚረዳና የሚንከባከብ መስሏት ነበር:: ሆኖም ግን ባለቤቷ ቋሚ የሆነ ሥራና ገቢ አልነበረውም:: በመሆኑም በወር ከ200 ብር በላይ አይሠጣትም ነበር:: ይህ ሁኔታ በምሽት ጎዳና ላይ ንግድ እንድትጀምር እንዳስገደዳት ትናገራለች:: ሁኔታውን በራሷ አንደበት ስትገልፀው "እንደሌሎች ባለትዳሮች ሁሉ እኔም ልጆች ወልጄ የማሳደግና ቤቴን የመምራት ፍላጎት ነበረኝ:: ይሁንና ባጋጠመኝ አስከፊ የኑሮ ሁኔታ ተገፋፍቼ ማታ ማታ እንደ ቅቅል ድንች፤ ቆሎና የመሳሰሉትን ለመሸጥ ጎዳና መውጣትና የበለጠ አሰቃቂ ኑሮ መጀመር ግድ ሆነብኝ" በማለት ትናገራለች:: ከዚህ ታሪክ የምንገነዘበው ምንም እንኳ ደሀ ባለትዳር ሴቶች በአባወራው ጥላ ስር የሚኖሩ ቢሆንም እነዚህ ሴቶች ለቤተሠቡ የኢኮኖሚ ምንጮች እንደሆኑና ቤተሠቡን የመመገብ ኃላፊነት እንደተጫነባቸው ነው::

ከላይ የተቀመጡ እውነታዎች የሚያሳዩት በገጠርም ሆነ በከተማ በአባወራና በእማወራ የሚመሩ ቤተሠቦች እንዳሉ ቢሆንም በኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳቢያ ከአባወራ ይልቅ በእማወራ የሚመሩ ቤተሠቦች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ነው:: ከዚህ በተጨማሪም አብዛኞቹ ላጤ ወንዶች ብቻቸውን ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ከእማወራዎች መኖሪያ ቤት የተወሰነውን ቦታ ተከራይተው እየኖሩ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል:: ይህ ሁኔታ የሚያመለክተው የቤተሠብ አባላት አወቃቀርና የቤተሠብ አደረጃጀች ከከተማ ድህነት ጋር ተያይዞ እየተለወጠ እንደሆነ ነው::

## 6 ሥርዓተ-ፆታ፣ የከተማ ሥራ እና የሴቶች የመሠረተ ልማት ተደራሽነት

የከተማ ሥራ ሲባል የተለያዩ መደበኛና ኢ-መደበኛ የሆኑ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ያካትታል:: በዚህ ዙሪያ ያሉ ተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፎች እንደሚያስረዱት በከተሞች የሚገኘው ደሀ ሠራተኛ በአብዛኛው የተሰማራው ኢ-መደበኛ በሆነ የገቢ ማስገኛ

ሥራዎች ነው። ኢ-መደበኛ ሥራዎችም ክፍያ አልባ የሆነ የቤተሠብ ሥራ፣ የጎዳና ላይ የሸቀጥ ንግድ፣ የቤት ውስጥ ሥራ፣ ያለውል በመደበኛም ሆነ ኢ-መደበኛ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ መሥራት፣ እና ማኅበራዊ እንክብካቤ ሥራዎችን ያካትታል (ILO, 2002)። በኢትዮጵያም ኢ-መደበኛ የሆነው የሥራ መስክ ከአጠቃላይ የሥራ መስክ 35% ይሸፍናል (CSA, 2011)። በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ ግለሠቦች የሕይወት ታሪክ እንደሚገልፀው አብዛኞቹ ኢ-መደበኛ በሆኑ ሥራዎች የተሠማሩ ናቸው። ከተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች መካከል የምግብ ሸቀጦችን በመንገድ ላይ መሸጥ፣ ልብስ ማጠብ፣ ሊስትሮነት፣ ድለላ እና ቦታ/ቤት ማከራየት ተጠቃሽ ናቸው።

## 6.1 የሽያጭ ሥራ ከገቢ ማስገኘት አንፃር

በዚህ ጥናት ተሳታፊ የነበሩ አብዛኞቹ ሴት የመረጃ ምንጮች የሚተዳደሩት እንደ እንጀራ፣ ቆሎ፣ ድንች፣ ሻይ፣ አረቄ፣ ቡና፣ ባሕላዊ መጠጦች፣ ውኃና አትክልት የመሳሰሉ የምግብ ሸቀጦችን በመሸጥ ነው። እንደዚሁም በቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩ አንዳንድ ወንድ የመረጃ ምንጮችም እንደ ሳንቡሳና ሲጋራ የመሳሰሉ የፍጆታ ሸቀጦችን በመሸጥ የሚተዳደሩ ሲሆን፤ ከፊሎቹ ደግሞ በአናጺነትና በዘበኝነት የሚሠሩ ናቸው።

እነዚህ የመረጃ ምንጮች ከተናገሩት መረዳት የምንችለው ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች እንደገቢ ምንጭ በመቁጠር መሥራት የጀመሩ መሆናቸውን ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት አሁን እየሠሩበት ያለው ቦታ ለፈጣን ምግቦችና ለትኩስ መጠጦች ከፍተኛ ፍላጎት ያለበት ነው። አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ የቀን ሠራተኛ በመሆኑ ለምግብና መጠጥ ከፍተኛ ፍላጎት አለ። ሴት የመረጃ ምንጮች እንደሚሉት በዶሮ ማነቂያ ሰፈር ጠም መዋልና ማደር የለም። በንፅፅር ለረጅም ሠዓት የቃለ-መጠይቅ መረጃ የሠጠች አንድ የጥናቱ ተሳታፊ (መረጃ ሰጪ1) እንደምትለው አትክልት በመሸጥ ከ10 ዓመታት በላይ በአካባቢው ቆይታለች። የመኖሪያ ቤቷ ለመኪና መንገድ ቅርብ በመሆኑ አትክልት ለመሸጥ ሩቅ ቦታ መሄድ አይጠበቅባትም። ምንም እንኳ ቋሚ የሆነ የገንዘብ መጠን በየቀኑ ማግኘት ባትችልም እንደምንም አብቃቅታ የተወሰነ ገንዘብ አባል በሆነችበት ዕድር ውስጥ ትቆጥባለች። ግለሰቧ ሁኔታውን ስትገለጽል "ሥራ ከሠራሽ ቢያንስ እንኳ የዕለት ምግብሽን መሸፈን ትችያለሽ" ብላለች።

መረጃ ሠጪ 17 በበኩሏ ኢ-መደበኛ በሆኑ የተለያዩ የሥራ መስኮች ተሠማርታ ለበርካታ ዓመታት እንደቆየች ትናገራለች። ቀደም ሲል በሹሩባ ሥራና በልብስ አጠባ፤ አሁን ደግሞ በመኖሪያ ቤቷ ደጃፍ ላይ ቡና በመሸጥ ሕይወቷን በመምራት ላይ

ትገኛለች። አሁን እየሠራች ያለውን ሥራ አስመልክታ ስትናገር ከቡና ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ጥሩ ቢሆንም ሕጋዊ የሥራ ቦታ ለማግኘት ግን እንደተቸገረች ትገልፃለች። ከምትሠራበት ቦታ ጋር በተያያዘ ከጎረቤቶቿ ጋር ብዙ ጊዜ ተጋጭታለች። እነዚህ ጎረቤቶቿ በዚህ ጉዳይ ክስ መስርተውባታል። እዚያ ቦታ ላይ እንድትሰራ ሕጋዊ ፈቃድ ባይኖራትም ሌላ አማራጭ በማጣቷ እስካሁን አላቋረጠችም። ፍርድ ቤት እዚያ ቦታ እንዳትሰራ የሚወስንባት ከሆነ ግን የት እንደምትሄድና ምን እንደምትሠራ ግራ ገብቷታል።

ኢ-መደበኛ በሆኑ የሥራ መስኮች መሠማራትና በመንገድ ላይ ሸቀጦችን በመሸጥ መኖር በብዙ ከተሞች እየተዘወተረ የመጣ ነገር ሆኗል። የተወሰኑ ሴት የመረጃ ምንጮች እንደሚሉት ከጎረቤት ጋር ከመጣላት እና በቀበሌ ከመከሰስ መንገድ ላይ መነገድ ተመራጭ ሥራ ነው። በጎዳና፣ በቡና ቤቶችና በምግብ ቤቶች እየተዟዟሩ የበሠለ ድንች፣ ቆሎና የመሳሰሉትን የምግብ ሸቀጦች ይሸጣሉ። እነዚህ ሴቶች እንደሚሉት በምሽት እየተዟዟሩ ሸቀጦችን መሸጥ በጣም ከባድ ሥራ ነው። ሆኖም ግን ቤተሠባቸውን መግበው ለማደር ይህን እንደመጨረሻ አማራጭ መውሰዳቸውን ይናገራሉ። መረጃ ሠጪ 7 እንደምትለው ደግሞ ለቤተሠብ ማስተዳደሪያ ገንዘብ ማፍራት ስላለባት በልጆቿን ሕይወት ዕጣ ፈንታ ላይ ሳይቀር ከባድ የሆነ ውሳኔ እንደምትወስን ትናገራለች። ይህ ሁኔታ ስታብራራ "የባለቤቴ ገቢ የቤተሠቡን ፍጆታና ወጪ የሚሸፍን አይደለም። ስለዚህ ገንዘብ ለማግኘት የሆነ ሥራ መሥራት አለብኝ። ዕድሜያቸው 3 እና 4 የሆነ ሁለት ልጆች አሉኝ። ቀኑን ሙሉ ልጆቼን ቤት ውስጥ ስንከባከብ እውላለሁ። ምሽት አካባቢ ግን እነርሱ ወደ መኝታቸው ሲሄዱ እኔም የበሠለ ድንች ለመሸጥ ከውጭ ቆልፌባቸው እወጣለሁ። ማንም ሰው ቢያንኳኳ በር እንዳይከፈቱም አስጠንቅቃቸዋለሁ። ምናልባት የእሳት አደጋ ከተከሰተ ግን በመስኮት ዘልለው እንዲወጡ እነግራቸዋለሁ። እንግዲህ ይህ ለእናትም ሆነ ለልጆች ምን ያህል ከባድ ውሳኔ እንደሆነ መገመት አያዳግትም" ብላለች።

መረጃ ሰጪ 5 እና 6 ተመሳሳይ አስተያየት የሠጡ ሲሆን የሆነ ሥራ መሥራት ካልተቻለ የኑሮ ጫናውን መቋቋም እንደሚከብድ ይናገራሉ። አስተያየት ሠጪዎቹ ሕጻናት ልጆች ያላቸው ሲሆን እነርሱን ከቤት ትቶ በመሄድ ሥራ ለመሥራት የመኖሪያ አካባቢያቸው ምቹ ስላልሆነ ሠፈር አከባቢ ልብስ በማጠብ ገቢ ማግኘት ብቸኛ አማራጫቸው እንደሆነ ይናገራሉ። ይህን ሁኔታ በተለይ መረጃ ሠጪ 5 ስታብራራ "ከአምስቱ ልጆቼ መካከል ሁለቱ በሽተኞች በመሆናቸው እነሱን መንከባከብ ይጠበቅብኛል። የሚያግዘኝ ዘመድ ደግሞ የለኝም። በዚህ ላይ ለሁሉም የቤተሠቡ አባል ምግብ ማዘጋጀት ይኖርብኛል። ምንም እንኳ ባለቤቴ ሳንቡሳ የሚሸጥ ቢሆንም የሚያገኘው ገንዘብ ሁሉንም የቤተሠብ አባል ለማስተዳደር አይችልም። ስለዚህ ልብስ

በማጠብ ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘት አለብኝ። በአንድ ልብስ ከ3-5 ብር እቀበላለሁ። በቀን የማጥበው የልብስ ብዛት ግን ይለያያል። ይህ ሥራ ደግሞ የማስጫ ቦታ በማግኘት ላይ የተወሰነ ነው። የማስጫ ቦታው በሌሎች ሰዎች የተያዘ ከሆነ የተሰጣው ልብስ እስከሚደርቅ መጠበቅ ይኖርብኛል" ብላለች።

ከዚህ መገንዘብ የምንችለው ምንም እንኳ ባል ቢኖራቸውም ሚስቶች ተጨማሪ ገቢ ለማግኘች በገቢ ማስገኛ ሥራዎች እንደሚሳተፉ ነው። ይህ ደግሞ አልፎ አልፎ በልጆች ደህንነት ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል። በተለያዩ ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች እንደተገለጸው ይሄ ሁኔታ የጊዜ ድህነት የሚባውን ይፈጥራል። የጊዜ ድህነት ሲባል የሚፈለገውን ነገር በተፈለገው ጊዜ ማድረግ አለመቻል እንደማለት ነው (Gammage, 2010) ።

ከወጣቶች ይልቅ ከቤት ውጭ ራሳቸውን እንደ አምራች ኃይል የማይቆጥሩት በዕድሜ የገፉ ሴቶች በቤታቸው ውስጥ እንጀራና ውኃ በመሸጥ ይተዳደራሉ። እነዚህ አዛውንት ሴቶች እንደሚሉት እንጀራ ከሌላ ቦታ ይገዙና 50 ሳንቲም በመጨመር በሠፈር ላሉ ሰዎች ይሸጣሉ። ምንም እንኳ ትርፉ አነስተኛ ቢሆንም የተወሰነ የቤት ወጪ ይሸፍንላቸዋል። ሌሎቹ ደግሞ በውኃ ላስቲክ ውስጥ የተሞላ ወይም የቧንቧ ውሃ ይሸጣሉ። በዚህ አካባቢ ባለ 20 ሊትር የቧንቧ ውኃ ከ1.50 እስከ 2.00 ብር ይሸጣል። ይህንን ጉዳይ መረጃ ሰጪ 11 ስትገልጽ፤ "ዋናው የገቢ ምንጭ ከውኃ ሽያጭ የሚገኝ ነው። ከጎረቤቶቼ ሁሉ የቧንቧ ውኃ ያለኝ እኔ ብቻ ስሆን ከድሮ ቀጣሪዬ የተሠጠኝ አንድ አሮጌ ማቀዝቀዣም አለኝ። ያገለገሉ የውኃ ፕላስቲኮችን እየሠበሰብኩ በውኃ እሞላና ፍሪጅ ውስጥ አስቀምጣቸዋለሁ። የቀዘቀዘ ውኃ በቀን ሠራተኞችና በጫት ቃሚዎች በጣም ተፈላጊ ነው። ጎረቤቶቼ ደግሞ የቧንቧ ውኃ ይገዙኛል። የማገኘው ገቢ ቢያንስ እንኳ የቡና ወጪዬን ይሸፍንልኛል" ብላለች።

ከነበሩን ውይይቶች መረዳት እንደተቻለው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በተለያዩ ኢ-መደበኛ የሥራ መስኮች ላይ ተሳታፊ ናቸው። ምንም እንኳ ምን ያህል ገቢ እንደሚያገኙ በትክክል ማወቅ ቢያስቸግርም፤ በቀን የሚያገኙት ገቢ የቀን ወጪያቸውን ይሸፍንላቸዋል። ባለትዳር ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት ቁርስና ምሳቸውን ከቤታቸው የሚበሉበት ጊዜ ውስን ነው። በአብዛኛው ከውጭ ገዝተው ነው የሚመገቡት። አንድ የቡድን ውይይት አባል ሁኔታውን ሲያብራራ "ከቤቴ ምግብ ስለመኖሩ እርግጠኛ አይደለሁም። ገንዘብ በሚኖረኝ ጊዜ ለባለቤቴ እሠጣታለሁ። ሆኖም ግን ባለቤቴ የምሰጣት ገንዘብ በቂ ምግብ መግዛት እንዳልቻለ አቤቱታዋን ሁል ጊዜ እሰማለሁ። ስለዚህ በማገኘው ገንዘብ ከውጭ ገዝቼ መመገብ አዘወትራለሁ" ብሏል።

የተወሰኑ ላጤ ወንድ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ደግሞ በሊስትሮነትና በድለላ እንደሚተዳደሩ ይናገራሉ። የሚያገኙት የቀን ገቢም የቀን ወጪያቸውን ይሸፍንላቸዋል። ከዚህም ተርፎ የተወሠነ ገንዘብ የሚቆጥቡም አሉ። ሊስትሮ የሚሠሩ ሰዎች ቋሚ የሆነ የመስሪያ ቦታ ያላቸው ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ግን እንደ ሁኔታውና እንደ ወቅቱ የሥራ ቦታቸውን የሚቀያይሩበት ሁኔታ አለ። አንድ ሳንቡሳ ሻጭ ሲናገር ደግሞ በየቦታውና በየመንገዱ እስከሚደክመው ድረስ በመዞር መሸጥ የሁልጊዜ ሥራው መሆኑንና ጊዜና ቦታ ለእርሱ ችግሮች እንዳልሆኑ ይገልፃል።

ከዚህ በላይ የተገለፁት እውነታዎች እንደሚናገሩት በከተማ የሚኖሩ ደሀ ሴቶችና ወንዶች ራሳቸውንና ቤተሠቦቻቸውን ለማስተዳደር ሲሉ ዝቅተኛ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው እንደሚገኙ መረዳት ይቻላል። ይሁንና መደበኛ ሥራ የሌላቸው ሴቶች በቤት ውስጥ ልጆቻቸውን በመንከባከብ መጠመዳቸው እንደወንዶች ሁሉ ውጪ ወጥተው ሥራ ለመሥራትና ገንዘብ ለማግኘት መሰናክል እንደሆነባቸው መገንዘብ አይከብድም። ሴቶች ለመሥራት የሚመርጡት የሥራ ዓይነት በራሱ በዕድገታቸው ላይ ተፅዕኖ አለው። ለምሳሌ ያህል ባህላዊ መጠጦች፣ ቡናና እንጀራ ሕዝብ በተጨናነቀበት ቦታ መሸጥ ያዘወትራሉ። ሴቶች በሚሠሯቸው የሠፈር ሥራዎች ባህሪና በቤት ውስጥ ልጆችን የመንከባከብ ኃላፊነት ሳቢያ ራቅ ያሉ ስፍራዎች ተንቀሳቅሰው የተሻሉ ሥራዎችን የመሥራት ችግር አለባቸው። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ በሚኖሩበት አካባቢ ሊሰሩ የሚችሉ ሥራዎችን ጠባቂዎች ሆነዋል።

## 6.2 መጠለያ

ከተሞች ለድሆቻቸው በርካታ ዕድሎችን ይፈጥራሉ። በከተሞች የሚታየው ቅይጥና ፈጣን የአኗኗር ዘዴ የድሆችንም ፍላጎት የሚያካትት ነው። ሆኖም ግን ብዙ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የከተማ ድሆች ሕዝብ በጣም በበዛበት፣ አደገኛና ለኑሮ ተመራጭ ባልሆነ አካባቢ ይኖራሉ። በበርካታ ታዳጊ አገሮች እንደሚገኙ ከተሞች ሁሉ አዲስ አበባም በበርካታ ጎስቋላ ሠፈሮች የተጨናነቀች ነች። ይህ ሁኔታ በጎልህ የሚታየው ደግሞ በዕድሜ ጠገብ ከተሞች ጠርዞች አካባቢ ነው። እንደ UN-HABITAT (2011:5) ጥናት 80% የሚሆነው የአዲስ አበባ ክፍል በደሳሳ ሠፈሮች የተሸፈነ ነው። ከዚህ ውስጥ 70% የሚሆነው በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኙ የኪራይ ቤቶች የሚገኙበት ነው። ለመጠለያ የሚደረግ ትግል ብዙውን ጊዜ ለመሬት ከሚደረግ ትግል ተነጥሎ አይታይም (Satterth, 2009)። ዝቅተኛ ኑሮ ላላቸው የከተማ ነዋሪዎች የቤት ጉዳይ ከድህነት የመውጫ መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል። የቤት ባለቤት የመሆን ጉዳይ ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ሲሆን መሬት መግዛትን፣ የይዞታ ማረጋገጫ ማግኘትን፣ ቤት መሥራትን፣ ከቤተሠቡ የኑሮ ዘዬ መለወጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ፍላጎት

ለማስተናገድ የሚደረግ የማሻሻያ ሥራን መሥራትንና እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ያካትታል (Moser, 2009)

ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ የሚኖሩ ወንድና ሴት የመረጃ ምንጮች እንደሚሉት መጠለያ የማግኘት ጉዳይ እጅግ በጣም ፈታኝ ነው። የተገኙ መረጃዎች የሚያሳዩት አብዛኛዎቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የቀበሌ ቤቶችን ተከራይተው የሚኖሩና ለዚህም በወር ከ2.50 እስከ 20.00 ብር የሚከፍሉ ናቸው። በጥናቱ ሒደት ማስተዋል እንደተቻለው አብዛኛዎቹ ቤቶች በጣም ጠባብና ባለ አንድ ክፍል ሲሆኑ መስኮት አልባ ወይም ትንንሽ መስኮቶች ያሏቸው ናቸው። በተቻለ መጠን አንዳንድ ቤተሠቦች የመኝታ ቦታቸውን ከማብሰያ ስፍራው በመጋረጃ ለመከለል ሞክረዋል። የሚጠቀሙበት መጋረጃ በአብዛኛው በጣም ያረጀና የቆሸሸ በመሆኑ ቤቱን የበለጠ በማጨለም አስቀያሚ ገፅታ አላብሶታል። ምግብ ለማብሰል የሚጠቀሙበት ከሠል ለቤቱ መቆሸሽና መጨለም የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል።

ሌሎቹ የመረጃ ምንጮች ደግሞ በአካባቢው ካለ ክፍት ቦታ ላይ የራሳቸውን ጊዜያዊ መጠለያ ሠርተው ያለክፍያ የሚኖሩ ናቸው። አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት እነዚህ ጊዜያዊ መጠለያ ሠርተው የሚኖሩ ግለሠቦች ቢያንስ ለሁለት ዓመታት ያህል የጎዳና ተዳዳሪ የነበሩ ናቸው። መረጃ ሰጪ 3 እንደገለፀችው ወንድ ልጇን እንደፀነሰች ከአክስቷ ጋር በመጣላቷ የምትኖርበት አጣች። ከዚያም ከቀበሌው ጽ/ቤት አጠገብ የራሷን መጠለያ በላስቲክ ሠርታ መኖር ጀመረች። እዚህ ላስቲክ ቤት ውስጥ ለሁለት አመታት የኖረች ሲሆን የሳንባ ነቀርሳና የኤች.አይ.ቪ. ተጠቂ ሆናለች። በመሆኑም ሥራ ሠርታ ራሷንና ልጇን መመገብ አልቻለችም። በመጨረሻም ምንም መገልገያ ነገር የሌላትና አራት ካሬ ሜትር ስፋት ያላት ጊዜያዊ መጠለያ ቀበሌው ሰጣት። በተመሳሳይ መልኩ መረጃ ሰጪ 4 የራሷን ገጠመኝ አጫውታናለች። ከባለቤቷ ጋር ከተለያዩ በኋላ እርሷና ሁለት ልጆቿ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ የጎዳና ተዳዳሪ መሆን ነበር። በዚህ ላይ በርካታ የጤና ችግሮች አሉባት። መጠለያ እንዲሰጣት ለቀበሌ ብታመለክትም ጊዜያዊ መጠለያ ከቀበሌ ልታገኝ የቻለችው ከሁለት ዓመታት የጎዳና ተዳዳሪነት ሕይወት በኋላ ነበር። እነዚህ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚኖሩባቸው የቀበሌ ቤቶች ባለአንድ ክፍል ከመሆናቸውም ባሻገር እርስ በርስ ተያይዘው የተሠሩ ናቸው። አብዛኞቹ አንድ ዋና በርና የጋራ በረንዳ አላቸው። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አንድ የጥናቱ ተሳታፊ ሲናገር "በቀበሌ ቤቶች ውስጥ ስትኖር የግል ነፃነት የሚባል ነገር የለም። ልብሶቻችንን በምንፈልግበት ጊዜ ማጠብ አንችልም። ምክንያቱም በግቢው ውስጥ የታጠቡ ልብሶችን የምናሠጣበት በቂ ቦታ የለም። የምንኖርበትን ቤት መጠገን ወይም የሆነ ማሻሻያ ማድረግ አንችልም" ብሏል።

በጥናቱ ሒደት በአካል መመልከት እንደተቻለው አብዛኞቹ ቤቶች በጣም ያረጁ፣ በቂ ብርሀን የሌላቸው፣ በሰዎች የተጨናነቁ ባለ አንድ ክፍል ናቸው። በእርግጥ መረጃዎች እንደሚያመለክቱ ኢ.ኤ.አ በ2008 በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ቤቶች እንዳሉ ነው። በከተማው ከሚገኙ ቤቶች መካከል 30% ያህሉ ብቻ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን 70% ያህሉ ቤቶች ግን እድሳት የሚጠይቁ ናቸው። በአዲስ አበባ ብቻ ያለውን የቤት ፍላጎት ለማሟላት ወደ 300,000 ያህል ተጨማሪ ቤቶች ያስፈልጋሉ (UN-HABITAT, 2008:6)።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት እናቶችና ሕጻናት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት እጅግ በጣም በጠበበ ክፍልና አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ነው። አብዛኛውን ጊዜ እናቶች ምግብ የሚያበስሉት፣ ቡና የሚያፈሉት፣ እንጀራ የሚጋግሩት፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን የሚያጥቡት እንዲሁም የታጠበ ልብሳቸውን የሚያደርቁት በዚችው ጠባብና በሰው በተጨናነቀች አንዲት ክፍል ውስጥ ነው። ልጆች ከት/ቤት ተመልሰው የሚያጠኑትና የቤት ሥራ የሚሠሩትም በዚችው ክፍል ውስጥ ነው። ሁሉንም የቤት ውስጥ ሥራዎች በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ማከናወን እጅግ ከባድ ሥራ ነው። ሴት የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት አማራጭ ካልጠፋ በስተቀር ሁሉንም የቤት ውስጥ ሥራዎች በጠባብ ክፍል ውስጥ ማከናወን ለአሠራርም ሆነ ለጤንነት አስቸጋሪ ነው። ቢያንስ እንኳን ክፍሉ ሠፊ ቢሆን ኖሮ ተከፋፍሎ የማብሰያና የመኝታ ቦታዎች ለየብቻ ይሆኑ ነበር። አንዳንድ የቡድን ውይይቱ ሴት አባላት እንደተናገሩት ሲያበስሉ በነበረበት ቦታ ለመመገብ ሲሞክሩ የምግብ ፍላጎታቸው ስለሚቀንስ በበቂ ሁኔታ ለመብላት ይቸገራሉ።

ወንድ የቡድን ውይይቱ አባላት እንደሚሉት ደግሞ የተከራዩት ቤት ሁሉንም የቤት ውስጥ ሥራዎች ማከናወን የማያስችል ቢሆንም የተወሰኑትን ሥራዎች ከቤት ውጪ ስለሚያከናውኑ ችግሩ የሴቶችን ያህል ከባድ ሆኖ አይታያቸውም። አንድ የቡድን ውይይቱ አባል ሲናገር “እኔ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ቤት የምገባው ልጆች ከተኙ በኋላ ነው፤ የምወጣውም በማለዳ ነው። ቤቱን የምጠቀምበት ሌሊቱን ለማሳለፍ ብቻ በመሆኑ ችግሩ ለኔ አይታየኝም” ብሏል። አንድ ሌላ የቡድን ውይይቱ ተሳታፊ እንደሚለው ደግሞ “ሴቶች ቢያንስ እንኳን ቤቱን ለቡና መጠጫነት ይገለገሉበታል፤ እኔ ግን ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ ጫት ለመቃም ብፈልግም ሊያስተናግደን የሚችል በቂ ቦታ ስለሌለው ለተጨማሪ ወጪ ዳርጎናል” ብሏል። ከዚህ በተጨማሪ የቤቱን የክፍል ጥበት በተመለከተ መረጃ ሠጪ 13 በሚከተለው ሁኔታ አብራርታልናለች “አንዱ ልጄ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነው፤ ሆኖም ግን ከቤት እየመጣ ነው ከኔ ጋር የሚያድረው። እንደምታየው በቤት ውስጥ እንደልብ የሚያንቀሳቅስ ቦታ የለም። አብዛኛውን ጊዜ ቤተ-መፃህፍት እያመሸ በጣም ዘግይቶ ነው ከቤት የሚገባው። ምክንያቱም የቤተሠቡ

አባላት እያወሩ አልጋ ላይ ቁጭ ብሎ ማጥናት በጣም ያስቸግረዋል”፡፡ ይህች ሴት ሁኔታውን ስታብራራ ከአንዲት የልብስ መያዣ ሳጥን ላይ ቁጭ ብላ ነበር፤ ይህች ሳጥን መሰል ነገር እንደመኝታም እንደምትጠቀምበትም ትናገራለች፡፡ እንደሴትዮዋ አገላለፅ አልጋዋ ለልጇ መኝታና ማጥኛ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፤ ቀን ላይ ደግሞ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ነው፡፡

እንደ መረጃ ምንጮች አገላለጽ ከሆነ የቀበሌው ሕዝብ ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ በመሆኑ የቀበሌ አካላት ትናንሽ መጠለያዎችን እየሠሩ ለደሀ የቀበሌው ነዋሪዎ እየሠጡ ነው፡፡ በሁሉም የቡድን ውይይቶች ወቅት ተሳታፊ የነበሩ ግለሠቦች እንዳሉትም ምንም እንኳ እነዚህ መጠለያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ባይሆኑም ይህንኑም በማግኘታቸው ደስተኞች እንደሆኑ በዚህ ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡ እነዚህን ትናንሽ መጠለያዎች በማግኘታቸው ከቤት አልባ ዜጎች የተሻለ ኑሮ እንዲገፉ እንዳስቻላቸው ገልጸዋል፡፡ መረጃ ሰጪ 11 ሁኔታውን ስትገልፅ “የምትበይው ነገር ይኑርም አይኑርም ዋናው ወሳኙ ነገር መኖሪያ ቤት ማግኘትሽ ነው፡፡ ይህች ደሳሳ ቤት ባትኖረኝ ኖሮ ምን እሆን ነበር?” ብላለች፡፡ አንድ በወንድ ልጃቸው ቤት የልጅ ልጃቸውን የሚንከባከቡ በዕድሜ የገፉ ሴት (መረጃ ሰጪ 19) ቤታቸው በአንፃራዊ መልኩ ሠፋ ያለና በአግባቡ የተደራጀ ነው፡፡ አዛውንቷ አኗኗራቸው በሚከተለው መልክ ገልፀዋል፡፡ “የቀን ጊዜዬን የማሳልፈው እዚህ ቤት የልጅ ልጄን በመንከባከብ ነው፡፡ ወደ ማታ አካባቢ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ፡፡ እንደምታዪው የልጄ ቤት የተሟላና ንፅህናውን የጠበቀ ነው፡፡ እኔ ግን ያች ጨለማና ትንሽ ቤቴ ሁሌም ትዝ ትለኛለች፡፡ ስለእርሷ ሳስብ ሙሉነት ይሠማኛል፡፡ ከቤት አልባዎቹና ጥገኛ ሆነው ከሚኖሩትም የተሻልኩ እንደሆንኩ ይሠማኛል” ብለዋል፡፡

አብዛኞቹ ሴት የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት ደግሞ ቤት አልባነት በተለይ ለሴቶችና ለእናቶች በጣም ከባድ ፈተና ነው፡፡ አንዲት ሴት ልጆቿን ይዛ ጎዳና ተዳዳሪ ስትሆን ሕይወት እንዴት አስቸጋሪ እንደሚሆን መረጃ ሠጪዎቹ በሀዘን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ርዕስ-ጉዳይ ዙሪያ መረጃ ሠጪ 17 የራሷን ገጠመኝ ተናግራለች፡፡ እርሷና ቤተሠቧ ከድሮ መኖሪያቸው ከተፈናቀሉ በኋላ ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ሁለት እህቶቿንና በሽተኛ እናቷን ይዛ በጎዳና ተዳዳሪነት ቆይታለች፡፡ የገጠማትን አሠቃቂ ሁኔታ ማስታወስ አትፈልግም፡፡ ቀን ፀሀዩን ለሊት ብርዱን መቋቋም ፈታኝ እንደነበር ትገልፃለች፡፡ ማንም ሰው የነበሩበትን ሁኔታ አይረዳላቸውም ነበር፡፡ የሚያውቁት ሰው ሲያያቸው ሀፍረት ይሠማቸው ነበር፡፡ አሁን ግን ጊዜያዊ መጠለያ ለሰጧት አካላት ምስጋናዋ የላቀ ነው፡፡ ቢያንስ እንኳን በምትኖርበት ግቢ ደጃፍ ላይ ቡና በመሸጥ የቀን ገቢ ማግኘት ችላለች፡፡

ሴት የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት በመኖሪያ ቤታቸው የመሥሪያ ቦታ ባለመኖሩ በገቢያቸው ላይ ተፅዕኖ ፈጥሯል። በቤታቸውና በግቢ ውስጥ በቂ ቦታ ቢኖር ኖሮ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ያከናውኑ ነበር። መረጃ ሰጪ 5 ስለዚህ ጉዳይ ስትናገር “በአሁኑ ሠዓት በሽተኛ ልጆቼን በቤት ውስጥ በመንከባከብ ላይ እገኛለሁ። ሁልጊዜ የሆነ ሥራ ለመጀመር አስባለሁ፤ ማለትም እንደ ሽሮ፣ በርበሬ እና ቅመማ ቅመም ያሉ የምግብ ሸቀጦችን ለመነገድ እመኛለሁ። ነገር ግን እነዚህን የምግብ ሸቀጦች ለማዘጋጀት የግል ቦታ የለኝም። በአካባቢው የሚተላለፉ በርካታ መንገደኞችም አሉ፤ ሁሌ መጠበቅም ከባድ ነው” ብላለች።

የዚህ ጥናት ግኝቶች እንደሚሳዩት መረጃ ሠጪዎች የሚኖሩት ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ባልተሟሉበት ቤት ውስጥ ነው። ቤት የሚል ስያሜ የሚሰጡትም ምግብ ስለሚያበስሉበትና ስለሚተኙበት ነው። ከወንዶች ይልቅ በአብዛኛው ሴቶችና ሕጻናት በዚህ ተጨናንቆ የመኖር ችግር የበለጠ ተጠቂዎችና ተጋላጮች እንደሆኑም ታይቷል።

## 6.3 ውኃ እና ንፅህና

ጥሩ ለሆነ የአኗኗር ዘዴ ውኃ እና ንፅህና ጠቃሚና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ባብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍሎች የመኖሪያ አካባቢን ንፅህና መጠበቅና ለኑሮ ምቹ ማድረግ የሴቶች ኃላፊነት ተደርጎ ስለሚቆጠር ለዚሁ ሥራ በጋራ ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። በአካባቢው የሚንቀሳቀሱና የሚጫወቱ ሕጻናትን የመከታተል ኃላፊነትም ለእነርሱ የተተወ የሥራ ድርሻ ነው። በቤት ውስጥ የጎደሉ ነገሮችን ማጤንና እንዲሟሉ ማድረግም የሴቶች ድርሻ ነው። ለመኖሪያ ሠፈሮች ብልሽትና ንፅህና ጉድለት ብዙውን ጊዜ በእነዚሁ በቆሻሻማ ደሳሳ ሠፈሮች የሚኖሩ ሰዎች ተጠያቂ ተደርገው ይወሠዳሉ። ምንም እንኳን ሕጻናትና ደሀ ሴቶች በንፅህና ጉድለቶች የበለጠ ተጠቂ ቢሆኑም፣ የውኃ አቅርቦት ችግርና የንፅህና ጉድለት (የመጸዳጃ ቤት እጦት) በከተሞች ለሚኖሩ አብዛኛዎቹ ድሆች የዕለት ተዕለት ችግሮች ናቸው። በድህነት ሰንሰለት ለታሰሩ የከተማ ነዋሪዎች ውኃ ማግኘት ብርቃቸው ሲሆን፤ የመጸዳጃ ቤት እጦት ወይም በጋራ መጸዳጃ ቤት መገልገል ደግሞ የተለመደ ነገር ነው። ቤተሠብን የመመገብ ኃላፊነት በሴቶች ላይ የተጣለ በመሆኑ ረጅም ርቀት በመጓዝ ውኃ በመቅዳት የቤተሠቡን የውኃ ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ያደርጋሉ፤ የልጆቻቸውን የግል ንፅህናም ይጠብቃሉ።

ይህ ጥናት በተከናወነበት የዶሮ ማነቂያ ሠፈር የውኃ ችግር የተለመደ ነው። ከሞላ ጎደል ሁሉም የሠፈሩ ነዋሪዎች ውኃ የሚጠቀሙት በአካባቢ ከሚገኘው የሕዝብ የውኃ ቦኖ በመግዛት ነው። ከሕዝብ የውኃ ቦኖ 10 ሊትር ውኃ በ1.50 ብር የሚሸጥ

ሲሆን ግለሠብ የቧንቧ ውኃ ሻጮች ግን ከ2.00 እስከ 2.50 ብር ያስከፍላሉ። በሠፈሩ የውኃ ቦኖ ያለ ሲሆን አገልግሎት የሚሰጠው ግን የውኃ ተቆጣጣሪው በሚኖርበት በተወሠነ ጊዜ ውስጥ ነው። የሠፈሩ ሰዎችም የሚችሉትን ያህል ውኃ መግዛት ይፈቀድላቸዋል። በሁሉም ቤተሠቦች ውስጥ ውኃ መቅዳት የሴቶች ኃላፊነት ነው። ብዙዎቹ የሠፈሩ ሴቶች በልብስ አጠባ ሥራ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ውኃ የመቅዳቱ ኃላፊነትም ለእነርሱው የተተወ ነው። እንደነዚህ ሴቶች አገላለፅ በቂ የውኃ አቅርቦት በማይኖርበት ጊዜ ለውኃ የሚያወጡት ገንዘብ ይጨምራል፤ ይኸም የልብስ አጠባ ሥራቸውን በተወሰነ ደረጃ ያስተጓጉለዋል።

ከውኃ ጋር በተያያዘ አንዲት የቡድን ውይይት ተሳታፊ ኃሳቧን ስትሠጥ "እያንዳንዷን የውኃ ጠብታ በአግባቡ ነው የምንጠቀመው። የምንቀዳበት ቦታ ሩቅ የሚባል ባይሆንም በየቀኑ ውኃ ማጓጓዝ በጣም አድካሚ ሥራ ነው። በመሆኑም እንደምንፈልገው ልብሶቻችንን አናጥብም፤ ልጆቻችንም አንድን ልብስ ለበርካታ ቀናት ይለብሳሉ" በማለት ተናግራለች። በዚህ አካባቢ የቧንቧ ውኃ ባለቤቶች ልዩ ጥቅም ያገኛሉ። መረጃ ሰጪ 11 እንደገለፀችው በሠፈሩ ብቸኛዋ የቧንቧ ውኃ ባለቤት በመሆኗ ጥሩ የገቢ ምንጭ ሆኖላታል። በየቀኑ የተወሰነ መጠን ውኃ በመሸጥ የሚያስፈልጋትን ነገር ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ታገኛለች።

ሴቶቹም ሆኑ ወንዶች የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የገለፁት ሌላ ጉዳይ ቢኖር የጋራ መጸዳጃ ቤት ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ነው። አንድ ባለ አንድ ቀዳዳ የመጸዳጃ ቤት ከ3-5 የሚሆኑ ቤተሠቦች በጋራ ይጠቀሙበታል። አንድ ቤተሠብ ደግሞ በአማካይ ከ5-6 አባላት የሚኖሩት ስለሆነ ይህ መጸዳጃ ቤት እስከ 30 ለሚደርሱ ሰዎች አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል ማለት ነው።

ይህንን ጥናት በሚደረግበት ወቅት በአካባቢው ያለውን የመጸዳጃ ቤት አስከፊ ሽታ በቀላሉ ለመገንዘብ ተችሏል። ይሁንና የአካባቢው ሕጻናትና ልጆች በዚህ መጥፎ ሽታ ባለው ግቢ ውስጥ ይጫወታሉ። መጸዳጃ ቤቱ በተራ የሚጸዳ ቢሆንም፤ የጽዳቱ ሁኔታ በውኃ መኖርና አለመኖር ይወሠናል። አንዳንዴ ውኃ ከቦኖው እስከ ጭራሹ ላይኖር ስለሚችል በዚህ ጊዜ ማንም ሰው ለመጸዳጃ ቤት ማፅጃ ውኃ ማባከን አይፈልግም። እንደሠፈሩ ሰዎች አገላለፅ እንዲህ አደገኛ ሽታ ባለው ስፍራ መኖር ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ቢገነዘቡም፤ ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው በአካባቢው እየኖሩ ነው። መጸዳጃ ቤቱን ማን እንደሚያፀዳው ተጠይቀው ሁሉም ሴት የመረጃ ምንጮች ሲመልሱ "ይሄ የሴቶች ኃላፊነት ነው፤ የሚጠያይቅ ጉዳይ አይደለም" ብለዋል። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አንድ ሴት ስትገልፅ "መጸዳጃ ቤት በማን መጽዳት አለበት የሚል ጥያቄ አስበን እንኳ አናውቅም፤ ሁላችንም የምንገነዘበው የሴቶች ኃላፊነት እንደሆነ ነው። እናም ውኃ በተገኘ ጊዜ እናጸዳዋለን" በማለት ተናግራለች። ስለ መጸዳጃ ቤት

ፅዳት ጉዳይ ከወንድ የቡድን ውይይቱ አባላት ጋር በተደረገ ውይይት እነርሱ ብዙውን ጊዜ የሚያሳልፉት ከቤት ውጪ ባለ ሥራ መስክ ስለሆነ መጸዳጃ ቤት የማፅዳት ሥራ የሚስቶቻቸው ኃላፊነት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን እነርሱ እንዲያጸዱ ቢጠየቁ ለማፅዳት ፈቃደኛ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

ምንም እንኳን የውኃ ቧንቧዎች ያሉት በማኅበረሠቡ አካባቢ ቢሆንም በየቀኑ የመቅዳቱና ውኃን በአግባቡ የመጠቀሙ ኃላፊነት በሴቶች ላይ መጣሉ ሥራቸውን አድካሚ ያደርገዋል፡፡ ይህ ጉዳይ ከሌሎች የተለመዱ የቤት ውስጥ ሥራዎች ጋር ሲጨመር ሸክሙን ያከብድባቸዋል፡፡ በጤናቸው ላይም ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በቤት አካባቢ ማሳለፋቸው በራሱ ከሌሎች የቤተሠብ አባላት በበለጠ ሁኔታ ችግሩ እንዲጸናባቸው ያደርጋል፡፡

## 6.4 የጤና አገልግሎት አቅርቦት

በአማካይ በከተሞች ያለው የጤና አገልግሎት ደረጃ በገጠር ካለው የተሻለ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ለሕብረተሠቡ የጤና አገልግሎት ማቅረብ የአንድ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት ኃላፊነት ነው፡፡ በቂና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎቶች ለጤናማ ዜጎችና ማኅበረሠብ ዕድገት ዋስትና ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በከተሞች ያለው የጤና አገልግሎት የተሻለ ቢመስልም በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች የሚጠቁሙት አብዛኞቹ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሠፈሩ የከተማ ነዋሪዎች የተሟላ የጤና አገልግሎት እንደማያገኙና ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ሠለባ እንደሆኑ ነው (Montagomery, 2009) ፡፡

ይህ ጥናት ያረጋገጠው ሌላው ጉዳይ አብዛኞቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊም በወረዳው በሚገኙ የጤና ተቋማት ነፃ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ነው፡፡ ሆኖም ግን አብዛኞቹ ሰዎች የጤና ጠንቅ የሆኑ በሽታዎች የሚተላለፉበትን ሁኔታ አያውቁም፡፡ የንፅህና ጉድለትና በተጨናነቀ ሁኔታ መኖራቸው ለበሽታ መዛመት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ የዚህ ጥናት መረጃ በግልፅ እንደሚያሳየው የዚህ ጥናት ተሳታፊ ከነበሩት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ የኤች.አይ.ቪ፣ የሳንባ ነቀርሳና የቆዳ በሽታ ተጠቂ እንደሆኑ ነው፡፡ ሕጻናት በተለያዩ የቆዳ በሽታዎች እንደሚሠቃዩ መረጃ በማሠባሠብ ሒደት ውስጥ በቀላሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አንድ የመረጃ ምንጭ እንደተናገረችው ደግሞ አንዱ ልጇ ችፌ በተባለው የቆዳ በሽታ መሠቃየት ከጀመረ አንድ ወር ሆኖታል፡፡ መጀመሪያ ላይ ወደ ጤና ተቋም ወስዳው መድኃኒት የተሰጠው ቢሆንም ብዙም ሊሻለው አልቻለም፡፡ ከዚያም ወደ አንድ የግል ክሊኒክ ወስዳው 200 ብር ከፍላ ብታሳክመውም ከህመሙ ሊድን አልቻለም፡፡ አሁን ደግሞ ወደ አለርት

ሆስፒታል እንድትወስደው ሰዎች ቢመክሯትም ሆስፒታሉ የሚጠይቃትን ገንዘብ ማግኘት ስላልቻለች እስካሁን አልወሰደችውም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ መረጃ ሰጪ 5 ሁለት ልጆቿ የታመሙባት መሆኑን ትናገራለች፡፡ ሴት ልጇ ከታመመችባት ወራት የተቆጠሩ ቢሆንም፤ በሽታዋ ምን እንደሆነ እስካሁን አታውቀውም፡፡ ሌላው ቀርቶ በጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የልጅቷን በሽታ ሊያውቁት አልቻሉም፡፡ አሁን ደግሞ ትልቁ ልጇ በመታመም ላይ በመሆኑ ሁለቱንም ልጆቿን የመንከባከብ ኃላፊነት ወድቆባታል፡፡ የልጆቿን በሽታ ምንነት የጤና ባለሙያዎች ሊያውቁት ባይችሉም፤ ጎረቤቶቿ ግን አልማዝ ባለጭራ ነው ስላሏት ወደ ባሕላዊ መድኃኒት አዋቂዎች ልትወስዳቸው ታስባለች፡፡ ይህች ሴት የልጆቹ በሽታ ተላላፊ ስለመሆን አለመሆኑ የምታውቀው ነገር ባለመኖሩ ራሷንና ሌሎች ልጆቿን እንዴት ከበሽታው መጠበቅ እንዳለባት አታውቅም፡፡

ተዛማጅ ፅሁፎች እንደሚያሳዩት የታመሙ ልጆችን የመንከባከብ፣ ምግብ ማብሰልና ቤተሠቡን መመገብ ለሴቶች የተተዉ ሥራዎችና ኃላፊነቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በሴቶች የጊዜ አጠቃቀም ላይ ራሱን የቻለ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ እነዚህ እናቶች በልጆቻቸው ህመምና የቤተሠቡን ፍላጎት ለማሟላት በሚያደርጉት ትግል ሳቢያ አካላዊና መንፈሳዊ ተፅዕኖዎች ያድሩባቸዋል፡፡ ሴት የቡድን ውይይት አባላት እንደገለፁት አንድ የቤተሠብ አባል በሚታመምበት ጊዜ ጫናው የሚያርፈው በእናቶች ላይ ነው፡፡ የተዘጋጀውን ምግብ ለበሽተኞችና ለጤነኛ የቤተሠብ አባላት እንዴት እንደሚያከፋፍሉት፣ ለህክምና የሚሆን ገንዘብ ምንና የት ሠርተው ማግኘት እንዳለባቸው እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ያስጨንቋቸዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ሌሎች የቤተሠብ አባላትን ቤት ትተው እንዴት የታመሙ ሰዎችን ሆስፒታል ውስጥ መንከባከብ እንደሚችሉ ሲያስቡ የአዕምሮ መጨነቅና ህመም ይሰማቸዋል፡፡

ሴትም ሆነ ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዳሉት እንዳማራጭ እየተወሰደ ያለው በሽተኞችን በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ክፍያ ወደሚጠይቀውና ጊዜያዊ መፍትሔ ወደሚሠጠው የግል ባሕላዊ መድኃኒት አዋቂዎች መውሰድ ነው፡፡ ሴት የከተማ ድሆች ደግሞ ወደ ባሕላዊ መድኃኒት አዋቂዎች በብዛት የሚሄዱ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ይህ የሚያሳየው በከተማ የሚኖሩ ደሀ ሴቶች ምን ያህል በችግሩ ታንቀው እየሞቱ መሆኑን ነው፡፡ ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎችም በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸውን አስተያየት ሠጥተዋል፡፡ የከፋ የጤና ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ የሚሄዱት ወደ ጤና ተቋም ቢሆንም ጤና ተቋማቱ ግን መድኃኒት የሚሰጧቸው ለሚታወቁ የህመም ዓይነቶች ነው፡፡ ውድ የሆኑ መድኃኒቶችን የሚጠይቁ ከባድ በሽታዎች ግን በእነዚህ ጤና ተቋማት ህክምና አይደረግላቸውም፡፡

## 6.5 የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት

ኤሌክትሪክ አንድ ዓይነት የኃይል ምንጭ ነው። ኤሌክትሪክ ዘርፉ ብዙ ጥቅም ያለው ቢሆንም ይህ ጥናት በተደረገበት ሠፈር ለሚኖሩ የከተማ ነዋሪዎች ያለው ተደራሽነት ግን በጣም ውሱን ነው። አብዛኞቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎችም በቤታቸው ውስጥ አንድ አምፖል ብቻ ነው ያላቸው። የግላቸው ቆጣሪ ያላስገቡበት ምክንያት ወይ ቆጣሪ ማስገባት ከአቅም አንፃር ስሚከብዳቸው ነው ወይም ደግሞ የኤሌክትሪክ ፍጆታቸው ከአንድ አምፖል አቅም በላይ ስላልሆነ ነው። በዓመት በዓል ቀናት ደግሞ ምግብ ለማብሰል ከሠሰል ሲጠቀሙ ዳቦ ለመድፋት እንጨትን እንዳማራጭ ይወስዳሉ። ጉብኝት በተደረገባቸው ቤቶች ሁሉ በዋና የኃይል ምንጭነት የሚያገለግለው ከሠል ነው።

ለአመቺነቱ ሲባል የዚህ ጥናት አድራጊ ወደ መረጃ ሰጪ ሰዎች ቤት የሄድኩት ጧት አካባቢ ነበር። ወደ እያንዳንዳቸው ቤት ስገባ ያጋጠመኝ ነገር የቡና ማፍላት ሥነ-ሥርዓት ነበር። የቡና ስኒዎች በባሕላዊ ረከቦት ላይ የተደረደሩ ሲሆን ከሸክላ የተሠራው ጀበና ደግሞ ከከሠል ምድጃው ላይ ተጥዶ ይፈላል። ቡና የሚጠጡ ሰዎች እንደገለፁልኝ በጠዋት ቡና የሚጠጡት ቀኑን ሙሉ ተነቃቅተው እንዲውሉ ነው። ምንም እንኳ የጋራ ማብሰያ ማድቤት ያላቸው ቢሆንም ማንኛቸውም ቢሆኑ የማድቤቱን ንፅህናና ደኅንነት የመጠበቅ ኃላፊነት አልወሰዱም። በመሆኑም አብዛኛዎቹ የሠፈሩ ሰዎች ማድቤቱን እንደሌለ በመቁጠር በእያንዳንዳቸው ቤት ምግብ ለማብሰል የሚጠቀሙት የከሰል ምድጃን ነው። ቴሌቪዥን፣ ሬድዮና የኤሌክትሪክ ምጣድ ያላቸው ግለሠቦች ደግሞ የራሳቸው የሆነ የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ያላቸው ናቸው። በቃለ-መጠይቁ ሒደት ተሳታፊ የነበረች አንድ ግለሠብ እንደተናገረችው በየግላቸው ቆጣሪ አለመኖሩ በኑሯቸው ላይ ጫና ፈጥሯል። ምክንያቱም በፈለጉበት ጊዜ እንጀራ መጋገር ባለመቻላቸው በየቀኑ ከውጭ እየገዙ እንዲመገቡ ተገደዋል። ከቤት ጋግሮ ከመጠቀም ጋር ሲነፃፀር ከውጭ እንጀራ ገዝቶ መጠቀም ለከፍተኛ ወጪ ይዳርጋል። በተጨማሪም ከውጭ የሚገዛ እንጀራ ቤት ውስጥ ከሚጋገረው ጋር ሲነፃፀር ጥራቱ በጣም ዝቅተኛ ነው።

በዚህ ሠፈር ለሚኖሩ ሰዎች ሬድዮና ቴሌቪዥን በጥቂት ቤቶች ብቻ የሚገኙ እንደቅንጦት የሚቆጠሩ ዕቃዎች ናቸው። በሚገርም ሁኔታ በእማወራ ከሚመሩ ቤተሠቦች መካከል አንድም ቴሌቪዥን ያለው የለም። ቴሌቪዥን ባለበት ቤተሠብ ደግሞ ቴሌቪዥኑን የገዛው አባወራው እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። ምናልባትም ይህ በድህነት ከሚኖሩ ቤተሠቦች አንፃር በአባወራ የሚመራ ቤተሠብ በተሻለ ሁኔታ የቅንጦት ዕቃ የመግዛት አቅም እንዳለው ነው።

## 6.6 ትምህርት

ትምህርት ለግለሠብና ለቤተሠብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሠረታዊ ኃብት ነው። ምንም እንኳ በፍልሠት የመጡና በጎስቋላ ሠፈር የሚኖሩ ቢሆኑም፤ ሁሉም ሴትና ወንድ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የተወሰነ የትምህርት ዕድል አግኝተዋል። በቃለ-መጠይቁ ተሳታፊ የነበሩ ሴቶች የትምህርት ደረጃ ከ3-9ኛ ክፍል ሲሆን አንድ በሰው ቤት ውስጥ በሠራተኛነት ታገለግል የነበረች የጥናቱ ተሳታፊ እንደተናገረችው አሠሪዎቿ እንድትማር ስለፈቀዱላት እስከተወሰነ ክፍል ድረስ ተምራለች። የትውልድ ቦታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የሠፈሩ ሰዎች ደግሞ የመማር ዕድሉን ያገኙት ከቤተሠብ ጋር በነበሩበት ወቅት መሆኑን ይናገራሉ። ሆኖም ግን ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች መቀጠል አለመቻላቸውን ይገልፃሉ። አንዳንዶቹ እንደሚሉት አሠሪዎቻቸው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ስለማይፈቅዱላቸው ማቋረጥ ግድ ሲሆንባቸው፤ ሌሎቹ እንደሚናገሩት ደግሞ ከቤተሠብ ተለይተው የግል ሕይወታቸውን በመጀመራቸውና ቀንም ሆነ ማታ በሥራ በመጠመዳቸው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዋል። አንዳንድ የጥናቱ ተሳታፊዎ ደግሞ ወደ ትዳር በመግባታቸውና ልጆች በመውለዳቸው ትምህርታቸውን መከታተል አልቻሉም።

አንድ ጥናት እንደሚጠቁመው በከተሞች አካባቢ ሴቶች በትምህርት ላይ የሚቆዩበት ጊዜ በአማካይ የወንዶችን ግማሽ ያህል ነው (Muzzin, 2008) ። ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሉት አዲስ አበባ ከመጡ በኃላ ምንም እንኳን ትምህርት የሚጀመሩበት ዕድል የነበራቸው ቢሆንም፤ ኑሮን ለማቃናት ላይ ታች ሲሉ ጊዜያቸውን በማጥፋታቸው ትምህርታቸውን መቀጠል አልቻሉም። ሁሉም ሴትና ወንድ የመረጃ ምንጮች እንደተናገሩት በትምህርታቸው አለመግፋታቸው ለተለያዩ የሕይወት ጫናዎች ተጋላጭ እንዳደረጋቸውና የወደፊት ዕጣ-ፈንታቸውንም ለመተንበይ ጋሬጣ እንደሆነባቸው ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት በትምህርታቸው ቢገፉ ኖሮ አሁን የተሻለና ቋሚ ገቢ ስለሚኖራቸው የተረጋጋ ሕይወትን በተሻለ አካባቢ መምራት ይችሉ እንደነበር ያስረዳሉ። ይህ ሁኔታ ወደፊት በልጆቻቸው እንዳይደገም በማለት ሁሉም የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ለትምህርት የደረሱ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እየላኩ እንደሆነም ጥናቱ አረጋግጧል። የአካባቢውም መንግሥትም የአካባቢውን ነዋሪዎች የኑሮ ድህነት በማየት ት/ቤትን በነፃ አቅርቧል። እንዲሁም CCF የተባለው ግብረ-ሠናይ ድርጅትም እንደ ት/ቤት ዩኒፎርምና፤ የትምህርት መረጃ ቁሳቁስ ለሁሉም የአካባቢው ተማሪዎች በነፃ በየዓመቱ በትምህርት መጀመሪያ ወቅት እንደሚያከፋፍል ከቁልፍ መረጃ ሠጪዎች ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ መረዳት ተችሏል።

## 6.7 *ማኅበራዊ ኃብት* (Social capital)

*ማኅበራዊ ኃብት ሲባል አንድ ግለሠብ ወይም ቤተሠብ ከዘመድ፣ ከጓደኛ እና ከተቋማት ጋር ሊመሠርት የሚችለው ግንኙነት ወይም ትስስር ማለት ነው። ይህ ዓይነት ግንኙነት ከሰዎች ጋር የሚኖርን ዝምድናና ትስስር ስለሚጨምር የገንዘብና የህሊና ጥቅም ይኖረዋል። ማኅበራዊ ግንኙነቶችና ተቋማት ለዚህ ትስስር መፈጠር ቁልፍ ሚና አላቸው። ምክንያቱም የሰዎችን ግንኙነት በማገድም ሆነ በማፍጠን የሰዎችንና የቤተሠቦችን ችሎታና ምርጫ ስለሚያካትት ነው* (Tizita, 2013)*። ሴቶችና ወንዶች ለማኅበራዊ ግንኙነት የሚገለገሉባቸው የተለያዩ ማኅበራዊ መረቦች እንዳሉ ጠቋሚ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ያህል ከታንዛኒያ* (Narayan, 1997) *እና ኬንያ* (Nyberge, 2004) *የተገኙ መረጃዎች እንደሚሳዩት ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ኢ-መደበኛ ለሆኑ አካባቢያዊ ተቋማት ቅርብ ሲሆኑ፤ ወንዶች ደግሞ መደበኛና ከፊል መደበኛ በሆኑ ድርጅቶች ላይ እንደሚያተኩሩ ያሳያሉ።*

*የዚህ ጥናት ተሳታፊ የሆኑ ሴቶችና ወንዶች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የተለያዩ ማኅበራዊ ተቋማት አካሎች ናቸው። እንደ ቀበሌው ቁልፍ የመረጃ ምንጮች መሠረት ለቀበሌው ሴት ነዋሪዎች የተዘጋጀ 'የቡና ጠጡ' ፕሮግራም እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ 'የቡና ጠጡ' ፕሮግራም ሴቶች ስለፅዳት፣ ጤናና ደህንነት ጉዳዮች ሥልጠና የሚሠጣቸው ሲሆን፤ ስለችግሮቻቸውም እንዲወያዩ ይበረታታሉ። በዚህ ጥናት ብሔርን መሠረት በማድረግ የተደራጁ የሴት ማኅበራት (ለምሳሌ የአማራ ሴቶች ማኅበር) በአካባቢው እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። በድርጅታቸው ውስጥ ስለጤና፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ችግሮች እንዲወያዩ የሚበረታቱ ሲሆን፤ የዚህ ድርጅት አባል የሆኑ መረጃ ሰጪዎችም ከድርጅቱ በርካታ ጥቅሞች እንዳገኙ ይናገራሉ። ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች ግን የዚህ ዓይነት ድርጅት አባል እንዳልሆኑ ይገልጻሉ። ሆኖም ግን በየቀኑ፣ በየሳምንቱና በየወሩ ገንዘብ የሚቆጥቡበት ዕቁብ እንዳላቸውና የዚህ የቁጠባ ማኅበር አባል እንደሆኑም ተናግረዋል። በቁጠባ ማኅበራት መሳተፋቸው የገንዘብ አቅማቸውን በማጠናከሩ ኑሮቸው እንዲሻሻል እንዳገዛቸውም ይመሰክራሉ።*

*በዚህ ጉዳይ ዙሪያ አንድ ወንድ የቡድን ውይይት አባል ተሞክሮውን አጫውቶናል። ግለሠቡ በቀን ሥራና በሊስትሮነት የሚተዳደር በመሆኑ ቋሚ የሆነ ገቢ ባይኖረውም በቀን ቢያንስ* 10 *ብር ዕቁብ ይጥላል። በዚህ ሁኔታ በዕቁብ የተወሰነ ገንዘብ ያጠራቀመ ሲሆን በዚህ ገንዘብም ቢያንስ ተንቀሳቃሽ ሱቅ (ሱቅ በደረቴ) በቅርቡ ለመጀመር ኃሳብ አለው። አንድ ሌላ መረጃ ሰጪ እንደገለጸው ደግሞ ሁሉም የቤተሠቡ አባላት ወደትውልድ ቦታቸው (ጉራጌ) ተመልሰው ሲሄዱ እርሱ ግን ሳንቡሳ መሸጥ ጀምሯል። ከዕቁብ የሚያገኘው ገንዘብ ቤተሠቦቹን ለመደገፍና*

በየዓመቱ መስከረም ላይ ለሚውለው የመስቀል ክብረ በዓል ወደ ትውልድ ቦታው እንዲሄድና እንዲያከብር አስችሎታል።

ከሴት የጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር በተደረጉ ውይይቶች ሁሉም ሴቶች ዕቁብ እንደሌላቸው ከመግለፃቸውም ባሻገር ዕቁብን እንደቅንጦት እንደሚቆጥሩትና የዕቁብ አባላትም ቋሚ ገቢ ያላቸው ሰዎች ናቸው ብለው እንደሚያስቡ ለማወቅ ተችሏል። ስለ ዕቁብ ሲጠየቁ ሁሉም ሴቶች በአግራሞት “የምንኖርበትን ቦታና የአኗኗር ሁኔታችንን ጎስቋላነት በአይንሽ እያየሽ እንዴት ስለ እቁብና ቁጠባ ትጠይቂናለሽ” የሚል ምላሽ ሠጥተዋል።

በኢትዮጵያ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች አባል የሚሆኑበት ሌላው ተቋም ደግሞ ዕድር ነው። ዕድር የቀብር ማስፈጸሚያ ማኅበር ሲሆን የማኅበሩ አባል ወይም የአባሉ ቤተሠብ በሚሞት ጊዜ ለቀብር ማስፈጸሚያ ክፍያ ይፈጽማል። ክፍያው በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ሊሆን ይችላል። በዚህ ጥናት ተሳታፊ የነበሩ የተወሰኑ ሴትና ወንድ ግለሠቦች ዕድር እንዳላቸው ተናግረዋል ሆኖም ግን ከሀያዎቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች መካከል ዕድር ያላቸው ሰባቱ ብቻ ሆነው ተገኝተዋል። በሌላ በኩል በቡድን ውይይቱ ተሳታፊ የነበሩ ወንዶች እንደገለፁት ሁሉም የወንድ ዕድር የሚባለው ማኅበር አባል እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል። ጥናቱ እንዳረጋገጠው የተወሰኑ ሴት መረጃ ሰጪዎች ዕድር ያልገቡበት ምክንያት አባል ለመሆን የሚያስፈልገውን እስከ 1,500 ብር የሚደርስ ቅድመ ክፍያ መክፈል ስለማይችሉ ነው። ሌሎቹ ደግሞ እስከ 15 ብር የሚደርሰውን ወርኃዊ መዋጮ መክፈል ስለማይችሉ የዕድር አባል እንዳልሆኑ ታውቋል። የተወሰኑ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ደግሞ ከሠፈሩ መቼ እንደሚባረሩ እርግጠኞች ስላልሆኑ የሠፈሩ ዕድር አባል ለመሆን አልቻሉም። ይህን ጉዳይ በተመለከተ መረጃ ሰጪ 9 ስትናገር “በሸራተን ሆቴል አካባቢ እኖር ነበር፤ ሆኖም ግን መንግሥት ለዘመናት ከምንኖርበት ሠፈር አፈናቅሎ አሁን በምታያት ኩሽና በምትመስል ደሳሳ ቤት ውስጥ ወረወረኝ። ጎረቤቶቼን፣ ዕድሬንና አጠቃላይ ማነቴን እዚያ ትቼ ነው የመጣሁት። ይገርምሻል ይኽ ቦታ ራሱ ለልማት ሥራ እንደሚፈለግ ከተነገረን ብዙ ጊዜ ቆይቷል። በመሆኑም ከዚህ ቦታ ደግሞ መቼ እንደምንባረር እርግጠኛ አይደለሁም። እናም ገንዘቤንና ጊዜዬን እርግጠኛ ባልሆንኩበት ጉዳይ ላይ ማጥፋት አልፈልግም” ብላለች። መረጃ ሰጪ 14 በበኩሏ “የተወለድኩት በዚሁ ቤት ውስጥ ሲሆን ለ36 ዓመታት ኖሬያለሁ። እናቴ ዕድር ነበራት። እሷ ከሞተች በኋላ የዕድሩ አባል ለመሆን ፈልጌ ስጠይቃቸው እንደ አዲስ ገቢ 1,500 ብር ጠየቁኝ። እንኳንስ ይህን ገንዘብ ለመክፈል ወርኃዊ የቤት ኪራይ የመክፈል አቅምም የለኝም” ስትል ገልፃለች። አንዳንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለፁት የዕድር አባል አለመሆን ጭንቀት ይፈጥራል። ከማኅበረሠቡ የተገለሉ ይመስላቸዋል፤ ከቤተሠብ

አባላት አንዱ ቢሞት ሊገጥማቸው የሚለው ችግር ይታያቸዋል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ሴቶች የዕድር መዋጮ የመክፈል አቅም ስለሌላቸው ነው። ምንም እንኳ ማኅበራዊ ኃብት የአዕምሮ እረፍትና ራሳቸውን ከማኅበረሠቡ ጋር ለማስተሳሰር የሚረዳ ቢሆንም በከተማ የሚኖሩ ድሆች ግን ካላቸው ውስንና ቋሚ ያልሆነ ገቢ ጋር በተያያዘ በጣም አናሳና ምናልባትም በፆታ በተለየ (በተከፋፈለ) በሚመስል ማኅበራዊ ኃብት ራሳቸውን ሲያስጠጉ ይታያል።

## 7 የፖሊሲ መነሻ ኃሳቦች

ማኅበረሠብ ሰው-ሰራሽ የሆኑ ችግሮችን ለመለየት፤ ለመታገልና ለማስወገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ምንም እንኳን ድህነት የሁለቱም ፆታዎች ዕይነተኛ ችግር ቢሆንም ይህ ጥናት እንደሚያሳየው ወንዶችና ሴቶች በድህነት የመጠቃት ደረጃቸው ግን በእጅጉ ይለያያል። በጥናቱ መሠረት ሴቶች በድህነት የመጠቃታቸው ደረጃ ከወንዶች ይበልጣል። ድህነትን መታገልና ማስወገድ የሁሉም ድርሻ ቢሆንም ፆታ-ተኮር ፖሊሲዎችና ኃሳቦች ግን ችግሩን ለማስወገድ መሠረታዊ ነገሮች እንደሆኑ ይታመናል። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት ከ1993 ጀምሮ የተለያዩ ፆታ-ተኮር ፖሊሲዎችን ሲያወጣ ቆይቷል። ፆታ-ተኮር ፖሊሲዎች ሲቀረፁ "የፆታ እኩልነት" እና "ሴቶችን ማጎልበት" የሚል አስተሳብ ተይዞ ሲሆን፤ ዓላማውም ለሴቶች ዕድሎችን በመስጠት ድጋፍ ማድረግ ነው። እንደ ቅጥር፣ ትምህርት፣ ጤና እና ሌሎች መሠረታዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ከሚገቡ ዕድሎችም መካከል ይጠቀሳሉ (Tvedten et al, 2008/13,5)።

የሴቶችን መብት አስመልክቶ ምላሽ ከሚጠቀሱ ዋና ዋና ሠነዶች መካከል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ዋነኛው ነው። ሕገ-መንግሥቱ ሴቶች በሁሉም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው በአንቀፅ 354 ያትታል። ይህም መብት ትምህርትን፣ ቅጥርን፣ ለኃብት ያላቸውን ተደራሽነትና ኃብት ማስተዳደርን ያካትታል።

የጋብቻ እኩልነት፣ የማበረታቻ ድጋፍ፣ ፕሮጀክቶችን መቅረጽና መተግበር (በተለይ በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ)፤ ኃብትና ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመያዝ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት እንዲሁም በቅጥር በክፍያ እና በዕድገት ጊዜ ከወንዶች እኩል የመታየት መብቶች በሕገ-መንግሥቱ ከተካተቱ የሴቶች መብቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው (FDRE, 1995:23)።

እንደሚታወቀው በ1993 የኢትዮጵያ ሴቶች ብሔራዊ ፖሊሲ ወጥቷል። የዚህ ፖሊሲ ዋና ዓላማዎችም መካከል በሴቶችና ወንዶች መካከል እኩልነት እንዲኖር ሁኔታዎችን

ማመቻቸት፤ በገጠር የሚኖሩ ሴቶች እንደ ትምህርትና ጤና የመሳሰሉ ማኅበራዊ ግልጋሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የተዛቡ አመለካከቶችን ማስወገድ፣ ሴቶችን የሚያገልሉ አስተሳሰቦችንና ተግባራትን መታገል ይገኙባቸዋል። ስለዚህ የፆታ ዕኩልነትና ፍትሐዊነት ጉዳዮች ተደራሽ የሚሆኑበት መሠረታዊ ኃሳቦች በፖሊሲው ውስጥ እንደተካተቱ መረዳት ይቻላል (የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት TGE, 1993)።

በ1993 የተቀረፀው የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ (NPP) የአገሪቱን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትና የአገሪቱን አቅም ለማመጣጠን የሚያገለግል መሣሪያ ነው። ፖሊሲው ትኩረት ከሚሠጣቸው ነገሮች አንዱ የፆታ ጉዳይ ሲሆን፤ ሴቶች የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን ለመቆጣጠር ያላቸውን ሚና በሠፊው ይገልጻል። ፖሊሲው አጥብቆ ከሚጠይቃቸው ጉዳዮች አንዱ የሴቶች ሁኔታ ከአንድ ማኅበረሠብ የመዋለድ ደረጃ ጋር በቀጥታ እንደሚዛመድ የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም የሴቶችን መብቶች የሚያረጋግጡ እንደትምህርት፣ ቅጥርና ሌሎች ሕጋዊ ዕቅዶች እንዴት ከመዋለድ ደረጃና ከሥነ-ተዋልዶ ጤና ጋር በቀጥታ እንደሚዛመዱ ያሳያል (TGE, 1993)።

የኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊስ ከሚያስቀምጣቸው ዝርዝር ዓላማዎች አንዱ የሴቶች ትምህርት የሚኖረውን ሚናና ጥቅምን አስመልክቶ የነበረውን የተሳሳተ ግምትና አስተሳሰብ የሚያስተካክል የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ነው። ፖሊሲው ሥርዓተ-ትምህርትና መጻህፍት ሲቀረፁ ለፆታ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ እንደሚደረግ ይገልጻል። እንደዚሁም በመምህራን ምልመላ፣ ሥልጠና እና በመማር ማስተማር ሒደት ውስጥ ዕኩል የሴቶች ተሳትፎ መኖር እንዳለበት ፖሊሲው ይገልፃል። ፖሊሲውን ተግባር ላይ ለማዋልም በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል (TGE, 1994)። ለምሳሌ ያህል በአሁኑ ጊዜ ዝቅተኛ አማካይ ውጤት (GPA) ያላቸው ሴቶች ለመምህርነት እንዲመለመሉ በመደረጉ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ያሉ የሴት መምህራን ቁጥር ከፍ ሊል ችሏል (Yeshimebrat, 2013) ።

ልማታዊ የማኅበራዊ ደህንነት ፖሊሲ ኅዳር 1996 በመንግስት መቀረጹ ይታወቃል። ይህ ፖሊሲ እንደሚለው ባለፉት አስርት አመታት የተከሰቱ ጦርነቶች፣ ረሀብና የኢኮኖሚ ቀውሶች ለእነዚህ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ማለትም ሴቶችን፣ አዛውንትን፣ ልጆችን፣ ወጣቶችንና አካል ጉዳተኞችን በእጅጉ ጎድቷል። ፖሊሲው ሴቶች በማንኛውም ነገር (ለምሳሌ በትምህርት፣ በቅጥር፣ ቁልፍ በሆኑ የውሳኔ ሰጭነት ቦታዎች) ውስጥ ያላቸው ውክልና ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልፃል። በመሆኑም በሁሉም ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና አገልግሎቶች ለሥነ-ፆታ ልዩ አትኩሮት መስጠት የሚኖርውን ጠቀሜታ ፖሊሲው ይጠቁማል (FDRE, 1996)።

በ1997 የተቀረፀው የባሕል ፖሊሲ እንደሚያሳየው ደግሞ በሴቶች ላይ የተሳሳተ አመለካከትና ጥላቻ እንዲኖር የሚያበረታቱ ባሕላዊ ባህሪያት፣ ተግባራትና አመለካከቶች ቀስ በቀስ መወገድ እንዳለባቸውና የፆታ ዕኩልነት የሚረጋገጥበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት ያብራራል፡፡

የፖሊሲው ይዘት በግልፅ የሚያሳየው ሴቶች የተመቻቸ ሁኔታ ያላገኙ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶች በሁሉም ባሕላዊ ክንዋኔዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል ለውጥ መደረግ እንዳለበት ፖሊሲው ያሠምርበታል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች ለተለያዩ ጥቅሞች ዕኩል መብት እንዳላቸው ዋስትና ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ ፖሊሲው በተለያዩ ባሕላዊ ክብረ-በዓላትና ተቋማት ላይ የሴቶችን እውቅናና የውሳኔ ሰጭነት ሥልጣንን ያበረታታል፤ የጎጂ ልማዶችን መወገድንና፤ የሴቶችን ደህንነት የሚያሳድጉ ባህላዊ ክንዋኔዎችን መጎልበትን ይደግፋል (FDRE, 1996)፡፡

የቤተሠብ ሕጉ በበኩሉ የልጃገረዶችን ዝቅተኛ የጋብቻ ዕድሜ ከ15 ዓመት ወደ 18 ዓመት ከፍ አድርጓል፡፡ ጋብቻ በቤተሠብ ሳይሆን በባልና ሚስት መካከል የሚፈፀም ውል መሆኑን ያረጋግጣል፤ በትዳር ውስጥ የሚፈራ ንብረት የጋራ መሆኑን ያትታል፤ ባሎች ውሳኔ ሲሠጡ ሚስቶቻቸውን ማማከር ግዴታ እንደሆነ ይናገራል፤ እንዲሁም ሕጻናትን የመንከባከብ ዕኩል መብት ለሴቶች ይሰጣል፡፡

ሌላው ለድህነት ቅነሳና ለዜጎች የኑሮ ደረጃ መሻሻል ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ሠነድ (Poverty Reduction Strategic Paper) ነው፡፡ ይህ ሠነድ ቁልፍ የሆኑ የማኅበራዊ ልማት ፕሮግራሞች ማለትም እንደ ትምህርትና ጤና ያሉት መሻሻል እንዳለባቸው በጥብቅ ያምናል፡፡ የጤና ተደራሽነት፣ የሴቶች የሥራ ጫና ቅነሳ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነት፣ የፖለቲካ ተሳትፎ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መወገድና የመሳሰሉት በዚህ ፖሊሲ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን የሚሞላ ተጨባጭ የሆነ ስትራቴጂ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፆታ ልዩነቶችን ሊያስተናግድ አልቻለም፡፡ ለምሳሌ ያህል በጋብቻ ውስጥ መደረግ ስለሚገባው የኃብት ክፍፍል ምንም የሚለው ነገር የለም፡፡ ትላልቅና ትናንሽ የኢኮኖሚ ስትራቴጂዎችም ፆታን ታሳቢ ያደረጉ አይደሉም፡፡

## 8 ማጠቃለያ

ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ የሚደረግ ፍልሠት ምክንያት የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች አስተማማኝ መሠረታዊ የገቢ ምንጭ በማይገኝባቸው ከተሞች ውስጥ እንዲኖሩ እንዳደረጋቸው ይህ ጥናት ያመለክታል፡፡ አቅመ-ቢስነት፣ ጥገኝነት፣ የጊዜ ድህነት፣

ተጋላጭነት፣ እርግጠኛ አለመሆን፣ የቤተሠብ አወቃቀር ለውጥና የድህነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሽግግር የሚሉ ፅንሰ ኃሳቦች ይህ ጥናት የተደረገበት ስፍራ መገለጫዎች ናቸው።

አቅመ-ቢስነት (ኃይል አልባነት) የሚለው ፅንስ ኃሳብ ጠቃሚ የሆኑ ኃብቶች ማለትም መደበኛ ትምህርት፣ መሠረታዊ የሕይወት ክህሎትና የገንዘብ እጦት ማለት ሲሆን የመደበኛ ትምህርት እጦትና ትምህርታቸውን መቀጠል አለመቻላቸው አብዛኞቹን (በተለይም ደግሞ ሴቶችን) ያለክህሎት እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል። በዚህ ረገድ ተገቢውን ክህሎት ባለመያዛቸው በመደበኛ የሥራ ዘርፎች ለመቀጠር ወይም ሕይወታቸውን ለማሻሻል እንዳልቻሉም ለማወቅ ተችሏል። ይህ ሁኔታ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ዝቅተኛ ገቢ ወደሚያስገኙ ኢ-መደበኛ የሥራ መስኮች እየመራቸው መሆኑንም መረዳት ተችሏል። ቋሚ የሆነ ገቢ አለመኖር እነዚህን ግለሠቦች ወደ ጎስቋላ የኑሮ ሁኔታ እየከተታቸው መሆኑንም በዚህ ጥናት ለማወቅ ተችሏል። በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊ ሴቶች የሌሎች የቤተሠብ አባላት፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥገኞች ለመሆን ተገድደዋል።

በቤት ውስጥ ሥራ የተሠማሩ ሴቶች ሕጻናትን በመንከባከብና በፍጥነት መሠራት ባለባቸው ሥራዎች የተጠመዱ ናቸው። ይህ ሁኔታ ጊዜያቸውን በትክክል እንዳይጠቀሙ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው በመሆኑ ለበለጠ ድህነት ተጋላጭ አድርጓቸዋል። በሌላ በኩል ወንዶች ጊዜያቸውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የመወሰን የተሻለ ነፃነት እንዳላቸው የታወቀ ሲሆን፤ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከቤት ውጪ ባለ ሥራ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። የመሠረታዊ ፍላጎቶች (ማለትም ምግብ፣ ገንዘብ እና ሥራ) እጦት የጥናቱ ተሳታፊዎችን ሕይወት በስጋት የተሞላ ከማድረጉ ባሻገር ወደ ፊት ምን መሥራት እንደሚችሉ የሚያሳይ ዕቅድ እንዳይኖራቸው አድርጓል። አብዛኛዎቹ ባገኙት የሥራ መስክ ላይ በመሠማራት የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት እንዲሯሯጡ ተገድደዋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ አዲስ ዓይነት የቤተሠብ አደረጃጀትና አወቃቀር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።

ከተለመደው የቤተሠብ አደረጃጀት ውጪ አብዛኞቹ ቤተሠቦች በእማወራዎች የሚመሩ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። በእማወራዎች የሚመሩ ቤተሠቦች ደግሞ በተፋቱ ሴት ልጆች፣ በልጅ ልጆችና በብዙ ሌሎች ጥገኞች የተሞላ ነው። በሌላ በኩል ወንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች በእማወራ በሚመራ ቤተሠብ ውስጥ አንድ የተወሰነ ቦታ ተከራይተው እየኖሩ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል። ወላጆች የተሻለ ሥራ እስካልሰሩ ድረስ ይህ ዓይነት የኑሮ ሁኔታና የገቢ ምንጭ ወደ ቀጣዩ ትውልድ መሸጋገሩ አይቀሬ ነው። ልጃገረዶችም የእናቶቻቸውን ፈለግ በመከተል በተለያዩ የቤት ውስጥና

የሥነ ተዋልዶ ሥራዎች ተጠምደው ይታያሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት ድህነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ መሆኑን ነው፡፡

በተለያየ ሁኔታ የተገለፀውን የድህነት ክስተቶች ለመቋቋም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ሴት የመረጃ ምንጮች የተወሰነ ሥራ በቤትና በግቢ ውስጥ በመሥራት ከጊዜ ድህነት ጋር ሲታገሉ ይታያሉ፡፡ እንዲሁም ውኃ በመሸጥ፣ ልብስ በማጠብና የመሳሰሉትን ሥራዎች በማከናወን አማራጭ የገቢ ምንጭ እየፈጠሩ ሲሆን፤ ይህን ለማድረግም የሚበሉትን ምግብ መጠንና ጥራት እስከመቀነስ የሚደርስ መስዋዕትነት ይከፍላሉ፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከግለሠቦችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆኑ የሚያገኙት ድጋፍ ግን እንደየግለሠቦቹ ማኅበራዊ ኃብት መጠን ይለያያል፡፡ ከሴቶቹ ይልቅ ወንዶቹ ችግሮቻቸውን በሚቋቋሙባቸው መንገዶች ላይ ትኩረት ሰጥተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ስደት፤ ሩቅ ቦታ ሄዶ መሥራት፣ የሥራ ቦታ መቀየርና የመሳሰሉት በወንዶች የሚከናወኑ አማራጮች ሲሆኑ ሴቶች ግን የተገኘውን ነገር እየተጠቀሙ ከመቀመጥ በስተቀር ከችግሮቻቸው የሚላቀቁበትን ስትራቴጂ የመጠቀም እንቅስቃሴያቸው ደካማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 9 ምክረ-ኃሳብ

በዚህ ጥናት ላይ እንደታየው ድህነት በሴትም ሆነ ወንድ የከተማ ነዋሪዎች ላይ በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል፡፡ በመሆኑም ድህነትን ለማስወገድ አንድ የተወሰነ ቀመር ማስቀመጥ የሚከብድ ነገር ነው፡፡ ሆኖም ግን ድህነት የሚገለፅባቸውን የተለያዩ መንገዶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊለኩና ሊተገበሩ የሚችሉ የተወሰኑ የድህነት መቀነሻና ማስወገጃ መንገዶችን ይህ ጥናት በምክረ-ኃሳብ ደረጃ ያቀርባል፡፡

- የቤት ውስጥ ሥራና የጊዜ አጠቃቀም የሚሠጠውን ዋጋ በገንዘብ ለክቶ ማስቀመጥና ለብሔራዊ ዕድገትም ያለውን ፋይዳ ማሳየት አስፈላጊ ነው፡፡
- እያደገ ያለውን የከተማ ሕብረተሠብ የአገልግሎትና የመሠረተ-ልማት ፍላጎት ሊያስተናግድ የሚችል ጠንካራ የአስተዳደር ተቋም መኖር ይገባዋል፡፡
- የሴቶችንና ወንዶችን ተፈጥሯዊ ዕውቀቶችን ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ የኢኮኖሚ ማሳደጊያ ፕሮግራሞን መንደፍ አስፈላጊ ነው፡፡
- የከተማ ነዋሪዎችን የሥራ ዕድል የሚያሠፉ የሥራ ፈጠራ ክህሎቶችን ማሳደግ፤ እነዚህ የሥራ ፈጠራ ክህሎቶችን ከማስፋፋት አንፃርም መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀዳሚ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የሚመለከታቸው ባለስልጣናትና የሥራ ኃላፊዎች መደበኛ ያልሆነውን የሥራ ኃይል ወደ መደበኛ ተቀጣሪነት የሚያመራበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡
- ሴቶችንና ወንዶችን እንደየፍላጎታቸውና ችሎታቸው በማደራጀት አነስተኛ ደረጃ ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡
- ልማታዊ ድርጅቶችና የሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በተመረጡ ፕሮግራሞች ላይ ራሳቸውን በማስገባት ሚናቸውን ሊጫወቱ ይገባል፡፡ ምርጫው ደግሞ ፆታን እንዲሁም የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶች ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡
- የወረዳና የቀበሌ መስተዳድሮች በሴቶች የሚመሩ ጠንካራ ድርጅቶች የሚጎለብቱበትንና ማኅበረሠቡ ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ የሚመጡበትን መንገድ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የሴቶችን የጊዜ ድህነት ለመቀነስ ስለማኅበረሠባዊ የህፃን እንክብካቤ ያለውን ግንዛቤ በፍጥነት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በቂ የሆነ የሕጻናት እንክብካቤ ድርጅት እንዲኖር ከማስቻሉም ባሻገር ወላጆች ልጆቻቸውን ያለምንም ስጋት እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ትተው ወደ ሥራቸው እንዲሄዱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- ለድህነት መከሠትና መቀጠል ዋና መንስኤ በሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ቀጣይ ጥናትና ምርመር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ የግል ኢኮኖሚያዊ ነፃነት መለኪያዎችና የእያንዳንዱን ሰው ፍላጎት ከማሟላት ችሎታ ላይ ያተኮረ ጥናት ቢደረግ ጉዳዩን በጥልቀት ለመረዳት ያስችላል፡፡

## ዋቢ መፃሕፍት

Bapat, Meera (2009) Poverty lines and lives of the poor: Underestimation of urban poverty, the case of India Poverty Reduction in Urban Areas Working Paper 20, IIED, London

Beall, Jo and Sean Fox (2007) Urban Poverty and Development in the 21st Century: Towards an Inclusive and Sustainable World, Oxfam GB Research Report, Oxfam, Oxford.

Chant, Sylvia (2007a) Gender, Cities and the Millennium Development Goals in the Global South, New Working Paper Series, Gender Institute, London School of Economics, London.

Chant, Sylvia (2007b) Gender, Generation and Poverty: Exploring the 'Feminisation of Poverty' in Africa, Asia and Latin America, Edward Elgar, Cheltenham, United Kingdom.

Chant, Sylvia (2011) 'Introduction', UN-HABITAT State of Women in Cities 2012/13, UN-HABITAT, Nairobi.

Doss, Cheryl. (2011). Gender Equality and Development. Background Paper Intrahoushohld Bargaining and Resource Allocation in Devloping Countries, World development report 2012. U.K.Department for International Development.

Eshetu G and Ruth Mace (2008), Fertility Decline Driven By Poverty: The Case Of Addis Ababa, Ethiopia,: Journal / Volume 40 / Issue 03 / May 2008, pp 339-358. Cambridge University Press 200

Gammage, Sarah (2010) 'Time Pressed and Time Poor:Unpaid Household Work in Guatemala', Feminist Economics, vol 16, no 3, pp79-112

Goldstein S., A. Goldstein and E Gurmu 2000, "Migration, gender and health survey in five regions of Ethiopia: 1998", Population Studies and Training Center, Brown University.

ILO (International Labour Organization), 2004, Gender and Migration in Arab States: the Case of Domestic Workers, ILO Regional Office for Arab States, Beirut.

________ (2002).Women and Men in the Informal Economy: A Statistical Picture, International Labour Office, Geneva.

________ (2011). Decent work for domestic workers, ILC.100/IV/1, International Labour Conference, 100th Session, 2011, International Labout Office, Geneva.

Mabala, Richard and Brian Cooksey (2008) Mapping adolescent vulnerability to HIV/AIDS in Dar es Salaam: results of an exploratory study, Joint Learning Initiative on Children and AIDS

Muzzin, Elisa, 2008. Urban Poverty in Ethiopia,A Multi-faceted and Spatial Perspective. The International Bank for Reconstruction and Development, The World Bank Washington, DC

Rakodi, Carole (2002) 'A Livelihood Approach - Conceptual Issues and Definitions', in Urban Livelihoods: A People-Centred Approach to Reducing Poverty, Carole Rakodi and Tony Lloyd-Jones (eds), Earthscan, London

Satterthwaite, David (2004) The under-estimation of urban poverty in low and middle-income nations, Poverty Reduction in Urban Areas Series, Working Paper 14, IIED, London

Tizita Mulugeta, 2013, Livelihood and Gender in Bati Woreda, North Woll: practices and resistance. Arctic University of Tromso.

Tolossa, Degefa (2010) 'Some realities of the urban poor and their food security situations: a case study of Berta Gibi and Gamachu Safar in the city of Addis Abeba, Ethiopia', Environment & Urbanization, vol 22, no 1, pp179-198.

UNFPA (2007) State of the World Population 2007: Unleashing the Potential of Urban Growth, United Nations Population Fund, New York

UN-HABITAT. 2007. Situation Analysis Of Informal Settlements In Addis Ababa. United Nations Human Settlements Programme.

UN-HABITAT. 2011. Condominium Housing in Ethiopia: The Integrated Housing Development Programme. United Nations Human Settlements Programme: Nairobi.

World Bank (2006), Vol II., Background Papers. Time to Move on? Internal Migration in Ethiopia and its Labor Market Implications

Yeshimebrat Mersha and others (2013), Factors Affecting Female Students' Academic Achievement at Bahir Dar UniversitCICE Hiroshima University, Journal of International Cooperation in Education, Vol.15 No.3 (pp.135-148)

# የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እና የድህነት ማስወገጃ እርምጃዎች በኢትዮጵያ

ፈለቀ ታደለ

## 1 መግቢያ

በዚህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የአረጋውያንና የአካል ጉዳተኞችን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በመዳሰስ፤ ለወደፊት መወሠድ ስላለባቸው የፖሊሲና የተግባር እንቅስቃሴዎች ምክረ-ኃሳብ ያቀርባል። ጥናታዊ ጽሑፉ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ተክፍሎ የቀረበ ሲሆን፤ በክፍል አንድ የጥናቱ ዓላማ፣ አሠራርና የመረጃ ምንጮችና ተብራርተዋል። በክፍል ሁለት የአረጋዊነትና አካል ጉዳተኝነት ትርጉሞች ተተንትነዋል። ክፍል ሶስት የአካል ጉዳተኞች ሁኔታ በኢትዮጵያ፣ የአካል ጉዳተኝነት ዓይነቶችና ዋና ዋና ምክንያቶች እና የአካል ጉዳተኝነትና ድህነት ቁርኝነት ተዳስሰውበታል። በክፍል አራት የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ አፈጻጸሞችና ምላሾቻቸውን ይመለከታል። እነዚህ የሕብረተሠብ ክፍሎች ያሉባቸውን ችግሮች ለመፍታትና እንደ የትምሕርትና የጤና አግለግሎት፣ የሥራ ዕድል፣ አመቺ መሠረተ-ልማትን በሚመለከት የተነደፉ ፕሮግራሞችና ምላሾች በዚህ ክፍል ተካትተዋል። በመጨረሻም ክፍል አምስት ወደፊት ምን መደረግ ይገባዋል የሚለውን ጉዳይ በመዳሠስ ምክረ-ኃሳብ ይሰነዝራል።

## 2 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- በኢትዮጵያ የአረጋውያንን እና የአካል ጉዳተኞችን ሁኔታ መዳሠስ፤
- የአረጋውያንን እና የአካል ጉዳተኞችን ችግሮች ለመቅረፍ የወጡ ፖሊሲና ፕሮግራሞች ያስገኙትን ምላሾችን መቃኘት፤
- የእነዚህን ምላሾች ጠንካራና ደካማ ጎኖች መገምገም፤
- ለወደፊት በመስኩ ለሚወጡ ፖሊሲዎችና ተግባራዊነታቸውን የሚረዱ ምክረ-ኃሳቦችን ማቅረብ ናቸው።

## 3 የጥናቱ አሠራር ዘዴዎችና የመረጃ ምንጮች

ጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ (Primary Sources) እና ሁለተኛ ደረጃ (Secondary Sources) የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የተካሄደ ነው። ቃለ-መጠይቅ ከመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ማሠባሠቢያ ዘዴዎች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ከተመረጡ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተወካዮች፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች

ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ከሚያካሂዱ ምሁራን ጋር ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል። በተጨማሪ በዚሁ የመጀመሪያ የመረጃ ምንጭ ስር በተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ከሚደረግላቸው አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ጋር ውይይት በማድረግና በዓይን በመመልከት መረጃ ተሠባስቧል።

በሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጮች ስር ጥናቱ በተለያዩ ድርጅቶችና የምርምር ተቋሞች (HAI, ACPF, Jimma University, MA students, CSA data (2007/ 2015)) የተሠሩ ጥናቶችን በዋና ማጣቀሻነት ተጠቅሟል። እንዲሁም የተለያዩ ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ ቁልፍ የሕግ እና የፖሊሲ ሠነዶችም ተጣቅሠዋል።

# 4 የአረጋዊነት እና አካል ጉዳተኝነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

## 4.1 የአረጋዊነት ትርጓሜ

አረጋዊነት አራት ዋና መሠረታዊ ኃሳቦችን በመንተራስ ሊተረጎም ይችላል። እነዚህም የዕድሜ ዘመን (chronology)፣ የአካል ብቃት (functional)፣ ማኅበራዊ ሁኔታ (social) እና አንፃራዊነት (subjective) ናቸው። ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ የተ.መ.ድ. (2007) እና የኢትዮጵያ መንግሥት የተቀበሉትን 60 ዓመት ዕድሜን "ጎልማሳና አዛውንት ሰዎች የሚለዩበት የዕድሜ መስመር" አድርገን እወስዳለን።

የተ.መ.ድ የጤና ድርጅት (WHO, 2004፡ 35) አረጋዊነትን "ከጉልምስና ቀጥሎ የሚመጣ፣ የማይቀለበስ አካላዊ አቅምን ቀስ በቀስ የሚቀንስ ተፈጥሯዊ የሥነ-አካል የለውጥ ሒደት" በማለት ይተረጉመዋል። በድርጅቱ ከተዘረዘሩት የዚህ የለውጥ ሒደት ውጤቶች መካከል አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ፣ እና ሌሎች ቀጣይ፣ እየተባባሱ የሚሄዱና የማይቀለበሱ (irreversible) የሠውነት አካላት ለውጦች ይገኙበታል። ድርጅቱ አረጋዊነት ወይም እርጅና በሽታ አለመሆኑን ያሠምርበታል። ነገር ግን በሒደት ተክለ-ሠውነት እና አካላዊ ድክመቶችን በማስከተል በሌሎች ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ሳቢያ ለተለያዩ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድልን እንደሚያሰፋ ያስገነዝባል።

## 4.2 የአካል ጉዳተኛነት ትርጓሜ

አካል ጉዳተኛነት ማለት "የሰው ልጅ በተፈጥሮው በተለመደ ሁኔታ ለመሥራት የሚችለውን ሥራ ለመሥራት አለመቻል ወይም ከመሥራት የሚገድብ ማንኛውም ዓይነት ጉዳት ነው" (WHO, 1976)። ኢትዮጵያ በ2010 ዓ.ም ያፀደቀችው የUNCRPD ስምምነት አንቀጽ 1 "አካል ጉዳተኛ ማለት የረጅም ጊዜ አካላዊ፣

የአዕምሮ፣ የማገናዘብ ዓቅም (intellectual) ወይም የስሜት ሕዋሳት ጉዳት ያለባቸውና ከሌሎች ጉዳዮች ጋር በመሆን ከሌሎች የሕብረተሠብ አካላት ጋር በእኩል ደረጃ ለመሳተፍ የማይችሉትን ያካትታል" ሲል ይተረጉመዋል፡፡

የ2007 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ከጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ መካከል 3,565,164 (4.8 ከመቶ) 60 እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል 532,063 ወይም 14.6% የሚሆኑት በከተሞች የሚኖሩ ሲሆኑ፤ የቀሩት 3,033,068 (85.1%) በገጠሩ የአገሪቱ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ይህ የአረጋውያን ብዛት በ2015 ዓ.ም ከጠቅላላው ሕዝብ ብዛት የ4.5% ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

**ምስል** 1፡- <u>በኢትዮጵያ የአረጋውያን ብዛት</u>፡፡




ምንጭ፡ HAI, 2004

የአረጋውያን አንፃራዊ ብዛት በ2050 ዓ.ም በእጥፍ እንደሚያድግ ይገመታል፡፡ ይህም 20% ከሚገመተው ከጊዜው የዓለም አማካይ አንፃራዊ የአረጋውያን ብዛት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ቢሆንም፤ ይደርሳል ተብሎ የሚገመተው የ9 ሚሊዮን አረጋውያን ቁጥር ቀላል አይሆንም፡፡

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ አረጋውያን ካለምንም የመንግሥት ድጋፍ እና ማኅበራዊ ዋስትና በድህነት ተኮራምተው ይኖራሉ፡፡ በአገሪቱ ከሚገኙት ከጠቅላላው አረጋውያን

መካከል ግማሽ ሚሊዮን ያህሉ ብቻ በወር በአማካይ 550 ብር የሚደርስ ቋሚ የጡረታ ዓበል ያገኛሉ፡፡

የአረጋውያን አንፃራዊ ብዛት መጨመር የማኅበራዊ አገልግሎት ድጋፍ በሚሠጡ ክፍሎች ላይ የተደራረቡ ጫናዎች የሚያሳድር ሲሆን፤ የእነዚህ አገልግሎትና ድጋፍ ሠጪ ክፍሎች አቅማቸው እንዲጎለብት ካልተደረገ በጫናዎቹ የተነሳ ለአረጋውያን የሚሠጧቸውን አገልግሎቶች በሚገባ ለመስጠት ሳይችሉ ይቀራሉ፡፡ በአረጋውያን ላይ አደጋ የሚደርሱና ተጋላጭነታቸውን ከሚያባብሱ ምክንያቶች መካከል የከተሜነት መስፋፋት፣ የወጣቶች ከአካባቢያቸው በስደት መልቀቅና የባሕላዊው የቤተሠብ ትስስርና ድጋፍ መላላት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ኸልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል በተባለ ግብረ-ሠናይ ድርጅት በእ.ኤ.አ በ2013 በተዘገበ አንድ አገር አቀፍ ጥናት የአረጋውያንን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በዝርዝር ለማመልከት ሞክሯል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚጠቁመው ከ1,070 ናሙና ሴትና ወንድ አረጋውያን መካከል፡-

- 79% የሚሆኑት በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ ይመገባሉ፤
- 78% የሚሆኑት የጤና ችግር አለባቸው፤
- 51% የሚሆኑት የቤተሠብ ድጋፍና እንክብካቤ አያገኙም
- 50% ገደማ የሚሆኑት ደግሞ የቤት ውስጥ ሥራና የልጅ ልጅ ማሳደግን የመሣሠሉትን ሥራዎች ካለ ምንም አጋዥ በራሳቸው ለማከናወን ይገደዳሉ፡፡

በጥናቱ 75% የሚሆኑት መላሾች ቢያንስ በአንድ የረጅም ጊዜ በሽታ የሚሠቃዩ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ አረጋውያኑን ከሚያጠቁ በሽታዎች መካከል የዓይን በሽታ (29.0%)፣ ሪህ (20.2%) እና የደም ግፊት (11.8%) የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዋና ዋና የጤና እክሎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም የሽንት ቱቦ ችግር፣ የመስማት (የጆሮ) ችግር እና የልብ በሽታም አረጋውያኑን ከሚያጠቁ የጤና ዕክሎች መካከል ተጠቅሰዋል (HAI, 2013፡ 24)፡፡

በዚህ ጥናት መሠረት የተመጣጠነና በቂ ምግብ አለማግኘት፣ የጤና እና የመጠለያ ችግሮች፣ አድልዎና መገለል የአረጋውያን የድህነት መገለጫዎች ሲሆኑ፤ እነዚህ ችግሮች በድህነታቸው ሳቢያ ይበልጥ የሚባባሱ ሆነው ተገኝተዋል (HAI, 2013፡ 43)፡፡

## 5 የአካል ጉዳተኞች ሁኔታ በኢትዮጵያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ሪፖርት (2007) እንደሚያመለክተው የአካል ጉዳተኝነት መጠን በኢትዮጵያ 1.09% (805,492) ይደርሳል። ነገር ግን ይህ አኃዝ ትክክለኛውን መጠን እንደማያመለክት ይታመናል። የሕዝብ ቆጠራው ጎዳና ተዳዳሪዎችን ያላካተተ (ከሶስት ጎዳና ተዳዳሪ ልጆች መካከል አንዱ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ ይገመታል) እና በባሕል ተፅዕኖና በግንዛቤ ማነስ ምክንያት ሰዎች አካል ጉዳተኞችና ቤተሠቦቻቸው አካል ጉዳተኝነታቸው እንዳይገልጹ ስለሚያግዷቸው (Mont, 2007) አኃዙ የአካል ጉዳተኞችን ብዛት በትክክል ያመለክታል ለማለት ያዳግታል። በተጨማሪም የ2007ቱ ቆጠራ የስጋ ደዌ፣ የሚጥል በሽታ (አዙሪት) እና የከፋ የአዕምሮ ችግር ካለባቸው በስተቀር የማገናዘብና የመማር ችግር ተጠቂዎችን ከአካል ጉዳተኞች ዝርዝር ውስጥ አላስገባም (WB/WHO, 2011)።

በሌላ በኩል የዓለም ባንክና የዓለም የጤና ድርጅት በጋራ ባወጡት የዓለም የአካል ጉዳተኞች ሪፖርት መሠረት በኢትዮጵያ 15 ሚሊዮን ሕጻናት፣ አዋቂዎችና አረጋውያን አካል ጉዳተኞች ይገኛሉ። ይህም ከጠቅላላው የሕዝብ ብዛት 17.6% ገደማ ይሆናል (WB/WHO, 2011)። ከፍተኛ ብዛት ያላቸው አካል ጉዳተኞች መሠረታዊ አገልግሎቶች ውስን በሆኑበት የገጠር አካባቢዎች ይኖራሉ። በኢትዮጵያ 95% የሚሆኑት አካል ጉዳተኞች በድህነት ይኖራሉ። አብዛኞዎቹ በቤተሠብ ዕርዳታና በልመና ኑሯቸውን ይገፋሉ።

አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ በመንግሥት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እና በዓለም ባንክ/የዓለም የጤና ድርጅት ሪፖርቶች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይታያል። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የአካል ጉዳተኞችን ብዛት ወደ 9 ሚሊዮን ሲገምት፤ የዓለም ባንክና የዓለም የጤና ድርጅት የጋራ ሪፖርት 15.8 ሚሊዮን ያደርሰዋል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን ሁኔታ ለመረዳት የሚረዳ በዕድሜ ክልል የተከፋፈለ ትንተና የያዙ ጥናቶች እጅግ ጥቂት በመሆናቸው የመረጃ ክፍተት ይታያል። ይህ ክፍተት ሁኔታዎችን በሚገባ በመረዳት ትክክለኛ ፖሊሲ ለመቅረጽና ችግር ፈቺ ፕሮግራሞችን ለመንደፍ ዕንቅፋት ሆኗል። በመሆኑም ወደፊት በሚደረጉ ብሔራዊ ቆጠራዎች ላይ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ጉዳዩን በስፋት ሊያስብበት ይገባል።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በቀጣዩ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ወቅት አካል ጉዳተኞችን የተመለከቱ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና እንዲጠናቀሩ ለመሥራት አቅዶ፤ የአካል ጉዳተኝነትን ትርጓሜ፣ የአካል ጉዳት ዓይነቶችንና ደረጃዎችን የያዘ ወጥ ሠነድ

ለማዘጋጀት ከ8 ተቋማት (ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዕምሮ ዕድገት ውሱንነት ያለባቸው ብሔራዊ ማኀበር፣ ከማየትና መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኀበር፣ ከኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማኀበር፣ ከኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኀበር፣ ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ቤሔራዊ ማኅበራት ፌዴሬሽን እና ከኒያ ፋውንዴሽን) የተውጣጣ የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራዎችን እንዲሠራ ለማድረግ መቻሉ ታውቋል። ይህም ሊበረታታ ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ አካል ጉዳተኞች የሚከተሉት ዋና ዋና ችግሮች ተጋርጠውባቸዋል፡-

- አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ በግለሠብ፣ በቤተሠብና በማኅበረሠብ ደረጃ የሠፈነው አሉታዊ አመለካከትና የግንዛቤ ዕጥረት፤
- የሕዝብ መገልገያ መሠረተ-ልማቶች ለአካል ጉዳተኞች አመቺ አለመሆናቸው፤
- የአካል ጉዳተኞችን መብት የሚያስከብር የሕግ፣ የአደረጃጀትና የአፈጻጸም ሁኔታዎች አለመሟላት፤
- ለአካል ጉዳተኞች የትምሕርትና የጤና አግልግሎቶች ተደራሽ አለመሆናቸው፤
- አካል ጉዳተኞች ያሉባቸውን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት በሥራ ዕድል፣ አነስተኛ ንግዶችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ መስኮች ላይ የተለየ ድጋፍና ዕድል አለማግኘታቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

**ምስል 2፡** <u>በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ብዛት በጉዳት ዓይነቶች</u>፡፡




*ምንጭ፡-* CSA, 2007፡፡

## 5.1 የአካል ጉዳተኝነት ዓይነቶችና ምክንያቶች

አይነስውርነት፣ በፖሊዮ ተጠቂነት የመጣ የአካል መጉደል፣ የመሥማት ችግር፣ የአዕምሮ ችግርና የሥጋ ደዌ ተጠቂነትን በኢትዮጵያ ዋና ዋና የአካል ጉዳት ዓይነቶች ናቸው፡፡ እርጅና ለአካል ጉዳተኛነት ያጋልጣል፡፡ ሲሶ የሚሆኑት የአካል ጉዳተኞች ዕድሜያቸው ከኃምሳ ዓመት መሆኑ ሲታይ በዕድሜ መግፋትና በአካል ጉዳተኝነት መካከል የምክንያትና ውጤት ግንኙነት እንዳለ ያመለክታል፡፡

በወሊድ ወቅትና ከወሊድ በኋላ የሚከሠቱ እንደ ተላላፊ በሽታዎች፣ በወሊድ ወቅት የሚያጋጥሙ የጤና ዕክሎች፣ በቂ ምግብ አለማግኘት፣ የተመጣጠነ ምግብ ዕጥረት፣ ጎጂ ባሕላዊ ድርጊቶች፣ ትክክለኛ የልጅ አስተዳደግና አያያዝ አለመኖር፣ የእርስ በርስ ጦርነትና በየጊዜው የሚከሠት ድርቅና ረሀብ ያሉ የአካል ጉዳትን የሚያስከትሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የአካል ጉዳተኝነትን በጊዜ ተገንዝቦ የመከላከል አቅም ውስን መሆን በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኛነትን ሁኔታ አስከፊ አድርጎታል፡፡

## 5.2 አካል ጉዳተኝነትና ድህነት

በአካል ጉዳተኝነትና በድህነት መካከል ጠንካራ ቁርኝት አለ። የሚከተለው ምስል ይህንን ቁርኝት በምክንያትና ውጤት ለማሳየት ይሞክራል።

**ምስል 3፡-** አካል ጉዳተኝነትና ድህነት ቁርኝት።




ምንጭ፡- ACPF, 2013

# 6 የድህነት ቅነሳ የፖሊሲና የፕሮግራም እርምጃዎች

## 6.1 አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን የሚመለከቱ የሕግ ማዕቀፎችና የፖሊሲ ዕርምጃዎች

በ1995 የጸደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራል ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 41(5) መንግሥት አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን "ለማቋቋምና ለመርዳት የአገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል" ሲል ደንግጓል።

## 6.2 ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች የመንግሥት ድጋፍ

የአካል ጉዳተኞችን የሥራ መብት በሚመለከት የወጣው አዋጅ (ቁጥር 568/2008) ማንኛውም የአካል ጉዳተኞችን የዕኩል የሥራ መብት የሚገድብ ሕግ፣ አሠራር፣ ልማድ፣ አመለካከት እና ሌሎች አድሏዊ ሁኔታዎችን ይሽራል። በተጨማሪም አሠሪዎች ለአካል ጉዳተኛ ሠራተኞቻቸው (በተለይም ለሴት አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች) አመቺ የሥራና የሥልጠና ሁኔታዎች እንዲያመቻቹ፣ ማንኛውንም ተገቢ

እርምጃዎችና ልዩ ድጋፍ እንዲሠጡ፣ እና ሥራቸውን ለማከናወንም ሆነ ሥልጠና ለመከታተል የሚረዳ ረዳት እንዲመድቡ ይደነግጋል፡፡

የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/2007 በበኩሉ ተገቢው ክህሎት ያላቸው አካል ጉዳተኞች በቅጥር፣ በዕድገት እና በሥራ ቅድሚያ እንዲሠጣቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ የሚሠራው በመንግሥት መ/ቤቶች ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የሠራተኞ ዓዋጅ ቁጥር 377/1994 እና የተሻሻለው ዓዋጅ ቁጥር 494/1999 ሠራተኛን በብሔር፣ በጾታ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ ተመሣሣይ ምክንያት በሠራተኛ መካከል ልዩነት ማድረግን ይከለክላል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሠን የወጣው ዓዋጅ (ቁጥር 691/2003) አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን የሙሉ ተሳትፎ እና ዕኩል የዕድል መብቶች እንዳላቸው ይገልጻል፡፡

የሕንፃ ግንባታ አዋጅ (ቁጥር 624/2009) ማንኛውም ሕንፃ በዲዛይንና በግንባታ ሂደት ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች አመቺ ሆኖ መሥራት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ፡-

- በሕዳር 24 ቀን 2002 የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ደንብ (ቁጥር 27/2002)፤
- የተ.መ.ድ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብት ስምምነትን (UN CRPD) ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀችበት አዋጅ (ቁጥር 676/2010)፤
- በሙያና ቴክኒክ ትምህርት ውስጥ የልዩ ፍላጎት ትምህርትን የሚደነግገው በ2009 የወጣው የማዕቀፍ ሠነድ፤
- ኢትዮጵያ ሁሉን የሕብረተሠብ ክፍል ያቀፈች አገር እንድትሆን ያለመው እና በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞችን የተሟላ የማቋቋም፤ የትምህርት፣ የክህሎት፣ የሥልጠናና ዕኩል የሥራ ዕድል፣ እንዲሁም በቤተሠቦቻቸው፣ በማሕበረሠቦቻቸውና በአገር ሕይወት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ፍላጎቶችን የዳሰሰው የብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች የድርጊት መርኃ-ግብር (2012-2021) የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ለማስከበር የወጡ የፖሊሲና ፕሮግራም እርምጃዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጡ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያፀደቀቻቸው የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች መብቶችን የሚያስጠብቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ብሔራዊ የድርጊት መርኃ-ግብር እና ፕሮግራሞችም ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል፡-

- የአረጋውያን የማድሪድ የድርጊት መርኃ-ግብር፤
- የአፍሪካ ማኅበራዊ ጥበቃ ማዕቀፍ (framwework)፤
- ብሔራዊ የማኅበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ፤
- ቀጥተኛ የማኅበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም (በከተማና በገጠር)፤
- ብሔራዊ የማኅበራዊ ጥበቃ 'ፕላትፎርም'፤
- የማኅበራዊ ድጋፍ ፈንድ መመሪያ፤
- በሶስት ክልሎች የተጀመረው የማኅበራዊ Cash Transform ፕሮግራም፤
- የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች አቅም ግንባታ ላይ የተሠማሩ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች፣ ሕብረቶችና ኮንፌዴሬሽኖች ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ይጠቀሳሉ።

## 6.3 የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

በኢትዮጵያ የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ለማስከበር፣ መሠረታዊ ማኅበራዊ ግልጋሎቶች የማግኘት መብታቸውን ለማስጠበቅ፣ ከማንኛውም አድልዎና ጥቃት እንዲጠበቁ ለማድረግ፣ በአገራዊ የልማት ሒደት ውስጥ ዕኩል ተሣትፎና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዱ መልካም የፖሊሲና ሕግ መሣሪያዎች ይገኛሉ። ነገር ግን እነዚህ የፖሊሲና የሕግ መሣሪያዎች በተገቢው ሁኔታ እየተተገበሩ ናቸው ለማለት አይቻልም።

ፖሊሲዎቹና ሕጎቹ በተገቢው ሁኔታ እንዳይተገበሩ ያደረጉ ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። የመጀመሪያው ምክንያት ብሔራዊ የተግባር ዕቅዱን አተገባበር ለማስተባበር በሕግ ኃላፊነት የተሠጠው የመንግሥት አካል የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በሁሉም ደረጃ ተካትቶ እንዲተገበር ለማድረግ የሚያስችለው አስገዳጅ የማስፈጸሚያ ሥልጣን፣ በቂ በጀትና በመስኩ የሠለጠነ የሠው ኃይል የሌለው መሆኑ ነው። በሁለተኛ ደረጃ አብዛኛዎቹ የመንግሥት መ/ቤቶች የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጣጣ ብቻ አድርገው መውሰዳቸው ሲሆን፤ ሦስተኛው እነዚህ መ/ቤቶች ለአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመድቡት በጀትና መዋቅር አለመኖሩ፤ ቢኖርም እጅግ አነስተኛ መሆኑ ነው።

የACPF (2013) እና የHAI (2013) የጥናት ግኝቶች እንደሚያሳዩት ምንም እንኳን አረጋውያንን እና አካል ጉዳተኞች በኢትዮጵያ ሕብረተሠብ ውስጥ ሙሉና ዕኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማስቻል ገና አያሌ ሥራዎች የሚቀሩ ቢሆንም፤ ከቅርብ

ዓመታት ወዲህ እንደ ማኅበራዊ ግልጋሎቶች (ትምሕርት፣ ጤና)፣ የመሠረተ-ልማት አውታሮች፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የማኅበረሠብ ግንዛቤ ማዳበር በመሳሰሉ በአንዳንድ ቁልፍ መስኮች መልካም መሻሻሎች ታይተዋል።

ምንም እንኳን በአመዛኙ በከተማ ቢሆንም፤ ትምህርት የሚያገኙ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ብዛት መጨመር አሳይቷል። በ2007 ዓ.ም 82,432 (47,876 ወንድ እና 33,998 ሴት) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የመደበኛ ትምህርት ተጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጧል። በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ 74,955 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል እንዲችሉ የማቴሪያልና የቁሳቁስ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል። ይሁን እንጂ በብሔራዊ ደረጃ የተደረገ ቅኝት እንደሚያመለክተው እጅግ ብዛት ያላቸው አካል ጉዳተኛ ልጆች/ሕጻናት ገና ማኅበረሠብ-አቀፍ ላይ የተመሠረተ የማቋቋሚያ ድጋፍ (community-based rehabilitation) አያገኙም (CSA, 2008)።

በኢትዮጵያ ለትምሕርት የደረሱ ሕጻናት ብዛት 15 ሚሊዮን ገደማ እንደሚሆንና ከእነዚህ መካከል 3 ሚሊዮን ያህሉ የልዩ ድጋፍ ትምሕርት የሚፈልጉ እንደሆኑ የትምሕርት ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። ነገር ግን ከእነዚህ የልዩ ድጋፍ ትምሕርት ከሚሹት ሕጻናት መካከል 1% የሚሆኑት ብቻ ዕድሉን እንደሚያገኙ አንድ ጥናት አሳይቷል (Asrat, 2010)።

አካል ጉዳተኞች በተገቢው ሁኔታ ትምህርት እንዲያገኙ እርምጃዎች በመወሠድ ላይ ይገኛሉ። ከሚወሠዱት እርምጃዎች መካከል ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት ክፍል ጋር በተፈረመው የጋራ መግባቢያ ሠነድ መሠረት የአካል ጉዳተኞች መብቶች በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካትተው እንዲሰጡ እና በጋራ ለመሥራት ታቅዶ በመተግበር ላይ ነው። በዚህ መሠረት የአካል ጉዳተኞች መብቶች፣ ኮንቬንሽንና ሌሎች አካል ጉዳተኞችን የተመለከቱ በአገራችን የወጡና አገራችን ተቀብላ ያፀደቀቻቸው ሕግጋት በሕግ በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካተው እንዲሰጡ ለማድረግ በ2006 ዓ.ም በተፈረመው የመግባቢያ ሠነድ መሠረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው 60 ወንድና 5 ሴት በድምሩ 65 የመንግሥት ተቋማት፣ የአካል ጉዳተኛ ማኅበራት፣ የማሕበረሠብ ተወካዮች፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት ክፍል ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም የተለያዩ የትምህርት ክፍሉ ተወካዮች በተገኙበት ሕግጋቱ በሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ስለመካተታቸው እና አካል ጉዳተኞችን አካቶ በመሥራት በኩል ያሉ ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች በሚሉ ርዕሶች ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ጠቃሚ ኃሳቦች በግብዓትነት እንዲወሰዱ ተድርጓል።

የመምሕራን የምልክት ቋንቋ ክህሎትና የልዩ ድጋፍ ሥልጠና እጥረት፣ የትምህርት ቤቶችና የትምህርት መርጃዎች በበቂ ሁኔታ አለማግኘት አካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርት እንዳያገኙ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መሆናቸውን ለዓለም "ትምሕርት ለሁሉም" የክትትል ሪፖርት (All Global monitoring report (2010)) የተዘጋጀው የኢትዮጵያ አካታች ትምሕርት (inclusive education) ሪፖርት በአጽንኦት ያመለክታል። በተጨማሪም ሪፖርቱ አካል ጉዳተኝነትን በህጻንነት በማወቅ ተገቢውን እንክብካቤና ዕርዳታ ለማድረግ የሚያስችል ፕሮግራም ከፍተኛ ክፍተት መኖሩን ይጠቁማል።

ሁሉን አቀፍ (inclusive) እና ልዩ ትምህርት ቤቶች ከገቡት አካል ጉዳተኛ ልጆች መካከል የተወሠኑት በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ከተወሠነ ክፍል በኋላ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ይገደዳሉ። ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ከሚገደዱባቸው ምክንያቶቸ መካከል፡-

- አብዛኛዎቹ ሁሉን አቀፍ ትምህርት ቤቶች አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከ5ኛ ክፍል በላይ ለማስተማር አለመቻላቸው (ምንም እንኳን የሙያ ሥልጠና ኮርሶች 10ኛ ክፍል ማጠናቀቅን በቅድመ-ሁኔታነት የሚጠይቁ ቢሆንም)፤
- አብዛኛዎቹ ት/ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ አለመሆናቸው፤
- የልዩ ድጋፍ ሥልጠና የወሰዱ መምህራን እጅግ በጣም ጥቂት መሆናቸው፤
- አብዛኛዎቹ ት/ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች የሚሆኑ መሣሪያዎች፤ ተስማሚ መማሪያ ክፍሎችና እንደ ብሬልና የድምጽ መቅጃ መሣሪያዎች የመሳሰሉ የትምህርት መርጃዎች የሌሏቸው መሆናቸው ይጠቀሳሉ።

ይህንን ችግር በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት (የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ) በተገኙበት የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ በሌሎች የትምህርት መስኮች ውስጥ ተካትቶ የሚሰጥበትን ሁኔታን ለማመቻቸት የሚያስችል ውይይት መካሄዱን በዚህ ጥናት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።

የእነዚህ ጥናቶች ውጤቶች በኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የትምህርት ፖሊሲን ዕውን ለማድረግ የልዩ ድጋፍ ትምህርት ስትራቴጂ በቂ ድጋፍ ያለው፣ የተጠናከረ፣ በሚገባ ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት መሆን እንደሚገባው ያመለክታሉ።

## 7 ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት

በኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞችን የማቋቋም እና የጤና አገልግሎት በ69% ጭማሪ አሳይቷል። አገልግሎቶቹን የማያገኙት አካል ጉዳተኞች ለምን እንደማያገኙ በሠጡት ምላሽ 28% የሚሆኑት ለአገልግሎቶቹ (በተለይም በሀኪም ለሚታዘዙላቸው መድኃኒቶች መግዣ) ለመክፈል አቅም የሌላቸው መሆኑን አመልክተዋል። በተጨማሪ 55% የሚሆኑት ያገኙት የጤና አገልግሎት በአካል ጉዳተኛ ልጆቻቸው ጤንነት ላይ እምብዛም ለውጥ አለማምጣቱን ገልጸዋል። የአካል ጉዳተኞች የአካል እንቅስቃሴ ማዕከላትን በቁሳቁስና የእንቅስቃሴ/የሠውነት ማጠንከሪያ መሣሪያዎች ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑ ተረጋግጧል።

አረጋውያንን በተመለከተ የሕክምና ዕርዳታ የሚሹባቸው የመጀመሪያ ሶስት የጤና ዕክሎች እንደቅደም ተከተላቸው የዓይን ችግር፣ (29%)፣ ሪህ (27.2%) እና የደም ግፊት (11.8%) ሆነው ተገኝተዋል። የፊኛ ችግር፣ የመስማት (የጆሮ) ችግር፣ እና የልብ ሕመም አረጋውያኑን ከሚያጠቁ የጤና ዕክሎች መካከል ይገኛሉ (HAI, 2013)።

የሥኳር በሽታ፣ ካንሠር፣ የልብ በሽታ፣ የዓይን ሞራ መሸፈን፣ የፊኛ ቱቦ ችግር፣ የሆድ ድርቀት፣ የጨጓራ በሽታ፣ የማየትና የመስማት ችግሮች እና የአዕምሮ ሕመም አረጋውያን የሚያጠቁ የማይተላለፉ በሽታዎች እንደሆኑ የቡድን ውይይት ተሣታፊዎችና ከጤና ተቋማት የመጡ ቁልፍ መረጃ ሠጪዎች ገልጸዋል። እነዚህ የማይተላለፉ በሽታዎች በስፔሻላይዝድ ባለሙያዎች ተከታታይ ክትትልና ሕክምና የሚጠይቁ ቢሆንም የዚህ ዓይነት ክትትል ለአብዛኛው አረጋዊ ተደራሽ እንዳልሆነ ያሠምሩበታል። በዕድሜ መግፋትና በዕርጅና ምክንያት በሚከሠቱ የጤና ዕክሎች ሕክምና ስፔሻላይዝድ ያደረገ ባለሙያ እጥረትም በስፋት ይታያል።

በሌላ በኩል ሕጻናትን ሊወገዱ ከሚችሉ አካል ጉዳተኛነት ለመጠበቅና የአካል ጉዳት ለደረሠባቸውም ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ መቅረጽና አሁን የሚታየውን ተደራሽ አለመሆን፣ የብቃት ችግር እና የሕክምና/ቁሳቁስ ዕጥረት እልባት መሥጠት ያስፈልጋል። በጤና አገልግሎት አሠጣጥ ውስጥ አረጋውያንን የሚያጠቁ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምናን ማጠናከር እና አረጋውያን የነፃ ህክምና አገልግሎት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ማመቻቸት በአረጋውያን የጤና አገልግሎች ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ዋና ዋና እርምጃዎች ናቸው።

## 8 የማኅበረሠብ ግንዛቤ ማጎልበት፣ መገለልና መድልዎን መቀነስ

የACPF ጥናት እንደሚያመለክተው ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው አካል ጉዳተኛ ልጆች በአካል ጉዳተኛነታቸው ሳቢያ በሌሎች ልጆችና አዋቂዎች አካላዊና ጥቃትና ዘለፋ እንደሚደርስባቸው አመልክቷል። እንዲሁም አያሌ አካል ጉዳተኛ ልጆች በደረሠባቸው ችግር ምክንያት በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ከመሳተፍ ታቅበዋል። ተንከባካቢዎች አካል ጉዳተኛ ልጆችን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባቸው የግንዛቤ ዕጥረት ያለባቸው መሆኑን የሚያመለክቱ ብዙ መረጃዎች ይታያሉ። የHAI (2012) ጥናት በበኩሉ በአረጋውያን ላይ የሚፈጸም ዘለፋና መብት ጥሠት መጨመሩን ሪፖርት አድርጓል። በተለይም የትዳር አጋሮቻቸው በሞት የተለዩባቸው አረጋውያን ሴቶች እንደ ቤትና መሬት የመሳሰሉ ንብረቶችን በተመለከተ ከፍተኛ የመብት ረገጣ እንደሚደርስባቸው ታውቋል። አረጋዊነትንና አካል ጉዳተኝነትን ከተመጽዋችነት ጋር ማያያዝ በስፋት የሚስተዋል ከመሆኑ ባሻገር የእነዚህን የሕብረተሠብ ክፍሎች አስተዋፅኦቸው ማኅበራዊ አገልግሎትን ፍትኃዊ ከማድረግና ሠብዓዊ መብት ማስከበርን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ እጅግ ውስን መሆኑ መገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም የአረጋውያንን እና የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማስከበር የሁሉም የልማት አካላት ተግባር በማድረግ በሕብረተሠቡ ውስጥ ያልተቋረጠ የግንዛቤ ማዳበር ሥራ ሊሠራ ይገባል።

በዚህ ረገድ አንዳንድ የተመዘገቡ ውጤቶች ይገኛሉ። ለምሳሌ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2006/7 ሪፖርት እንደሚጠቁመው 1,034 አዲስ የአረጋውያን ማኅበራት እንዲቋቋሙና 974 ነባር ማኅበራት እንዲጠናከሩ ድጋፍ ለመስጠት፣ እንዲሁም 1,017 አዲስ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት እንዲቋቋሙና 1,605 ነባር ማኅበራት እንዲጠናከሩ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ፤ በ6 ክልሎችና በሁለት ከተማ መስተዳደሮች (ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ድሬዳዋና አዲስ አበባ) 445 አዲስ የአረጋውያን ማኅበራት የተቋቋሙ ሲሆን፤ 905 ቀድሞ የተቋቋሙ የአረጋውያን ማኅበራትን የማጠናከር ድጋፍ ተሰጥቷል። እንዲሁም በ5 ክልሎችና በሁለቱ ከተማ መስተዳደሮች (ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ አፋር፣ ደ/ብ/ብ/ሕ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ) 299 አዲስ ማኅበራትን የማቋቋምና 492 ቀድሞ የተቋቋሙ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራትን የማጠናከር ድጋፍ ተሰጥቷል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በፌዴራል ደረጃ ለሚገኙ 30 የጤናና የፍትሕ ተቋማት የመረጃ ዴስክ ሠራተኞች የምልክት ቋንቋ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ፤ ሥልጠናውን ለመስጠት የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን በማከናወን ለ25 ሴቶችና ለ2 ወንዶች በድምሩ ለ27 በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ የጤና እና የፍትሕ ተቋማት የመረጃ ዴስክ ሠራተኞች እንዲሁም በክፍለ ከተማ ውስጥ የወንጀል

ምርመራ ሥራ ለሚሠሩ ፖሊሶች ለተከታታይ 22 ቀናት የምልክት ቋንቋ ሥልጠና ተሰጥቷል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማኅበራት በቁጥር መበራከትና ለባለ ድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫና ክህሎት ማሳደጊያ ተግባራት ቢከናወኑም አሁንም በአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰውን መድልዎና መገለል ለመግታት አልተቻለም። አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች እንደ ሕዝብ የትራንስፖርት አውታሮች፣ የመኖሪያ ቤቶች ፕሮጀክቶች እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመሳሰሉ መሠረተ-ልማቶች ለመጠቀም አሁንም ሲቸገሩ ይታያሉ። በዚህ ረገድ የወጡ ሕጎች በሚገባ በሥራ ላይ ሲውሉ አይታይም። የአረጋውያንን እና አካል ጉዳተኞችን መብቶችን ለማስከበር የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ለማስፈጸም እና በከተማ የቀላል ባቡር አገልግሎት፣ የከተማ አውቶቡስ እና የከተማ ልዩ ልዩ ሕንፃዎች ለመጠቀም እንዲችሉ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይልና ተከታታይ ክትትል ሲደረግ አይታይም።

**ምስል 4፦** <u>የከተማ ቀላል የባቡር መወጣጫ እና ኮንዶሚኒየም ፎቅ መወጣጫ ደረጃ</u>።



(ፎቶ፦ ኤርና ምንተስኖት) ይህ መወጣጫ ምን ያህል ለአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ተደራሽ ነው?

**ምስል 5፡-** የኮንዶሚኒየም ፎቅ መዳረሻ የብረት መወጣጫዎች።



(ፎቶ፡ ኤርና ምንተስኖት) ይህ ዲዛይን ምን ያህል የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን ዕውቀት አካትቷል?

**ምስል 6፡-** በአዲስ አበባ የቀላል ከተማ ባቡር መዳረሻ።



(ፎቶ ኤርና ምንተስኖት) መቼ ይሆን አሳንሰሩ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን በቂ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው?

የአካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን የሕንፃ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎችን የሠራተኛና ማኅበራዊ ሚኒስቴር ከከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ለመሥራት ታቅዶ፤ በ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት በጋራ ሊሠሩ የሚችሉ ተግባራትን በመለየት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። በዚህ መሠረት የአገራችን የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና ክትትል እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታን በመዳሰስ እና በሕንፃ አዋጁ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞ ስለመፈፀሙ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች (አፋር፣ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ክልሎች) በአካል በመገኘት ድጋፍና ክትትል የማድረግ፤ የሚገነቡ ሕንጻዎችና መንገዶች ለአረጋዊያንና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው እንዲሠሩና ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው በአዲስ አበባ ከተማ በአስሩም ክፍለ ከተሞች ለሚገኙ የግንባታ ተቆጣጣሪ መሃንዲሶች፣ አርክቴክቶች፣ ለሕንፃ ሹም ባለሙያዎች፣ ለሚመለከታቸው ቢሮዎች እና ባለድርሻ አካላት በአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽን እና በሕንፃ አዋጁ ዙሪያ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት 34 ወንድ 20 ሴት በድምሩ 54 ተሳታፊች እንዲሳተፉ የማድረግ ተግባራት በሠራተኛና ማኅበራዊ ሚኒስቴር መከናወናቸው የሚበረታታ ነው።

እንዲሁም በአገሪቱ የሚገነቡ ሕንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው ስለ መሠራታቸው፣ የሕንጻ ሹም በተሾመባቸው ከተሞች የሕንፃ አዋጁን፣ ደንብና መመሪያውን መሠረት በማድረግ የሕንፃዎች ግንባታ ፈቃድ ተሠጥቶ ሕንፃዎች እየተገነቡ መሆናቸውን እና ግንባታቸው የተጠናቀቁ ሕንፃዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ እየተሰጣቸው ለአገልግሎት እየዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የማረጋገጫ ዝርዝር በማዘጋጀት በሁሉም ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች በመገኘት ክትትልና ቁጥጥር መደረጉ ታውቋል። ይሁን እንጂ ይህ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።

አካል ጉዳተኞች በመደበኛው የሥራ ዘርፍ ቀጥሮ የማሠራት ባሕል እጅግ ዝቅ ያለ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ የመንግሥት ቢሮዎች ከግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ2009 የተደረገ ጥናት ኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞችን ከሥራ ገበያው በማግለል የሚደርስባት ኢኮኖሚያዊ ጉዳት በ667 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወይም ከጠቅላላው አገር አቀፍ ምርት (GDP) 5% እንደሚሆን ገምቷል (Sabastian, 2009)።

መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ወደ ዘርፉ (በተለይ በቤት ውስጥ የሚሠሩ የሙያ ሥራዎች) ለመግባት የሚያግዱ ምክንያቶች የሉበትም። የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) ያካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው 60% የሚሆኑት በሥራ ዕድሜ ክልል ያሉ አካል ጉዳተኞች ሥራ አጥ ሲሆኑ፤ ከእነዚህ መካከል ከአራቱ ሦስት እጅ የሚሆኑት በገጠር በግላቸው እንደ ግብርና፣ ከብት

ማርባትና የደን ልማት በመሳሰሉ ሥራዎች ተሠማርተው ይገኛሉ። ልመና፣ በዕምነት ተቋማትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚሠጡ ቋሚ ዕርዳታዎች በከተሞች አካል ጉዳተኞች የሚተዳደሩባቸው ዋና መንገዶች ናቸው።

አካል ጉዳተኞች ተደራጅተው ለራሳቸው ሥራ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ። አያሌ አገር-በቀልና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የክህሎት ሥልጠናና የመነሻ ካፒታል/ብድር በመስጠት እንዲሁም በገቢ ማመንጫ ሥራ ላይ ለመሠማራት እንዲችሉ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ጥረቱን ለመደገፍ ሲሞክሩ ይታያሉ። በዚህም በተፈጠረው ኢኮኖሚ ዕድል በርካታ አካል ጉዳተኞችና የአካል ጉዳተኛ ልጆች ቤተሠቦች ለመጠቀም ችለዋል።

በHAI (2012) ጥናት በናሙናነት ከተያዙት መካከል 47% የሚሆኑት አረጋውያን ኑሯቸው በዘመዶቻቸው ዕርዳታ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሲገልጹ፤ 19% የሚሆኑት ደግሞ በጡረታ የሚኖሩ መሆናቸውን አሳውቀዋል። በገጠር አካባቢዎች መሬታቸውን ኮንትራት መስጠት እና የእኩል ማሳረስ አረጋውያን ከሚተዳደሩባቸው መንገዶች 10% እና 7% ይይዛሉ። 4.5% ያህሉ ደግሞ በልመና ኑሯቸውን ይገፋሉ።

የአረጋውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሻሻል የሚከተሉት ተግባራት ተጠናክረው መካሄድ ይኖርባቸዋል፦

- የከተማና የገጠር ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች ለአረጋውያን ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት/ማሻሻል፤
- የኑሮ ሁኔታና ውድነትን ባገናዘበ መንገድ የጡረታ ክፍያን በየወቅቱ ማስተካከል፤
- የማኅበረሠብ አቀፍ ድጋፍ አገልግሎትን ማጠናከር ናቸው።

## 9 የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ማኅበራት መጠናከርና ድምፅ ማሰማት

ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራትን የማቋቋም ንቅናቄ ከተጀመረ አምስት አስርተ-ዓመታት ይጠጋል። ሁለቱ የመጀመሪያ ሁለቱ አንጋፋ በአካል ጉዳተኞች የጠቋቋሙ ማኅበራት የኢትዮጵያ አይነስውራን ማኅበር (1960 ዓ.ም) እና የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ማኅበር (1970) ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ የአረጋውያን ማኅበርም ተመስርቶ ከ50 በላይ ከሚሆኑ በመስኩ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተዳምሮ በአረጋውያን ላይ የሚደርሱትን የመብት ጥሠቶችና መብቶችን ለማስከበር ሠፊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። የእነዚህ ማኅበራት መስፋፋት በመስኮቹ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ

ድርጅቶች መብዛት ጋር ተዳምሮ የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ትኩረት እንዲያገኝ፣ በሕብረተሠቡ መካከል ግንዛቤ እንዲዳብር እና መብታቸው እንዲከበር የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ነገር ግን ማኅበራቱ ተጠናክረው የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ በሚገባ እንዳይወጡ ዕንቅፋት የሆኑባቸው ተግዳሮቶች ይታያሉ። ከእነዚህ መካከል በነፃ ተደራጅተው የመንቀሳቀስ መብታቸውን የሚጋፋው የ90:10 መመሪያ አንዱ ነው። ይህ ማኅበራቱ የበጀታቸውን ከ10% በላይ ከአገር ውጭ ማግኘት እንደማይችሉ በመንግሥት የወጣው መመሪያ ማኅበራቱ ከውጭ አገራትና ዓለም አቀፍ ምንጮች ገቢ የማሠባሠብ ዓቅማቸውን ገድቦታል። ከዚህ በተጨማሪ አገልግሎት በሚሠጡ እና በመብት ጉዳይ በሚሠሩ በጎ አደራጎት ድርጅቶች መካከል ትስስር (network) መመስረትን የሚያግደው መመሪያ ማኅበራቱ በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ትስስር እንዳይፈጥሩ በማገድ የማኅበራቱን እንቅስቃሴ ውስን አድርጎታል።

## 10 ምክረ ኃሳብ

የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን ሁኔታ ለማሻሻል በፖሊሲና የማስፈጸሚያ የሕግ ማዕቀፍ በማውጣት ረገድ በጎ ተግባራት ተከናውነዋል፤ የዕለት ችግሮቻቸውንም በመቅረፍና ሕይወታቸውን በማሻሻል ረገድም በጎ ጅምሮች ታይተዋል። ነገር ግን የወጡትን ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ በማድረግና በአፈፃፀም በኩል ገና ብዙ እንደሚቀር ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ይጠቁማሉ። መልካም የፖሊሲና የሕግ አፈፃፀም እንዲኖር በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ብቃት ያለው መዋቅር ያስፈልጋል። እንዲሁም አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችንና መብታቸውን በተመለከተ በሕብረተሠቡ መካከል የሠፈነው አሉታዊ አለመካከት የበለጠ ሊሻሻል ይገባዋል። ለዚህም የሁሉም ባለድርሻ አካላት ያላሰለሰ ጥረት ያስፈልጋል።

## ዋቢ መፃሕፍት

ACPF (2011) Children with disabilities in Ethiopia: The Hidden Reality. Addis Ababa: The African Child Policy Forum.

Asefa A. (2008) Status of victim assistance in Ethiopia report.[Presented to the standing committee on victim assistance and socio-economic reintegration in Geneva, 3 June 2008].MoLSA.

Central Statistics Agency (CSA) The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia: Results for Country Level, Statistical Report, Addis Ababa, C.S.A, August 2012.

Asrat A. (2010) Special needs education: a challenge that needs to be addressed. Walta Information Centre.Available at www.waltainfo.com/index. (accessed, 10.10.2015).

Central Statistics Agency (CSA) The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia: The Situation of Older People in Ethiopia, Addis Ababa, CSA, 2011.

Central Statistics Authority (2008). Summary and statistical Report of the 2007 population and housing census.FDRE population census commission. Addis Ababa.

Education for All Fast Track Initiative.(2010) 2009 Annual Report. Available at: www.educationfasttrack.org [accessed 08.10.15].

Lewis I. (2009) Reaching the marginalized: education for disabled people in Ethiopia and Rwanda [background paper prepared for the Education for All Global Monitoring Report 2010].

Federal Democratic Republic of Ethiopia (FDRE) Proclamation of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Federal NegaritGazeta, 1st Year, No.1, Addis Ababa, 1995.

HelpAge International (2014) Social Protection Policy and the Piloting of Social Cash Transfer Project in Tigray: Insights from Field Practice, (unpublished. PPP).

HelpAge International (2013) Vulnerability of Older People in Ethiopia : The Case of Oromia, Amhara and SNNP Regional States, Addis Ababa, Ethiopia.

HelpAge International (2013) The State of Health and Ageing in Ethiopia: A Survey of Health Needs and Challenges of Service Provisions. Addis Ababa, Ethiopia.

HelpAge International ( 2012) Vulnerability of Older People in Ethiopia : The Case of Oromia, Amhara and SNNP Regional States (Unpublished Report), Addis Ababa, Ethiopia.

HelpAge International (2010) The Living Condition and Vulnerability of Poor Urban People in Addis Ababa. Assessment Report. Addis Ababa, Ethiopia.

Japan International Cooperation Agency (2012) Country Profile on Disability: Federal Democratic Republic of Ethiopia ( unpublished Report). Addis Ababa, Ethiopia.

Kassahun Yibeltal (2013) Ethiopia Law and Policy Situation of Persons with Disabilities in Ethiopia, Unpublished PPP Report), Addis Ababa.www.dppc.govt.et ( accessed on 12 .10.15).

Ministry of Education (2010) Education Sector Development Program iV(2011-2014). Program Action Plan. Addis Ababa: Ministry of Education.

Ministry of Labour and Social Affairs (MoLSA) (2014) 2006/07 E.C Annual Performance Report (Amharic Version) MoLSA, Addis Ababa

Ministry of Labour and Social Affairs (MoLSA), National Plan of Action on Older People (1998-2007 E.C), MoLSA, Addis Ababa, 2006

Ministry of Labour and Social Affairs (MoLSA), National Plan of Action Disabilities (2012-2021), MoLSA, Addis Ababa, 2012.

Mont D. (2007) Measuring disability prevalence [social policy discussion paper no 0706]. World Bank.

Tirussew T. (2006) 'Overview of the Development of Inclusive Education in the Last Fifteen years in Ethiopia'. In Savolainen H., Matero M. and Kokkala H. (eds). (2006). When All means all: experiences in three African countries with EFA and children with disabilities.

World Bank and World Health Organization (2011).World Report on Disability, Washington, D.C.

World Health Organization (1976) Document A29/INFDOCI/1, Geneva, Switzerland.

World Health Organization (WHO) (2006) The Health of the People: The African Regional Health Report, Brazzaville, WHO Regional Office for Africa.

YetnebershNigussie (2013) General Overview of Disability in Ethiopia.PPP (Unpublished Report).

# የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው የልማት ሚና

ገብሬ ይንቲሶ፣ ደበበ ኃይለገብርኤል እና ከልክላቸው አሊ

## 1 መግቢያ

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች) ከ1950ዎቹ[1] ዓመታት ጀምሮ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች በተለያዩ ምክንያቶች በፍጥነት አድገዋል፣ ተበራክተዋልም፡፡ እየተባባሠ የመጣው የዓለም የፖለቲካ ቀውስ፣ ብዝሀ-ብሔር በሆኑ አገራት ውስጥ የተስፋፋው አለመረጋጋት፣ የግሎባላይዜሽን መፋጠን፣ የተባባሰ ሠብዓዊ ቀውስና መንግሥታት የሚጠበቅባቸውን ግልጋሎቶች ለዜጎቻቸው ለመስጠት አለመቻላቸውና በሕጋዊነት ለማስተዳደር አለመቻላቸው ለመያዶች መበራከት በምክንያቶች ከሚጠቀሱት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Fisher, 1997)፡፡

በመሆኑም መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚወሠዱ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የጋራ ዕርምጃዎች የፖለቲከኞችን፣ የልማት ወኪሎችን፣ የለጋሾችን፣ የማሕበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎችና የመሳሰሉትን ባለድርሻ አካላትን ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ ስበዋል፡፡ ባለፉት አስርተ ዓመታት መያዶች በአካባቢ ልማት ፕሮጀክቶች፣ በሠብዓዊ መብት ተሟጋችነት እና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በመሳሰሉ መስኮች በስፋትና በንቃት በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ እርስ በርሳቸው፣ ከመንግሥት እና ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች እና ለጋሾች ጋር በመተባበር ተልዕኳቸውን ለመወጣት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡

በኢትዮጵያም በ1970ዎቹ አጋማሽ ከደረሰው ሠብዓዊ ቀውስ ጀምሮ የሲቪል ሶሳይቲ ድርጅቶች በዕርዳታና መልሶ ማቋቋም፣ በአቅም ግንባታ፣ በአገልግሎት አቅርቦት፣ በመልካም አስተዳደር ተሟጋችነት እና በልማት ሥራዎች ድጋፍ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ የሲቪል ሶሳይቲ ድርጅቶች ከፍተኛ ኃብት በማንቀሳቀስ ቀዳሚ ለሆኑ ብሔራዊ የልማት ሥራዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ አንዳንድ በቅርብ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ከአንዳንድ የተወሠኑ ጥናቶች (ለምሳሌ Dessalegn et al, 2008) እና ወቅታዊ የድርጅቶች ሪፖርቶች በተጨማሪ የሲቪል ሶሳይቲ ድርጅቶችን የልማት አስተዋፅኦን የሚያሳዩ ሦስት ዋና ዋና ጥናቶች በአገር አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ተሠርተዋል (Abebe et al, 2004; Cerritelli et al, 2008; Gebre et al, 2014)፡፡

[1] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመታት በሙሉ (በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር) እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ናቸው፡፡

በ2004 የተደረገው የመጀመርያው ጥናት የአውሮፓ ሕብረትና እና የቀድሞው የኢትዮጵያ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር በጋራ ያሠሩት ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥናት ደግሞ ቀደም ሲል የተሠራውን እንዲያጠናክር ታስቦ በ2008 በአውሮፓ ኮሚሽን የሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ የተሠራ ነው።

ሦስተኛውና የመጨረሻው ጥናት በ2014 በአውሮፓ ኮሚሽን ሁለተኛው የሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ እና በሲቪል ሶሳይቲ የድጋፍ ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ የተካሄደ ነበር። ሦስቱ ጥናቶች የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በአገሪቱ ያላቸውን ስርጭት፣ ያንቀሳቀሱትን የኃብት መጠን፣ የሚተገብሯቸውን የፕሮጀክቶች ብዛት፣ ዓይነት እና ስርጭት ያሳያሉ። በዚህም ባለፉት አስርት ዓመታት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ከዕርዳታ አቅራቢነት እና የጎደለ ሞይነት ወደ ዋና የልማት አጋርነት ተሸጋግረዋል ማለት ይቻላል።

ይህ ጽሁፍ በ2014 በተደረገው የመጨረሻው መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ላይ በተሠራው የማፒንግ ማሻሻያ ጥናት ላይ የተመሠረተ ነው።[2] ሙሉ ጥናቱ ሠፊ ሆኖ የተለያዩ ዝርዝር ጉዳዮች የሚዳስስ ነው። የለጋሾች ፕሮፋይሎች፣ የደምብ ማዕቀፎች፣ ልማትና ዲሞክራሲ በጥናቱ የተሸፈኑ ጉዳዮች ሲሆኑ፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ዓይነቶች (ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች፣ የሕብረት ሥራ ማኅበሮች፣ ክልላዊ ድርጅቶች፣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ድርጅቶች፣ ራስ አገዝ ቡድኖች እና ሌሎች) በዝርዝር ተተንትነዋል። ይህ ጽሑፍ ግን ከዚህ ሠፊ ጥናት በመነሳት የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያተኩር ይሆናል። የትኩረት ጉዳዮቹም የሲቪል ሶሳይቲ ማኅበራት ፕሮጀክቶች ቴማቲክ/ሴክቶራል ሽፋን፤ ፕሮጀክቶቹ ለአገር ልማት ያበረከቱት አስተዋፅኦ፤ እና ድርጅቶቹ በሥራ ሂደት የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ናቸው።

በጥናቱ ሂደት ፋይል የተደረጉ ሠነዶች፣ የሥራ ሪፖርቶች፣ የፖሊሲ እና ሕግ ሠነዶች እንዲሁም የጥናት ሪፖርቶች ታይተዋል። በኢትዮጵያ በሚገኙት በዘጠኙም ክልላዊ መንግሥቶች እና በሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች ውስጥ በመንቀሳቀስ መረጃዎች ተሠብስበዋል። የሴክተር መሥርያ ቤት ተወካዮች በቃለ-መጠይቆች እና በክልላዊ የአስተያየት ዎርክሾፖች ላይ ተሳትፈዋል፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ደግሞ በቃለ-መጠይቆች፣ በቡድን ውይይቶች እና በክልላዊ ዎርክሾፖች ተሳትፈዋል። ከሁለቱም ወገን የተውጣጡ ተወካዮች የጥናቱ ውጤት በቀረበበት አገር አቀፍ ወርክሾፕ ላይ ተሳትፈው በአስተያየታቸው አዳብረውታል።

[2] ሁለተኛው የአውሮፓ ሕብረት የሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ እና የሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም ለመጀመርያው ጥናት ድጋፍ ቢያደርጉም በዚህ ጥናት ውስጥ ያሉ አስተያየቶች እና መደምደሚያዎች በሙሉ የጸሐፊዎቹ ናቸው።

ከዚህ አጭር መግቢያ እና መጨረሻ ላይ ከሚቀርበው አጭር የማጠቃለያ ኃሳቦች ውጭ ይህ ጽሑፍ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት:: እነዚህም የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ቁጥር፣ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት፣ እና የፕሮጀክቶቻቸው የሥራ መስኮች (thematic areas)፤ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ለቀዳሚ ብሔራዊ የልማት ዕቅዶች ያላቸው አስተዋፅኦ እና ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑትን[3] ለመድረስ ያደረጉት ጥረት እና የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በብዛት የሚያጋጥሟቸው የሕግ እና የኃብት እጥረት ማነቆዎች ናቸው::

# 2 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት፣ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት እና የሴክተር ሽፋን

## 2.1 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት

የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ የቅርብ ጊዜ መረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ 3,077 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች/መያዶች እንደሚገኙ ቢያመለክትም፤ ከክልል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የተሰባሰበው መረጃ ግን በዘጠኙ ክልሎች እና በሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች ውስጥ በፌዴራል ደረጃ የተመዘገቡ 1,364 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብቻ እንደሚንቀሳቀሱ ያሳያል:: በኤጀንሲው እና በክልል ቢሮዎቹ መረጃዎች መካከል የተፈጠረው ልዩነት በተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሠባል::

የመጀመሪያው ሊሆን የሚችለው ምክንያት በተለያዩ ክልሎች የልማት ሥራ ለመሥራት በኤጀንሲው የተመዘገቡ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በሁሉም ክልሎች በአንድ ጊዜ ፕሮጀክታቸውን ላይጀምሩ መቻላቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በፈንድ እጥረት እና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት ፕሮጀክቶቻቸውን እስከጭራሹ ሳይጀምሩ ሊቀሩ ይችላሉ የሚል ነው:: በሦስተኛነት የሚጠቀሠው ምክንያት ጥቂት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ለክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ሪፖርት ሳያደርጉ በዝቅተኛ የመንግሥት መዋቅር ላይ ካሉ አካላት ጋር ብቻ የሥራ ስምምነት በመፈራረም በክልሎች ውስጥ ሥራ ሊጀምሩ ይችላሉ የሚል ነው::

[3] "ለመድረስ አስቸጋሪ" የሚለው ኃሳብ በርቀት፣ በኃብት ክፍፍል ቸልተኝነት፣ ወይንም የፖሊሲ ትኩረት በማጣት ምክንያት የተገለሉ ሕዝቦች/ማሕበረሠቦች፣ ጉዳዮች፣ ቦታዎች ወይም ድርጅቶችን ያመለክታል::

**ሠንጠረዥ 1፡-** <u>የተመዘገቡና ሥራ ላይ ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ቁጥር በክልል (2014)</u>፡፡

| ተ.ቁ | ክልል | በኤጀንሲው የተመዘገቡ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች | በሥራ ላይ ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ | 1,406 | 241 |
| 2 | ደ/ብ/ብ/ሕ | 1,015 | 216 |
| 3 | አማራ | 994 | 188 |
| 4 | ትግራይ | 720 | 88 |
| 5 | አፋር | 452 | 51 |
| 6 | ሶማሌ | 404 | 57 |
| 7 | ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ | 390 | 45 |
| 8 | ሐረሪ | 360 | 33 |
| 9 | ጋምቤላ | 271 | 20 |
| 10 | አዲስ አበባ | 1838 | 364 |
| 11 | ድሬዳዋ | 468 | 61 |
| | ድምር | 3,077[4] | 1,364 |

*ምንጭ፡- ከኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ እና ከክልል ሴክተር ቢሮዎች የተጠናቀረ፡፡*

በሌላ በኩል አንዳንድ ድርጅቶችን ደጋግሞ በመቁጠር የተነሳ ከክልሎች የተገኘው የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ቁጥር በአገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ያሉትን የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ትክክለኛ ብዛት እንደማያንፀባርቅም ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

በ2014 ከአንድ ጊዜ በላይ የተቆጠሩ ድርጅቶች ተቀንሠው በተደረገ ዳግም ቆጠራ በሥራ ላይ ያሉት ድርጅቶች ብዛት ከ1,364 ወደ 870 ዝቅ ብሎ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ከዘጠኙ ክልሎች ውስጥ በስድስቱ ክልሎች (ትግራይ፣ አማራ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ እና ሐረሪ) እና ሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች ውስጥ የልማት ፕሮጀክቶችን የሚተገብሩ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት ከ2008 ዓ.ም. ጋር ሲነፃፀር ጭማሪ ያሳየ ከመሆኑ በላይ፤ ይህ ጭማሪ ከሶማሌ ክልል በቀር በሁሉም ክልሎች መጠኑ ከፍተኛ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና ጋምቤላ ክልሎች በሥራ ላይ ያሉ ድርጅቶች ብዛት መቀነስ አሳይቷል፡፡ የዚህን

[4] ይህ ቁጥር በክልሎች በሥራ ላይ ይገኛሉ ተብለው የሚጠበቁ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አጠቃላይ ድምር ሳይሆን በኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ተመዝግበው የሚገኙ ማኅበራትን ብዛት የሚያመለክት ነው፡፡

መቀነስ ትክክለኛ ምክንያት ለመረዳት ተጨማሪ የተሟላ ጥናት የሚያስፈልግ ቢሆንም፤ የእነዚህ ክልሎች የተወሰኑ ክፍሎች ከማዕከል በጣም የራቁ በመሆናቸው ሳቢያ የፕሮጀክትና አስተዳደራዊ ወጪዎችን በ70፡30 ቀመር የገደበው የመንግሥት መመሪያ ድርጅቶቹ ወደነዚህ ራቅ ያሉ አካባቢዎች ሄደው እንዲሠሩ ስላላበረታታቸው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አሳድሯል።

በሌላ በኩል የዓለም አቀፍ መያዶች ቁጥር በብዙ ክልሎች ጭማሪ ሲያሳይ፤ በጥቂቶች ቀንሷል። የዕምነት ተቋማት ድርጅቶች ቁጥር ደግሞ ከሶማሌና ሐረሪ ክልሎች እና ከድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር በስተቀር በሁሉም ክልሎች ቀንሷል። ለዓለም አቀፍ መያዶች ቁጥር መጨመር ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል ነባር ድርጅቶች ፕሮጀክቶቻቸውን ቀደም ሲል ወዳልደረሱባቸው ክልሎች እያስፋፉ መሆናቸው አንዱ ሲሆን፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ መረጃ በግልጽ እንደሚያሳየው[5] አዳዲስ መያዶች ወደአገር ውስጥ መግባታቸው እና ኤጀንሲው በሌሎች አገር በቀል ድርጅቶች አማካይነት በተዘዋዋሪ እንደአገናኝ የሚሠሩ ዓለም አቀፍ መያዶችን አሠራር የሚያግድ ፖሊሲ መከተሉም ይጠቀሳሉ[6] (TECS፣ 2013)።

በአጠቃላይ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በሥራ ላይ ካሉት 870 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች መካከል 381ዱ የውጭ መያዶች ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ 489 ደግሞ ዕድገታቸው በአንጻራዊ ደረጃ ዝቅተኛ የሆኑ አገር በቀል ድርጅቶች ናቸው። ሠንጠረዥ 2 እንደሚያመለክተው ከ2008 እስከ 2014 ባሉት ዓመታት የዕምነት ተቋማት የልማት ድርጅቶች ቁጥር መቀነስ ያሳየ ሲሆን ለዚህ መቀነስ የኃይማኖት ተቋማት የልማት ሥራቸውን ከመንፈሳዊ ሥራቸው እንዲለዩ ከሚደረግባቸው ጫና ጋር የተገናኘ መሆን አለመሆኑን በውል ለማወቅ ያዳግታል።

[5] ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ በተገኘ መረጃ መሠረት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ከሚገኙት 348 ዓለም አቀፍ መያዶች ውስጥ 137ቱ ከ2010 እስከ 2014 ባሉት ዓመታት (በ2010 ዓ.ም 77፣ በ2012 ዓ.ም. 26፣ በ2013 ዓ.ም 27 እና በ2014 ዓ.ም 7) የተመዘገቡ ናቸው።

[6] ከአገር ውስጥ መያዶች ጋር በመተባበር የሚሠሩ 'ኢንተርሜዲያሪ' መያዶች በቀጥታ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ እንዲሳተፉ ታዝዋል። ይህም የአገር ውስጥ አጋሮቻቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

**ሠንጠረዥ 2፡- የዓለም አቀፍ መያዶች እና የኃይማኖት ተቋማት ድርጅቶች ክልላዊ ስርጭት፡፡**

| ተ.ቁ. | ክልል | ዓለም አቀፍ መያዶች | | የኃይማኖት ተቋማት ድርጅቶች | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2008 ዓ.ም | 2014 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2014 ዓ.ም |
| 1. | ኦሮሚያ | 53 | 106 | 33 | 21 |
| 2. | ደ/ብ/ብ/ሕ | 28 | 51 | 17 | 10 |
| 3. | አማራ | 34 | 57 | 14 | 8 |
| 4. | ትግራይ | 14 | 21 | 8 | 6 |
| 5. | አፋር | 11 | 7 | 8 | 6 |
| 6. | ሶማሌ | 22 | 39 | 2 | 6 |
| 7. | ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ | 14 | 14 | 12 | 4 |
| 8. | ሐረሪ | 3 | 4 | 3 | 6 |
| 9. | ጋምቤላ | 7 | 6 | 10 | 4 |
| 10. | አዲስ አበባ | 44 | 61 | 38 | 27 |
| 11. | ድሬዳዋ | 5 | 15 | 1 | 7 |
| | ድምር | 235 | 381 | 146 | 105 |

ምንጭ፡- የ2008 የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ጥናት እና የክልል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች 2014፡፡

## 2.2 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ጂኦግራፊያዊ ስርጭት

በብዙ ክልሎች ውስጥ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ዞናዊ ስርጭት ያልተመጣጠነ ሆኖ ይታያል፡፡ ድርጅቶቹ በክልል ዋና ከተማዎች፣ ለመድረስ ቀላል በሆኑ አካባቢዎች (ለምሳሌ የተመቻቸ አውራ መንገድ የሚገባባቸው አካባቢዎች) እና ለአዲስ አበባ ወይም ለክልል ዋና ከተሞች ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች ቦታ ላይ የመከማቸት አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡ በአብዛኛዎቹ ክልሎች የሚታየው የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ያልተመጣጠነ ዞናዊ ስርጭት እንደሚከተለው ባጭሩ ቀርቧል፡፡ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ክልል 68% የሚሆኑት ድርጅቶች በሀዋሳ እና በአምስት ማዕከላዊ ዞኖች ማለትም ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ሀዲያ እና ጉራጌ ይገኛሉ፡፡ በኦሮሚያ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች (62.5%) ለአዲስ አበባ ቅርብ በሆኑት በሸዋ እና አርሲ ውስጥ በሚገኙ ሰባት ዞኖች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በርቀት የሚገኙት የወለጋ (ምዕራብ)፣ የሐረርጌ (ምስራቅ) እና ጉጂ (ደቡብ) አካባቢ ዞኖች በድርጅቶቹ ተመራጭ አይደሉም፡፡

በትግራይ ክልል የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በመቀሌ (ዋና ከተማዋ) እና በደቡባዊ ዞን ተከማችተው ይገኛሉ። በ33 ድርጅቶች ከተከናወኑ 105 ፕሮጀክቶች ውስጥ 45% የሚሆኑት መቀሌ ከተማ በምትገኝበት በደቡባዊ ትግራይ የሚገኙ ሲሆን፤ በርቀት የሚገኙት የምዕራባዊ ዞን ክፍሎች (ፀገዴ እና ሁመራ) በድርጅቶቹ እምብዛም ተመራጭ አይደሉም። በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ ክልል ከፍተኛው የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ጥርቅም (26.4%) በሠሜን ሸዋና እና ደቡብ ወሎ ዞኖች ሲገኝ፤ ዝቅተኛው የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ቁጥር የተመዘገበው ደግሞ በዋግ ህምራ እና በኦሮሚያ ዞኖች ውስጥ ሆኖ ተገኝቷል። በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ከሚገኙት 46 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች መካከል 26ቱ (56.5%) የሚንቀሳቀሱት በአሶሳ ዞን ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለት ዞኖች እያንዳንዳቸው 10 ድርጅቶች ብቻ አሏቸው። በሶማሌ ክልል አብዛኛዎቹ ድርጅቶች በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ የመንገድ ዳር ወረዳዎች ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። ማዕከላዊ ቦታው ጂግጂጋ የሆነው ፋፈን ዞን በሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ሲሆን፤ ከድሬዳዋ ወደ ጂቡቲ በሚወስደው አውራ መንገድ ላይ የሚገኘው ሲበን ዞን በሁለተኛነት ይከተላል።

በ2014 ዓ.ም የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በአምስት ክልሎች (ማለትም አዲስ አበባ፣ ኦሮሚያ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ፣ አማራ እና ትግራይ እንደ ቅደም ተከተላቸው) እንደተከማቹ አገር አቀፍ የስታቲስቲክስ መረጃ ያሳያል። ይህ ሁኔታ በ2008ም ተመሳሳይ የነበረ ሲሆን፤ አዳጊ ክልሎች (አፋር፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ እና ሶማሌ) አንገብጋቢ የልማት ሥራዎች ፍላጎት ቢኖራቸውም የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ክልላዊ ስርጭት አልተቀየረም። ለዚህ ያልተስተካከለ ስርጭት የተለያዩ ምክንያቶች ይሠጣሉ። ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አብዛኛዎቹ የመንግሥት ባለስልጣናት በሠጡት አስተያየት ርቀትና እና ተደራሽነት፣ ሰዎች ያሉባቸውን ችግሮች ለይቶ የመሥራት ቁርጠኝነት ማነስ፣ እና የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አመቺ ባልሆኑ ቦታዎች ለመንቀሳቀስ ያለመፈለግ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዎቹ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተወካዮች ላልተስተካከለው ስርጭት ምክንያቶቹ መንግሥት ያወጣቸው የሲቪል ማኅበራት ደንቦችና መመሪያዎች የፈጠሯቸው ማነቆዎች (በተለይ በ70፡30ው መመሪያ የሥልጠና እና የትራንስፖርት ወጪዎች እንደ አስተዳደራዊ ወጪዎች መቆጠራቸው)፣ ሩቅ እና አስቸጋሪ በሆኑ ቦታዎች ለመሥራት የፖሊሲ ማበረታቻ አለመኖር፣ በከተማ እና ማዕከላዊ በሆኑ ቦታዎች ጉልህ የልማት ፍላጎቶች መኖር፣ እና ሩቅ ቦታዎች ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በሚገባ ሊተገበሩ የሚችሉ መሆናቸውን ለለጋሾች ለማሳመንና ፈንድ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆናቸው ላይ አስምረው ያስረዳሉ።

## 2.3 የፕሮጀክቶች የሴክተር ስርጭት

የ2014 ጥናት በኢትዮጵያ በሲቪል ማኅበር ድርጅቶች እየተተገበሩ ያሉ 2,604 ፕሮጀክቶች እንዳሉ ያሳያል፡፡ ከክልል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በ2014 በአገሪቱ የተካሄዱ ፕሮጀክቶች በስምንት አቢይ መስኮች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ እነዚህም ጤናና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ትምሕርትና ሥልጠና፣ ሕጻናትና ሴቶች፣ ግብርናና የኑሮ ዋስትና ማረጋገጫ (livelihood)፣ የተቀናጀ ልማት፣ ውኃና የአካባቢ ንጽህና፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች ናቸው፡፡ እነዚህ መስኮች ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና ከሚሌኒየም የልማት ግቦች ጋር ይጣጣማሉ፡፡

የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በፕሮጀክቶቻቸው ቅድሚያ የሚሰጧቸው የልማት መስኮች ከክልል ክልል ይለያያሉ፡፡ በአዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና ሐረሪ ከፕሮጀክቶች ብዛት መገንዘብ እንደሚቻለው ሕጻናትና ሴቶች የአብዛኛዎቹን ድርጅቶች ትኩረት ስበዋል፡፡ በሶማሌ ክልል ምናልባት ክልሉ ለአካባቢያዊ ቀውስና የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ የተጋለጠ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ፕሮጀክቶች የኑሮ ዋስትና ማረጋገጫ ስትራቴጂዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ድርጅቶቹ ከመንግሥት የሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅርብ በመተባበር ይሠራሉ፡፡ ለምሳሌ የደ/ብ/ብ/ሕ ጤና ቢሮ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመቀነስ፣ በሥነ-ተዋልዶ ጤናና የቤተሠብ ምጣኔ፣ በግልና የአካባቢ ንጽህና፣ በወባ ቁጥጥር፣ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም፣ የሕጻናትን ሞት በመከላከልና በሕጻናት እንክብካቤ፣ በሥነ-አመጋገብ፣ በዓይን ሕክምና፣ በትሮፒካል በሽታዎች ቁጥጥር፣ በጤና ማኔጅመንት እና ኢንፎርሜንሽን ሲስተም፣ የጤና ሥርዓትን በማጎልበት፣ በሆስፒታል ሕንጻ ግንባታ እና የሆስፒታል አቅም ግንባታ ዙርያ ከ100 በላይ ከሚሆኑ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት እንደሚሠራ ሪፖርት አድርጓል፡፡

በመካሄድ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ላይ የተደረገ ዳሰሳ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አራት ዋና ዘርፎች ላይ እንደሚያተኩሩ ያሳያል፡፡ እነዚህም (እንደቅደም ተከተላቸው) ሴቶች እና ሕጻናት፣ ግብርና እና የኑሮ ዋስትና ማረጋገጫ፣ ጤና እና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ትምህርት እና ሥልጠና ናቸው፡፡ የ2008ቱ ጥናት ተመሳሳይ ቅደም ተከተልን ያሳየ ሲሆን፤ በ2014 አራቱም መስኮች በፕሮጀክቶች ቁጥር እና በበጀት ዕድገት አሳይተዋል፡፡ ከእነዚህ ምልከታዎች በመነሳት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በአገሪቱ ሠብዓዊ ልማት ላይ መልካም ሥራ እየሠሩና የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያበረከቱ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ጥረቶችም የአገሪቱን ሠብዓዊ ካፒታል (human capital) በማሻሻል ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ልማትን በማምጣት ረገድ የረጅም ጊዜ ተፅዕኖ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡-** እየተካሄዱ ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ፕሮጀክቶች ቴማቲክ ስርጭት፡፡

| | ክልል | የሴክተር/ቲማቲክ ስርጭት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሕጻናትና ሴቶች | ጤናና ኤችአይቪ/ኤድስ | ትምሕርት | ግብርና እና ላይቭሊሁድ | የተቀናጀ ልማት | ውሃና የአካባቢ ንጽህና | የአካባቢ ልማት | ሌሎች | ድምር |
| 1 | ደ/ብ/ብ/ሕ | 136 | 113 | 55 | 57 | 125 | 53 | 14 | 42 | 595 |
| 2 | ኦሮሚያ | 201 | 69 | 64 | 27 | 51 | 28 | 25 | 26 | 491 |
| 3 | አማራ | 126 | 119 | 62 | 73 | 40 | 35 | 21 | 27 | 503 |
| 4 | ትግራይ[7] | - | - | - | - | - | - | - | - | 99 |
| 5 | አፋር | 15 | 8 | 16 | 15 | 0 | 4 | 2 | 3 | 63 |
| 6 | ሶማሌ | 11 | 41 | 28 | 72 | 0 | 12 | 6 | 0 | 170 |
| 7 | ሐረሪ | 28 | 11 | 17 | 0 | 0 | 2 | 0 | 6 | 64 |
| 8 | ጋምቤላ | 7 | 13 | 9 | 6 | 5 | 4 | 1 | 5 | 50 |
| 9 | ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ | 19 | 15 | 15 | 6 | 9 | 1 | 0 | 3 | 68 |
| 10 | አዲስ አበባ | 219 | 51 | 28 | 0 | 86 | 3 | 2 | 1 | 390 |
| 11 | ድሬዳዋ | 22 | 26 | 26 | 6 | 8 | 4 | 1 | 18 | 111 |
| | **ድምር** | **784** | **466** | **320** | **262** | **324** | **146** | **72** | **131** | **2,604** |

ምንጭ፡- ከክልል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች መዝገቦች የተጠናቀረ (2014)፡፡

# 3 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ለልማት ያደረጉት አስተዋፅኦ

## 3.1 ኃብት ማሠባሠብ

**ከውጭ የተገኘ ኃብት-** የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ለብሔራዊ የልማት ግቦች ያደረጉትን አስተዋፅኦ ከውጭ ምንጮች ለማመንጨት ከቻሉት የገንዘብ መጠን እና በአገሪቱ ውስጥ ከሚተገብሯቸው የፕሮጀክቶች ብዛት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በ2008 ዓ.ም ድርጅቶቹ በ10 ቢሊዮን ብር በጀት 2,020 ፕሮጀክቶች እየተገበሩ የነበረ ሲሆን፤ ከታች ያለው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው በ2014 ዓ.ም 870 የሚሆኑ የሲቪል

[7] ከክልሉ የተገኘው መረጃ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ጵሮጀክቶች በሥራ መስኮች ተለያተው አልተቀመጡም፡፡

ማኅበር ድርጅቶች በ35.76 ቢሊዮን ብር በጀት ከ2,600 በላይ ፕሮጀክቶችን እያካሄዱ ነበር፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አኃዞች እንደሚያመለክቱት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የፕሮጀክቶች ብዛትና የማስፈጸሚያ በጀት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ዕድገት አሳይተዋል፡፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአማራና የደ/ብ/ብ/ሕ ክልሎች የተገኙ መረጃዎች የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የፕሮጀክት በጀቶች ተከታታይ ጭማሪ ማሳየታቸው ያመለክታሉ፡፡ በሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አማካኝነት ወደ አማራ ክልል የተንቀሳቀሰው አጠቃላይ ገንዘብ በ2012 ከነበረበት 5.3 ቢሊዮን ብር፤ በ2013 ወደ 6.4 ቢሊዮን ብር፤ እንዲሁም በ2014 ወደ 6.5 ቢሊዮን ብር አድጓል፡፡ በተመሳሳይ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በጀት በ2008 ከነበረበት 2.2 ቢሊዮን ብር በ2011 ወደ 4.3 ቢሊዮን ብር እና በ2014 ወደ 6.7 ቢሊዮን ብር አድጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 4፡-** <u>የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት፣ የፕሮጀክቶች ብዛትና የበጀት መጠን</u>፡፡

| ተ.ቁ. | ክልል | በሥራ ላይ ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት | የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ፕሮጀክቶች ብዛት | የበጀት መጠን (በብር) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ | 241 | 491 | 11,939,630,929 |
| 2 | ደ/ብ/ብ/ሕ | 214 | 595 | 6,755,640,155 |
| 3 | አማራ | 159 | 503 | 6,516,435,881 |
| 4 | አዲስ አበባ | 364 | 390 | 3,436,868,441 |
| 5 | ሶማሌ | 57 | 170 | 2,661,864,441 |
| 6 | ትግራይ | 98 | 99 | 2,278,057,291 |
| 7 | አፋር | 44 | 63 | 256,807,796 |
| 8 | ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ | 46 | 68 | 750,592,329 |
| 9 | ሐረሪ | 33 | 64 | 264,000,000 |
| 10 | ጋምቤላ | 26 | 50 | 901,530,206 |
| 11 | ድሬዳዋ | 61 | 111 | - |
| | **ድምር** | **1,343** | **2,604** | **35,761,427,762** |

ምንጭ፡- ከክልል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች መዝገቦች የተጠናቀረ (2014)፡፡

**<u>የአገር ውስጥ ኃብት፡-</u>** በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች እና በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ የኃብት ችግርን ለመቅረፍ የሞከሩ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አሉ፡፡ በአንዳንድ ክልሎች አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የገንዘብ ችግርን በበጎ ፈቃድ አግልግሎት እና በንቁ የአባላት ተሳትፎ ለማካካስ ሲሞክሩ ተስተውሏል፡፡ በዚህ ረገድ የትግራይ ወጣቶች ማኅበር ተሞክሮ በአርአያነት ሊጠቀስ ይገባዋል፡፡ ማኅበሩ 15,000

ወጣቶችን በማነሳሳት 6,700,000 ብር የሚገመት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል። በትግራይ ባሉ ብዙሀን ማኅበራት መካከል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እጅግ ስኬታማና ከማንኛውም የአገሪቱ አካባቢዎች የላቀ ሆኖ ታይቷል። ለዚህ ምክንያቱ በክልሉ ያለው ልዩ ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ሲሆን በተለይ በ1970ዎቹ እና በ1980ዎቹ በነበረው የርስ በርስ ጦርነት እና ከ1990ዎቹ በኋላ በነበረው የድሕረ-ጦርነት የመልሶ ግንባታ ሂደት የበጎ ፈቃድ ሥራ ዋና አስተዋፅኦ በማድረግ መልካም ልምድ በማስፈኑ እንደሆነ ይታመናል።

በሚገባ የተደራጁ እና ጥሩ ትስስር ያላቸው እንደ ትግራይ ልማት ማኅበር፣ የኦሮሞ ልማት ማኅበር እና አንዳንድ ኃይማኖታዊ ድርጅቶች ለዋና ተልዕኳቸው ማሳኪያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎችን ያካሂዳሉ። ነገር ግን ከመንግሥት መመሪያዎች ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሳ ለአብዛኛዎቹ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሠማራት የሚሞከር አማራጭ አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል (Gebre, 2011)። በተመሳሳይ ሁኔታ የአባላት መዋጮ፣ የግል ልገሳ እና ከሕዝብ መዋጮ ለመሰብሰብ መሞከር ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አስተማማኝ የገቢ ምንጭ አይደሉም።

## 3.2 የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ እና ለምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች ያላቸው አስተዋፅኦ

የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አመጧቸው የሚባሉት ተጨባጭ ስኬቶች ምንድን ናቸው ለሚለው ጥያቄ ድርጅቶቹ ከመንግሥት ድርጅቶች ጋር በአጋርነት በመሥራት ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ጂ.ቲ.ፒ.) እና ለምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች ጉልህ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን በ2014ቱ ጥናት ላይ የተሳተፉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተወካዮች ይናገራሉ። የማኅበራትና የመንግሥት ትብብር ውጤት ናቸው ከሚባሉት ተጨባጭ ውጤቶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የእናቶች እና ሕጻናት ሞት መቀነስ፣
- የወሊድ መከላከያ መጠቀምን በማስፋት የቤተሠብ ምጣኔን ማስፋፋት፣
- የልጃገረዶችን እና የሴቶች ጤንነትና ትምህርት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መዋጋት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ሳምባ ነቀርሳ እና ወባ መከላከል እና ቁጥጥር፣
- ወላጆቻቸውን ላጡ እና ለጥቃት የተጋለጡ ሕጻናት እና ለደሀ ቤተሠብ ሕጻናት ትምሕርት እንዲዳደረስ ማድረግ፣
- ምግብ በማቅረብ እና የአገር ውስጥ ጉዲፈቻ እንዲስፋፋ በማድረግ ሕጻናትን መንከባከብ፣

- ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ለኤድስ ሕሙማን እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣
- የውኃ እና የአካባቢ ጤንነት ጥበቃ አገልግሎትን ማስፋፋት፣
- የሴቶችን ገቢ እና የሴት ልጆች የትምሕርት ሁኔታን በማሻሻል የሴቶችን አቅም ማጎልበት፣
- በዝቅተኛ ዕርከን ላሉ የመንግሥት ተቋማት የአቅም ግንባታ ማድረግ።

የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በማሕበረሠብ ተሳትፎ፣ በማይክሮፋይናንስ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ፣ በአቅም ግንባታ፣ ውጤታማ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በማካሄድ እና እንደ ማሕበረሠብ ውይይት የመሳሰሉ አሳታፊ መንገዶችን በመከተል ለውጥ ማምጣታቸውን በአጽንዖት ይጠቅሳሉ። የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ፕሮጀክቶች ሕጻናትን፣ ሴቶችን፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አባወራዎች እና ማሕበረሠቦችን ጨምሮ በሚሊዮኖችን ለሚቆጠሩ ዜጎች ጥቅም መስጠታቸው ግልጽ ነው። አንድ ተጠቃሚ በተለያዩ ድርጅቶች በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች በተደጋጋሚ የመቆጠር ዕድሉ ከፍተኛ ስለሆነ የተጠቃሚዎችን ትክክለኛ ቁጥር ለማወቅ አዳጋች ቢሆንም በክልል የሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በአጋርነት ለተጫወቱት ተመስጋኝ ሚና እውቅና ይሰጣሉ።

## 3.3 ለመድረስ የሚያስቸግሩትን መድረስ

ለመድረስ የሚያስቸግሩ ጉዳዮችን፣ ሰዎችን፣ ድርጅቶችን እና አካባቢዎችን መድረስ እንደ የሲቪል ማኅበራት የድጋፍ ፕሮግራም (CSSP)፣ የሁለተኛው የአውሮፓ ሕብረት የሲቪል ማኅበራት ፈንድ፣ እና አውሮፓ ኢንስትሩመንት ፎር ዲሞክራሲ ኤንድ ሂዩማን ራይትስ (European Instrument for Democracy and Human Rights) ለመሳሰሉ ለጋሽ ድርጅቶች ፕሮግራሞች ዋነኛ ገጽታ ነው። ለመድረስ የሚያስቸግሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚባሉት ሩቅ በሆኑ ቦታዎች የሚኖሩ እና በማሕበራዊ ሁኔታዎች፣ በሙያ፣ በጤና፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳተኝነት ወ.ዘ.ተ. የተገለሉ ማሕበረሠቦችን ይጨምራል። አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አንዳንድ የተገለሉ የማሕበረሠብ ክፍሎች ፍላጎቶች እና ችግሮች ላይ ለመሥራት ሲሞክሩ ይታያሉ። ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑ የሕብረተሠብ ክፍሎች ላሉባቸው ችግሮች ምላሽ ለመስጠት ገና ብዙ መሠራት ቢኖርበትም፤ ከላይ በተጠቀሱት ለጋሽ ፕሮግራሞች ጥረት ጥቂት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ያደረጓቸው ሥራዎች ተገቢው ዕውቅና ሊሠጣቸው ይገባል።

በለጋሽ ፕሮግራሞች እና በሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የተደረጉ ድጋፎች ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑ የሕብረተሠብ ክፍሎች አካል የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን በማደራጀትና

ከአጋሮች ጋር በመተባበር ባህላዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት እንዲጥሩ አበረታትተዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በሀዲያ ዞን የሚገኙ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች *ሃሮ ቴሳ* (አዲስ ተስፋ) የሚባል የአካባቢው ሰዎች አባል የሆኑበት ድርጅት አቋቁመዋል፡፡ በትግራይ ኦቲስቲክ ልጆች ያሏቸው እናቶች ከኦቲዝም ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቋቋም ተደራጅተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አሁንም ትግራይ ውስጥ በስጋ ደዌ በሽታ የተጠቁ ሰዎች ትኩረቱን በሽታው ያለባቸው ሰዎች ላይ ያደረገ ፕሮጀክት የሚያካሂድ ድርጅት አቋቁመዋል፡፡ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በአካል ጉዳተኞች እና በአረጋውያን የተቋቋሙ ብዙ ማኅበሮች የሚገኙ ቢሆንም በገንዘብና በማቴሪያል እጥረት እና በአቅም ችግር የተነሳ ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት ሲቸገሩ ይታያሉ (Gebre et al, 2013)፡፡

በብዙ የደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ዞኖች ማሕበራዊ ማግለል በጣም የተስፋፋ ነው (Freeman and Pankhurst, 2003)፡፡ ማንጃ እና ማና (በዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ጎፋ እና አንዳንድ የወላይታ ክፍሎች)፣ ፉጋ (በሀዲያ፣ ከምባታ፣ እና ጉራጌ)፣ እና ሀድቾ (በሲዳማ) ማኅበረሠቦች በክልሉ መገለል ከሚያጋጥማቸው የሕብረተሠብ ክፍሎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን ለመድረስ የሚያስቸግሩ ሰዎች ቁጥር፣ በእነርሱ ላይ እየሠሩ ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ብዛት፣ እየተሠሩ ያሉ የሥራ ዓይነቶች፣ እና እነዚህ ሥራዎች እያመጧቸው ያሉትን ለውጦች ለመረዳት የሚያስችል በቂ መረጃ ባለመኖሩ ይህንን የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት ተጨማሪ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 3.4 አዳዲስ አሠራሮችን ማስተዋወቅ

የሥራ ብቃትን እና ውጤታማነትን፣ ወጪ ቅነሳን፣ የባለቤትነት መንፈስን ለማዳበርና እና የፕሮጀክቶችን ዘላቂነት ለማረጋገጥ የተለያዩ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የተለያዩ አዳዲስ ስትራቴጂዎችን አምጥተዋል፡፡ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ኃሳቦችን ወደ ተጨባጭ ሥራዎች ለመቀየር እንዲችሉ ለጋሾች የተለያዩ አዳዲስ አሠራሮችን በማስተዋወቅ እና ድጋፍ በመስጠት የተጫወቱት ሚና ወሳኝ ነበር፡፡ ይህንን በሚመለከት ቀጥሎ የተመለከቱት አምስት ተሞክሮዎች ችግሮችን በመፍታትና ለልማት ዓላማዎች አስተዋፅኦ በማድረግ ረገድ የአዳዲስ የአሠራሮችን ጠቀሜታ ያሳያሉ፡፡

የመጀመርያው ተሞክሮ በደ/ብ/ብ/ሕ እና በኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም በተወሰነ ደረጃም በሌሎች ክልሎች ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የንግድ ትስስር (value chain) ያለበት የሽቀጥ አመራረት ዘዴን በማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ተጠቃሚዎቹ የሚሠሩትን ሥራ ለመለየት፣ ምርት ለማምረት እና ያመረቱትን ወደ

ገበያ በመውሰድ ለጅምላ ነጋዴዎች ወይም በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እንዲችሉ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸዋል። የንግድ ትስስር ሽቀጥ አመራረት ዘዴ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አምራቾች ምርታቸውን በቀጥታ ለተጠቃሚዎች እንዲያቀርቡ በማስቻል ወደ አትራፊ ደላላ ኪስ የሚገባውን ገቢ እንዲያድኑ ድጋፍ የሚደረግበት ሁሉን አቀፍ የአሠራር ሂደት ነው። ሁለተኛው ተሞክሮ በአርብቶ አደር አካባቢ የሚሠሩ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተንቀሳቃሽ የትምሕርትና የጤና እንክብካቤ አገልግሎትን የሚሰጡበት ሲሆን፤ ይህ አሠራር ከቦታ ቦታ ዝውውር ላይ ለተመሠረተው የአርብቶ አደር ማሕበረሠቦች አኗኗር ዘይቤ ላይ ጣልቃ ሳይገቡ የጤናና የትምሕርት አገልግሎት እንዲያቀርቡ አስችሏቸዋል።

ሦስተኛው ተሞክሮ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ያሉ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የዕደ ጥበብ ሙያተኞች የሚያጋጥማቸውን መገለል እና የሴቶች ግርዛትን በኢኮኖሚ በማጎልበት፣ በትምሕርት፣ በማሕበረሠብ ውይይትና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ለመቀነስ የቻሉበት ነው። አራተኛው ምሳሌ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ውስጥ ያሉ ሰባት ዓለም አቀፍ መያዶች በአንድ ላይ በመሆን የሚሠሩት ሲሆን፤ የሥራቸው ዋና ትኩረት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ቢሆንም የግብርና ልማትን፣ የተፈጥሮ ኃብት አስተዳደርን፣ ሥነ-ምግብን፣ ሥነ-ጾታን፣ የአቅም ግንባታን፣ የአደጋ ስጋት ቁጥጥርን እና የንግድ ትስስር ልማትን በውጤታማነት ያቀናጀ አሠራር ለመፍጠር ችለዋል። አምስተኛው ተሞክሮ በትግራይ ክልል በድህረ-ጦርነት መልሶ ግንባታ ወቅት የትግራይ ልማት ማኅበር አራት ባለድርሻ አካላትን ማለትም ማሕበረሠቡን፣ መንግሥትን፣ ዲያስፖራውን እና ማኅበሩን በማስተባበር “ከዳስ ወደ ክላስ” የተባለ የትምህርት ቤት ግንባታ በመጀመር በክልሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ትምሕርት ቤቶች እንዲገነቡ አድርጓል። በዚህ ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ ባለድርሻ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

## 4 ተግዳሮቶች እና ውስንነቶች

በሁሉም ክልሎች የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ያጋጠሟቸው ችግሮች ከሞላ ጎደል ተመሳሳዮች ሲሆኑ ሲጠቃለሉም ከሕግና እና መዋቅራዊ ጉዳዮች፣ ከኃብት ማሠባሠብ፣ ከለጋሾች ተደራሽነት እና ፍላጎት፣ ከመንግሥት ተቋማት ጋር ያለ ደካማ ትብብር፣ ከራሳቸው የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የውስጥ አቅም ማነስ እና ከክልሎች የመሠረተ-ልማት አለመዳበር ጋር የተያያዙ ናቸው።

## 4.1 የደምብ (ሬጉላቶሪ) ችግሮች

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማኅበራትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 621/2009 ሥራ ላይ መዋል ለሲቪል ማኅበር ድርጅቶች መልካም ዕድሎችን የማምጣቱን ያህል ቀላል የማይባሉ ችግሮችንም ማስከተሉ ይገለጻል። በበጎ ጎኑ አዋጁ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ሕጋዊ፣ ተጠያቂነት ያላቸው፣ እና ግልጽ እንዲሆኑ በማድረግ በዘርፉ ለረጅም ጊዜ የነበረውን ጉድለት እንዲስተካከል የረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ሌሎች ተግዳሮቶችን ፈጥሯል። ከአዋጁ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች ከዚህ በታች አጠር ብለው ቀርበዋል።

**የ70፡30 መመርያ፡-** የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ከበጀታቸው ቢያንስ 70% የሚሆነውን ለፕሮግራም ሥራዎች እና ቀሪውን 30% ደግሞ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲያውሉ ይጠበቅባቸዋል። ብዙ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተወካዮች መመሪያው ለሥራ ማስኬጃ 30% ማውጣት የማያስፈልጋቸውን ጠንካራ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን የጠቀመ ሲሆን፤ በአንፃሩ አነስተኛ የሆኑትንና ውስን ኃብት ያላቸው ማኅበራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያደርግ አድሎአዊ ነው ይላሉ። በተጨማሪም አንዳንድ በፕሮግራም ሥራነት መታቀፍ የነበረባቸው ሥራዎች በአስተዳደር ሥራነት በመቆጠራቸው እንደ ጥናትና ምርምር፣ ክትትልና ግምገማ፣ ሥልጠና፣ የትብብር ሥራን የመሳሰሉትን ከማዳከሙ በላይ ርቀት ባላቸው ስፍራዎች እና ለመድረስ በሚያስቸግሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን ለመጀመር ያለውን ተነሳሽነትን በማቀዝቀዝ አፍራሽ ሚና ይኖረዋል በማለት ይገልጻሉ[8] (በተጨማሪም Long & Regassa፣ 2013; Kassahun, 2013 ይመልከቱ)።

**የ90፡10 መመርያ፡-** "የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች" እና "የኢትዮጵያ ማኅበራት" በመባል የተለዩት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ከገቢያቸው ከ10% በላይ ከውጭ ምንጮች መቀበል እንደማይችሉ መመሪያው ይደነግጋል። መረጃ ሠጪዎች እንደሚገልጹት ይህ መመሪያ በመብት ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን አቅም ወስኗል። የክልል ሕጎች ከኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ የ90፡10 መመርያ ጋር እንዲጣጣሙ ሲባል በክልል የተመዘገቡ ድርጅቶች ከገቢያቸው ከ10% በላይ ከውጭ ምንጮች መቀበል አይችሉም። ቢሆንም አንዳንድ ለጋሽ ድርጅቶች (በዋናነት የአውሮፓ ሕብረት እና የዓለም ባንክ) ከመንግሥት ጋር ተደራድረው አንዳንድ ከውጭ የሚገኙ ገንዘቦች እንደ አገር ውስጥ

---

[8]አካል ጉዳተኝነትና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በመሳሰሉ የተወሰኑ መስኮች ላይ ለሚሠሩ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች አንዳንድ የአስተዳደር ወጪዎች የፕሮግራም ወጪዎች ተብለው እንዲመደቡ የ70፡30 መመርያው መከለሱን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

ምንጭ እንዲቆጠሩ በመደረጉ የተወሰኑ በመብት ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ድርጅቶች እነዚህን ገንዘብ በመቀበል በመብትና በማጎልበት (ኢምፓወርመንት) ላይ ለመሥራት ችለዋል፡፡

***ገቢ ማመንጨት፡-*** የገቢ ማመንጨት ሥራዎች በቀጥታ ከሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ዋና ተልዕኮ ጋር የተያያዘ እንዲሆንና የገቢ ማመንጫው ሥራ አስተዳደር ደግሞ ከበጎ አድራጎት ሥራው መለየት እንዳለበት የሚያስገድደው መመሪያ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የገቢ ማመንጫ ሥራዎች እንዳይሠሩ ወይም ለመሥራት እንዳያስቡ አድርጓቸዋል፡፡ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት የግሉ ዘርፍ የማይጠየቀውን ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲያሟሉ መደረጉ መመሪያው አድሎአዊ ነው አስብሏል፡፡ በመሆኑም በገቢ ማመንጫ ሥራዎች በመሳተፍ ከአገር ውስጥ ምንጮች ገንዘብ የማሰባሰቡ ተስፋ ለአብዛኛዎቹ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የጨፈገገ ሆኗል፡፡

***መዋቅራዊ ችግሮች፡-*** የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን ለመመዝገብ እና ለመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት የፌዴራል መንግሥት አካል የሆነው የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ በክልሎች የራሱ መዋቅርም ሆነ ተወካዮች የሌሉት በመሆኑ በክልል ለሚገኙ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተደራሽ አይደለም፡፡ ለአዲስ ምዝገባ ለማካሄድ፣ ፈቃድ ለማሳደስ፣ እና ለሌሎች ጉዳዮች የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ወደ አዲስ አበባ መጓዝ ያለባቸው ሲሆን ለጉዞ የሚያወጡት ወጪ እንደ አስተዳደራዊ ወጪ ይቆጠራል፡፡ ኤጀንሲው የፌዴራል ተቋም እንደመሆኑ ክልላዊ ቅርንጫፍ ቢሮዎችን መክፈት አስቸጋሪ ቢሆንም የክልል የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የሚፈልጓቸውን አንዳንድ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ስልጣን ቢሰጣቸው ችግሩ ሊቀረፍ ይችላል፡፡

የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ከተዛማጅ የሴክተር መስርያ ቤቶች ጋር የትብብር ስምምነት እንዲሁም ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ጋር የሥራ ስምምነቶች እንዲፈራረሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ፕሮጀክቶቹን መፈጸማቸውን ለመከታተል የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ነው፡፡ ነገር ግን በብዙ ክልሎች ባሉ የሴክተር መሥርያ ቤቶች ውስጥ ያሉ መረጃ ሰጭዎች እንደሚገልጹት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በዝርዝር ተረድቶ ግምገማ እና ቁጥጥር ለማድረግ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የሙያዊ ዕውቀት ችግር አለባቸው፡፡ እንዲሁም ሁሉንም ፕሮጀክቶች ለመከታተልም የሚበቃ የሰው ኃይልም የላቸውም፡፡ በመሆኑም የሴክተር መሥርያ ቤቶች ዕውቀቱና ለሥራውም የሚበቃ የሰው ኃይል ስላላቸው የሥራ ስምምነቶቹን እንዲፈራረሙ ሥልጣን ሊሠጣቸው ይገባል የሚል አስተያየት በስፋት ይሰነዘራል፡፡

## 4.2 ውጥረት ያለበት ግንኙነት

አዋጅ ቁጥር 621/2009 ሥራ ላይ ከዋለ ጀምሮ በመንግሥት እና በብዙ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች መካከል ያለው ግንኙነት በውጥረት የተሞላ ሆኗል፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት የሁለቱም ወገን ተወካዮች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ቅሬታ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተወካዮች የመንግሥት ተወካዮች ለድርጅቶቻቸው አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ አንዳንድ ባለስልጣናት የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን በጥቅሉ ኪራይ ሰብሳቢ እና የኒዮሊበራል አስተሳሰብ አራማጅ ናቸው በማለት የሚጠቀሙት አገላለጽ ድርጅቶቹ በሕዝብ ፊት ያላቸውን ገጽታ እንደጎዳ በጥናቱ ወቅት በተሳታፊዎች ሪፖርት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም መንግሥት ለብዙሀን ማኅበራትና ለልማት ማኅበራት የሚያደርገውን የተለየ ድጋፍ አድሎአዊ ነው በማለት አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተወካዮች ቅሬታቸውን ይገልጻሉ (Ayalew and Ezana, 2011 ይመልከቱ)፡፡ በአጠቃላይ በአንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በኩል የመንግሥት ባለሥልጣናትን ተፈልገው የማይገኙ እና የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ጉዳዮች የማያሳስባቸው ቢሮክራሲዎች አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ ይታያል፡፡ ነገር ግን ሁሉም መላሾች በዚህ አመለካከት አይስማሙም፡፡ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅት መሪዎች ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ጠንካራ የትብብር ግንኙነት እንዳላቸው ያሠምራሉ፡፡

በሌላ በኩል ከሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ጋር በቅርበት የሚሠሩ አንዳንድ የመንግሥት ተቋማት ተወካዮች የሚያሳስቧቸው ጉዳዮች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ራሳቸው እናደርጋቸዋለን ያሏቸውን ሥራዎች አይፈጽሙም፤ ከመንግሥት አጋሮች ጋር የፈረሟቸውን ስምምነቶች እና ሥራ ላይ ያሉትን መመርያዎች እና ደምቦች አያከብሩም ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ ነካ ነካ አርገው በሚሄዷቸው ነገሮች ላይ ያተኩራሉ፣ የፕሮጀክት ጊዜያቸው ካለቀ በኋላ ንብረቶችን ለማስረከብ ያቅማማሉ፣ መነሻ ጥናት (ቤዝላይን) ሳይሰሩ እና ገንዘብ ሳያገኙ ፕሮጀክቶችን ለመጀመር ይወስናሉ፣ እናም በድንገት ፕሮጀክቶችን ያቋርጣሉ ሲሉ ያብራራሉ፡፡

## 4.3 ኃብት ማሠባሠብ

ለአብዛኛዎቹ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ዓለም አቀፍ መያዶች ዋና የገቢ ምንጫቸው ከለጋሾች የሚገኙ ፈንዶች ናቸው፡፡ ነገር ግን አሁን ባለው ጥብቅ እና ውስብስብ መስፈርት የተነሳ የውጭ ፈንድ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡ ብዙ አነስተኛ የሲቪል ማኅበር

ድርጅቶች የለጋሾችን መስፈርቶች ለማሟላት አቅም ያንሳቸዋል፡፡ በዚህ ሳቢያ የውጭ ፈንዶች አቅም ባላቸው ጥቂት የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ቁጥጥር ስር ሆኖ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል፡፡ በቅርብ ዓመታት አንዳንድ የፈንዲንግ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ EU-CSF II እና CSSP) የውጭ ፈንድ ለትናንሽ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ተደራሽ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ከመጀመራቸው በተጨማሪ የትብብር ፈንዲንግ አሠራርን መስርተዋል፡፡ ለጋሾች በተወሠኑ የልማት መስኮች ብቻ በመሳተፍ ሌሎች መስኮችን ለመርዳት ፈቃደኝነት አለማሳየታቸው የውጭ ፈንድ የማግኘት ዕድልን ወስኖታል፡፡ የተወሰኑ መስኮች ለምሳሌ የተገለሉ ሰዎች ችግር (አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን) የመሣሠሉት ጉዳዮች በቂ የለጋሾችን ትኩረት አላገኙም (Gebre et al, 2013)፡፡ ለጋሾች መድረስ በሚያስቸግሩ ጉዳዮች እና ሰዎች ላይ የሚሠሩ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ በቅርብ የጀመሩት ጥረት ሊበረታታ ይገባል፡፡ በለጋሾች የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ዕድሜ እና የዘላቂነት ጉዳይ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን የሚያሳስቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በለጋሾች ላይ የተመሠረቱ ፕሮጀክቶች ብዙ ጊዜ የጊዜ ገደብ አለባቸው፣ ዕድሜያቸው አጭር ነው፣ እና ሊራዘሙም ላይራዘሙም ይችላሉ፡፡ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን ተፅዕኖ ዘላቂ ለማድረግ ለጋሾች አሠራራቸውን ከፕሮጀክት ወደ ፕሮግራም ፈንዲንግ ሊቀይሩ ይገባል፡፡

አብዛኛዎቹ ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በለጋሽ ድርጅቶች ገንዘብ ላይ በጣም ጥገኛ ሲሆኑ፤ ከአገር ውስጥ ኃብት በማሠባሠብ ረገድ እያደገ ከመጣው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎችን ከማስተባበር የዘለለ እምብዛም የተሳካ አይደለም፡፡ በገቢ ማመንጫ ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ እና ከሕዝብ መዋጮ ለመሠብሠብ ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንድ የመመሪያ ማነቆዎች ያግዳሉና የመመሪያዎችን መሻሻል የሚሹ ብዙዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ኃብት ማሠባሠብ የሚያስኬድ ስትራቴጂ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተፅዕኗቸው ዘላቂ እንዲሆን እና በውጭ ገንዘብ ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ለመቀነስ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ከአገር ውስጥ ገንዘብ ለማግኘት ዕኩል ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ግብርና፣ ማዕድን ማውጣት፣ አገልግሎት መስጠት፣ ከሕዝብ መዋጮ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ዝግጅቶችን ማድረግ፣ እና የግሉን ዘርፍ የለጋሽነት ተሳትፎ ማበረታታት እንደአማራጭ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

## 4.4 የውስጥ ግንኙነቶች

በሲቪል ማኅበር ድርጅቶች መካከል በአብዛኛው መደጋገፍ እና መተባበር የለም ማለት ይቻላል፡፡ ብዙ ድርጅቶች በተመሳሳይ መስክ እና በተመሳሳይ ጂኦግራፊያዊ ቦታ እየሠሩ አይተዋወቁም፣ አይናበቡም፡፡ የኔትዎርኪንግ እና ግንኙነት አለመኖር የሥራ ድግግሞሽ እና የኃብት ብክነትን አስከትሏል ለማለት ያስደፍራል፡፡ በሲቪል ማኅበር

ድርጅቶች መካከል ላለው ደካማ ግንኙነት ምክንያቶች ውጫዊና ውስጣዊ ናቸው። የጥምረቶችን ሚና ካዳከሙት ውጫዊ ምክንያቶች መካከል ኔትዎርኮች የፕሮግራም ወጪ እንዳይኖራቸው መደረጉ አንዱ የሕግ ማነቆ ሲሆን፤ በተለያዩ የምዝገባ ዘርፎች ያሉ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በተመሳሳይ መስክ ላይ ቢሠሩም በአንድ ኔትወርክ ውስጥ አባል መሆን እንደማይችሉ የተጣለው ገደብ ሌላው ማነቆ ሊሆን ይችላል። ብዙ ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ስለሌሎች መሠል ድርጅቶች ለማወቅ እና አብሮ ለመሥራት ንቁና ቀጣይነት ያለው ጥረት እንደማያደርጉም ልብ ማለት ያስፈልጋል።

## 5 ማጠቃለያ ኃሳቦች

ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች የተለያዩ ስትራቴጂዎችን በመጠቀም ለኢትዮጵያ ቀዳሚ የልማት ዕቅዶች ጠቃሚ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ከስትራቴጂዎቻቸውም ውስጥ ከውጭ ምንጮች ብዙ ፈንድ ማሠባሠብ፣ አዳዲስ ኃሳቦችን እና አሠራሮችን ማስተዋወቅ፣ የትምሕርት እና የክህሎት ሥልጠና መስጠት፣ የቁሳቁስ/መሣርያዎች ድጋፍ ማቅረብ፣ የንግድ ሥራ ዕድሎችን መፍጠር፣ እና የማሕበረሠብ ተሳትፎን እና ባለቤትነትን ማጎልበት ይገኙበታል። የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ እና የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች እንዲሳኩ ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር በመተባበር ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል የሚያስብሉ ጠንካራ ምክንያቶች አሉ። የሚሠሩባቸውን የሕብረተሠብ ክፍሎች ተጨባጭ ችግሮች ከመፍታት ጎን ለጎን ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ዕድገት በአገሪቱ እንዲመጣ ለማድረግ ሠብዓዊ ካፒታልን ለማሻሻል ሲሠሩ ይስተዋላል።

ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች በኢትዮጵያ ግዙፍ እና ሠፊ ተሳትፎ ቢኖራቸውም ለዕድገት ሂደቱ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ መስኮች የሚያስፈልጋቸውን ትኩረት ሳያገኙ ቆይተዋል። ከእነዚህም መካከል የአካባቢ ጥበቃ፣ ከአየር ንብረት ለውጥ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተፅዕኖ፣ የፓብሊክ ሰርቪስ ጥራት እና መጠን፣ ሥራ ፈጣሪነት፣ የኃይል ምንጭ፣ ቴክኖሎጂ፣ ሠብዓዊ መብትና ዲሞክራሲ፣ የፍትህ እና ደህንነት ተደራሽነት፣ የፖሊሲ ውይይት ተሳትፎ፣ ፍልሠት እና ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ግጭት እና የሠላም ግንባታ፣ የተገለሉ የሕብረተሠብ ክፍሎች እና አገር በቀል ዕውቀት ይገኙበታል። ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል አንዳንዶቹ በአቅም ውስንነት የሲቪል ሶሳይቲ ማኅበራትን ትኩረት ሳያገኙ የቆዩ ሲሆን ለጋሾች ይህንን ችግር ሊፈቱት ይችላሉ። ሌሎቹ ደግሞ የሕግ ማነቆ ስላለባቸው ወደ ጎን የተተዉ ስለሆነ የመንግሥት ትኩረት ያሻቸዋል።

ጠባብ የሆነው የአገሪቱ የፖሊሲ ማዕቀፍ ከደካማ ኔትዎርኪንግ እና በቂ ካልሆነው የአገር ውስጥ ኃብት ማሠባሠብ ሥራ ጋር ተዳምሮ ሲቪል ማኅበር ድርጅቶች ሩቅ

የሆኑ የአገሪቱን ክፍሎች የመድረስ እና ይበልጥ ዘላቂ የሆኑ ፕሮጀክቶችን የመተግበር አቅማቸውን እንዳያጎለብቱ አግዷቸዋል። ስለዚህ የተሻለ የፖሊሲ ሁኔታ መፍጠርና የሲቪል ሶሳይቲ ማኅበራትን አቅም ማጠናከር ለአገር ልማት እና ለዲሞክራሲያዊ ሂደቱ መጎልበት ያላቸውን ሚና እንዲጨምሩ ያስችላቸዋል ተብሎ ይታሠባል። ሲቪል ሶሳይቲ ማኅበራትም አዳዲስ አሠራሮችን ለማስተዋወቅ፣ ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን ለማጠናከር፣ እና በለጋሾች እና/ወይም መንግሥት ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ለመቀነስ መጣር ይኖርባቸዋል። በመንግሥት እና በሲቪል ማኅበር ድርጅቶች መካከል ያለመተማመንና የውጥረት መንፈስ የፈጠሩትን ጉዳዮች ዋና ምክንያት በመመርመር መግባባት የሠፈነበት ግንኙነት እና ያልተቆጠበ ትብብር የሚያመጡ ሁኔታዎችን መፍጠር ይገባቸዋል።

## ዋቢ መፃሕፍት

Abebe Chekol, Bereket Luol, Teketel Abebe, Christopher Clapham, Gil Long and Mark Sinclair (2004) Mapping Non-State Actors in Ethiopia. A research study commissioned by the European Union and the Ministry of Capacity Development, Ethiopia. Addis Ababa.

Ayalew Gebre and Ezana Amdework. (2011) Mass-Based Societies in Ethiopia: Prospects and challenges. A study conducted by Atos Consulting and Forum for Social Studies through TECS Project. Addis Ababa

Cerritelli, William Emilio, Akalewold Bantirgu, and Reya Abagodu (2008) Update MappingStudy of Non-Sate Actors in Ethiopia. A study financed by the European Commission Civil Society Fund in Ethiopia. Addis Ababa

Dessalegn Rahmato, Akelewold Bantirgu, and Yoseph Endeshaw (2008) CSOs/NGOs inEthiopia: Partners in development and good governance. A research report prepared for an ad hoc CSO/NGO Task Force. Addis Ababa.

Freeman Dina and Alula Pankhurst (2003) Peripherial people: The excluded minorities of Ethiopia (eds.) Red ea Press. Lawrenceville, NJ.

Gebre Yntiso, Dagne Shibiru and Temesgen Chibsa (2014) Rapid Assessment of Self-HelpGroups in Ethiopia. A study conducted for DAG by Atos Consulting through TECS Project. Addis Ababa

Gebre Yntiso, Merhatsidk Mekonnen, and Abebe Gebre-Medhin (2013) CSO Support to People Living with Disabilities and the Elderly. A study conducted for DAG by Atos Consulting and Forum for Social Studies through TECS project. Addis Ababa

Gebre Yntiso (2011) Civil Society Organisations and Income Generation Activities in Ethiopia.A study conducted for DAG by Atos Consulting through TECS Project. Addis Ababa

Kassahun Berhanu (2012) Rapid Assessment of the Impact of the New Ethiopian CSOLegislation on the Operation of CCRDA’s Member Organisations. A study conducted by CCRDA. Addis Ababa

Long, Gil and Regassa Aboma (2013) The Impact of the Proclamation on Charities and Societies' Networks. A study conducted by Atos Consulting through TECS Project, Addis Ababa.

Tracking Trends in Ethiopia's Civil Society Project (TECS), Information Bulletin No.9, November (2013) On Ethiopian Resident Societies License Renewal Issues.

# በድህነት ቅነሳ ላይ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሚና

ተሾመ በየነ

## 1 መግቢያ

የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ለመዋጋት ከፍተኛ መሣሪያ መሆኑን በአብዛኛው በኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነት ቅነሳ ጥናት ላይ የተሠማሩ ምሑራን ይስማሙበታል። የትኛውም አገር ይሁን ክፍለ አህጉር ያለ አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን መቀነስም ይሁን መቅረፍ አይቻለውም። ሆኖም ግን በኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና ሕጎች እና በድህነት መካከል ያሉት ግንኙነቶች እስካሁን ድረስ ሙሉ ለሙሉ ተለይተው የታወቁ ናቸው ለማለት አያስደፍርም።

ይህ ጽሁፍ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ በተለይም በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ያለውን ድርሻ፣ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ (Infrastructure)፣ በድህነት ቅነሳ አቅጣጫዎች እና ፖሊሲዎች ላይ ያሉትን አስተዋፅኦዎች ለመዳሰስ ይሞክራል።

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በድህነት ቅነሳ ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ጥናቶች ያሳያሉ። የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ስንልም መደበኛ ባልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ (informal sector) የበላይነት የተያዘ ማለታችን ነው።

በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚታዩት ተግዳሮቶች መካከል ቀረጥና የቀረጥ አስተዳደር፣ የፋይናንስ ችግሮች፣ የዋጋ መናር፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ እንዲሁም ሙስናና የውጭ ምንዛሪ ችግር በዋነኛነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ተግዳሮቶችም ተመልሰው የግሉ-ዘርፍ ድህነትን በመቀነስ ረገድ ሊጫወተው የሚችለውን ሚና ላይ ደንቃራ ይሆናሉ።

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ተከታታይና ወጥነት ያለው ድህነትን ማዕከል ያደረገ አዎንታዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የተመቻቹ ዕድሎች ሊፈጠሩለትና ድጋፍም ሊደረግለት ይገባል። በመስኩ የተሠማሩና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ያለውን ሁኔታ ለማሻሻልና ለማሳደግ በአገርና በዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በፍጥነት አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችል የተመቻቸ የፖሊሲ ድባቦችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

## 2 የድህነት ትርጓሜና ልኬት

በየትኛውም የዓለም ክፍል የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ቁልፍና የመጀመሪያው ግብ ድህነትን መቀነስ ነው። በአሁኑ ሠዓት በዓለማችን ላይ

ከ1.4 ቢሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕዝቦች በቀን ከ1.25 ዶላር (26 ብር ገደማ) በታች በሆነ ገቢ ይኖራሉ:: 22,000 ሕጻናት ድህነት ወለድ በሆኑ በሽታዎች ይሞታሉ:: ከዚህ ሌላ 1.7 ቢሊዮን የሚሆኑ ሕዝቦች የንፁህ ውኃ እጥረት አለባቸው፤ 2.3 ቢሊዮን የሚሆኑ ሕዝቦች በውኃ ወለድ በሽታዎች ይሰቃያሉ:: በሌላ በኩል 12 መቶኛ የሆነው የዓለም ህዝብ የዓለማችንን 85 መቶኛ ውኃ ይጠቀማል (World Bank, 2013)::

ድህነትን የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ መልክ ይገልጹታል:: አብዛኛውን የሚያስማማ የድህነት ትርጓሜ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፤

> አንድ ሰው ለኑሮ የሚያስፈልገውን ወሳኝ ቁሳቁስ ወይም ገንዘብ ሲያጥረው እና ሲቸገር በድህነት ሁኔታ ውስጥ አለ ይባላል:: በሌላ በኩል ፍጹም ድህነት/ችጋር የሚባለው (Absolute poverty and/or destitution) ደግሞ እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል፤ "መሠረታዊ የሰው ልጆች ፍላጎት ማለትም ምግብ፣ ውሃ፣ የጤና እንክብካቤ፣ መጠለያ፣ ትምህርትና ንፅህናን ማጣት"::

በሌላ በኩል፤ **'አንፃራዊ ድህነት'** የሚባል ሌላ ጠቃሚ ጽንሠ-ኃሳብ ጥቅም ላይ ውሏል:: **'አንፃራዊ ድህነት'** ድህነትን በማሕበረሠብ-አቀፍ አውድ ውስጥ የሚያይ ሲሆን የጽንሠ-ኃሳቡ ህልውናም የሚመሠረተው አሁንም በማሕበራዊ አውድ ውስጥ ነው:: በተለይም ደግሞ አንፃራዊ ድህነት የአጠቃላይ ገቢ አለመስተካከልን (income inequality) የሚመለከት ሲሆን በተለይ ከጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ ከአማካኝ (median) ገቢ በታች የሆኑት ሠዎች በመቶኛ ያሰላል::

ከዚህ ሌላ የተባበሩት መንግሥታት ድህነትን የተረጎመበት ሠፊ አግባብ ማየቱ ጠቃሚ ነው::

> አንድ ሰው ምርጫና አማራጮችን ዝግ ሲሆኑበት፤ የሚገባውን ክብር ሲያጣ እንዲሁም በማሕበረሠቡ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ በውጤታማነት ለመንቀሳቀስ አቅም ሲያጥረው ድህነት ውስጥ ነው ያለው ይባላል::

ይህም ራሱ ሲተነተን ቤተሠቡን በበቂ ሁኔታ ለመመገብና ለማልበስ ሲቸግረው፤ ራሱንና ቤተሠቡን ለማስተማር ሲቸገር፤ እህል ዘርቶ የሚያበቅልበትን መሬት ሲያጣ፤ ወይም ራሱን የሚችልበት ሥራ ሳይኖረው ሲቀር እንዲሁም ብድር ለማግኘት ዕድሉ ሲጠብበት ድህነት ውስጥ እየኖረ ነው ይባላል:: ከዚህ ሌላ ሕይወትን በስጋት መምራት፤ ግለሠቦች፤ ቤተሠብ እንዲሁም ማሕበረሠብ ከሰፊ እንቅስቃሴ ሲገለሉ፤

ለጥቃት ሲጋለጡ እና በአስከፊና የተራቆተ አካባቢ ውስጥ ሲኖሩ በድህነት አረንቋ ውስጥ አሉ ይባላል።

## 3 ድህነትን ለመለካት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

ድህነትን ለመለካት ሶስት ጉዳዮችን በጥምር ማየት ያስፈልጋል። እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### *ሀ. የመልካም አኗኗር (welfare) ተስማሚ መለኪያዎችን*

ከድህነት መለኪያዎች መካከል ከተስማሚ መለኪያዎች ውስጥ የተሻለውና ለእውነታ ቀረቤታ ያለው ከገቢ መለኪያ ይልቅ የፍጆታ መለኪያ ነው። የቤተሠብ መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚሟላት አቅም ይበልጥኑ የሚገመተው በገቢ ሳይሆን በፍጆታ አቅሙ ነው። ከዚህ አባባል የሚመነጨው እንድምታ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማኅበረሠብ ክፍሎች ከገቢያቸው በላይ ፍጆታ ሊኖራቸው እንደሚችል ነው።

### *ለ. የድህነት መስመር*

የድህነት መስመሮች ድህነት ውስጥ ያለውን የሕብረተሠብ ክፍል ከድህነት ውጭ ካለው ለመለየት የምንጠቀምባቸው መለያ የኑሮ ድንበሮች (cut-off point) ናቸው። ከዚህም የተነሳ ከተቀመጠው መስመር በታች ያለው ሕዝብ በድህነት ውስጥ የሚኖር ነው ተብሎ ይወሰዳል። እነዚህ መስመሮች በፍጆታ መጠኖች፣ የገቢ መጠኖች ወይም የተወሠነ የትምህርት ደረጃ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በርካታ መስመሮችን በአንዴ በመጠቀም የተለያዩ የድህነት ገጽታዎችን ማሳየትም ይቻላል። ከላይ እንደተጠቀሠው በገቢና በፍጆታ ስርጭት መነሻ የሚቀመጠው አንፃራዊ ድህነትም በአብዛኛው ከአማካይ የአገሪቱ ገቢ አንጻር በመቶኛ የሚለካ ነው።

በሌላ በኩል ፍፁም ድህነት የሚለካው ከመሠረታዊ ፍላጎት አንፃር ዜጎች ያሉበት ደረጃ በመውሠድ ነው። ገንዘባዊ መለኪያውን ስናይ በአብዛኛው የመሠረታዊ የምግብ ፍላጎት ለሚሟላት የሚያስፈልገውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ ነው። በዚህ መለኪያ በአኃዝ የማይሰፍሩ የተለያዩ መለኪያዎች (qualitative measures) ጭምር ጥቅም ላይ ይውላሉ። ዞሮ ዞሮ የፍጹም ድህነት መለያ መስመር የማስቀመጡ ጉዳይ የተወሰነ ግምታዊነት እንደሚያጠቃው እሙን ነው። ለዚህ ጽንሠ-ኃሳብ ዋስትና የሚያረጋግጥለት ዕሙን ጉዳይ ግን ማሕበረሠቡ ድህነትን የሚለካበትና የሚረዳበትን አውድ ያገናዘበ ትርጉም መስጠቱ ነው።

የዓለምን ባንክ ድህነትን በተመለከተ የሚሰጠው ትርጓሜ ስንመለከት ደግሞ ማንኛውም ዜጋ ገቢው በቀን ከ1.25 ዶላር በታች ከሆነ ከድህነት ወለል በታች

እንደሆነ ይወሰዳል:: በአሁኑ ጊዜ ይህንን ገቢ ወደ 2.5 የአሜሪካን ዶላር በቀን አሻሽሎታል::

## ሐ. አገራዊ ቀመር ማዘጋጀት

የድህነት መስመር ከተቀመጠ በኋላ እና ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በስታቲስቲካዊ ዘዴ ተሰልቶ አገራዊ የሆነ አጠቃላይ ቀመር ማዘጋጀት እና በዚሁ መሠረት ስለድህነት ስፋት እና ጥልቀት ድምዳሜ መስጠት ነው::

ፍፁም ድህነት (Absolute poverty) በኢትዮጵያ የሚለካው የአንድ ቤተሠብ ፍጆታ በአንድ ጎልማሳ ፍጆታ መጠን ተሰልቶ በ2011 ዓ.ም ከተቀመጠው የብሔራዊ ድህነት ወለል መጠን ብር 3,781 በዓመት ጋር በማወዳደር ነው። ይህ የድህነት ወለል መጠን ለምግብና ከምግብ ውጭ የሆኑ ፍጆታዎችን በዓመት ለማሟላት የሚያስችል ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሦስት በስፋት የሚጠቀሱ የድህነት መለኪያ ዘዴዎች አሉ። እነሱም የድህነት ክስተት ብዛት (Incidence of poverty/Head count index) የሚባለው ከጠቅላላው የሕዝብ ቁጥር ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ሰዎች አንፃራዊ ብዛት (Proportion) ነው። የድህነት ጥልቀት (Depth of poverty/Poverty gap) የሚባለው የሚያሳየው በድህነት ያሉ ሰዎች ከድህነት ወለል በታች ምን ያህል ርቀት ላይ እንዳሉ ነው። ይህ ማለት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ሰዎች ፍጆታ በአማካይ ከድህነት ወለል (3,781 ብር በዓመት) በታች በምን ያህል ርቀት መኖሩን መለካት ማለት ነው።

ሌላው የድህነት መለኪያ ደግሞ የድህነት አስከፊነት (squared poverty gap) ልኬት የሚባለው ነው። ይህም የድህነትን አስከፊነት የሚለካው ዜጎች ከድህነት መስመር ያላቸውን ርቀት ብቻ ሳይሆን በድህነት በሚኖሩት መካከል ያለውን ልዩነትም ጭምር ነው። በመሆኑም ከድህነት መስመሩ በርቀት ላይ ላሉ ዜጎችና ገቢያቸው ከፍ ላሉ ዜጎች በትንተናው ሂደት ከፍ ያለ ክብደት ይሰጣል። እንዲሁም መለኪያው የጥልቀት መጠንም ሁሉንም ሕዝብ ከድህነት ለማውጣት የሚያስችል አስፈላጊ የኃብት መጠንን በእያንዳንዱ ግለሠብ ደረጃ አስልቶ ለማወቅ ያገለግላል (World Bank, 2013)::

## 4 ድህነት ቅነሳ በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ከታወቀችባቸው ገጽታዎች አንዱ በአገሪቱ ሲንከባለል የቆየው የድህነት ሁኔታ ነው:: ይህም ሁኔታ አብዛኛውን የሕብረተሠብ ክፍል ለተመጣጣኝ ምግብ እጥረት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለምግብ እጦት ችግር አጋልጦት ቆይቷል:: ለዚህም

ምክንያቶቹ ተብለው የሚጠቀሱት አስከፊ የሆነ የአካባቢ መራቆት፣ አነስተኛና የተበጣጠሰ የመሬት ይዞታ፣ ከግብርና መስክ ውጭ ያሉት የሥራ መስኮች የሥራ ዕድል የመፍጠር እጥረት፣ የራስን የገቢ ምንጭ ለመፍጠር የክህሎትና የመነሻ ገንዘብ እጥረትና ደካማ የሆነ የገጠር ከተማ ቁርኝት ለድህነት መባባስ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

ኢትዮጵያ ከ1990ዎቹ ጀምሮ የምትከተለው የልማት መርህ ድህነትን በማስወገድ ላይ ያተኮረ ነው። ለዚህም የልማት ፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች ልማቱ መሠረተ ሠፊ፣ ፈጣን እና ዘላቂ እንዲሆን ከፍተኛ ርብርብ እንዲደረግ በግልጽ ያስቀመጠ መሆኑ አዎንታዊ ልዩነት እንዲፈጠር መነሻ ሆኗል። የመንግሥት የልማት ፖሊሲ ሞዴል ዓላማ ድህነት ቅነሳ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ሞዴል በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች መንግሥት ጠንካራ ሚና እንዲኖረው እና በመሠረታዊ ግልጋሎቶች ላይ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ከፍተኛ እንዲሆን ታሳቢ ያደረገ ነው። የግብርና መር ኢንዱስትሪ ስትራቴጂው የግብርናው ዕድገት አጠቃላይ የኢኮኖሚውን ዕመርታ ይፈጥራል የሚል ዕሳቤም ይዟል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ በድህነት ቅነሳ ላይ ያተኮረ ዘርፈ-ብዙ ፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫዎችን በመተግበር ብሔራዊ የኢኮኖሚ ልማት ግቦችን በማረጋገጥ ላይ ትገኛለች። ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ 8.3% ዓመታዊ የዕድገት ምጣኔ በማሳየት ላለፉት 10 ዓመታት አመርቂ ዕድገት አስመዝግቧል። (World Bank, 2013)። ምንም እንኳን ዕሴት በመፍጠር ረገድ የግብርናው ዘርፍ አሁንም ከፍተኛ ድርሻ ያለው ቢሆንም ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ያለው ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል (በ2004 ዓ.ም ካለው የ52% ድርሻ በ2014 ወደ 40% ዝቅ ብሏል)። በአንፃሩ የአገልግሎት ዘርፉ ድርሻ እየጨመረ ሄዷል (በ2004 ዓ.ም ከነበረው የ37% ድርሻ በ2014 ወደ 46% ከፍ ብሏል)።

በውስጡ ባቀፈው የሕዝብ (መስኩ በተሠማራው የሰው ኃይል) ቁጥር ሲታይ ግብርና አሁንም ከፍተኛ የሆነ ድርሻ ይወስዳል። ምንም እንኳን ለአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከአምሳ በመቶ በታች ቢሆንም በቀጠረው እና በሚያስተዳድረው የዜጋ ቁጥር አንፃር ሲታይ ግን ከዚህም ከፍ ያለ ነው። 2008/9 በአገራችን በሥራ መስክ ላይ ተሠማርተው የነበሩት ዜጎች ቁጥር 38.7 ሚሊዮን ሲሆን ይህም ከአጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብ ቁጥር ኃምሳ ከመቶ የሆነውን ድርሻ ይዟል። ይህንኑ አሀዝ በዘርፍ ለይተን ስናየው 28.6 ሚሊዮን (73.9 ከመቶ) የሚሆኑትን ተቀጥረው የሚሠሩት በግብርና መስክ ሲሆን 2.9 ሚሊዮን (7.5 ከመቶ) በኢንዱስትሪው እና 7.2 ሚሊየን (18.6 ከመቶ) የሚሆኑት በአገልግሎት ዘርፍ ላይ ተሠማርተዋል።

እንደ የዓለም ባንክ የዳሰሳ ሪፖርት (2015) ኢትዮጵያ ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ አመርቂ የድህነት ቅነሳና የተቀናጀ ብልፅግና አሳይታለች፡፡ ለምሳሌ በ2000 ዓ.ም ኢትዮጵያ ከአለም ከፍተኛ የድህነት መጠን ካላቸው ጥቂት አገሮች ውስጥ አንዷ እንደነበረች በጊዜው የነበረው መረጃ ያሳያል፡፡ 56% ያህሉ የአገሪቱ ሕዝብ በቀን ከአሜሪካን ዶላር 1.25 (በመግዛት አቅም መጣኔ) በታች እና 44% ከብሔራዊ የድህነት ወለል በታች ይኖር ነበር፡፡ በ2011 ዓ.ም ግን ከ30% በታች የሆነው የአገሪቱ ሕዝብ ብቻ ከብሔራዊ የድህነት ወለል በታች እና 31% ያህሉ ደግሞ በቀን ከ1.25 የአሜሪካን ዶላር በታች ይኖራል፡፡

በተጨማሪም የተለያዩ መሠረታዊ ግልጋሎቶች ጥቅል እጦትን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ መሻሻል መታየቱ በተለይም በገጠር የአገሪቱ ክፍሎች የጤና፣ የትምህርት እና የንፁህ የመጠጥ ውኃ ፍላጎቶችን በሚሟላት ረገድ እመርታ ታይቷል፡፡ በምዕተ-ዓመቱ መነሻ በጤና፤ በትምህርትና በንፁህ ውኃ አቅርቦት ከአስር ቤተሠቦች አራቱ ከፍተኛ ዕጥረት የነበረባቸው ሲሆን በ2011 ዓ.ም ግን ከአስሩ ቤተሠብ አንዱ ብቻ የእነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶች ዕጥረት ተጠቂ ነው፡፡ በአጠቃላይ የትምህርት፣ የጤናና የንፅህና (Sanitation) ተደራሽነት በፈጣን ሁኔታ በመሻሻሉ ተጠቂና ተጎጂ የነበሩ የሕብረተሠብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አጠቃላይ የወሊድ ምጣኔ በ1995 ዓ.ም 7 ልጆች በ1 እናት የነበረ ሲሆን በ2011 ግን ወደ 4 ልጆች በ1 እናት ደረጃ ወርዷል፡፡ በተመሳሳይ መልክ የሕጻናት መቀጨጭ ከ58% ወደ 44% ዝቅ ብሏል፡፡ የመብራትና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲሁ በእጥፍ ዕድገት አሳይቷል፡፡

በሌላ በኩል የገጠሩ ክፍል የኑሮ ሁኔታ አሁንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ በግልጽ የሚስተዋል ሆኖ ያለው የኃብት ልዩነት ግን አነስተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ ከ2005 እስከ 2011 ባሉት ዓመታት በከተሞች የሚታይም ቢሆንም መጠነኛ ማሽቆልቆል አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ እንደ የዓለም ባንክ ዘገባ ከሆነ የኃብት ልዩነትን በማሳየት ጥቅም ላይ የዋለው ታዋቂው ቀመር ማለትም የጊኒ ቀመር (Gini Co-efficient) በኢትዮጵያ የኃብት ልዩነት የመባባስ ሁኔታ ማሳየቱን ያመለክታል፡፡ በ2000 ዓ.ም. በአገር ደረጃ ከነበረበት የ0.30 ምጣኔ በ2011 ወደ 0.371 አድጓል፡፡ በከተማና በገጠር ለያይተን ስንመለከት ደግሞ በከተማ በዚሁ ተመሳሳይ ጊዜ ከ0.34 ወደ 0.371 ሲያድግ፤ በገጠር ደግሞ አነስተኛ ጭማሪ ማለትም ከ0.27 ወደ 0.274 አሳይቷል፡፡ ነገር ግን ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት ጋር ሲነጻጸር አሁንም በኢትዮጵያ የዜጎች የኃብት ልዩነት አነስተኛ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ይህም በአዎንታዊነት የሚወሰድ ነው፡፡

## 5 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ለመዋጋት ከፍተኛ መሣሪያ መሆኑን አብዛኛው በዘርፉ የተሠማሩ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ የትኛውም ሐገር ይሁን ክፍለ-አህጉር ያለ አስተማማኝ ኢኮኖሚ እድገት ድህነት መቀነስም ይሁን መቅረፍ አይችልም፡፡ ሆኖም ግን በኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እና በድህነት መካከል ያሉት ግንኙነቶች ቀጥተኛ እና የማያሻሙ አይደሉም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የኃብትን አለመስተካከል (ልዩነትን) የማስፋት ውጤት ሊኖረው የመቻሉን ያክል ትርጉም ያለው ለውጥ የማያስገኝበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል፡፡

አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት የሥራ ዕድልን በመፍጠር የድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴን ሊያፋጥን እና ውጤትም እንዲያስገኝ ሊያደርገው ይችላል፡፡ አስፈላጊ የሆኑ የኢንዱስትሪና የንግድ እንቅስቃሴዎችንም በሚሚሚቅ መንግሥት ከቀረጥ እና ከሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ገቢ እንዲሰበስብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ይህም ገቢ በራሱ መንግሥት ለኢኮኖሚው መሠረት የሆኑትን የመንግሥት ፍጆታዎች ማለትም ለጤና፤ ለትምህርት፤ ለመንገድ፣ ለመብራት እና ስልክ ዝርጋታ እንዲሁም በአጠቃላይ ለሌሎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ዜጎችን ከድህነት በማውጣት ረገድ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ያግዘዋል፡፡

## 6 የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ለድህነት ቅነሳ ያለው አስተዋፅኦ

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የተለያየ ትርጓሜ ይሰጠዋል፡፡ አንዳንዶቹ በመንግሥት ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ያልዋለ ማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ይሉታል፡፡ ይህም ማናቸውም የግል ድርጅትና መንግሥታዊ የሆኑ የንግድ ድርጅቶችን በመጨመር የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ (private sector) ብለው ይሰይሙታል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በመንግሥት ቁጥር ስር ያልሆኑት የኢኮኖሚ አካላቶችን ሆነው በገበያ ሕግጋት የሚመሩ ባለቤትነታቸው የግለሠቦች የሆኑ አነስተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ወይም በግለሠቦች የተያዙ ድርጅቶች ወይም የኢኮኖሚ ተቋማት የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ተብሎ ይጠራል ይላሉ፡፡

### 6.1 የግሉ ክፍል-ኢኮኖሚ የሥራ ዕድገት ከማስገኘት አንፃር ያለው ሚና

በ2008/09 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ 95.8 ከመቶ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 5 ከመቶ የሚሆኑት በግል ድርጅቶች (ኮርፖሬሽኖች ጨምሮ) ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ቀሪው 90.8 ከመቶ የሚሆኑትን መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ (informal sector) ውስጥ ተሠማርተው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ በግብርና ሥራ ውስጥ ያሉትን ስናወጣ ከግብርና ውጭ ባለው የሥራ ዕድል የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ድርሻ 25.2 ከመቶ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡-** የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ድርሻ በሥራ ተቀጣሪነት ከጠቅላላው ኢኮኖሚ በመቶኛ፡፡

| ዓመት | እርሻ | ኢንዱስትሪ | አገልግሎት | ሥራ ተቀጣሪነት (እርሻን ሣይጨምር) |
|---|---|---|---|---|
| 2004/05 | 78.65 | 6.95 | 10.63 | 17.58 |
| 2005/06 | 79.95 | 7.37 | 9.06 | 16.43 |
| 2006/07 | 78.59 | 7.09 | 9.34 | 16.43 |
| 2007/08 | 76.05 | 7.2 | 12.83 | 20.03 |
| 2008/09 | 73.31 | 7.06 | 15.04 | 22.52 |

ምንጭ፡ CSA (2009)

## 6.2 የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በአጠቃላይ አገር ውስጥ ምርት (GDP) ላይ ያለው ሚና

ከ2004/5 እስከ 2008/09 ዓ.ም ባሉት ዓመታት የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ውስጥ ያለው ድርሻ 84.7 ከመቶ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የግል ኮርፖሬሽን (በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉትን ሳይጨምር) 25.1 ከመቶ የሆነውን ድርሻ ሲይዙ መደበኛ ያልሆኑት የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ (informal sector) የሚባሉት 59.1 ከመቶውን ድርሻ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ይዘው ተገኝተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡-** የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ድርሻ በአጠቃላይ በአገር ውስጥ ምርት (GDP) የሥራ ዕድል በመፍጠርና በኢንቨስትመንት በመቶኛ፡፡

| ዓመት | በአጠቃላይ በአገር ውስጥ ምርት (በነበረው ዋጋ) | በአጠቃላይ በአገር ውስጥ ምርት (በነበረው ዋጋ) | የሥራ ተቀጣሪነት | በኢንቨስትመንት |
|---|---|---|---|---|
| 2004/05 | 80.7 | 81.5 | 96.2 | 43.8 |
| 2005/06 | 81.4 | 81.4 | 96.4 | 39.0 |
| 2006/07 | 81.8 | 81.3 | 95.0 | 33.8 |
| 2007/08 | 83.9 | 80.9 | 96.1 | 37.0 |
| 2008/09 | 84.7 | 80.1 | 95.8 | 46.1 |

ምንጭ፡ Kolli (2010)

## 6.3 የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በኢንቨስትመንት ላይ ያለው ሚና

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በኢንቨስትመንት ያለውን ድርሻ ስንመለከት በ2008/09 በጠቅላላው በአገሪቱ ካለው ጠቅላላ ኢንቨስትመንት መካከል 46.1 ከመቶ የሚሆነው የዚሁ ክፍለ-ኦኮኖሚ ድርሻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ አሀዝ በ2004/05 ከነበረው የግል ኢንቨስትመንት ጋር ሲወዳደር በ34.7 ከመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ ዓመት የመንግሥት ኢንቨስትመንት ዕድገት 30.7 ከመቶ ነበር፡፡

## 6.4 አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና የድህነት ቅነሳ

አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሥራ ዕድል በመፍጠር የመንግሥት ገቢን በማሳደግና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እና የኢንተርፕሪነርሺፕ ክህሎት በማሳደግ ረገድ ትልቁን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡

የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ከፍተኛ ድርሻውን የሚይዙት ጥቃቅን፤ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የዜጎች ገቢን በማሳደግና ለአብዛኛው በተለይም ተገልለው (marginalized) የሚገኙ የሕብረተሠብ ክፍሎችን በማነቃቃት ትልቁ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በተለይም ደግሞ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴና ዕቅዶች ውስጥ ትልቅ ቦታ እየተሰጣቸው የሚገኙት ከዚህ በመነጨ ነው፡፡ ለምሳሌ በዓለም ባንክ በተደረገ ጥናት መሠረት በፔሩ በ15 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ የተጀመሩ አነስተኛና መደበኛ ያልሆኑ የንግድና የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች 9.4 ቢሊዮን ገደማ የሚሆን ተጨማሪ ገቢ በድህነት ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ ዜጎች ከማስገኘታቸውም በላይ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ዕድልን በ28 ከመቶ ጨምሯል፡፡ ይህም የሚሳየው እነዚህ መደበኛ ባልሆኑ የንግድና የአገልግሎት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች ለድህነት ቅነሳ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ ቦታ እንዳላቸው ነው፡፡

## 6.5 የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በመሠረተ-ልማት ዝርጋታ

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ (በቴሌኮሙኒኬሽን፣ ኢነርጂ፣ ትራንስፖርት፣ ውኃና የአካባቢ ንጽህና) እና መሠረታዊ አገልገሎቶችን በመስጠት ወደ ገበያ የመግባቱ ጉዳይ ያለው ዕንድምታ በተለያዩ አካላትና በዘርፉ በተሠማሩ ባለሙያዎች ወጥ የሆነ አቋም ላይ አልተደረሰበትም፡፡ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ጥብቅና አበክረው የቆሙ አካላት የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በመሠረተ ልማት ዝርጋታና መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማሻሻል እና ተደራሽነትን በማፋጠን ብሎም ድህነትን በመቀነሱ ረገድ ሠፊ ሚና ሊሰጠው ይገባል ይላሉ፡፡ በተጨማሪም በአግባቡና በተደራጀ መልኩ ከተከናወነ መንግሥት ለማኅበረሠቡና ለዜጎቹ በመስጠት ላይ ያለው አገልግሎት የሚያሳድርበት የበጀት ጫና በመቀነስ ውስን ኃብቱን ሌሎች ቁልፍ

ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲያውል ያስችለዋል የሚል መከራከሪያ ይቀርባሉ፡፡

በሌላ በኩል የግል ባለኃብቱ በመሠረተ ልማት ግንባታ መሳተፉን የሚተቹ አካላት ይህ እንቅስቃሴ አደጋዎችንና ችግሮችን ሊያመጣ ይችላል ብለው ያምናሉ፡፡ ይኸውም የግል ባለኃብቱ ብዙውን ጊዜ ኪሳራን ለመቀበል ዝግጁ ባለመሆኑ ምክንያት ያለ የመንግሥት መተማመኛ እና ቅድመ ክፍያ ወደ እንደነዚህ መሠል እንቅስቃሴ መግባት አይፈልግም ይላሉ፡፡

በድህነት ውስጥ የሚገኙ የሕብረተሠብ ክፍሎች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የዓለም ባንክ ያስቀመጠው ሞዴል “out-based Aid” (OBA) ሁሉንም የአገልግሎት ክፍያ ተጠቃሚው እንዲከፍል የሚያደርግ ሲሆን መንግሥት ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ክፍያውን በድጎማ እንዲፈጽም በአማራጭነት አስቀምጧል፡፡

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ያለውን ጠቀሜታና አዎንታዊ ሚና ግምት ውስጥ ያስገቡ የተለያዩ የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች ተዘጋጅተው ይገኛሉ፡፡ በዚህ ረገድ እነዚህ የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች የመንግሥት የርእዮተ አለም ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች ናቸው ወይስ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የንግድ እንቅስቃሴ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ በተለይም አብዛኛው ክርክር የሚነሳው በድህነት የሚኖሩ አገራት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂያቸው በገበያ ኃይሎች ሙሉ ለሙሉ መተማመን አይገባውም በሚል መሠረተ ኃሳብ ላይ በመንተራስ ነው፡፡ ብዙ ጥናቶች በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ውስጥ በአብዛኛው እንደ ድክመት የሚጠቅሱት የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሚና በግልጽ አለመቀመጡ ሲሆን በተለይም ደግሞ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሊኖረው የሚገባ ድርሻ በበቂ ሁኔታና በግልጽ አለመቀመጡ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ግን መጠኑና የግንኙነቱ ጥብቅነት ላይ ልዩነት ቢኖርም የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ዕድገት ቦታ መስጠት ያለበት እና በተለይም በረጅም ጊዜ ክንውን ቁልፍ ሚና እንዲጫወት የሚመክሩ ናቸው፡፡

## 7 የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ምን ተጨማሪና የተመቻቸ አማራጭ ዕድሎችና ድጋፍ ያስፈልጉታል?

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያስረዱት የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ከተጋረጡበት ተግዳሮቶች መካከል ቀረጥና የቀረጥ አስተዳደር፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የዋጋ መናር፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ሙስና፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ዋነኞቹ ሲሆኑ፤ እነዚህም የግል

ዘርፉ ድህነትን በመቀነስ ረገድ የሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች እና መሠናክሎች ናቸው ማለት ይቻላል።

የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ተከታታይና ወጥነት ያለው ድህነት የመቀነስ እንቅስቃሴን ለማበረታታትና ለማዳበር እንዲችል የተመቻቹ ዕድሎችን መፍጠርና ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል። በመስኩ የተሠማሩ ክፍሎችና ሌሎች የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትም በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ዙሪያ ያለውን የንግድ ድባብ ማሻሻልና የተመቻቸ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

በመሆኑም በፖሊሲው ዙሪያ፡-

- በፖለቲካው ሁኔታና በቢሮክራሲው ዙሪያ- የተረጋጋ የፖለቲካና የመልካም አስተዳደር ሁኔታ መፍጠር፤
- በማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ዙሪያ- የተረጋጋ የማክሮኢኮኖሚ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
- በንግድ ፖሊሲ ዙሪያ- ሊያሠራ የሚችል የገበያ ሥርዓትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በአገር ውስጥና በውጭ ኢንቨስትመንት ረገድ- ለአገር ውስጥና ለውጭ ኢንቨስተሮች ማበረታቻ መስጠት፤
- በሠው ኃይል ልማት ዙሪያ- የዳበረ የሠው ኃይል ገበያ መፍጠር፤
- በፋይናንስና በፋይናንስ ሥርዓቱ ዙሪያ- የተረጋጋ፣ አስተማማኝና የተቀላጠፈ የፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋት፤
- በንግድ ሕጉ ዙሪያ- አስተማማኝና ተመጣጣኝ የንግድ ክፍያና መመሪያዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

## Reference


Asian Development Bank Private Sector and poverty reduction URL www.adb.org/Documents/pocies/privatesector/private0103.asp?=polices

Bijimakers Leon, Linder Marianne The World Bank's Private Development Strategy: Key Issues and risks. ETC Crystal. April 2003.

CSA, 2009 Statistical Report from 2004/05 t0 2009/2010. Addis Ababa .Ethiopia

Candadian international Development Agency: Expanding Oportunities through Private Sector Development. July 2003 URL: www.Agcdi-cida.gc./cida_ind.nsf/AllDoclds/

FoX James w: The treatment of the Private sector in African PRSPs and APRs. Report to the Bueau for Africa. USAID/Washington. November 2004.

Fox James W.et.al Poverty reduction strategy papers: review of private sector participation.

Globalization challenge Initiative: Growing dangers of service apartheid. How the World Bank group, private Sector (PSD) strategy threatens infrastructure and basic service provision. News & nitices for IMF and World Bank watchers. Volume2, number 5, win Ter 2002.

GTZ: Econmoic development and employmention. Privte sector promotion Sectoral themes from A to Z.

Inter- American Development Bank: Private sector Development Strategy. January 2004

Malloch Brown Mark: Poverty Reduction, the Private Sector and the millennium Development Goals: A Framwork for a new future Royal Institute for internation Affairs. London. January 2003.

